ጀን ቢቸሬ

የሰይጣን ሽንገላ

ከአደገኛ የመሰናከል
ወጥመድ ነጻ ሆኖ
መኖር

ከ 1,000,000 ኮፒዎች በላይ በዓለም ዙሪያ እየተሰራጩ ነው

በጽሞና ማሰላሰያ የታከለበት

የተከበርህ ወዳጄ

ይህ መልእክት በሕይወት ዘመንህ ተጋፍጠህ ከማታውቀው በጣም ጠቃሚ እውነት ጋር ፊት ለፊት ያጋፍጥሃል። በልበ ሙሉነት እንዲህ የምለው ጸሐፊው እኔ በመሆኔ ሳይሆን፣ ውስጡ ካለው ርዕሰ ጉዳይ የተነሣ ነው። ይህ መልእክት ከሰማይ እንደ ሆነ አምናለሁ፤ የእኔ ስም መጽሐፉ ላይ የተጠቀሰው የተቀበልኩት እኔ ስለ ሆንኩ ብቻ ነው። የሰይጣን ሽንገላ ዐቢይ ሐሳብ የሆነው መሰናከያ ልንጋፈጠውና ልናሸንፈው የሚገባ እጅግ አደገኛ ከሆኑ ዕንቅፋቶችና ወጥመዶች አንዱ ነው።

ይህ መጽሐፍ ከታተመ ዐሥር ዓመት ሆኖታል፤ አሁን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኮፒዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በዓለም ዙሪያ ታትመዋል። በዚህ መልእክት ሕይወታቸው ከተነካ፣ ከምርኮኝነት ነጻ ከሆኑና፣ የጠላትን ማነቆ አራግፈው መጣል የሚችሉበትን ኃይል ካገኙና፣ እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ወዳለው የበለጠ ነገር መግባት ከቻሉ ወገኖች ብዙ ምስክርነቶች ከዓለም ዙሪያ ይደርሱናል።

አሁን ደግሞ ለእነርሱ ላለኝ ፍቅር መገለጫ እንዲሆን ለመሪዎችና ወደ ፊት መሪዎች ለሚሆኑ ወገኖች ይህን መጽሐፍ እንድሰጣቸውና ውስጡ ባለው መልእክት እነርሱም ሌሎች ከእስራት እንዲፈቱ መርዳት እንዲችሉ ጌታ በግልጥ ሐሳቡን ወደ ልቤ አምጥቷል።

ወዳጆቹ፣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ያለውን መልእክት ወደ መንፈሴ ካመጣ ወዲህ፣ ሕይወቴ ሥር ነቀል በሆነ መልኩ ተለውጧል። በዚህ መጽሐፍ ያካፈልኩትን እውነት ስትመረምሩ፣ የእናንተም ሕይወት እንዲለወጥ ጸሎቴ ነው። በራሳችሁም ሆነ እናንተ በምታገለግሉዋቸው ሰዎች ይህ መልእክት ስላመጣው በጐ ተጽዕኖ መስማት እፈልጋለሁ።

በክርስቶስ ወንድማችሁ

ጆን ቢቭሬ

Messenger International
MessengerInternational.org

የሰይጣን

ሹክሹክታ

በጽሞና ማሰላሰያ የታከለበት

ጆን ቢቸሬ

ትርጉም፡- በኮስፋዬ መስፍን

The Bait of Satan

John Bevere

© 2015 Messenger International

www.Messegerinternational.org

Originally Published in English

ከ www.cloudlibrary.org በነጻ ለመውሰድ በአማርኛ ያሉ ተጨማሪ መጻሕፍት፡- ተሰፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኃይል - ጽናት - የጽናት መጽሐፍ የጥናት መመሪያና በጽሞና ማሰላሰያ - በጅን ቢቭሬ - የሰይጣን ሸንገላ - በጅን ቢቭሬ፤ እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ - በሊዛ ቢቭሬ እንዲሁም የ30 ደቂቃ መልእክቶች የያዙ 12 ቪድዮና ኦዲዮ ሲዲዎች፡፡

ለማባዛት፣ በኢንተርኔት ለማሰራጨት፣ ጠቃሚ ሐሳቦችን ለመጠቀም ወይም ይህን የአማርኛ መልእክት ከሌሎች ጋር ለመከፋፈል ትበረታታላችሁ፡፡

የመጽሐፉን ደራሲ ለማግኘት - JohnBevere@ymail.com

Translated to Amharic by – Tesfaye Mesfin

Computer Setting by – Betelhem Minas

ማውጫ

መቅድም iv

መግቢያ 1

1. ማን ነው የሚሰናከል? – እኔ?. 5

2. የብዙዎች መሰናከል 15

3. ይህ እኔ ላይ እንዴት ሊደርስ ቻለ?. 28

4. አባቴ፣ አባቴ! 40

5. የቤተ ክርስቲያን ወሮበሎች 56

6. ከእውነታው መደበቅ 72

7. ጽኑ መሠረት 85

8. የሚናወጥ ነገር ሁሉ ይናወጣል 102

9. የመሰናከያ ዐለት 122

10. እንዳናሰናክላቸው 142

11. ይቅር ካላላችሁ – ይቅር አትባሉም 155

12. በቀል – አደገኛው ወጥመድ 172

13. ከወጥመዱ ማምለጥ 186

14. የመጨረሻው ግብ – ዕርቅ 198

መደምደሚያ ርምጃ መውሰድ 210

ማስታወሻዎች 213

መቅድም

ይህ እጅህ ያለው መጽሐፍ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ሊያጋጥምህ ከሚችል እውነት ዋናው ነው ማለት ይቻላል። ይህን በልበ ሙሉነት የምናገረው እኔ ስለ ጻፍኩት ሳይሆን ከርዕሰ ጉዳዩ የተነሣ ነው። መሰናከያ ዋናው የሰይጣን ሽንገላ ወይም ማጥመጃ ነው። ብዙ ጊዜም አንድ ግለ ሰብ ሊጋፈጠውና ሊያሸንፈው የሚገባ በጣም አስቸጋሪ ዕንቅፋት ነው።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ብዙ ታላላቅና አስገራሚ ተአምራት ሲፈጸሙ ዐይተው ነበር። የዕውራን ዐይኖች ሲበሩና ሙታን ሲነሡ በመደነቅ ተመልክተው ነበር። እነርሱን ለማጥፋት የመጣውን ማዕበል ፀጥ እንዲል ኢየሱስ ሲያዝዘው ሰምተዋል። ጥቂቱ እንጀራና ዓሣ በተአምር በርክቶ ሺዎች ሲመገቡ ዐይተዋል። ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራትና ድንቅ ነገሮች ተዘርዝረው አያልቁም፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የዓለም መጻሕፍት እንኳ ሊይዙት አይችሉም።

ተአምራዊውን የእግዚአብሔር እጅ በእንዲህ ያለ ከአእምሮ በላይ በሆነና ግልጽ በሆነ መልኩ የሰው ልጅ ከዚያ በፊት ዐይቶ አያውቅም። ደቀ መዛሙርቱ እጅግ መደነቃቸውና መገረማቸው እውነት ቢሆንም፣ ወደ መጠራጠር ዳርቻ የገፉዋቸው እነዚህ ተአምራት አልነበሩም። ተግዳሮቱ የመጣው በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማብቂያ ላይ ነው። ‹‹ወንድምህ...በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድልህና ሰባት ጊዜ፣ ‹ተጸጽቻለሁ› እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር በለው›› በማለት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሮ ነበር። በዚህ ጊዜ ወዲያውኑ የሰጡት ምላሽ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ እምነታችንን ጨምርልን›› የሚል ነበር (ሉቃስ 17÷3-5)። የተመለከቱዋቸው ተአምራት፣ ሙታንን ለማስነሣት ወይም ማዕበልን ፀጥ ለማድረግ እምነትን ጨምርልን በማለት እንዲለምኑ አላደረጉዋቸውም፤ እንደዚያ ያሰኛቸው የበደለዋቸውን ይቅር እንዲሉ የሰጣቸው በጣም ቀላል የሚመስል ትእዛዝ ነበር!

ኢየሱስ፣ ‹‹ሰዎችን የሚያሰናክል መምጣቱ አይቀርም›› ብሏል (ሉቃስ 17÷1)። ትልቁ ቁም ነገር መሰናክል መምጣቱ

ሳይሆን፣ እኛ የምንሰጠው ምላሽ ምን መሆን አለበት የሚለው ነው። በጣም የሚያሳዝነው፣ ጥቂቶች ሳይሆኑ በጣም ብዙዎች መሰናከላቸውና አሁንም የዚያ እስረኞች ሆነው ያሉ መሆናቸው ነው።

ይህ መጽሐፍ ለአንባቢዎች ከቀረበ ዐሥር ዓመት ሆኖታል። በዚህ ወቅት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተገለጠው የእግዚአብሔር እውነት የተነሣ ከተፈወሱና ሕይወታቸው ከተለወጠ ግለ ሰቦች፣ ቤተ ሰቦችና አገልግሎቶች እጅግ ብዛት ያላቸው ደብዳቤዎችና በርካታ ምስክርነቶች ደርሰውናል። ለእናንተ መበረታቻ የሚሆኑ ደብዳቤዎችን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለዐይነት አካትተናል። ስለ ሁሉም እጅግ ደስ ይለናል፤ ክብሩንም ሁሉ ለእግዚአብሔር እንሰጣለን!

አንድ ክርስቲያን መሪ፣ ‹‹ቤተ ክርስቲያናችን በጣም በሚያሰጋ ሁኔታ ለመከፋፈል ተቃርቦ ነበር። ነገሮች ተስፋ የሌላቸው ይመስለ ነበር። *የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኘው መጽሐፍ ለእያንዳንዱ መሪ ሰጠሁ። የመከፋፈለ ስጋት ተወገደ፤ አሁን አንድ ሆነናል!›› ብሏል።

መጽሐፉ በያዘው መልእክት አያሌ ትዳሮች ከመፍረስ ድነዋል። በቅርቡ በኔብራስካ ንግግር ካደረግሁ በኋላ ባልና ሚስት የሆኑ ሰዎች ወደ እኔ መጥተው ነበር። ሚስትየዋ፣ ‹‹ከዐሥር ዓመት በፊት በዚህ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰናክዬ ነበር። ከዚህ የተነሣ መራራና ጠርጣሪ ሆንኩ፤ ሁሌም ራሴንና የያዝኩትን ዐቋም ላለማስነካት እከላከል ነበር። ከመራራነቴ የተነሣ ትዳሬ ክፉኛ ተበጠበጠ፤ ባሌም ሊፈታኝ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ። ጌታን በማመን ያልዳነ ሰው ስለ ነበር ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት እንዲኖረው አይፈልግም ነበር። በዚህ መሓል አንድ ሰው *የሰይጣን ሽንገላ* የተባለውን መጽሐፍ እጄ ላይ አኖረ። በጥንቃቄ አነበብኩት፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከመሰናከልና ከምሬት ነጻ ሆንኩ። ባሌ የሕይወቴን መለወጥ ሲያይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትና አዳኝነት አመነ፤ እኔን ለመፍታት ጀምሮት የነበረውንም ሂደት አቋረጠ›› በማለት ነገረችኝ። ይህን ስትነግረኝ ባልዋ ፈገግ ብሎ አጠገቧ ቆሞ ነበር። እርሷ ተናግራ ስታበቃ እርሱም በሕይወቱና በቤቱ የተደረገውን ደስ የሚል ለውጥ መሰከረ።

በጣም ልቤን የነካኝን ምስክርነት የሰማሁት በኔፕልስ ፍሎሪዳ እያገለገልኩ በነበረ ጊዜ ነበር። ገና ንግግር ማድረግ ከመጀመሬ በፊት በመካከለኛው ዕድሜ ክልል ያለ አንድ ሰው ጉባኤው መካከል ቆሞ፣ ‹‹በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በእኔና በእግዚአብሔር መካከል አንድ ዓይነት ግድግዳ ያለ ያህል ይሰማኝ ነበር። እንዲህ ያሉ ስብሰባዎች ላይ ብዙ ጊዜ እገኛለሁ፣ ግን ሌሎች በእግዚአብሔር መገኘት ሲባረኩ እኔ ግን ገለልተኛና ድንዙዝ ሆኜ እታዘባለሁ። ሌላው ቀርቶ በምጸልይበት ጊዜ እንኳ መፈታትና የእግዚአብሔር ሓልዎት አይሰማኝም። ከጥቂት ሳምንቶች በፊት *የሰይጣን ሸንገላ* የተሰኘው መጽሐፍ እጄ ገባ፤ ወዲያውኑ ዳር እስከ ዳር አነበብኩት። ከዓመታት በፊት በሰይጣን ሸንገላ ተታልዬ እንደ ነበር ገባኝ። ገና የስድስት ወር ልጅ እያለሁ ትታኝ በመሄድዋ እናቴን በጣም እጠላት ነበር። ወደ እርሷ ሄጄ ይቅር ልላት እንደሚገባ ተረዳሁ። በሰላሣ ስድስት ዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ደውዬ አነጋገርኳት። ‹‹እማማ፣ ትተሽኝ በመሄድሽ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አንቺ ላይ ቂም ይዤ ኖሬአለሁ›› አልኳት። እርሷም ማልቀስ ጀመረች፣ ‹‹አንተን ትቼ በመሄዴ ላለፈው ሰላሣ ስድስት ዓመት ራሴን በመጥላት ነው የኖርኩት›› አለችኝ።

በመቀጠል፣ ‹‹ይቅር አልኳት፤ እርሷም ራሷን ይቅር አለች፤ አሁን በሁለታችን መካከል ዕርቅ ሆኖአል።›› እጅግ በጣም የሚገርም ነገር የተናገረው ይህን ካለ በኃላ ነበር፤ ‹‹አሁን ከእግዚአብሔር የለየኝ ግድግዳ ተወግዷል!››

እዚህ ነጥብ ላይ ፍጹም ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። እንደ ምንም ብሎ ታግለና፣ ‹‹አሁን በእግዚአብሔር ፊት እንደ አንድ ሕፃን አለቅሳለሁ›› አለ።

የእንዲህ ዓይነቱን እስራት እውነታና ብርታት እኔም ዐውቀዋለሁ። ለዓመታት የዚህ ስቃይ ምርኮኛ ሆኜ ነበር። ይህ መጽሐፍ የግምት ወይም የይመስለኛል አነጋገር አይደለም፤ በጉልህ የሚታይ፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እኔ ራሴ ያለፍኩበትን እውነት ይዞአል። እያነበባችሁ እያለ፣ እምነታችሁን እንዲጨምር ጌታን ጠይቁት! እምነታችሁ ሲያድግ እርሱ ይከበራል፣ እናንተም በደስታ ትሞላላችሁ! እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።

- ጆን ቢቭሬ

መግቢያ

እንስሳ አጥምዶ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፣ ወጥመዱ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ከሁለት ነገሮች አንዱ እንደሚያስፈልግ ይረዳል። እንስሳው ሳያውቅ እንዲገባበት ድብቅ ቦታ ላይ መሆን አለበት፤ እንስሳውን ለማሳሳትና ለመሸንገል ወጥመዱ ላይ መብል የሚሆን አጓጊ ነገር መደረግ አለበት።

እጅግ አታላይና ገዳይ ወጥመዶቹን ሲዘረጋ የነፍሳችን ጠላት ሰይጣን እነዚህ ሁለት ዘዴዎችን ይጠቀማል። ወጥመዶቹ ድብቅና የሚያማልሉ ናቸው።

ሰይጣንና ሰራዊቱ ብዙዎች እንደሚስቡት ቂል አይደሉም። ሰይጣን እጅግ ተንኰለኛ ነው፤ በማታለል ደስ ይሰኛል። በሚያደርገው ሁሉ ድብቅ፣ ሸረኛ፣ ብልጥና ሸንጋይ ነው። በዚህ ላይ ራሱን እንደ ብርሃን መልእክተኛ ማቅረብ እንደሚችል አትርሱ። በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት መልካምና ክፉን መለየት ካልተማርን፣ ወጥመዶቹን ላናውቅ እንችላለን።

እጅግ አሳሳችና ስውር ከሆኑ ሽንገላዎቹ አንዱ፣ ማንኛውም ክርስቲያን ላይ ደርሶ የሚያውቅ ማለትም መሰናከያ ነው። ወጥመዱ ላይ ስለ ተቀመጠ ብቻ እስካለ ድረስ ማንኛውም መሰናከያ በራሱ ጐጂ ነው ማለት አይደለም። ስናነሣውና አፋችን ስናገባው፣ ስንመገበውና በልባችን ስናወጣ ስናወርደው ያኔ እንጠመዳለን። የተሰናከለ ሰዎች - ጉዳትን፣ ቁጣን፣ ንዴትን፣ ቅናትን፣ ቅርታን፣ ፀብን፣ መራርነትን፣ ጥላቻንና ምቀኝነትን የመሳሰለ ብዙ ፍሬዎች ያፈራሉ። ጥቂቶቹ መሰናከያን አንሥቶ የመውሰድ ውጤቶች፣ ስድብ፣ ጥቃት፣ መቁሰል፣ መከፋፈል፣ መለያየት፣ የሻከረ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ክህደትና ከእምነት ወደ ኃላ ማለት ናቸው።

ብዙ ጊዜ ደግሞ የተሰናከለ ሰዎች መጠመዳቸውን እንኳ አያውቁትም። በተደረገባቸው በደል ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ ከሁኔታቸው በግልጽ ይታወቃለ። እነርሱ ግን ያንን አይቀበለም። ጠላት እኛን ከሚያሳውርበት አደገኛ መንገድ አንዱ ራሳችን ላይ ብቻ እንድናተኩር ማድረግ ነው።

ይህ መጽሐፍ ያንን አደገኛ ወጥመድ ያጋልጣል፤ እንዴት ከዚያ ማምለጥና ነጻ ሆነን መኖር እንደምንችል ያመለክታል። ከመሰናከያ ነጻ መሆን ለማንኛውም ክርስቲያን አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም፣ በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ መሰናከያ መምጣቱ እንደማይቀር ኢየሱስ ተናግሮአል (ሉቃስ 17÷1)።

በአሜሪካ ባለ አያሌ ቤተ ክርስቲያኖችና ይህን መልእክት በሰበክሁበት ሌሎች አገሮች ከሕዝቡ 50 እጅ በላይ እንዲጸለይላቸው ወደ ፊት በመምጣት ምላሽ ይሰጣሉ። ይህ በጣም ብዙ ቢሆንም፣ ሁሉም ምላሽ ሰጥቷል ማለት ግን አይደለም። አንዳንዶቹን ትዕቢት ምላሽ ከመስጠት ይይዛቸዋል። ከዚህ ወጥመድ ሲፈቱ ሰዎች ሲፈወሱ፣ ነጻ ሲወጡ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉና ለጸሎታቸው መልስ ሲያገኙ ዐይቻለሁ። ብዙ ጊዜ ነጻ ከሆኑ በኃላ በዚህ አጭር በቅጽበት የተቀበሉትን ለዓመታት ሲፈልጉ እንደ ነበር ይናገራሉ።

በሃያኛው መቶኛ ዓመታት የመጨረሻ ክፍል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕውቀት በጣም ጨምሯል። ምንም እንኳ ዕውቀት ቢበዛም አሁንም በአማኞች፣ በመሪዎችና በማኅበረ ምዕመኑ መካከል የበለጠ መከፋፈል ያለ ይመስላል። ምክንያቱ – ከእውነተኛ ፍቅር መጥፋት የተነሣ መሰናከያ መብዛቱ ነው። ‹‹ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር ግን ያንጻል›› (1 ቆሮንቶስ 8÷1)። መደበኛ የሕይወት መንገድ ነው ብለን እስክናስብ ድረስ ብዙዎች በዚህ አደገኛ ወጥመድ ተይዘዋል።

ይሁን እንጂ፣ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት እውነተኛ አማኞች ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታ ይተባበራሉ። ዛሬም ቢሆን፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወንዶችና ሴቶች ከዚህ መሰናከያ ወጥመድ እንደሚፈቱ አምናለሁ። መንፈሳዊ መነቃቃት አገሮችን ሲያዳርስ በማየት ረገድ ይህ ዋና ከሚባሉት ነገሮች አንዱ ነው። ከዚህ በፊት

እርሱን ለማየት ታውረው የነበሩ የማያምኑ ሰዎች በእኛ እርስ በርስ መዋደድ ኢየሱስን ይዩታል።

እንዲሁ ለመጻፍ ብቻ ተብሎ መጽሐፍ በመጻፍ አላምንም። እግዚአብሔር ይህን መልእክት ልቤ ውስጥ አቀጣጥሎታል፤ ዘላቂ ፍሬ ሲያስገኝም አይቻለሁ። ይህን መልእክት ከተሰበከሁበት አንድ አገልግሎት በኃላ አንድ ፓስተር፣ ‹‹በአንድ ጊዜ ይህን ያህል ሰዎች ነጻ ሲሆኑ አይቼ አላውቅም ነበር›› ብሏል።

ይህ ግን፣ የመጀመሪያው ብቻ መሆኑን እግዚአብሔር ለልቤ ተናግሮኛል። ይህን መጽሐፍ ሲያነቡና መንፈስ ወደ ልባቸው ለሚያመጣው ጉትጎታ ሲታዘዙ ብዙዎች ነጻ ይሆናሉ፣ ይፈወሳሉ፣ እንደ ገና ይታደሳሉ። በእነዚህ ገጾች ያሉ ቃሎችን ስታነቡ እውነተኛው መምህርና አጽናኝ በግል ለእናንተ ተግባራዊ እንደሚያደርጋቸው አምናለሁ። እንደዚያ ሲያደርግ፣ ይህ የተገለጠ ቃል ለሕይወታችሁና ለአገልግሎታችሁ ታላቅ ነጻነት ያመጣል። እስቲ፣ ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት እንጸልይ፣

አባት ሆይ፣ ይህን መጽሐፍ እያነበብኩ እያለ በመንፈስህ ቃልህን እንድትገልጥልኝ እለምንሃለሁ። አንተን ከማወቅ፣ ውጤታማ በሆነ ሁኔታም ከማገልገል ያገደኝን ማንኛውንም በልቤ ያለ ድብቅ ነገር ግልጥ አድርገው። መንፈስህ ልቤ ውስጥ የሚያኖረውን እቀበላለሁ፤ አንተ ለእኔ የምትፈልገውን እንዳደርግ ጸጋህን እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ። ይህን መጽሐፍ ሳነብ በምሰማው ድምፅህ የበለጠ አንተን በቅርበት እንዳውቅ እርዳኝ።

ለሚገጥመን መሰናክል

የምንሰጠው ምላሽ

የወደ ፊት ሕይወታችንን ይወስናል።

የሰይጣን ሽንገላ ሕይወትና አገልግሎችንን ለውጦአል። በትንሹ ከሃያ ጊዜ በላይ ቪዲዮዎቹን ተመልክተናል፤ ደግመን ደጋግመን መጽሐፉን አንብበናል። የራሳችንንና የብዙ ሌሎች ሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ አገልግሎታችን በመጽሐፉና በቪድዮ ትምህርቶቹ ሲጠቀም ነበር። መልእክቱ ኃያልና ወቅታዊ ነው።

- ኤስ ኪው ኮኔክቲከት

1

ማን ነው የሚሰናከል? – እኔ?

ማን ነው የሚሰናከል? – እኔ?

ሰዎችን የሚያሰናክል መምጣቱ አይቀርም።

- ለ.ቃሰ 17÷1

በመላው አሜሪካ እያገለገልኩ ስዘዋወር ጠላት ከሚጠቀምባቸው በጣም አደገኛና አሳሳች ወጥመዶች አንዱን መረዳት ችዬአለሁ። ብዛት ያላቸው ክርስቲያኖችን እስረኛ አድርጓል፤ የሰዎችን መቀራረብ ለያይቶአል፤ ቀድሞኑ በመካከላችን የነበሩ የመለያየት ገደቦችን አስፍቶአል። ይህ የመሰናከያ ወጥመድ ነው።

መሰናከያው በሕይወታቸው ካሳደረው ቁስልና ጉዳት የተነሣ ብዙዎች በተጠሩበት መጠራት በሚገባ መንቀሳቀስ አልቻሉም። ሙሉ ዐቅማቸውን እንዳይጠቀሙ ሽባና ስንኩል ሆነዋል። ብዙ ጊዜ ደግሞ ያንን ጉዳት ያደረሰባቸው አማኝ ወገናቸው ሊሆን ይችላል። ይህም፣ መሰናከያው ክህደት የተፈፀመባቸው ያህል ከባድ ሆኖ እንዲሰማቸው አድርጓል። መዝሙር 55÷12-14 ላይ ዳዊት፣ ‹‹የሚዘልፈኝ ጠላት አይደለምና፤ ቢሆንማ ኖሮ በታገሥሁ ነበር፤ የሚጠላኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ ባላንጣ አይደለም፤ ቢሆንማ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር። ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ፤ እኩያዬ፣ ባንጀራዬና ወዳጄ፤ በእግዚአብሔር ቤት አብረን በሕዝብ መካከል ተመላለስን፤ ደስ የሚል ፍቅር በአንድነት ነበረን›› በማለት ዳዊት ጉዳቱን ይገልጣል።

መሰናከያው የመጣው ጐን ለጐን ተቀምጠን አብረውን ከዘመሩ፤ ምናልባትም ስብከት ሲያቀርብ በነበረ ወንድም በኩል ሊሆን ይችላል። በአንድነት ደስ የሚሉ ቀኖች አሳልፈናል፤ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፈናል፤ ምናልባትም ቢሮዎች ተጋርተናል። አብሮነታችን ከዚያ ይበልጥ የቀረበ ሊሆንም ይችላል። አብረን አድገናል፤ ምስጢር ተከፋፍለናል፤ ጐን ለጐን ተኝተናል። ግንኙነቱ ጥብቅ ወይም ቅርብ የመሆኑን ያህል የደረሰብን በደልም እንደዚያው ያምማል! በአንድ ወቅት በጣም ይቀራረቡ በነበሩ ሰዎች መካከል በዚያው ልክ ከፍተኛ መጠላላት ሲፈጠር ይታያል።

በጣም ዘግናኝ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በባልና ሚስት መካከል መሆኑን የሕግ ሰዎች ይናገራሉ። የአሜሪካ ሚዲያዎች ተስፋ በቆረጡ የቤተ ሰብ አባሎች ቤት ውስጥ ስለሚፈጸሙ ግድያዎች በየጊዜው ያወራሉ። በመሠረቱ ቤት፣ ጥበቃና የሚያስፈልገንን የምናገኝበት፣ የምናድግበት፣ ፍቅር ሰጥተን ፍቅር የምንቀበልበት ቦታ መሆን ሲገባው ብዙ ጊዜ ግን የጉዳትና የስብራ ምንጭ ሲሆን ይታያል። ከፍተኛ የደም መፋሰስ የተደረገባቸው ጦርነቶች የእርስ በርስ ማለት ወንድም ከወንድሙ ጋር፣ ልጅ ከአባቱ ጋር ወይም አባት ከልጁ ጋር ያደረጋቸው ጦርነቶች መሆናቸውን ታሪክ ያሳያል።

መሰናክል የሚመጣባቸው መንገዶች የቱንም ያህል ውስብስብ ወይም ቀላል ቢሆኑም፣ ሰዎች ከሰዎች ጋር የሚፈጥሩትን ግንኙነት ብዛት ያህል ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም። ያም ሆኖ፣ ምንጊዜም ይህ እውነት እንደ ተጠበቀ ነው። በጣም ሊጐዱዋችሁ የሚችሉት በጣም ሲያስቡላችሁ የነበሩት ናቸው። ከእነርሱ የበለጠ መልካም ነገር ትጠብቃላችሁ፤ ያለ ምንም ስስት ራሳችሁን ትሰጧቸዋላችሁ። ብዙ ወይም ከፍ ያለ ነገር የመጠበቅን ያህል ውድቀቱም በዚያው ልክ ከባድ ይሆናል።

ራስ ወዳድነት ማኅበረ ሰባችንን ገዝቶአል። በዙሪያቸው ካለት ሰዎች አስታዋሽ ማጣትና ጉዳት ይልቅ ብዙዎች የሚፈልጉት የራሳቸውን ጥቅም ነው። ይህ ግን ሊያስደንቀን አይገባም።

በመጨረሻው ዘመን ሰዎች፣ ‹‹ራሳቸውን የሚወዱ›› እንደሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይናገራል (2 ጢሞቴዎስ 3÷2)። ይህን የምንጠብቀው ከማያምኑ ሰዎች ነው፤ ጳውሎስ ግን እየተናገረ ያለው ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ስላለች አይደለም። ውስጥ ስላለች ነው የተናገረው። ከዚህ የተነሣ ብዙዎች ቆስለዋል፤ ተጐድተዋል፤ መራሮች ሆነዋል። ተሰናክለዋል! ያም ሆኖ፣ ሰይጣን ወጥመድ ውስጥ መውደቃቸውን እንኳ አያውቁም።

ታዲያ፣ ጥፋቱ የእኛ ነውን? በዚህ ዓለም እስከኖርን ድረስ መሰናከያ መምጣቱ እንደማይቀር ኢየሱስ በጣም ግልጽ አድርጐአል። መሰናከያው ሲመጣ ግን አብዛኞቹ አማኞች ይደነግጣለ፣ ግራ ይጋባለ፣ በጣም ይደነቃለ። እንዲህ ያለ በደል የደረሰብን እኛ ብቻ የሆንን ይመስለናል። ይህ ደግሞ ምሬት ሥር እንዲያቆጠቁጥ ያጋልጠናል። ስለዚህ መሰናከያ ሳይመጣ፣ መዘጋጀትና መታጠቅ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም ለዚያ የምንሰጠው ምላሽ የወደ ፊት ሕይወታችንን ይወስናል።

አሳሳቹ ወጥመድ

ለ.ቃስ 17÷1 ላይ ያለው፣ ‹‹መሰናከያ›› የሚለው ቃል የተወሰደው ስካንዳሎን - *(Skandalon)* ከሚሰኝ ግሪክ ቃል ነው። መጀመሪያ ቃሉ የሚያመለክተው ማሳሳቻው የሚደረግበት የወጥመዱን ክፍል ለማመልከት ነበር። ስለዚህ ቃሉ አንድ ሰው መንገድ ላይ ወጥመድ ማኖርን ያመለክታል።[1] አዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው ጠላት የሚጠቀምበትን ወጥመድ ነው። መሰናከያ ሰዎችን ምርኮኛ ለማድረግ ዲያብሎስ የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው። ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፣

> የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግሥተኛም መሆን ይገባዋል፤ እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር ንስሓን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል፤ ይኸውም ወደ አእምሮአቸው ይመለሳለ፤ ፈቃዱን

ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጐ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመድም ያመልጣሉ በማለት ነው።

- 2ኛ ጢሞቴዎስ 2÷24-26

የሚጣሉ ወይም እርስ በርስ የሚጋጩ ወገኖች ወጥመድ ውስጥ ይወድቃሉ፤ የዲያብሎስንም ፈቃድ ለማድረግ ምርኮኞች ይሆናሉ። ከዚያ የበለጠ አስደንጋጩ ግን ምርኮኞች መሆናቸውን እንኳ አለማወቃቸው ነው! እንደ ኮብላዩ ልጅ ያለበትን ትክክለኛ ቦታ በመገንዘብ እነርሱም ወደ ልባቸው መመለስ ይኖርባቸዋል። እነዚህ ወገኖች ከንጹሕ ይልቅ መራራ ውሃ እያፈለቁ መሆናቸውን አያውቁም። አንድ ሰው ከሳተ ትክክል ባይሆን እንኳ፣ ትክክል ነኝ ብሎ ያምናል።

የመሰናከሉ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ የተሰናከሉ ሰዎችን ሁሉ በሁለት ዋና ዋና ምደቦች መክፈል እንችላለን። (1) ተገቢ ያልሆነ ነገር የደረሰባቸው ወይም የተደረገባቸው ወይም (2) ተገቢ ያልሆነ ነገር ደርሶብናል ወይም ተደርጐብናል ብለው የሚያምኑ። ሁለተኛው ምድብ ውስጥ ያሉ ሰዎች በደል እንደ ደረሰባቸው በሙሉ ልባቸው ነው የሚያምኑት። ብዙ ጊዜ ደግሞ የሚደርሱባቸው መደምደሚያዎች ትክክል ካልሆነ መረጃ የተወሰዱ ናቸው። ወይም ደግሞ መረጃቸው ትክክል ቢሆን እንኳ፣ መደምደሚያቸው የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። በዚህም ሆነ በዚያ፣ እነርሱ ይጐዳሉ፤ ማስተዋላቸውም ይጨልማል። መስሎ በታያቸው ተባራሪ ወሬ ይገምታሉ፣ ይፈርዳሉ።

የልብ ትክክለኛ ሁኔታ

ጠላት አንድን ሰው ከተሰናከለበት ሁኔታ እንዳይወጣ ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ መሰናከያውን ድብቅ ማድረግና በትዕቢት መሸፈን ነው። ትዕቢት ያላችሁበትን ትክክለኛ ሁኔታ እንዳትቀበሉ ያደርጋችኃል።

አንድ ወቅት ላይ በአንዳንድ አገልጋዮች ክፉኛ ተጐድቼ ነበር። ሰዎች ይመጡና፣ ‹‹አንተ ላይ እንዲህ ማድረጋቸው

ያሳዝናል፣ መቼም በጣም ተጐድተሃል፤ አይደለም እንዴ?›› ይሉኝ ነበር።

እኔ ግን ወዲያውኑ፣ ‹‹ደኅና ነኝ፤ ምንም አልተጐዳሁም›› በማለት እመልስ ነበር። በሰዎች ተበድያሁ ማለት ትክክል አይደለም ብዬ አስብ ስለ ነበር ጉዳቴ ጨርሶ እንደሌለ እቆጥር ነበር። ወይም ዐምቄ እይዘው ነበር። ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ራሴን በዚያ መልኩ አሳምኜው ነበር፤ መጐዳቴ እውነት ነበር። ትዕቢት ግን ልቤ ያለበትን እውነተኛ ሁኔታ ሸፈነብኝ።

ትዕቢት እውነቱን እንዳትቀበለ ይይዛችኃል። ዕይታችሁን ያሳስታል። ሁሉም ደኅና ነው ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ በፍጹም አትለወጡም። ትዕቢት ልባችሁን ያጠነክራል፤ ማስተዋላችሁንም ያጨልማል። ነጻ ከሚያወጣችሁ የልብ መለወጥ ወይም ንስሐ ያግዳችኃል (2 ጢሞቴዎስ 2÷24-26 ይመ)።

በሌላ በኩል ደግሞ ትዕቢት ራሳችሁን ተጠቂ አድርጋችሁ እንድትመለከቱ ያደርጋችኃል። ዝንባሌያችሁ፣ ‹‹በደል ተፈጽሞብኛል፤ ፍርድ ተጣምሞብኛል፤ ስለዚህ ልክ ነኝ ማለት ነው›› የሚል ዐይነት ይሆናል። ንጹሕ መሆናችሁንና በሐሰት እንደ ተከሰሳችሁ ስለምታምኑ ይቅር ማለት አትፈልጉም። ሆኖም የልባችሁ እውነተኛ ዝንባሌ ከእናንተ የተደበቀ ቢሆን እንኳ፣ ከእግዚአብሔር የተሰወረ አይደለም። በደል ስለ ተፈጸመባችሁ ብቻ ያንኑ በልባችሁ እንድታብላሉ ፈቃድ አልተሰጣችሁም። ሁለት ስሕተት አንድ ትክክል አይሆንም!

መፍትሔው

ከዮሐንስ ራእይ እንደምንመለከተው ኢየሱስ ለሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን የተናገረው ራሳቸውን ሀብታም፣ ባለ ጸጋና ምንም የማይጐደለው አድርገው ማየታቸውን በመናገር፣ ‹‹ጐስቋላ፣ ምስኪን፣ ድኻ፣ ዕውርና የተራቆትህ›› በማለት ያለበትን እውነተኛ ሁኔታ በመግለጥ ነበር (ራእይ 3÷14-20)። የኢኮኖሚ ጥንካሬያቸውን እንደ መንፈሳዊ ጥንካሬ ቆጥረውት ነበር። ትዕቢት እውነተኛውን ሁኔታ ሰወረባቸው።

ዛሬም ቢሆን፣ ብዙዎች እንደዚህ ናቸው። እነዚያ በደል ያደረሱብኝ አገልጋዮችን በተመለከተ የተሰማኝን ቅርታ ማየት እንዳልቻልኩ ሁለ፣ እርሱም እውነተኛ የልባቸውን ሁኔታ አያዩም። ምንም ጉዳት እንዳልደረሰብኝ ራሴን አሳምኜ ነበር። ካለበት መሳት እንዲወጣ ኢየሱስ ለሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር፣ የእግዚአብሔርን ወርቅ ግዛ፤ እውነተኛውን የልብህን ሁኔታ በሚገባ እይ አለው።

የእግዚአብሔርን ወርቅ መግዛት

ከነበረበት መሳት እንዲላቀቅ ኢየሱስ የሰጠው የመጀመሪያ መመሪያ፣ ‹‹በእሳት የነጠረ ወርቅ (ከእኔ) ግዛ›› የሚል ነበር (ራእይ 3÷18)።

የነጠረ ወርቅ ለስላሳና በቀላሉ መተጣጠፍ የሚችል፣ ከዝገት ወይም ከሌሎች ነገሮች የነጻ ነው። ወርቅ ጠንካራ፣ በቀላሉ የማይተጣጠፍና ለዝገት የተጋለጠ የሚሆነው፣ ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ጋር (ለምሳሌ መዳብ፣ ብር፣ ኒኬልና ከመሳሰሉት) ሲደባለቅ ነው። ይህ ድብልቅ፣ ቅይጥይጥ (አሎይ) ይባላል። ባዕድ ንጥረ ነገሮች ከእርሱ ጋር የመደባለቃቸውን ያህል ወርቁ ይጠነክራል። በተመሳሳይ መልኩ የቅይጥይጡ መጠን ሲቀንስ ወርቁ ለስላሳና በቀላሉ የሚተጣጠፍ ይሆናል።

የዚህን ተጓዳኝ ሐሳብ በቀላሉ ማየት ይቻላል፤ ንጹሕ ልብ እንደ ንጹሕ ወርቅ - ለስላሳ፣ ልል እና ተጣጣፊ ነው። ዕብራውያን 3÷13 ከኃጢአት አሳሳችነት የተነሣ ልብ እንደሚጠነክር ይናገራል! በደል ወይም መሰናክል ቶሎ መፍትሔ ካልፈለግንለት ምሬትን፣ ቂጣንና ቅርታን የመሳሰሉ ብዙ የኃጢአት ፍሬዎች ያፈራል። ቅይጥይጥ ነገር ወርቅን እንደሚጠነክር ሁለ፣ ይህም ባዕድ ነገር የእኛን ልብ ያጠነክራል። እንዳንነቃ በማድረግ ለስላሳነትን ይቀንሳል ወይም ጨርሶ ያስወግዳል። የእግዚአብሔርን ድምፅ ከመስማት ችሎታ እንሰናከላለን። በትክክል እንዳናይ ይጨልምብናል። ይህ ደግሞ የበለጠ ለመሳት ምቹ ሁኔታ ያዘጋጃል።

ወርቅን ለማጥራት የመጀመሪያው ርምጃ፣ እስኪደቅ ድረስ መፍጨትና ፍለክስ ከሚባል ንጥረ ነገር ጋር መደባለቅ ነው። ከዚያ ድብልቁ ምድጃ ውስጥ ይደረግና ከፍተኛ በሆነ ሙቀት ይቀልጣል። ቅይጥይጥና ንጹሕ ያልሆኑ ነገሮች ፍለክስ በተባለው ነገር ስለሚሳቡ ይንሳፈፋለ። ወርቁ ግን (ክብደት ያለው ነገር) ሥር ይቀራል። ከዚያም ንጹሕ ያልሆኑት ነገሮች (መዳብን፣ ብረትን፣ ዚንክን የመሳሰሉ ከፍለክስ ጋር የተጣመሩ ነገሮች ይወገዱና ንጹሑ ነገር ብቻ ይቀራል።

እስቲ እግዚአብሔር የሚለውን ስሙ፤

እነሆ እንደ ብር ባይሆንም አንጥሬሃለሁ፤

በመከራ እቶን ፍትኜሃለሁ።

- ኢሳይያስ 48÷10

እንደ ገና፣

አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኃል። እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት፣ በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደ ተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው።

- 1 ጴጥሮስ 1÷6-7

ይቅር አለማለትን፣ ፀብን፣ ምሬትን፣ ቂጣን፣ ምቀኝነትንና የመሳሰሉትን ንጹሕ ያልሆኑ ነገሮች በሕይወታችን ካለው የእግዚአብሔር ባሕርይ ልባችንን ለማንጻት፣ እግዚአብሔር በመከራ፣ በፈተናና በችግር ውስጥ ልባችንን ያጠራል።

እሳት፣ መከራና ችግር በሌለበት ቦታ ኃጢአት በቀላሉ ይደበቃል። ብልጽግናና ስኬት በሞላበት ጊዜ፣ ሌላው ቀርቶ እጅግ ዐመፀኛው እንኳ ደግና ቸር መስሎ ሊታይ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የመከራ እሳት ንጹሕ ያልሆነውን ነገር ያስወግዳል።

በሕይወቴ ገጥሞኝ በማያውቅ ከባድ ችግር ውስጥ ያለፍኩበት ጊዜ ነበር። በጣም ለሚቀርቡኝ ሰዎች እንኳ በጣም አስቸጋሪና እብሪተኛ ሆኜ ነበር። ቤተ ሰቤና ወዳጆቼም ገለል ያደርጉኝ ጀመር።

‹‹ይህ ሁሉ ቁጡ ባሕርይ የመጣው ከየት ነው? ከዚህ በፊት እንዲህ አልነበርኩም!›› በማለት አምርሬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽኩ።

ጌታም፣ ‹‹ልጄ፣ ንጹሕ ያልሆነ ነገር የሚወጣው ወርቅን እሳት ውስጥ ሲያደርጉት ነው። እነዚህ ነገሮች ለአንተ ባይታዩህም፣ ሁሌም ለእኔ ግልጽ ነበሩ። እንግዲህ የወደ ፊት ሕይወትህን የሚወስን ምርጫ ቀርቦልሃል። ሚስትህን፣ ወዳጆችህን፣ ፓስተርህንና አብረውህ የሚሠሩ ሰዎች ላይ እንደ ተቆጣህ ትቀራለህ ወይም ደግሞ ይህን የኃጢአት ቆሻሻ በእውነተኛ መልኩ በማየት ንስሓ ታደርጋለህ ይቅርታንም ትቀበላለህ፤ እኔም እነዚህ ንጹሕ ያልሆኑ ነገሮችን በራሴ መንገድ ከሕይወትህ አስወግደለሁ›› የሚል መልስ ሰጠኝ።

ያለህበትን ሁኔታ በሚገባ እይ

ከመሳት ነጻ መሆንን በተመለከተ አጥርቶ ማየት ሌላው ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮአል። በደል ሲደርስብን ብዙ ጊዜ ራሳችንን እንደ ተጠቂ እናይና የበደሉንን እንወቅሳለን። ከዚህም የተነሣ ምሬታችን፣ ይቅር አለማለታችን፣ ቁጣችን፣ ምቀኝነታችንና ቅርታችን ገንፍሎ ሲወጣ ትክክል እንደ ሆነ እንቆጥራለን። ‹‹ለማየት እንድትችል ዐይንህን በኩል እድትኳል እመክርሃለሁ›› በማለት ኢየሱስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነው (ራእይ 3÷18)። ምን እንድታይ? የልብህን እውነተኛ ሁኔታ እንድታይ! ‹‹ትጋ፣ (ቅና) ንስሐም ግባ›› በማለት ቀጥሎ ኢየሱስ እንዳዘዘው የምንሆነው በዚያ መንገድ ብቻ ነው። ንስሓ የምትገቡት ሌሎች ሰዎችን መውቀስ ስታቆሙ ብቻ ነው።

ሌሎችን ስንወቅስና የራሳችን ዐቋም ለማስረገጥ ስንከራከር እንታወራለን። እኛ ራሳችን ዐይን ውስጥ ግንድ የሚያህል ነገር እያለ ከወንድማችን ዐይን ትንሽ ጉድፍ ለማውጣት

እንታገላለን። ከዚህ ነጻ የሚያወጣን የእውነት መገለጥ ነው። ምን ጊዜም የእግዚአብሔር መንፈስ ኃጢአታችንን የሚያሳየን ያ ኃጢአት ከእኛ በሚቆረጥበት ሁኔታ ነው። ያ ደግሞ ኃጢአት ማድረጋችን ማመን እንጂ ፍርድ አያስከትልም።

ይህን መጽሐፍ እነበባችሁ እያለ እውነተኛ የልባችሁን ሁኔታ እንድታዩ የእግዚአብሔር ቃል የማስተዋል ዐይናችሁን እንዲያበራና ከያዛችሁ ማንኛውም በደል ነጻ እንድትሆኑ ጸሎቴ ነው። ትዕቢት እውነትን ከማየትና ንስሐ ከመግባት ወደ ኃላ እንዲይዛችሁ አትፍቀዱ።

የተሰናከለ ክርስቲያን ሕይወት ቢቀበልም፣

ከፍርሃት የተነሣ የተቀበለውን ሕይወት

መግለጥ የማይችል ሰው ነው።።

ሃያ ስምንት ዓመት አብረን ከኖርን በኃላ የዛሬ ዐሥር ዓመት ባሌ ጥሎኝ ሄዶ ነበር፤ ለዚያ ያቀረበው ምክንያት፣ <<ደስ ስላላለኝ>> የሚል ነበር። ሰማይ ምድሩ የዞረብኝ መሰለኝ። የእርሱ ጥሎኝ መሄድ ካስከተለው ጉዳት መተውና፣ ተፈላጊ ያለ መሆን ስሜት ለመውጣት ብዙ ዓመት ፈጅቶብኛል። ባሌን ይቅር እንድለው እንዲረዳኝ እግዚአብሔርን ጠይቄ ነበር፤ እንደዚያ የሆነ መስሎኝም ነበር፤ ሆኖም፣ ጉዳቱ ገና ልቤ ውስጥ ነበር፤ ከዚያ መላቀቅ አልቻኩም። እርሱን ባየሁ ጊዜ ሁሉ በጣም ያምመኝ ነበር። *የሰይጣን ሽንገላን* ካነበብኩ በኃላ የቀድሞ ባሌን እንዳናግረውና ይህን በደል በመያዜ ይቅር እንዲለኝ እንድጠይቀው መንፈስ ቅዱስ ሐሳብ ልቤ ውስጥ አኖረ። ከዐሥር ዓመት በኃላ ለመጀመሪያ ጊዜ ተነጋገርን። አሁን እንደ ተፈወስኩና ነጻ እንደ ሆንኩ ከልቤ አምናለሁ! ለረጅም ጊዜ ከገዛኝ ከዚህ የባርነት ቀንበር ነጻ ስላደረገኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

- ዲ.ቢ. ኒውዮርክ

2

የብዙዎች መሰናከል

በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ በርስ አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ ይጠላላሉም። ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችን ያስታሉ። ክፋት ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።

- ማቴዎስ 24÷10-13

በዚህ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ምልክቶች እየተናገረ ነው። ደቀ መዛሙቱ፣ ‹‹የመምጣትህ ምልክት ምንድነው?›› በማለት ጠይቀውት ነበር።

እኛ ያለነው እርሱ በሚመለስበት ዋዜማ ላይ እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። የሚመለስበትን ትክክለኛ ቀን ይኼ ነው ብሎ ለመጠቆም የሚደረግ ሙከራ ጥቅም የለውም። ያንን የሚያውቅ እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ የመመለሱን መዳረሻ ወይም ወቅት ማወቅ እንደሚቻል ተናግሮአል። በቤተ ክርስቲያን፣ በእስራኤልና ተፈጥሮ ውስጥ በዚህ ዘመን እያየን ያለው ትንቢት ፍጻሜ ከዚህ በፊት ታይቶ አያውቅም። ስለሆነም ማቴዎስ 24 ላይ ኢየሱስ በተናገረለት ጊዜ መዳረሻ ወይም ወቅት ላይ እንዳለን በልበ ሙሉነት መናገር እንችላለን።

ከመመለሱ በፊት ከሚታዩ ምልክቶች አንዱ፣ ‹‹ብዙዎች ይሰናከላሉ...›› የሚለው መሆኑን ልብ አድርጉ፤ ጥቂቶች ሳይሆን፣ ብዙዎች።

በመጀመሪያ፣ ‹‹የሚሰናከሉት እነማን ናቸው?›› ብሎ መጠየቅ አግባብ ነው። ክርስቲያኖች ናቸው ወይስ መላው ማኅበረ ሰብ? ማንበብ ስንቀጥል መልሱን እናገኛለን፤ ‹‹ክፉት ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል።›› እዚህ ላይ ፍቅር ለሚለው የግሪኩ ቃል አጋፔ ነው። አዲስ ኪዳን ውስጥ ፍቅር ለሚለው ቃል በርካታ ግሪክ ቃሎች ጥቅም ላይ ውለዋል፤ በጣም የተለመዱት ሁለቱ አጋፔ እና ፊልዮ ናቸው።

ፊልዮ በወዳጆሞች መካከል ያለውን ፍቅር ያመለክታል። ሁኔታዎችን መሠረት ያደረገ ፍቅር ነው። ፊልዮ፣ ‹‹አንተ ጀርባዬን እከክልኝ እኔም የአንተን አክልሃለሁ›› ወይም፣ ‹‹ጥሩ ሰው ከሆንህልኝ እኔም እንደዚያው እሆንልሃለሁ›› የሚል ፍቅር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አጋፔ፣ በልጆቹ ልብ ውስጥ የፈሰሰ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ኢየሱስ ለእኛ በነጻ የሰጠን ዐይነት ፍቅር ነው። ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ አያስገባም። ምግባርን መሠረት ያደረገ አይደለም፤ ላደረገው ምላሽ አይጠብቅም። ችላ ቢባል፣ ቢገፉ እንኳ በልግስና የሚሰጥ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ካልረዳን – መጀመሪያውኑ ካልተቀበለ መልስ በማይሰጠው ራስ ወዳድ በሆነው ዐይነት ፍቅር ብቻ ነው ሰዎችን የምንወደው። ሆኖም፣ አጋፔ ምላሹ ምንም ይሁን ምን፣ እንዲሁ ይወዳል። ይህ አጋፔ ፍቅር መስቀል ላይ ሆኖ የበደሉትን ይቅር ያለ ጊዜ፣ ኢየሱስ የገለጠው ፍቅር ነው። ስለዚህም፣ ኢየሱስ፣ ‹‹ብዙዎች›› ያላቸው አጋፔ ፍቅራቸው የቀዘቀዘባቸው ክርስቲያኖች ናቸው ማለት ነው።

ለአንድ ሰው ፍቅሬን ለመግለጥ የምችለውን ሁሉ አደርግ የነበረበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። ሆኖም፣ እርሱን ለመውደድ የሚቻለኝን ሁሉ ባደርግም፣ ያ ሰው የሚሰጠው ምላሽ ነቀፋና ጥላቻ ብቻ ነበር። ይህ በወሮች ለሚቆጠር ጊዜ ቀጠለ። አንድ ቀን ግን በጣም ሰለቸኝ።

‹‹አሁንስ መርሮኛል፤ ስለዚህ ጉዳይ ግልጽ እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ፤ ለዚህ ሰው ያንተን ፍቅር ባሳየሁ ጊዜ ሁሉ፤ የሚመልስልኝ ቂጣ ብቻ ነው!›› በማለት በእግዚአብሔር ፊት አጉረመረምኩ።

ጌታ እንዲህ በማለት ይናገረኝ ጀመር፡፡ ‹‹ጆን፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ያለህን እምነት ማዳበር አለብህ!››

‹‹ምን ማለት ነው ጌታ ሆይ?›› በማለት ጠየቅሁ፡፡

‹‹ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ ጥፋትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ግን፣ ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል፡፡ በጐ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ካልቆረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን›› የሚለውም ቃል ነበር ወደ ልቤ ያመጣው (ገላትያ 6÷8-9 ይመ.)፡፡

የእግዚአብሔርን ፍቅር ከዘራችሁ፣ የምታጭዱት የእግዚአብሔርን ፍቅር እንደ ሆነ መግንዘብ አለባችሁ፡፡ ከዘራችሁበት የእርሻ ቦታ ባታጭዱ እንኳ፣ ወይም እናንተ በፈለጋችሁት ፍጥነት ባታገኙት እንኳ፣ በዚህ መንፈሳዊ ሕግ ላይ ያላችሁን እምነት ማዳበር ይኖርባችኃል፡፡

ጌታ መናገሩን ቀጠለ፡፡ ‹‹በጣም ችግር ላይ በነበርኩ ሰዓት የቅርብ ወዳጆቼ ጥለውኝ ሄደው ነበር፡፡ ይሁዳ አሳልፎ ሰጠኝ፤ ጴጥሮስ ካደኝ፤ የተቀሩትም ሕይወታቸውን ለማዳን ሸሹ፡፡ ከሩቅ ሆኖ የተከተለኝ ዮሐንስ ብቻ ነበር፡፡ ከሦስት ዓመት በላይ ሳስብላቸው ነበር፤ እመግባቸውና አስተምራቸው ነበር፡፡ ሆኖም፣ ለዓለም ኃጢአት ስሞት የበደሉኝን ሁሉ ይቅር አልኩ፡፡ ጥለውኝ ከሄዱት ወዳጆቼ ጀምሮ መስቀል ላይ እስከ ሰቀሉኝ ሮማውያን ወታደሮች ድረስ ከበደል እስራት ፈታሁዋቸው፡፡ እነርሱ ይቅር እንድላቸው አልጠየቁኝም፤ ያም ሆኖ፣ በነጻ ሰጠሁዋቸው፡፡ በአባቴ ፍቅር እምነት ነበረኝ፡፡ ፍቅር ስለ ዘራሁ ከእግዚአብሔር መንግሥት ወንዶችና ሴቶች ልጆች ፍቅርን እንደማጭድ አውቅ ነበር፡፡ ከመሥዋዕታዊ ፍቅሬ የተነሣ፣ እነርሱም መልሰው ይወዱኛል፡፡

‹‹እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኃለሁ፡፡ እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሐዩን ለክፉዎችና ለደጐች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኃጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል፡፡ የሚወዷችሁን ብቻ

የምትወዱ ከሆነ ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀራጮችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን?›› (ማቴዎስ 5÷44-47)።

በጉጉት መጠበቅ

እየሰጠሁ ያለሁት ፍቅር፣ በመንፈስ የምዘራው እስከ ሆነ ድረስ የኃላ ኃላ ያንኑ የፍቅር ፍሬ እንደማጭድ ተረዳሁ። ከየት እንደማጭድ አላውቅም፣ ግን መከሩ እንደሚመጣ አውቃለሁ። ፍቅር የሰጠሁት ሰው ፍቅር ባይመልስልኝም፣ ከእንግዲህ ያንን እንደ ውድቀት አልቆጥረውም። ይልቁን ያንኑ ሰው ለመውደድ የበለጠ ነጻ ያደርገኛል። ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ተረድተው ቢሆን ኖሮ፣ ተስፋ በመቁረጥ አይሰናከሉም ነበር። ብዙውን ጊዜ ግን የምንመላለሰው በእንዲህ ዐይነቱ ፍቅር አይደለም። የምንመላለሰው ራስ ወዳድ በሆነ ፍቅር ነው፤ የጠበቅነውን ካላገኘን በቀላሉ ተስፋ እንቆርጣለን።

ከሰዎች የምጠብቅ ከሆነ፣ እነዚያው ሰዎች ሊያሳዝኑኝ ይችላሉ። ከጠበቅሁት በታች ሆነው በመገኘታቸውም ተስፋ ያስቆርጡኛል። ከሰዎች ምንም የማልጠብቅ ከሆነ ግን፣ የምሰጠው ማንኛውም ነገር በረከት እንጂ፣ እንዲመለሰልኝ የምፈልገው ዕዳ አይሆንም። ከምንቀራረባቸው ሰዎች አንዳች ነገር የምንጠብቅ ከሆነ፣ ራሳችንን ለመሰናከል እናዘጋጃለን። ብዙ በጠበቅን መጠን የመሰናከል ዕድላችንም ይሰፋል።

ራስን መከላከያ አጥር?

> የተበደለ (የተሰናከለ) ወንድም ከተመሸገ ከተማ ይበልጥ የማይበገር ነው።
>
> - ምሳሌ 18÷19

የተበደለን (የተሰናከለ) ወንድም ወይም እኅት ካለበት ሁኔታ ውስጥ ማውጣት የተመሸገች ከተማን ያህል ከባድ ነው። በጥንት ዘመን ትልልቅ ከተሞች ዙሪያቸውን አጥር ነበራቸው። ይህ አጥር ለከተሞቹ ጥበቃ አስተማማኝ ዋስትና ነው። አጥሩ የማይፈለጉ

ነዋሪዎችና ወራሪዎች ወደ ውስጥ እንዳይገቡ ያግዳል። መግባት የሚፈልጉ ሁሉ በሚገባ ይመረመራሉ። ግብር ያልከፈለ፣ እስኪከፍሉ ድረስ መግባት አይፈቀድላቸውም። ለከተማዋ ሰላም ወይም ደኅንነት ስጋት እንደ ሆኑ የሚታሰቡ ሰዎች ወደ ውስጥ እንዳይገቡ ይደረጋል።

በደል ወይም ጉዳት ከደረሰብን፣ ልባችንን ለመጠበቅና ወደ ፊት ሊመጣ ከሚችል ቁስል ራሳችን ለመከላከል አጥር እናበጃለን። ሰዎችን በጥንቃቄ እንመርጣለን፤ ይጐዱናል ብለን የምንፈራቸውን ወደ ውስጥ መግባት እንከለክላቸዋለን። የእኛ የሆነ አንዳች ነገር አለበት ብለን የምናስውን ሁሉ እናጣራለን። እነዚህ ሰዎች ዕዳቸውን ሁሉ እስካልከፈሉ ድረስ እንዲገቡ አንፈቅድላቸውም። ሕይወታችንን የምንከፍተው የእኛ ወገን እንደ ሆኑ ለምናስበው ብቻ ይሆናል።

ያም ሆኖ ግን፣ ‹‹የእኛ ወገን›› የምንላቸውም ጭምር ሊሰናከሉ ወይም እኛን ሊያሰናክሉ ይችላሉ። ስለሆነም እነርሱን ከመርዳት ይልቅ ቀድሞውኑ በነበረው አጥር ላይ ተጨማሪ ነገሮች እንክባለን። እኛ ሳናውቀው እነዚህ አጥሮች ራሳችንን የምንከልልበት እስር ቤት ይሆኑብናል። እዚያ ነጥብ ላይ ስንደርስ፣ ወደ ውስጥ የሚገቡትን በተመለከተ ጥንቃቄ ከማድረግ አልፈን፣ በጣም ስለምንፈራ እኛ ራሳችን ከምሽጋችን መውጣት አንፈልግም። የተሰናከሉ ወይም የተበደሉ ክርስቲያኖች ወደ ውስጥና ውስጥ ያለውን መመርመር ላይ ነው የሚያተኩሩት። መብታችንንና ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት በጥንቃቄ እንከልላለን። ለወደፊት ምንም ጉዳት እንደማያገኘን እርግጠኞች ለመሆን በምናደርገው ጥረት ጉልበታችንን እናደክማለን። ጉዳትን ለመቀበል ዝግጁ እስካልሆንን ድረስ፣ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ የማያስገባ ፍቅር፣ መስጠት አንችልም። ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ የማያስገባ ፍቅር፣ እኛን ለመጉዳት እንኳ ለሌሎች መብት ይሰጣል።

ፍቅር የራሱን አይፈልግም፤ የተበደሉ ወይም የተሰናከሉ ሰዎች ግን የበለጠ የራሳቸውን የሚፈልጉና በራሳቸው ውስጥ የተገደቡ ይሆናሉ። እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲፈጠር፣ የእግዚአብሔር

ፍቅር ይቀዘቅዛል። ለዚህ ተፈጥሮአዊ ምሳሌ የሚሆኑን በቅድስት አገር ያሉ ሁለት ወንዞች ናቸው። የገሊላ ባሕር በነጻነት ይቀበላል፤ በነጻነት ውሃ ይሰጣል። ውስጡ ብዙ ሕይወት አለ፤ የተለያዩ የዓሣና የዕፅዋት ዘሮችን ይመግባል። የገሊላ ባሕር በዮርዳኖስ ወንዝ በኩል አድርጐ ሙት ባሕር ውስጥ ይገባል። ሙት ባሕር ግን ውሃ ወደ ውስጥ ያስገባል እንጂ፣ ወደ ውጭ አያወጣም። ውስጡ ሕይወት ያላቸው ዕፅዋት ወይም ዓሦች የሉም። ሕያው የሆነው የገሊላ ባሕር ውሃ ከታቆረው ሙት ባሕር ጋር ሲቀላቀል ሙት ይሆናል። ታምቆ እስከ ተያዘ ድረስ ሕይወት አይቀጥልም፤ መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠትም አለበት።

የተበደለ ወይም የተሰናከለ ክርስቲያን ሕይወት የሚቀበል፣ ሆኖም፣ ከፍርሃት የተነሣ ሕይወት የማያወጣ ነው። በዚህ ምክንያት አጥሩ ውስጥ ወይም የበደል እስር ቤቱ ውስጥ የሚመጣ ውሃ እንኳ ይበከላል፤ ሕይወት ሰጪ አይሆንም። አዲስ ኪዳን ይህን አጥር ምሽግ ይለዋል።

> የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው። በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን።
>
> - 2 ቆሮንቶስ 10÷4-5

እነዚህ ምሽጐች ወደ ውስጥ የሚገባ መረጃ ሁሉ፣ የሚብላላበት አጉል ምክንያቶችና ክርክሮችን ይፈጥራሉ። ምንም እንኳ፣ በመጀመሪያ የተሠሩት ለመከላከል ሊሆን ቢችልም፣ በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ ስለሚነሡ የስቃይና የጠማማ ነገር ሁሉ ምንጭ ይሆናሉ።

ማንኛውንም ነገር ባለፈ ጊዜ ከደረሰብን ጉዳት፣ ስብራትና ቁስል አንጻር የምንመለከት ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ለማመን ያዳግተናል። እርሱ፣ በእርግጥ እንደ ተናገረው መሆኑን ማመን አንችልም። ሌላ ሰው በሕይወታችን ባኖረው መለኪያ ወይም ሚዛን ስለምንመዝነው መልካምነቱንና ታማኝቱን እንጠራጠራለን። ይሁን

እንጂ፣ ይዋሽ ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም (ዘኁልቁ 23÷19)። መንገዱ እንደ መንገዳችን፣ ሐሳቡም እንደ ሐሳባችን አይደለም (ኢሳይያስ 55÷8-9)።

በደል የደረሰባቸው ሰዎች የእነርሱን ዐቋም የሚደግፉላቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ፈልገው ማግኘት ይችሉ ይሆናል፤ ይህ ግን ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል መረዳት አይደለም። ፍቅር የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት፣ ስለሚያስታብይና ሕግ አክራሪነትን ስሚያስከትል ጥፋት የሚያደርስ ኃይል ይሆናል (1ኛ ቆሮንቶስ 8÷1-3)። ይህ ደግሞ ይቅር ባይ ባለመሆናችን ንስሐ ከመግባት ይልቅ ራሳችንን እንድናጸድቅ ያደርጋል።

እንዲህ ያለው ዝንባሌ የመሳት ከባቢ ይፈጥራል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅር የሌለበት ዕውቀት ወደ መሳት ነው የሚያደርሰው።

ብዙዎች እንደሚሰናከሉ ከተናገረ በኃላ ወዲያውኑ ሐሰተኛ ነቢያት እንደሚነሡ ኢየሱስ ያስጠነቅቃል፤ ‹‹ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችን ያስታሉ›› (ማቴዎስ 24÷11)። የሚስቱት ብዙዎች እነማን ናቸው? መልሱ – ፍቅራቸው የቀዘቀዘ፤ የተሰናከሉት ናቸው የሚል ይሆናል (ማቴዎስ 24÷12)።

ሐሰተኛ ነቢያት

ሐሰተኛ ነቢያትን ኢየሱስ፣ ‹‹የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች›› ብሏቸዋል (ማቴዎስ 7÷15)። ክርስቲያኖች የሚመስሉ፣ (የበግ ለምድ የለበሱ) የራሳቸውን የሚፈላልጉ ሰዎች ናቸው፤ ሆኖም፣ ውስጣቸው ተኩላ ነው። ተኩላዎች የባዘኑ በጎችን ያጠቃሉ። ማኅበረ ምዕመኑ መካከልም ሆነ ምስባክ ላይ ይገኛሉ። ሾልከው እንዲገቡና እንዲያስቱ ጠላት የላካቸው ናቸው። በትምህርታቸው ወይም በትንቢታቸው ሳይሆን፣ በፍሬያቸው ተለይተው መታወቅ አለባቸው። ብዙውን ጊዜ ትምህርታቸው ጤነኛ ይመስላል፤ ሕይወትና አገልግሎታቸው ግን እንደዚያ አይደለም። የአንድ አገልጋይ ወይም አንድ ክርስቲያን እውነተኛ ማንነት የሚኖረው እንጂ የሚሰብከው አይደለም።

ብዙ ጊዜ ተኩሎች የሚከታተሉት ጤነኞቹንና ብርቱዎችን ሳይሆን፣ የቆሰሉትንና ወጣት የሆኑ በጐችን ነው፡፡ ተኩሎች ለሰዎች የሚያስፈልገውን ሳይሆን፣ ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ጤናማ አስተምህሮ አይፈልጉም፤ እነርሱ የሚፈልጉት ለመስማት ደስ የሚያሰኛቸውን ነው፡፡ እስቲ የመጨረሻ ቀኖችን በተመለከተ ጳውሎስ የሚናገረውን እንመልከት፡፡

> ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ፡፡ ሰዎች... ለዕርቅ የማይሸነፉ ይሆናሉ...ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤ ኃይሉን ግን ክደዋል፡፡ ከእነዚህ ራቅ!...ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል፣ ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ፡፡ እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ዘውር ይላሉ፡፡
>
> \- 2 ጢሞቴዎስ 3÷1-5፤ 4÷3-4

እነዚህ ሰዎች ሃይማኖታዊ መልክ ወይም፣ ‹‹ክርስትና›› እንዳላቸው ልብ አድርጉ፤ ኃይሉን ግን ይክዳሉ፡፡ ኃይሉን የሚክዱት እንዴት ነው? ለዕርቅ የማይሸነፉ ከመሆን ይልቅ፣ ወደ ዕርቅ አድራጊነት ወይም ይቅር ባይነት ክርስትና ሊለውጣቸው እንደሚችል በመካድ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ነን በማለት ይመካሉ፤ ‹‹የአዲስ ልደት›› ልምምድ እንዳላቸው ይናገራሉ፤ ግን የሚመኩበት ነገር ልባቸውን ዘልቆ ሲገባና የክርስቶስን ባሕርይ ሲያላብሳቸው አይታይም፡፡

መረጃ ሰብሳቢ ትውልድ

እነዚህ የሳቱ ወንዶችና ሴቶች ለዕውቀት ከፍ ያለ ጥማት እንዳላቸውና ተግባር ላይ ስለማያውሉት ግን ሕይወታቸው እንደማይለወጥ ጳውሎስ በትንቢት አስቀድሞ ማየት ችሎአል፡፡ ‹‹ሁልጊዜ ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ ሊደርሱ አይችሉም›› በማለት ነበር የገለጣቸው (2 ጢሞቴዎስ 3÷7)፡፡

ጳውሎስ በዚህ ዘመን ቢኖር ኖሮ፣ አስቀድሞ የተናገረው እየተፈጸመ መሆኑን ተመልክቶ ያዝን ነበር፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ

ኮሌጆችን፣ ሰሚናሪዎችን፣ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን በመካፈል የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀታቸውን የሚያደረጁ ብዙ ወንዶችና ሴቶችን ይመለከት ነበር። የበለጠ ራስ ወዳድና ስኬታማ ሕይወት መኖር የሚያስችላቸው፣ ‹‹አዲስ መገለጥ›› ሲያሳድዱ ይመለከት ነበር። ‹‹ለጽድቅ›› በሚል ሽፋን አንዱ አገልጋይ ሌላውን ፍርድ ቤት ሲያቆመው ያይ ነበር።

ክርስቲያን ጽሑፎችና የሬድዮ ስርጭቶች የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ስማቸውን ጠርተው ሲያጠቁ ያይ ነበር። በደልን ወይም መሰናከያን ለመሸሽ፣ ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን የሚሯሯጡ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እናምናለን የሚሉ ወገኖችን በትዝብት ያይ ነበር፤ እነዚህ ወገኖች በክርስቶስ ጌትነት እንደሚያምኑ ቢናገሩም፤ የበደላቸውን ሰው ይቅር ማለት ግን አይፈልጉም። እነዚህን ሁሉ ሲያይ ጳውሎስ፣ ‹‹እናንተ የራሳችሁን ጥቅም የምታሳድዱ ግብዞች ንስሐ ግቡ፤ ካላችሁበትም መሳት ውጡ›› በማለት ይጮኽ ነበር።

ካለፋችሁባቸው አያሌ ሰሚናሪዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች ወቅታዊና አዲስ መገለጥ ማግኘታችሁ ወይም ምን ያህል መጻሕፍት ማንበባችሁ፣ ሌላው ቀርቶ ምን ያህል ሰዓቶች መጸለያችሁና በጥናት ማሳለፋችሁ ምንም ማለት አይደለም። በደል ደርሶባችሁ ወይም ተሰናክላችሁ ከሆነና ይቅር ማለትና ንስሐ መግባት የማትፈልጉ ከሆነ፣ ገና እውነትን ወደ ማወቅ አልደረሳችሁም። ስታችኋል፤ ግብዝ በሆነ አኗኗራችሁም ሌሎችን ግራ አጋብታችኋል። አገኘን የምትሉት መገለጥ የቱንም ያህል ረቂቅ ቢሆን እንኳ፣ ፍሬያችሁ የሚናገረው ግን ሌላ ታሪክ ነው። እውነት ሳይሆን ስሕተትን፣ ጥሩ ሳይሆን መራራ ውሃ የሚያፈልቅ ምንጭ ትሆናላችሁ።

አሳልፎ መሰጣጠት

በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ በርስ አሳልፈው ይሰጣጣላሉ።

- ማቴዎስ 24÷10

እስቲ ይህን ጥቅስ እንመርምር። ረጋ ብለን ካነበብን እያደገ የሚመጣ ሂደት እናያለን። መሰናከል ወደ መካካድ፣ መካካድ ደግሞ ወደ መጠላላት ያደርሳል።

ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው የተበደለ ወይም የተሰናከለ ሰዎች ራሳቸውን የሚከላከሉበት አጥሮች ያበጃሉ። ትኩረታችን ሁሉ ራስ መከላከል ላይ ይሆናል። የቱንም ያህል ዋጋ የሚጠይቅ ቢሆን እንኳ፣ ራሳችንን መከላከልና ሁሌም በተጠንቀቅ መሆን እንዳለብን እናስባለን። ይህ አሳልፎ ወደ መሰጣጠት ሊያደርሰን ይችላል። አሳልፈን በመሰጣጠት በሌሎች ሰዎች፣ እንዲያውም በጣም የቅርባችን በሆኑ ወገኖች ኪሳራ የራሳችንን ጥበቃ እናጠናክራለን ወይም የራሳችንን ጥቅም ብቻ እናሳድዳለን።

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አሳልፎ መሰጣጠት የሚመጣው፣ አንድ አማኝ በሌላው አማኝ ጉዳት የራሱን ጥቅም ወይም ደኅንነት ማስጠበቅ ሲፈልግ ነው። መቀራረቡ ጥብቅ የመሆኑን ያህል፣ አሳልፎ መሰጣጠቱ የሚያስከትለውም ጉዳት ከባድ ይሆናል። በምንም መልኩ ቢሆን ሌላውን ወገን አሳልፎ መስጠት፣ በከፍተኛ ደረጃ ኪዳን ማፍረስ ነው። አንዱ ሌላውን አሳልፎ ከሰጠና እውነተኛ ንስሐ ካልተከተለ በቀር ቀድሞ የነበረውን ግንኙነት ወይም ዝምድና ማደስ ይከብዳል።

አሳልፎ መሰጣጠት ደግሞ አደገኛ ውጤት ወደሚያስከትል ጥላቻ ይመራል። መጽሐፍ ቅዱስ ወንድሙን የሚጠላ ማንኛውም ሰው፣ ነፍሰ ገዳይ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል፤ ነፍሰ ገዳይ ደግሞ የዘላለም ሕይወት አይኖረውም (1 ዮሐንስ 3÷15)።

በዚህ ዘመን በአማኞች መካከል እየተፈጸመ ላለው መሰናክል (በደል)፣ አሳልፎ መሰጣጠትና ጥላቻ አያሌ ምሳሌዎች መኖራቸው ምንኛ አሳዛኝ ነው። እንደ ተለመደ ነገር እስኪቆጠር ድረስ በቤተ ሰብም ሆነ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እየበዛ መጥቷል። አንድ አገልጋይ ሌላውን አገልጋይ ፍርድ ቤት ሲያቆመው ብናይ እንኳ፣ ስለ ደነዘዝን ሐዘን አይሰማንም። አንደኛው ወገን ፍቺ ከመፈለጉ የተነሣ ክርስቲያን ባልና ሚስት እርስ በርስ ሲካሰሱ አይተን የምንገረምበት ዘመን ያለፈ ይመስላል። የቤተ ክርስቲያን

መከፋፈል የተለመደና የሚጠበቅ ነገር እየሆነ መጥቷል። በአገልጋዮች መካከል ያለው መጠላለፍ የረቀቀ ነው። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ይህ ሁሉ የሚደረገው ለእግዚአብሔር መንግሥት ወይም ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም በሚል ሽፋን መሆኑ ነው።

> ሌሎች ክርስቲያኖች እንዳያጠቋቸው ወይም ጥቅም እንዳይቀርባቸው ለማረጋገጥ ‹‹ክርስቲያኖች›› በንቃት ለመብታቸው ይከላከላሉ። ምናልባት አዲስ ኪዳን የሚመክረንን ዘንግተን ይሆን? እንግዲህ በመካከላችሁ መካሰስ መኖሩ ራሱ ውድቀታችሁን ያሳያል። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን?
>
> - 1ኛ ቆሮንቶስ 6÷7

ምናልባት ኢየሱስ የተናገረውን ዘንግተን ይሆን?

> እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኃለሁ።
>
> - ማቴዎስ 5÷44

ወይስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ዘንግተን ይሆን?

> ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቁጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ።
>
> - ፊልጵስዩስ 2÷3

በእነዚህ የፍቅር ሕጐች የማንኖረው ለምንድነው? ሌላው ቀርቶ ራሳችን እስከ መታለል ድረስ እንኳ ቢሆን፣ ሕይወታችንን ለሌላው ከመስጠት ይልቅ እርስ በርስ ተላልፈን የምንሰጣጠው ለምንድነው? ምክንያቱም ፍቅራችን ስለ ቀዘቀዘ ነው፤ ይህም ራሳችንን መከላከል እንድንፈልግ አድርጐናል። ከሚገባ በላይ ለራሳችን የምናስብና የምንተጋ እስከ ሆንን ድረስ የሚያሳስበንን ሁሉ በልበ ሙሉነት ለእግዚአብሔር መስጠት አንችልም።

ኢየሱስ በደል በደረሰበት ጊዜ፣ በጽድቅ ለሚፈርደው እግዚአብሔር ነፍሱን አደራ ሰጠ እንጂ፣ መልሶ አልበደለም። እኛ የእርሱን ፈለግ እንድንከተል ተመክረናል።

> የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌ ሊተውላችሁ ነው። እርሱ ኃጢአት አላደረገም፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም። ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ።
>
> - 1 ጴጥሮስ 2÷21-23

የሚያስችል አምላክ

በሥጋ ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ ወደምንታመንበት ደረጃ እንምጣ። ብዙዎች የእነርሱ ምንጭ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ ሆኖም፣ እንደ ሙት ልጆች ይኖራሉ። ‹‹እርሱ ጌታዬና አምላኬ ነው›› በማለት አንደበታቸው ቢመሰክርም፣ ሕይወታቸውን የሚመሩት በራሳቸው መንገድ ነው። የበደል ወይም የመሰናከል ኃጢአት ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ አይታችኋል። በወቅቱ መፍትሔ ካልተሰጠው በደል ወይም መሰናከያ የኃላ ኃላ ወደ ሞት ያደርሳል። ሆኖም፣ የመሰናክልን ፈተና ስትቃወሙ፣ እግዚአብሔር ታላቅ ድል ይሰጣችኋል።

ሊያጠፋን በፈለገ ጊዜ ሁሉ

ዲያብሎስ እኛን ማጥፋት ቢችል ኖሮ

ከረጅም ጊዜ በፊት ጠራርጐ ያጠፋን ነበር።

መጽሐፉን ከማንበቤ በፊት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የማላደርግበት ደረጃ ላይ ደርሼ ነበር። በጌታ የዳንኩ ብሆንም፣ በእኔና በእግዚአብሔር መካከል አንድ ጥሩ ያልሆነ ነገር ነበር። ችግሩ በጌታ በኩል እንዳልነበር አውቃለሁ፤ ያም ሆኖ፣ ችግር መኖሩን እንጂ፣ ችግሩ ምን እንደ ነበር አላወቅሁም ነበር። አንድ ቀን ጓደኛዬ ቤት እያለሁ፤ *የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኘው በጆን ቢቭሬ የተጻፈው መጽሐፍ አየሁ፤ እቤት አመጣሁና ማንበብ ጀመርኩ፣ መጽሐፉን ማስቀመጥ አልቻልኩም። የሚያረሰርስ ቅባት ያለው መጽሐፍ በመሆኑ መንፈሴ ይመገበው ጀመር። መጽሐፉ ግማሽ ላይ እንደ ደረስኩ፤ በእኔና ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት መካከል የቆመው የመሰናከል ወይም የበደል መንፈስ እንደ ነበር ተረዳሁ።

- ሲ.ሲ ጆርጂያ

3

ይህ እኔ ላይ
እንዴት ሊደርስ ቻለ?

ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው...

እናንተ እኔን ለመጉዳት አሰባችሁ አድርጋችሁት ነበር...

እግዚአብሔር ግን ለበጎ ነገር አዋለው።።

- ዘፍጥረት 50÷19-20

ወጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የተሰናከለ ወይም በደል የደረሰባቸው ሰዎችን በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ከፍለናቸው ነበር። (1) በእውነት በደል የተፈጸመባቸው ወይም የተሰናከለ እና (2) እንደ ተበደለ ወይም እንደ ተሰናከለ የሚያስቡ፣ በመሠረቱ ግን እንደዚያ ያልሆኑ። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪው ምድብ ውስጥ ስላለት ጥቂት ማለት እፈልጋለሁ።

በእውነት በደል ደርሶባችሁ ቢሆን እንኳ፣ በዚ ምክንያት የመሰናከል መብት ይኖራችኃል ወይ? የሚል ጥያቄ በማቅረብ እንጀምር። መልስ ለማግኘት ያዕቆብ በጣም ይወደው የነበረውን ልጅ የዮሴፍን ሕይወት እንመልከት (ዘፍጥረት 37-48)።

ሕልም ቅዠት ሲሆን

የዮሴፍ የያዕቆብ ዐሥራ አንደኛ ልጅ ነበር። አባቱ ከሌሎች ወንድሞቹ አስበልጦ ይወደው ስለ ነበርና በጎብረ ቀለማት ያጌጠ ልብስ ስለ ሰጠው ወንድሞቹ በቅናት ጠልተውት ነበር። እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሁለት ሕልሞች ሰጠው። በመጀመሪያው

የታሠሩ እህል ነዶዎች እርሻ ውስጥ አዩ። የእርሱ ነዶ ተነሥቶ ቆመ፤ የወንድሞቹ ነዶዎች ግን ለእርሱ ነዶ ሰገዱ። በሁለተኛው ሕልሙ ፀሐይ፣ ጨረቃና ዐሥራ አንድ ከዋክብት (አባቱን፣እናቱንና ወንድሞቹን የሚወክል) ለእርሱ ሲሰግዱ አዩ። እነዚህን ሕልሞች ለወንድሞቹ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የእርሱን ስሜት አልተጋሩም። እንዲያውም ከበፊት የበለጠ ጠሉት።

ይህ ከሆነ በኋላ ብዙ ሳይቆይ፣ የአባታቸውን መንጋዎች ለማሰማራት ወንድሞቹ ከቤት ራቅ ብለው ሄዱ። ሁኔታቸውን ዐይቶ እንዲነግረው ያዕቆብ ዮሴፍን ላከው። ወደ እነርሱ በመምጣት ላይ እያለ ያዩት ወንድሞቹ፣ ‹‹ባለ ሕልሙ እየመጣ ነው፤ ይዘን እንግደለው! ያኔ ሕልሙ የት እንደሚያደርሰው እናያለን!›› በማለት እርሱ ላይ አሤሩ። ስለዚህም እንዲሞት ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። በዱር አውሬ እንደ ተበላ አባታቸውን ለማሳመን ልብሱን በእንስሳ ደም ለወሱ።

ይሁን እንጂ፣ ጉድጓድ ውስጥ ከጣሉት በኋላ፣ ወደ ግብፅ የሚመጡ እስማኤላውያን ነጋዴዎች ሲመጡ አዩ። ‹‹እዚያ ጉድጓድ ውስጥ እንዲሞት ብንተወው እኛ ምንም ጥቅም አናገኝም፤ ይልቁን፣ እርሱን ለባርነት በመሸጥ ጥቂት ገንዘብ ብናገኝ ይሻላል፤ ያኔ ከሞተ ሰው ያልተሻለ ይሆናል›› የሚል ሐሳብ ይሁዳ አቀረበ። ስለዚህ በሃያ ጥሬ ብር ሸጡት። ዮሴፍ አሰናክለውአቸው ስለ ነበር፣ እነርሱ ደግሞ ከውርስና ከቤተ ሰቡ ለመነጠል አሳልፈው ሰጡት። ይህን ሁሉ ያደረጉት ከአንድ አባትና እናት የተወለዱ ወንድሞቹ መሆናቸውን ልብ አድርጉ።

በሌላ አገር የምንኖር ሰዎች ባሕላችን ከእነርሱ የተለየ በመሆኑ እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር በሚገባ መረዳት ይከብደናል። ከዚያ የከፋ ነገር ቢኖር እርሱን መግደል ብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን አንድ ሰው ወንዶች ልጆች መወለዱ በጣም አስፈላጊ ነበር። ወንዶች ልጆች የስሙ መጠሪያ፣ የርስት የንብረቱ ሁሉ ወራሾች ይሆናሉ። የዮሴፍ ወንድሞች በአባቱ ስም መጠራትንና የርስቱ ተካፋይ የመሆንን

መብት ነጥቀውታል። ስሙን ደምስሰዋል፤ ማንነቱን ገፍፈዋል። ለዮሴፍ ክቡርና ውድ የነበረ ነገር ሁሉ ብን ብሎ ጠፍቷል።

አንድ ሰው ወደ ሌላ አገር ተወሰዶ ለባርነት ከተሸጠ፣ በዕድሜ ዘመኑ ሁሉ ባሪያ እንደ ሆነ ይቀር ነበር። የሚያገባት ሴት እንደ እርሱ ባሪያ ትሆናለች፤ የሚወልዳቸው ልጆችም ባሪያዎች ይሆናሉ!

መቼም፣ ባሪያ ሆኖ መወለድ ከባድ እንደሚሆን ግልጽ ነው፤ ሆኖም፣ የወደ ፊት ሕይወትን መለወጥ የሚችል ሀብት ወራሽ ሆኖ መወለድና፣ ያንን ሁሉ ግን ማጣት ደግሞ፣ ከዚያ የባሰ ነበር። ዮሴፍ ያለፈ ማንነቱን ባያውቅ ኖሮ ይሻለው ነበር። አሁን እርሱ በቁሙ የሞተ ያህል ነበር። ምናልባትም ወንድሞቹ ገድለውት ቢሆን ኖሮ ይሻለው እንደ ነበር ሳያስብ አልቀረም። ዋናው ነጥብ የዮሴፍ ወንድሞች ያደረጉት ከባድ ጭካኔ መሆኑን ማሳየት ነው።

በራሴ መንገድ ያቀረብኩትን የዮሴፍን ታሪክ ስታነቡ፣ ምናልባትም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል እንደሚሆን አውቃችሁ ይሆናል። መጨረሻውን የምታውቁ ከሆነ ደግሞ ታሪኩን የበለጠ ጣፋጭ ያደርገዋል። ለዮሴፍ ግን ሁኔታው እንደዚያ አልነበረም። አባቱን ወይም እግዚአብሔር የሰጠው ሕልም ሲፈጸም በፍጹም ማየት የማይችል መስሎ ነበር የታየው። እርሱ በባዕድ አገር የነበረ ባሪያ ነው። ከግብፅ ወደ አገሩ መመለስ አይችልም። እስኪሞት ድረስ የሌላው ሰው ንብረት ይሆናል።

የዮሴፍ የተሸጠው ጲጥፋራ ለሚሉት የፈርዖን ባለ ሥልጣን ነበር። ዐሥር ዓመት ያህል ይህን ባለ ሥልጣን አገለገለ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከቤተ ሰቡ አንድም ቃል አልሰማም፤ ሞቷል ብሎ አባቱ እንደሚያምን አውቋል።

ጊዜ እያለፈ በሄደ ቁጥር፣ ዮሴፍ በጌታው ዘንድ ሞገስ አገኘ፤ ጲጥፋራ ዮሴፍን በንብረቱ ሁሉ ላይ ኃላፊ አድርጐ ሾመው።

ሆኖም፣ የዮሴፍ ሁኔታ መልካም እየሆነ ቢመጣም፣ በዚሁ ጊዜ በጌታው ሚስት ልብ ውስጥ መጥፎ ነገር እየተጠነሰሰ ነበር። ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርግ ጠየቀችው።

በየቀኑ ልታሳስተው ትሞክር ነበር፤ እርሱ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። አንድ ቀን እርሱ እና እርሷ ብቻቸውን ቤት ውስጥ እያለ አንድ ጥግ እንዲይዝ አደረገችና ከእርሷ ጋር እንዲተኛ አስገደደችው፤ እርሱ ግን እምቢ ብሎ መጐናጸፊያውን እጇ ላይ ጥሎ ሸሸ። ይህን በማድረጉ የተናደደችው ሴት፣ ዮሴፍ ሊደፍራት ሙከራ አድርጐ እንደ ነበር ተናገረች። ጲጥፋራ ዮሴፍን ወህኒ ቤት አሳሰረው።

የፊርያን እስር ቤት በአንዳንድ አገሮች እንዳለት እስር ቤቶች እንደ ነበሩ ማሰብ የለብንም። በአሜሪካ ባለ ብዙ እስር ቤቶች ውስጥ አገልግያለሁ፤ የቱንም ያህል ደስ የማይለ ቢሆኑ እንኳ፣ ከፊርያን እስር ቤቶች ጋር ሲነጻጸሩ ጥሩ የሚባለ ናቸው። የፊርያን እስር ቤት የፀሐይ ብርሃን አይገባበትም፤ መንቀሳቀሻ ቦታ የለውም፤ ቀዝቃዛና ሙቀትም ሆነ ብርሃን የማያገኘው ነበር። እዚያ የሚገቡ እስረኞች ‹‹የመከራ እንጀራ›› እየበለ የሚሞቱበትን ቀን ይጠብቃለ (1ኛ ነገሥት 22÷27)። መዝሙር 105÷18 እንደሚነግረን የዮሴፍ እግሮች በእግር ብረት ተላልጠው ነበር፤ የብረት ማነቆ ውስጥ ገብቶ ነበር። መጀመሪያውኑ እንዲሞት ታስቦ ነበር ወደዚያ እስር ቤት የተጣለው።

ግብፃዊ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት የመፈታት ዕድል ይኖረው ነበር፣ ነገር ግን በአስገድዶ መድፈር የተከሰሰ ከሌላ አገር የመጣ ባሪያ ስለ ነበር የመፈታት ተስፋ አይኖረውም፤ ቢኖረውም በጣም ጥቂት ነው።

እዚያ እርጥብና ቀዝቃዛ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ዮሴፍ ምን ያስብ እንደ ነበር ገምታችሁ ታውቃላችሁ? ምናልባት፣ *ዐሥር ዐመት ያህል ጌታዬን በቅንነትና በታማኝነት አገልግያለሁ። እንዲያውም ከገዛ ሚስቱ ይልቅ በተሰጠኝ አደራ እኔ ለእርሱ ታማኝ ነበርኩ። በየዕለቱ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ታጠአት እየሸሸሁ ለእግዚአብሔርና ለጌታዬ ታማኝ ሆኜ ኖሬአለሁ። ታዲያ፣ ምን ጠቀመኝ? እስር ቤት መጣል?*

ትክክል የሆነውን ነገር ባደረግሁ መጠን፣ የእኔም መከራ በዚያው ልክ እየከፋ የሚሄድ ይመስላል። እግዚአብሔር እንዴት እንዲህ እንዲሆን ይፈቅዳል? እርሱ ራሱ የገባልኝንም ተስፋ ቃል

ሞምር ወንድሞቹ ከእግዚአብሔር ወሰደው ይሆን? ብርቱና ኃያል የሆነው የኪዳኑ ጌታ ለምን እኔን ለመርዳት ጣልቃ ሳይገባ ቀረ? አፍቃሪና ታማኝ አምላክ በርሱ በተማመኑ አገልጋዮቹ ላይ እንዲህ ማድረግ ነበረበት? ለምን እኔ ላይ እንዲህ ሆነ? እንዲህ ያለ ስቃይ የሚደርስብኝ ምን ሰላደረግሁ ነው? ከእግዚአብሔር የተሰጠኝን ተሰፋ ከማመኔ ወጪ ምንም በደል አልፈጸምኩም የሚለ ሐሳቦች ወደ አእምሮው ሳይመጡ አልቀረም።

እስር ቤት ውስጥ ያለው ነጻነት በጣም የተገደበ ነበር፣ ይሁን እንጂ፣ እየደረሰበት ላለው ሁለ የሚሰጠውን ምላሽ የመምረጥ ነጻነት ነበረው። ታዲያ፣ በወንድሞቹ፣ ውሎ አድሮም በእግዚአብሔር ይሰናከልና ምሬት ያድርበት ይሆን? የተገባለትን ተሰፋ እርግፍ አድርጐ ይረሳ ይሆን?

እግዚአብሔር እየተቆጣጠረ ነውን?

መከራው እስኪያበቃ ድረስ ይህ እግዚአብሔር እርሱን ለወደፊቱ መሪነት እያዘጋጀው እንደ ነበር ዮሴፍ አንዴ እንኳ እንዳላሰበ እገምታሁ። ታዲያ፣ ወደ ፊት የሚያገኘውን ሥልጣን ወንድሞቹ ላይ እንዴት ይጠቀምበት ይሆን? ከደረሰበት መከራ ዮሴፍ መታዘዝ እየተማረ ነበር። ወንድሞቹ በጥንቃቄ ያዘጋጁት ተንኰል እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መሣሪያ ሆኗል። ታዲያ፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለው ዓላማ እንዲፈጸም የተገባለትን ተሰፋ አጥብቆ ይይዝ ይሆን?

ዮሴፍ ሕልሞቹን ያየ ጊዜ እርሱ የተለየ ሰው ለመሆኑ እንደ ማረጋገጫ ወስዶአቸው ይሆን ይሆናል። ሥልጣን የሚሰጠው ለማገልገል እንጂ፣ የተለየ ሰው ለመሆን እንዳይደለ ገና አልተማረም ነበር። ብዙውን ጊዜ በእንዲህ ያለው ሥልጠና ወቅት ከእግዚአብሔር ታላቅነት ይልቅ፣ የማይቻሉ የመሰሉን ነገሮች ላይ እናተኩራለን። በዚህ ጊዜ ተሰፋ እንቆርጥና ለዚያ ምክንያት ናቸው የምንላቸውን ሰዎች መወቀስና መክሰስ እንጀምራን። እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ነገር እንዳይደርስብን ማድረግ ይችል ነበር - ግን አላደረገም። ስለሆነም ብዙ ጊዜ እርሱንም ሞምር እንወቅሳለን።

ምናልባትም፣ ‹‹ስለ እግዚአብሔር በማወቀው መሠረት ኖሬአለሁ፡፡ ሕጉን ወይም ባሕርዩን አልተላለፍኩም፡፡ ያደረግሁት ነገር ቢኖር፣ እርሱ የሰጠኝን ሕልም መናገር ብቻ ነበር፡፡ ታዲያ፣ ውጤቱ ምን ሆነ? ወንድሞቼ አሳልፈው ሰጡኝ፤ ለባርት ተሸጥሁ! አባቴ ሞቷል ብሎ ስለሚያስብ እኔን ለመፈለግ ወደ ግብፅ አይመጣም›› የሚል ሐሳብ ወደ ዮሴፍ አእምሮ ይመጣ ይሆናል፡፡

ለእርሱ ዋና ተጠያቂዎች ወንድሞቹ ናቸው፡፡ እስር ቤት የመጣለ ምክንያት እነርሱ ናቸው፡፡ በሕልሙ ባየው መሠረት እግዚአብሔር ወደ ሥልጣን ሲያመጣው ነገሮች ምን ያህል እንደሚለወጡ ምናልባት በአእምሮው ያወጣ ያወርድ ይሆናል፡፡ የወደ ፊት ሕይወቱን ወንድሞች ባያጨናግፉበት ኖሮ ሁኔታው ምንኛ የተለየ መልክ ይኖረው ነበር፡፡

እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙን እኔና እናንተም ሌሎችን ተጠያቂ እናደርጋለን፡፡ ለምሳሌ፣

‹‹ሚስቴ ባትኖር ኖሮ፣ ይኼኔ አገልግሎት ውስጥ እሆን ነበር፡፡ ዕንቅፋት ሆናብኛለች፤ ሕልሜን እንዳልነበር አድርጋለች፡፡››

‹‹ወላጆቼ እንደዚያ ባያደርጉ ኖሮ፣ ጤናማ ሕይወት ይኖረኝ ነበር፡፡ ዛሬ ላለሁበት ሁኔታ ተጠያቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ ሌሎች ጥሩ ወላጆች ሲኖራቸው እኔ ግን ለምን ሳይኖረኝ ቀረ? እናትና አባቴ ባይፋቱ ኖሮ፣ ምናልባት የእኔም ትዳር ጥሩ ይሆን ነበር፡፡››

‹‹ውስጤ ያለውን የጸጋ ስጦታ ፓስተሬ ባያፍንብኝ ኖሮ፣ ይኼኔ በነጻነት እጠቀምበት ነበር፡፡ የአገልግሎት ዓላማዬን አጨናግፎብኛል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች እኔን በጥርጣሬ እንዲመለከቱ አድርጓል፡፡

‹‹የቀድሞ ባሌ እንደዚያ ባያደርግ ኖሮ፣ እኔና ልጆቼ እዚህ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ አንወድቅም ነበር፡፡››

‹‹ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያቺ ሴት ባትኖር ኖሮ፣ ከመሪዎቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት ይኖረኝ ነበር፡፡ ጥሩ ስሜንና የወደ ፊት ተስፋዬን በሐሜት አጨልማለች፡፡››

ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም። ለደረሰባችሁ ሁሉ ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግና እንደ እዚያ ባይሆን ኖሮ፣ ነገሮች የተለየ መልክ ይኖራቸው እንደ ነበር ማሰብ በጣም ቀላል ነው። አሁን ያላችሁበት ተስፋ መቁረጥ የእነርሱ ጥፋት ውጤት እንደሆነ ታስባላችሁ።

ግን፣ አጽንየት ሰጥቼ አንድ ነገር ልንገራችሁ - *ማንኛውም ወንድ፣ ማንኛዋም ሴት፣ ሕፃን ወይም ጋሬን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሊያወጣችሁ አይችልም!* ዕጣ ፈንታችሁ ያለው በእግዚአብሔር እንጂ፣ በማንም እጅ ውስጥ አይደለም። የዮሴፍ ወንድሞች እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ለማጥፋት ብዙ ጥረዋል። ዮሴፍን በተመለከተ ሁሉም ነገር ያበቃለት መስሏቸው ነበር። በገዛ አንደበታቸው፣ *‹‹...ኑ እንግደለውና ጉድጓድ ውስጥ እንጣለው... እሰቲ፣ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን››* ብለው ነበር (ዘፍጥረት 37÷20)። እርሱን ለማጥፋት ተዘጋጅተው ነበር፤ ነገሩ የታሰበበት እንጂ፣ በድንገት የተደረገ አልነበረም። ያሰቡት፣ ያለሙት እንዲጨናገፍ ሞክረው ነበር።

ወንድሞቹ ለባርት ሲሸጡት ሲመለከት እግዚአብሔር በመገረም፣ *‹‹እንግዲህ ምን ላድርግ፣ ዮሴፍን አስመልክቶ የነበረኝን ዕቅድ ወንድሞቹ አበላሽተውብኛል፤ ቶሎ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ››* የሚል ይመስላችኃል? አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሟቸው ብዙ ሰዎች በዚህ መልኩ የሚያስቡ ይመስላል።

ዮሴፍ እንደ ብዙዎቻችን ቢሆን ኖሮ፣ ወንድሞቹን መበቀል ስለሚችልበት መንገድ ያስብ ነበር። *‹‹አንዴ እጄ ይግቡ እንጂ፣ የእጃቸውን እሰጣቸዋለሁ፤ እንዳደረጉብኝ አደርግባቸዋለሁ፤ እንዲያውም እገድላቸዋለሁ››* በማለት ያስብ ነበር። ግን ዮሴፍ የዚህ ዓይነት ዝንባሌ ቢኖረው ኖሮ፣ እግዚአብሔር ከዚያ እስር ቤት እንዲወጣ አያደርግም ነበር። ምክንያቱም ወንድሞቹን መግደል ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አባቶችን መግደል ይሆን ነበር። ይህ ደግሞ ክርስቶስ የሚወለድበትን የይሁዳን ነገድ ይጨምራል።

አዎን፣ ያን ሁሉ በደል ዮሴፍ ላይ ያደረሱት የእስራኤል ነገድ አባቶች ናቸው። ትልቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር

ለአብርሃም ቃል ገብቶ ነበር። የሴፍ መበቀል አላሰበም፤ በእርሱም ሆነ በወንድሞቹ ሕይወት የእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጸመ።

ከዚህ የከፋ ይኖር ይሆን?

እስር ቤት ውስጥ የሴፍ ከባድ መከራ ቢደርስበትም፣ ጥሩ ዕድል ያገኘውም እዚያው እያለ ነበር። ከየሴፍ ጋር ሁለት ሰዎች ታስረው ነበር፤ ሁለቱም ሕልም አለሙ። የሴፍ ሕልማቸውን ፈታላቸው፤ ሕልማቸው በሚገርም ትክክለኛነት ተፈጸመ። በሕልሙ መሠረት አንደኛው ወደ ቀድሞ ሥራው ሲመለስ፣ ሌላው ግን መገደል ነበረበት። ወደ ቀድሞ ሥራው የሚመለሰውን ሰው በፈርዖን ፊት ሞገስ በሚያገኝ ጊዜ እርሱንም እንዲያስታውሰው የሴፍ ለመነው። ሰውየው ወደ ቀድሞ ቦታው ከተመለሰ ሁለት ዓመት ቢያልፈውም የሴፍን አላስታወሰውም። ይህ ለየሴፍ ሌላ ክህደት ነበር፤ ለመሰናከል ሌላ አጋጣሚ ሊሆን የሚችል ነበር።

ምን ጊዜም እግዚአብሔር ፅቅድ አለው

በኃላም አንድ ቀን ፈረዖን በጣም አስገራሚ ሕልም አለመ። አስማተኞቹና ጠቢባኑ ሕልሙን መፍታት አልቻሉም። ወደ ቀድሞ ሥራው የተመለሰው ሰውየ የሴፍ ትዝ ያለው ይኸኔ ነበር። እስር ቤት እያለ የእርሱንና የጓደኛውን ሕልም እንዴት እንደ ፈተላቸው ተናገረ። የሴፍ ወደ ፈርዖን ተወሰደ፤ ሕልሙ ስለሚመጣው የራብ ጊዜ እንደሚያመለክት ነገረው፤ ለዚያ ችግር እንዴት መዘጋጀት እንዳለበትም መከረው። ፈርዖን ወዲያውኑ የሴፍን ሾመው፤ በመላው ግብፅ ከእርሱ ቀጥሎ ሁለተኛው ሰው አደረገው። እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ የሴፍ እየመጣ ላለው ከባድ የራብ ጊዜ ተዘጋጀ።

በኃላም ራቡ በዘመኑ ይታወቁ ወደ ነበሩ ከተሞች ሁሉ በተዳረሰ ጊዜ ወንድሞቹ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ መጡ። የሴፍ ወንድሞቹ ላይ ቂም ይዞ ቢሆን ኖሮ፣ ያ ምቹ ጊዜ ይሆን ነበር። እስር ቤት ሊያስገባቸው፣ ሊያሰቃያቸው፣ ሌላው ቀርቶ ሊያስገድላቸው እንኳ ይችል ነበር፤ በግብፅ ሁለተኛው ሰው በመሆኑም ለምን እንዲህ ታደርጋለህ ብሎ ማንም አይጠይቀውም

ነበር። ዮሴፍ ግን ምንም ሳይከፍለ እህል ሰጣቸው። በኋላም በግብፅ ባለ ምርጥ ቦታ ለቤተ ሰባቸው መኖሪያ ሰጣቸው። ዮሴፍ የረገሙትን መረቀ፤ ክፉ ላደረጉበት መልካም አደረገ። (ማቴዎስ 5÷44 ይመ)።

እነርሱ ከማድረጋቸው በፊት እግዚአብሔር የዮሴፍ ወንድሞች የሚያደርጉትን ያውቅ ነበር። እንዲያውም ለዮሴፍ ሕልሙን ከመስጠቱ በፊት ወይም ከእነዚያ ሰዎች አንዱ እንኳ ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር የሚያደርጉትን ያውቅ ነበር።

እንደ ገና ሲገናኙ አንድ ርምጃ ወደ ፊት በመሄድ ዮሴፍ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ተመልከቱ። ‹‹አሁንም እኔን በመሸጣችሁ አትቆጩ፣ በራሳችሁም አትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል እኔን ወደዚህ ልኮኛል። በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፤ ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበስብባቸው አምስት ዓመታት ገና አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፉ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ። ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም›› አላቸው (ዘፍጥረት 45÷5-8)።

ዘማሪው የሚለውንም ተመልከቱ፣ ‹‹በምድሪቱ ላይ ራብ ጠራ፤ የምግብንም አቅርቦት ሁሉ አቋረጠ፤ በባርነት የተሸጠውን ሰው፣ ዮሴፍን ከእነርሱ አስቀድሞ ላከ›› (መዝሙር 105÷16-17)።

ዮሴፍን ወደ ግብፅ የላከው ማነው? ወንድሞቹ ወይስ እግዚአብሔር? ከሁለት ምስክሮች አፍ፣ የላከው እግዚአብሔር መሆኑን ተመልክተናል። ዮሴፍ ለወንድሞቹ በግልጽ፣ ‹‹ወደዚህ የላካችሁኝ እናንተ አይደላችሁም›› ብሏቸዋል። መንፈስ የሚለውን ስሙ!

ቀደም ብዬ እንዳልኩ፣ ማንኛውም ሚች ሰው ወይም ጋኔን በሕይወታችሁ ያለውን የእግዚአብሔር ዕቅድ ማጨናገፍ አይችልም። ይህን እውነት አጥብቃችሁ ብትይዙ ነጻ ያወጣችኃል።

ሆኖም፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሊያወጣችሁ የሚችል አንድ ሰው ብቻ አለ፤ ያም ሰው እናንተ ናችሁ!

የእስራኤልን ልጆች አስቡ። ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋው ምድር እንዲያደርሳቸው እግዚአብሔር አዳኝ ልኮላቸው ነበር። አንድ ዓመት በምድረ በዳ ከቆዩ በኃላ ምድሩን እንዲሰልሉ መሪዎች ተላኩ። የተላኩት ግን እያጉረመረሙ ተመለሱ። ከእነርሱ ይልቅ ግዙፎችና በሚሊታሪ ዐቅማቸው ጠንካሮች የነበሩትን በምድሩ የነበሩትን ሕዝብ ፈርተው ነበር።

ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ሕዝቡ ሁሉ ከመሪዎቹ ጋር ተስማሙ። ሕዝቡ እግዚአብሔር ከግብፅ ያወጣቸው ሊያጠፋቸው እንደ ሆነ አሰቡ። በሙሴና በእግዚአብሔር ተሰናከለ። ይህ ሁኔታ ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ ቀጥሎ ነበር። በእነርሱ መሰናከል፣ ያ ትውልድ እንደሚሰጣቸው እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ምድር በፍጹም እንዳያዩ ተደረጉ።

በከፍተኛ ተነሳሽነት እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ የነበሩ ብዙዎች፣ በክፉ ሰዎች ወይም በሥጋውያን ክርስቲያኖች በደል ስለ ደረሰባቸው በሕይወታቸው በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሰዎች በደል ተፈጽሞባቸዋል ይሁን እንጂ፣ ይህ መሰናከል እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ካለው ፈቃድ ለማውጣት ጠላት ያለውን ዓላማ ያስፈጽማል።

ከመሰናከል ራሳችሁን የምትጠብቁ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንደ ሆናችሁ ትዘልቃላችሁ። ከተሰናከላችሁ ግን የእርሱን ዓላማና ፈቃድ ለመፈጸም በምርኮ በጠላት ትወሰዳላችሁ። ከመሰናከል ነጻ ሆኖ መኖር በጣም ጠቃሚ ነው።

እግዚአብሔር ሳያውቀው በእኛ ላይ ምንም ነገር እንደማይደርስ ማስታወስ ይኖርብናል። እርሱ በፈለገ ጊዜ ሰይጣን እኛን ማጥፋት ቢችል ኖሮ፣ እርሱ የሰው ልጅን በጣም ስለሚጠላ ግና ዱሮ ጠራርጎ ያጠፋን ነበር። ምንጊዜም ይህን ቃል አትርሱ።

በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ

እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኃል።

- 1 ቆሮንቶስ 10÷13

‹‹መውጫ መንገዱን›› እንጂ፣ ‹‹ማምለጫ መንገዱን›› አለማለቱን ልብ አድርጉ። የቱንም ያህል ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን፣ እኛ ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ከባድ ሁኔታ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቀዋል፤ ከዚያ መውጣት የምንችልበትንም መንገድ ያዘጋጃል። እኛ በመታዘዝና ከመሰናከል ነጻ በመሆን ከጸናን፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ የተጨናገፈ መስሎ ቢታየን እንኳ፣ እንዲያውም ዕቅዱ የሚፈጸምበት መንገድ ይሆናል።

ስለዚህ ይህን አስታውሱ - ባለ መሰናከል ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ እርሱም ከእናንተ ይሸሻል (ያዕቆብ 4÷7)። ዲያብሎስን የምንቃወመው ባለ መሰናከል ነው። ሕልሙ ወይም ራእዩ እናንተ ካሰባችሁት በተለየ ሁኔታ ይፈጸም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ቃሉና ተስፋው በፍጹም ሳይፈጸም አይቀርም። ጭንገፋ የሚመጣው ባለ መታዘዝ ነው።

ሌላ ዓይነት ተላልፎ መሰጣጠት

ብዙዎች እንደ ዮሴፍ በወንድሞቻቸው በደል አልደረሰባቸውም። ያንን ያደረጉ ጠላቶቹ ቢሆኑ ኖሮ፣ ይህን ያህል አያምም ነበር። ያንን ያደረጉ ግን የሥጋና የደም ወንድሞቹ ነበሩ። እርሱን ማበረታታት፣ መደገፍ፣ መከላከልና ለእርሱ ማሰብ የነበረባቸው እርሱ ነበሩ። ዮሴፍ ላይ ከደረሰው የበለጠ በደል ይኖር ይሆን?

ከወንድም ወይም ከእኅት ንቀት

ወይም ጥላቻ ቢደርስ አንድ ነገር ነው፤

ንቀቱ ወይም ጥላቻው ከአባት ሲመጣ ግን

ፍጹም ሌላ ነገር ነው።

የመለስተኛና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህር ነኝ። በሕይወቴ በርካታ መገለጦችን የሰጠኝን *የሰይጣን ሸንገላ* የተሰኘውን መጽሐፍ በቅርቡ አንብቤአለሁ። ቪድዮውን ከተማሪዎቼ ጋር አብረን ተመልክተናል፤ እያንዳንዱ ሰው በደሉን እስኪናዘዝና የእግዚአብሔርን ይቅርታ እስኪጠይቅ ድረስ፣ የመንፈስ ቅዱስ ክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ በጣም ኃያል ነበር። ብዙ ተማሪዎች በዓመቱ ውስጥ ያሳለፉት ጥሩ ቀን ያ ቀን እንደ ነበር ተናግረዋል። አንዲት ልጅ በከፍተኛ ደረጃ ተጣልታው ከነበረ አባቷ ጋር ዕርቅ አደረገች። ሌላዋ ከሴት አያቷ ከደረሰባት ከባድ ቁስል የመፈወሷ ሂደት ጀመረ። እነዚያን ልጆች እግዚአብሔር ብርቱ በሆነ መንገድ በእውነት አገለገላቸው። ስለዚህ መልእክት በጣም አመሰግናለሁ።

- አር ኤፍ ኢንዲያና

4

አባቴ፣ አባቴ!

... አባቴ ሆይ፣... ክፉት ወይም ዐመፅ አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ፤ ተረዳልኝም፤ እኔ ክፉ አልሠራሁብህም፤ አንተ ግን ሕይወቴን ለማጥፋት እያሳደድኸኝ ነው።

- 1 ሳሙኤል 24÷11

ባለፈው ምዕራፍ የገዛ ወንድሞቹ ዮሴፍን ለማጥፋት ሞክረው እንደ ነበር ተመልክተናል። ከዚህ ክህደት የተነሣ የደረሰበትን ስብራት ተመልክተናል። ምናልባት፣ እናንተም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ትሆኑ ይሆናል። በጣም የቅርባችሁ በሆኑ ሰዎች፣ ፍቅርና ብርታትን ይሰጡናል ብላችሁ በጠበቃችኋቸው ሰዎች ተከድታችሁ ይሆናል።

በዚህ ምዕራፍ በገዛ ወንድሞች ከመከዳት የበለጠ አስከፊ ስለሆነ ጉዳትና ስብራት መናገር እፈልጋለሁ። አንድ ሰው በወንድሙ መናቁና መጠቃቱ አንድ ነገር ነው፤ በአባቱ መናቅና መጠቃቱ ግን ፍጹም የተለየ ነገር ነው። ስለ አባቶች ስናገር የግድ በሥጋ ስለ ወለዱን ሰዎች ብቻ መናገሬ ሳይሆን እኛን እንዲመሩ እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ሰዎች ሁሉ ማመልከቴ ነው። እነዚህ ሰዎች ይወዱናል፤ ያስተምሩናል፤ አስፈላጊውን ሁሉ ያሟሉልናል፣ ይጠነቀቁልናል ብለን የምናስባቸው ሰዎች ናቸው።

የፍቅር - የጥላቻ ግንኙነት

ክህደት ስለ ፈጸመ አንድ አባት ለመመልከት እስቲ በንጉሥ ሳኦልና በዳዊት መካከል የነበረውን ግንኙነት እንመልከት (1ኛ ሳሙኤል 16-31)። ነቢዩ ሳሙኤል ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ዳዊትን በቀባው ጊዜ ገና ከመገናኘታቸው በፊት እንኳ ሕይወታቸው

የተ፟ያ፟ያዘ ነበር። ሳሙኤል በቀባው ጊዜ፣ ‹‹ይኸ’ኮ ሳኦልን የቀባው ሰው ነው፤ ስለዚህም እኔም በእርግጥ ንጉሥ ልሆን ነው!›› በማለት ሳ፟ያስብና ሳ፟ይጓጓ አልቀረም።

በእግዚአብሔር በማመፁ ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረው ሳኦልን ክፉ መንፈስ እ፟ያሰ፟ቃየው ነበር። ስ፟ቃዩ ሻል የሚለው አንድ ሰው በገና ሲ፟ጫወትለት ነበር። አገል፟ጋዮቹ እፊቱ ተቀምጠ እርሱን የሚ፟ያገለግል ወጣት ሰው መፈለግ ጀ፟ምረው ነበር። ከንጉሡ አገል፟ጋዮች አንዱ ለዚሁ ተግባር የእሴ፟ይ ልጅ ዳዊትን ጠቆመ። ወደ ቤተ መንግሥት መጥቶ እንዲ፟ያገለግለው ሳኦል ወደ ዳዊት መል፟እክተኛ ላከ።

ምናልባትም ዳዊት፣ *በነቢዩ በኩል የተ፟ገ፟ባ፟ልኝ ተስፋ ቃል መፈጸም እየ፟ጀመረ ነው።* *ያለ ጥርጥር በንጉሡ ዘንድ ሞገስ እ፟ያገኘሁ ነው።* *አ፟ዎን፣ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ የምልበት ጊዜ መጥቶአል* በማለት አሰበ ይሆናል።

አንድ ቀን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ውጊ፟ያ ላ፟ይ ለነበሩ ታላላቅ ወንድሞቹ አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች ይዞላቸው እንዲሄድ አባቱ ዳዊትን አዘዘው። ጦርነቱ ቦታ ሲደርስ ታላቁ ፍልስጥኤማዊ ጦረኛ ጎ፟ልያድ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላ፟ይ ሲ፟ያላግጥ አየ፤ ይህም ዐ፟ርባ ቀን ሙሉ እንደዚ፟ያው እንደ ነበር ተረዳ። ይህን ታላቅ ጦረኛ ለሚ፟ያሸንፍ ልጁን እንደሚ፟ድርለት ንጉሡ ቃል ገብቶ እንደ ነበረም ሰማ።

ወደ ንጉሡ ሄዶ ያንን ጦረኛ ለመግጠም እንዲ፟ፈቅ፟ድለት ጠየቀ። ጎ፟ልያድን ገደለ፤ በተገባው ቃል መሠረትም የሳኦልን ልጅ አገባ። በዚ፟ያ ጊዜ በሳኦል ዘንድ መወደድን አግ፟ኝቶ ነበር፤ በንጉሡ ቤተ መንግሥትም መኖር ጀ፟ምሮ ነበር። የሳኦል ልጅ ዮ፟ናታን ከዳዊት ጋር ዘላለማዊ የወዳ፟ጅ፟ነት ኪዳን አደረገ። ሳኦል ለዳዊት በሚሰጠው ሥራ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር እ፟ጅ በእርሱ ላ፟ይ ነበር፤ ይከ፟ናወ፟ንለትም ነበር። ከገዛ ልጆቹ ጋር በአንድ ጠረ፟ጴዛ ዙሪ፟ያ ተቀምጠ እንዲመገብ ንጉሡ አዘዘ።

በተደረገለት ሁሉ ዳዊት በጣም ተደነቀ። ቤተ መንግሥት ውስጥ እየኖረ ነበር፤ ከንጉሡ ማዕድ ይመገባል፤ በዚህ ላይ የንጉሡን ልጅ አግብቶአል፤ የንጉሡ ወንድ ልጅ የዮናታን ጥብቅ ጓደኛ ሆኖአል፤ በዚህ ላይ ደግሞ በሚያደርገው ዘመቻ ሁሉ እየተሳካለት ነበር። ሌላው ቀርቶ በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ መወደድን አግኝቶ ነበር። የተነገረለት ትንቢት በዐይኖቹ ሥር እየተፈጸመ ነበር።

ሳኦል ከሌሎቹ አገልጋዮቹ ሁሉ አስበልጦ ዳዊትን ያቀርበው ነበር። አባት ሆኖለት ነበር። ሳኦል እንደሚያስተምረው፣ እንደሚያሠለጥነውና አንድ ቀን በታላቅ ክብር ዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጠው ዳዊት እርግጠኛ ነበር። በእግዚአብሔር ታማኝነትና መልካምነት ዳዊት ደስ ተሰኝቶ ነበር። በአንድ ቀን ውስጥ ግን ነገር ሁሉ ተለወጠ።

ሳኦልና ዳዊት ጐን ለጐን ሆነው ከጦርነት ዐውደ ግንባር ሲመለሱ፣ ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ የመጡ ሴቶች፣ ‹‹ሳኦል ሺህ ገደለ፤ ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ›› በማለት እየዘፈኑና እየጨፈሩ ተቀበሏቸው። ይህ ሳኦልን አስቆጣው፤ ከዚያ ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ ጥላቻ አደረበት። ዳዊት በገና እየደረደረለት እያለ ሳኦል ሁለት ጊዜ ሊገድለው ሞክሮ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሳኦል ዳዊትን የጠላው እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደ ነበረና ከእርሱ ጋር ግን እንዳልነበረ በማወቁ ነበር። ዳዊት ሸሽቶ ሕይወቱን ማዳን ግድ ሆነበት፤ ሌላ የሚሄድበት ቦታ ስላልነበረው ወደ ምድረ በዳ ሸሸ።

‹‹እንዴ፣ ምን እየሆነ ነው?›› በማለት ዳዊት ግራ ተጋባ። ‹‹የተገባልኝ ተስፋ ቃል እየተፈጸመ ነበር፤ አሁን ግን ሁሉም እንዳልነበር ሆነ። አስተማሪዬና አሠልጣኜ የምለው ሰው ሊገድለኝ እየፈለገ ነው። ታዲያ፣ ምን ላድርግ? ሳኦል የተቀባ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው። እርሱ በጠላትነት ከተነሣብኝ ሌላ ምን ዕድል አለኝ? እርሱ ንጉሥ ነው፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾመ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ግን፣ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ እንዲሆን ፈቀደ?››

ሦስት ሺህ ምርጥ የእስራኤል ጦረኞች ይዞ ከአንዱ ምድረ በዳ ወደ ሌላው ምድረ በዳ፣ ከአንዱ ዋሻ ወደ ሌላው ዋሻ፣ ሳኦል ዳዊትን አሳደደ። ዓላማቸው አንድ ብቻ ነበር - ዳዊትን ማጥፋት።

በዚህ ጊዜ የተስፋ ቃሉ እንደ ጉም በነነ። ከእንግዲህ ዳዊት በቤተ መንግሥት አይደለም፤ ከንጉሡ ማዕድ እየተመገበ አይደለም። ወና ዋሻዎች ውስጥ መኖርና የዱር ፍሬዎች መመገብ ጀመረ። ከእንግዲህ ከንጉሡ ጋር ጦን ለጦን አይሄድም፤ ይልቁን በአንድ ወቅት እጦኑ ሆነው ሲዋጉ በነበሩት ወዳጆች እየታደነ ነው። የሞቀ አልጋ የለም፤ የሚታዘዙት አሽከሮች የሉም፤ በቤተ መንግሥት የነበረው ምቾት ሁሉ ቀርቷል። ሚስቱ ለሌላ ተድራለች። አንድ አገር የሌለው ሰው ላይ የሚደርስበት ብቸኝነት እርሱም ላይ ደርሷል።

ልብ አድርጉ፤ ዳዊትን ከሳኦል ጥበቃ ሥር ያደረገው እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አልነበረም። ታዲያ፣ እንዲህ እንዲሆን መፍቀድ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ያንን ያቀደው ለምንድነው? በአንድ ወቅት የነበረውን ክብር በድንገት አጥቷል። ይህ ሁሉ በሳኦል ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ በእግዚአብሔርም ጭምር እንዲሰናከል ለዳዊት ምቹ አጋጣሚ ነበር። መልስ ያላገኘላቸው ጥያቄዎች እየበዙ መጡ፤ የእግዚአብሔርን ጥበብና ዕቅድ ለመጠራጠር ተፈተነ።

ማንኛውንም ዋጋ በመክፈል ይህን ወጣት ለመግደል ሳኦል ቆርጦአል፤ ያንን ካላደረገ ዐርፎ የሚተኛም አይመስልም። ኖብ በሚባል ከተማ የነበሩ ካህናት ለዳዊት ምግብ፣ መጠለያና በአንድ ወቅት የጦልያድ የነበረውን ሰይፍ ሰጡት። ከሳኦል ፊት እየሸሸ መሆኑን ካህናቱ አያውቁም ነበር፤ እንዲያውም የንጉሡን ሥራ ለመፈጸም ወደዚያ የመጣ መስሏቸው ነበር። ዳዊትን በተመለከተ እግዚአብሔርን ጠየቁ፤ ከዚያም ወዳሰበበት እንዲሄድ አሰናበቱት።

ሳኦል ይህን ሲሰማ በጣም ተቆጣ። ሰማንያ አምስት ንጹሐን የጌታ ካህናት ገደለ፤ በኖብ ከተማ የነበሩ ማንኛውንም ወንድ፣ ሴት፣ ልጅ፣ የሚጠባ ሕፃን፣ ላም፣ አህያና በጦችን ሁሉ ጨፈጨፈ፤ አማሌቃውያን ላይ ማድረግ የነበረበትን በእነዚያ ምስኪኖች ላይ

አደረገ። እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነበር። ታዲያ፣ መጀመሪያውኑ እግዚአብሔር በእንዲህ ያለ ሰው ላይ መንፈሱን ያሳረፈው ለምንድነው?

አንድ ጊዜ ዳዊት በዓይንጋዲ ምድረ በዳ እንደ ነበር ሳኦል ዐወቀ፤ ስለዚህም ሦስት ሺህ ጦረኞች አስከትሎ ያሳድደው ያዘ። ጉዞ ላይ እያለ ዳዊት ውስጡ መደበቁን ሳያውቁ በአንድ ዋሻ መግቢያ ላይ ዕረፍት አድርገው ነበር። ዳዊት ቀስ ብሎ ከተደበቀበት ወጥቶ የሳኦልን ልብስ ጫፍ ቆረጠና ማንም ሳያውቅ ሾልኮ ሄደ።

ሳኦል ከዋሻው ለመሄድ ሲነሣ ዳዊት ወደ መሬት ጐንበስ ብሎ እጅ እየነሣ፣ ‹‹አባቴ ሆይ፣ የልብስህ ቁራጭ ይኸው በእጄ ላይ ተመልከተው!... አሁንም ክፋት ወይም ዐመፅ አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ ተረዳልኝም፤ እኔ ክፉ አልሠራሁብህም፤ አንተ ግን ሕይወቴን ለማጥፋት እያሳደድኸኝ ነው›› በማለት ፊኸ (1 ሳሙኤል 24÷11)።

ዳዊት ወደ ሳኦል የፊኸው፣ ‹‹አባቴ፣ አባቴ!›› እያለ ነበር። በጣም ግልጽ በሆነ አነጋገር፣ ‹‹ልቤን እየው! እባክህ አባት ሁነኝ። የሚያጠፋኝ ሳይሆን፣ የሚያሠለጥነኝ መሪ እፈልጋለሁ!›› ማለቱ ነበር። ሳኦል ሊገድለው እያሳደደው እያለ እንኳ የዳዊት ልብ አሁንም በተስፋ እንደ ተሞላ ነበር።

አባቶች ወዴት አሉ?

አያሌ ክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች ይህ ዓይነቱን ፈኸት ሲያሰሙ ታዝቤአለሁ፤ አብዛኞቹ ወጣቶችና የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ናቸው። እውነተኛ አባት፣ ደቀ መዝሙር የሚያደርጋቸው፣ የሚወዳቸው፣ የሚደግፋቸውና የሚያበረታታቸው ሰው ይፈልጋሉ። ‹‹መጥቼ ምድርን በርግማን እንዳላጠፋ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች (መሪዎች)›› እመልሳለሁ በማለት እግዚአብሔር የተናገረው በዚህ ምክንያት ነው (ሚልክያስ 4÷6)።

ካለፉት ዓመታት ወዲህ አገራችን አባቶች (ማለትም፣ አስተዋይ መካሪዎችና አሳዳጊ መንፈሳዊ መሪዎች) አጥታለች፤ ዛሬ

ሁኔታችን አስከፊ እየሆነ መጥቷል። በቤተ ሰብ፣ በቤተ ክርስቲያንና በትምህርት ቤቶች ያሉ አብዛኞቹ መሪዎች ተተኪ ትውልድ ከማፍራት ይልቅ የራሳቸውን ግብ በማሳካቱ ሥራ ተጠምደዋል።

ከዚህ ዝንባሌ የተነሣ እነዚህ መሪዎች ራእያቸውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደ ማገልገያ መሣሪያ ከመጠቀም ይልቅ የራእያቸው ማስፈጸሚያ ገንዘብ ማግኛና መጠቀሚያ አድርገዋቸዋል። የእነርሱ ራእይ እስከ ተሳካ ድረስ፣ የሕዝቡ ስብራትና ኪሳራ ለእነርሱ ምንም ማለት አይደለም። ፍትሕ፣ ምሕረት፣ ታማኝነትና ፍቅር በሌለበት ሁኔታ እንኳ ቢሆን፣ ስኬት ከተገኘ ሁሉም ነገር ትክክል እንደ ሆነ ያስባሉ። ውሳኔዎች የሚደረጉት ገንዘብን፣ የተከታይ ቁጥር ብዛትንና ውጤትን መሠረት በማድረግ ነው።

ይህ ደግሞ ዳዊት ላይ ለደረሰው ዓይነት ክህደት መንገድ ይከፍታል፤ ሳኦል ዳዊት ላይ በደል የፈጸመው ለመንግሥቱ በማሰብና በመቆጨት ነበር። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በእነዚህ መሪዎች ተቀባይነት አለው፤ ምክንያቱም እነርሱ የሚፈልጉት "ወንጌል" መስፋፋቱን ነው።

ካደረባቸው ጥርጣሬ የተነሣ አብረዋቸው ያሉ ሰዎችን የጐዱ ምን ያህል መሪዎች ይኖሩ ይሆን? እነዚህ መሪዎች ተጠራጣሪዎች የሆኑት ለምንድነው? የእግዚአብሔር ሳይሆን፣ የራእያቸው አገልጋዮች ስለሆኑ ነው። እንደ ሳኦል ሁሉ ጥሪያቸውን ይጠራጠራሉ፤ ያ ደግሞ ቅንዓትና ትዕቢት ያመጣል። አንዳንድ ሰዎች ውስጥ ከእግዚአብሔር የሆኑ ባሕርያት ያያሉ፤ ለእነርሱ እስከ ጠቀመ ድረስ በእነዚህ ሰዎች መጠቀም ይፈልጋሉ። ለመንግሥቴ ስጋት ነው ብሎ እስካሰበበት ጊዜ ድረስ ሳኦልም ቢሆን፣ በዳዊት ስኬት ደስተኛ ነበር። በኋላ ግን ዳዊትን ከደረጃው አወረደው፤ እርሱን የሚገድልበት ምክንያትም ይፈልግ ጀመር።

በነገራቸው ሁሉ ተጠያቂ የሚሆኑለት ሰው ከሚፈልጉ አያሌ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ጋር ተነጋግሬአለሁ። እነዚህ ወጣቶች ደቀ መዝሙር ለሚያደርጋቸውና ለሚያሳድጋቸው መሪ ራሳቸውን ማስገዛት ይፈልጋሉ። የፈለጉትን ባለ ማግኘታቸውም ብቸኝነትና

ነጠላነት ይሰማቸዋል። ይሁን እንጂ፣ በዳዊት ያደረገውን እግዚአብሔር በእነርሱም ሕይወት ማድረግ ስለሚፈልግ በእንዲህ ዓይነት መጣል ክህደት እንዲያልፉ ይፈቅዳል። መንፈስ የሚናገረውን በጥንቃቄ አድምጡ።

ሳኦል እርሱን እንደ ዐመፀኛና ክፉ ሰው መቁጠሩ ዳዊትን በጣም አሳስቦት ነበር። ‹‹የፈጸምኩት በደል ምንድነው?›› በማለት ዳዊት ብዙ ጊዜ ልቡን ሳይመረምር አልቀረም። ‹‹አንተን እንድገድል ሰዎች ገፋፍተውኝ ነበር፤ እኔ ግን አይሆንም አልኩ። እኔ ያደረግሁት ነገር ቢኖር፣ የልብስህን ጫፍ ቆርጬ መውሰድ ብቻ ነው፤ ክፋት ወይም ዐመፅ አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ፤ ተረዳልኝም›› በማለት የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር (1 ሳሙኤል 24÷11)። ለሳኦል ያለውን ፍቅር ግልጽ ካደረገ፣ ወደ ቀድሞ ቦታው እንደሚመልሰውና ትንቢቱም እንደሚፈጸም ዳዊት አስቦ ነበር።

አባታችው ወይም የሚያምኑት መሪያችው የጠላችውና የናቃችው ሰዎች ብዙ ጊዜ ጥፋቱን ራሳችው ላይ ያደርጋሉ። ምን አጠፋሁ? ልቤ ንጹሕ አይደለም ይሆን? የሚሉ ሐሳቦች እስረኛ ይሆናሉ። አንዳንዴም፣ ለመሆኑ መሪው እኔ ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደረገ ማን ይሆን? በማለት ያስባሉ። ከዚያም ንጽሕናችውን ለመሪዎቻችው ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ። የእነርሱን ታማኝነትና አስፈላጊነት ካሳዩ፣ ተቀባይነት የሚያገኙ ይመስላቸዋል። አሳዛኙ ግን፣ ብዙ ሙከራ ባደረጉ መጠን፣ በዚያው ልክ የተናቁና የተረሱ የሚመስላቸው መሆኑ ነው።

ማን ይበቀልልኛል?

ሊገድለው ሲችል እርሱን አለመግደሉን ሲረዳ ዳዊት ጥሩ ሰው መሆኑን ሳኦል ተቀብሎ ነበር። ስለዚህም እርሱና አብረውት የነበሩ ሰዎች ከዚያ ቦታ ሄዱ። *ከእንግዲህ ንጉሡ ወደ ቦታዬ ይመልሰኛል፤ የተነገረልኝ ትንቢት በቅርቡ ይፈጸማል። በእርግጥ የልቤን ንጽሕና ያያል፤ በደለኛ አለመሆኔንም ያውቃል* በማለት ዳዊት አሰበ ይሆናል።

ግን ተሳስቶአል። ብዙም ሳይቆይ ዳዊት በኤኬላ ተራራ እንዳለ ሰዎች ለሳኦል ነገሩት። አሁንም ሳኦል ሦስት ሺህ ወታደሮች አስከትሎ ዳዊን ማሳደዱን ቀጠለ። ይህ ዳዊትን በጣም ሳያስቆጣው እንድልቀረ እርግጠኛ ነኝ። እውነቱን ባለ መረዳት ሳይሆን፣ በዓላማ የእርሱን ሕይወት ማጥፋት እየፈለገ መሆኑ በጣም ግልጽ ሆነለት። በዚያ ጊዜ የዳዊት ልብ ምንኛ ተጐድቶ ይሆን? በመሠረቱ ሳኦል የዳዊትን ልብ ቅንነት ያውቃል፤ ያም ሆኖ ግን እርሱን ማጥፋት እየፈለገ ነው።

አቢሳን አስከትሎ ዳዊት ሳኦል ሰፈረበት ቦታ ሹልክ ብሎ ገባ። እግዚአብሔር ጭልጥ ያለ እንቅልፍ እንዲወስዳቸው አድርጐ ስለ ነበር አንድ ጠባቂ እንኳ አላያቸውም። ሁለቱ ሰዎች ሳኦል ተኝቶ ወደ ነበረበት ድንኳን ገቡ። አቢሳ ለዳዊት ‹‹ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ ላይ ጥሎታል፤ አሁንም እኔ አንድ ጊዜ በጦር ወግቼ ከመሬት ጋር ላጠብቀው፤ መድገምም አያስፈልገኝም!›› አለው (1ኛ ሳሙኤል 26÷8)።

ሳኦልን መግደል እንዲፈቅደለት ዳዊትን ለመጠየቅ አቢሳ በቂ ምክንያት ነበረው። በመጀመሪያ ሳኦል ሰማንያ አምስት ንጹሐን ካህናትን በግፍ ገድሎአል!

ሁለተኛ፣ ሳኦል ዳዊትና ተከታዮቹን ለመግደል ሦስት ሺህ ወታደሮች አስከትሎ መጥቷል። ጠላትን ቀድመህ ካልገደልከው እርሱ እንደሚገድልህ የታወቀ ነው የሚል ነበር የአቢሳ ምክንያት። ይህ ደግሞ ራስን ማዳን ነው። ማንኛውም ፍርድ ቤት አልሞት ባይ ተጋዳይነትን ይቀበላል!

ሦስተኛ፣ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን በነቢዩ ሳሙኤል በኩል እግዚአብሔር ዳዊትን ቀብቶታል።

አራተኛ፣ ዳዊትና አቢሳ ያለ አንዳች ችግር ሰተት ብለው ሳኦል ተኝቶ ወዳለበት ቦታ እንዲገቡ ሰራዊቱ ሁሉ እንዲያንቀላፋ ያደረገ እግዚአብሔር ነበር። ሳኦል እንዲገደል ባይፈልግ ኖሮ፣ እግዚአብሔር ለምን እንደዚያ አደረገ? በአቢሳ አስተሳሰብ ዳዊት በዚህ ዕድል ካልተጠቀመ፣ ከእንግዲህ እንዲህ ያለ ዕድል አያገኝም።

ምክንያቶቹ ትክክል ይመስላለ።። ምክንያቶቹ አሳማኝ ናቸው፤ በዚህ ላይ ደግሞ ሐሳቡ የመጣው እንደ ወንድሙ ከሚቆጥረው ወዳጁ ነበር።። ዳዊት ቂምና ጥላቻ ቢኖረው ኖሮ፣ ሙሉ በሙሉ ትክክል እንደ ሆነ ይቀበል ነበር፤ አቢሳ ሳኦልን በጦር ወግቶ እንዲገድለው ይፈቅድለት ነበር።።

ግን የዳዊትን መልስ ስሙ፣ ‹‹አትግደለው! እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን አንሥቶ ከበደል ነጻ የሚሆን ማን ነው? ... ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ራሱ ይቀሥፈዋል ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል ወይም በጦርነት ይሞታል።። እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን ከማንሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ!›› (1 ሳሙኤል 26÷9-11)።።

ንጹሐን ሰዎችን የገደለ፣ እርሱንም ለመግደል እያሳደደ ቢሆን እንኳ፣ ዳዊት ሳኦልን መግደል አልፈለገም።። በቀልን ለእግዚአብሔር ተወ እንጂ፣ ዳዊት አልተበቀለም።።

እውነት ነው፣ ነገሩ እዚያ ላይ እንዲያበቃ ማድረግ ለዳዊትም ሆነ ለእስራኤል ሕዝብ ቀላል ነበር።። ሕዝቡ እረኛ እንደሌለው መንጋ ሆኖ እንደ ነበር ያውቃል።። ለጨካኝ ተኩላ ጥቃት ተጋልጠው እንደ ነበረም ያውቃል።። ለራሱ አለመከላከል ለዳዊት ከባድ ነበር፤ የሚወደውን ሕዝብ ከእብድ ንጉሥ አለመታደግ ደግሞ ከዚያ የበለጠ ለእርሱ ከባድ ነበር።። ሳኦል እፎይ የሚለው እርሱን በመግደል ብቻ እንደ ሆነ ቢያውቅም፣ ዳዊት ግን እርሱን ላለመግደል ወሰነ።።

መጀመሪያ ላይ እርሱን ባለ መግደሉ ዳዊት የልቡን ንጽሕና አሳየ።። ሳኦልን ለመግደል ሁለተኛ ዕድል ቢገጥመውም፣ እርሱ ያንን ማድረግ አልፈለገም።። ሳኦል በእግዚአብሔር የተቀባ ነበር፤ ስለዚህ ፍርዱን ለእግዚአብሔር ተወ።።

በዚህ ዘመን የዳዊት ዓይነት ልብ ያለን ስንቶቻችን ነን? ምናልባት በጥይት ሰዎችን አልገደልንም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ በሌላ ጥይት - በምላሳችን እርስ በርስ እንገዳደላለን።። ‹‹አንደበት (ምላስ) የሞትና የሕይወት ኃይል አላት›› (ምሳሌ 18÷21)።።

ከጉዳትና ተስፋ መቁረጥ የተነሣ በሚሰነዘሩ ቃሎች ቤተ ክርስቲያን ይበጠበጣል፤ ቤተ ሰብ ይከፋፈላል፤ ትዳር ይፈርሳል፤ ፍቅር ይጠፋል። በቤተ ሰብ እና በመሪዎች ከደረሰብን በደል የተነሣ በምሬትና በቁጣ በተሳለ ቃሎች መልሰን እንዋጋለን። ያለን መረጃ እርግጠኛና ትክክለኛ ቢሆንም፣ ዓላማችን ንጹሕ ላይሆን ይችላል።

ምሳሌ 6÷16-19 በወንድማማች መካከል ጠብና መለያየትን መዝራት በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ እንደ ሆነ ይናገራል። ሆን ብለን መለያየትን ለመፍጠር፣ የሰዎችን ጎብረት ወይም መልካም ስም ለማጥፋት፣ አንድን ነገር የምንደጋግም ከሆነ፣ ነገሩ እውነት ቢሆን እንኳ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው።

የመሪውን ኃጢአት ለመግለጥ እግዚአብሔር እየተጠቀመብኝ ይሆን?

እኔና ሚስቴ ወደ አሁን አገልግሎታችን ከመግባታችን በፊት ሰባት ዓመት ሙሉ የርዳታ አገልግሎት ውስጥ ነበርኩ፤ የወጣቶች ፓስተርም ነበርኩ። የወጣቶች ፓስተር በነበርኩ ጊዜ እኔን ወይም የማቀርበውን መልእክት የማይወድ አንድ ሰው ነበር። እንደ ማንኛውም ሰው ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል አያሳስበኝም ነበር፤ ይህ ሰው ግን እኔ ላይ ሥልጣን ያለው ሰው ነበር።

ለወጣቶች ጠንከር ያለ የንጽሕናና የቅድስና መልእክት እንዳቀርብ እግዚአብሔር ልቤ ውስጥ እንዳኖረ እምነት ነበረኝ፤ የዚያ ሰው ልጅ ደግሞ እኔ የማስተምራቸው ወጣቶች ቡድን ውስጥ ነበር።

የዚህ ወጣት ልብ በመልእክቱ በጣም ተነካ። አንድ ቀን ወደ እኛ መጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ። እርሱም ሆነ ሌሎች ወጣቶች እንዲከተሉ ከማስተምረው አንጻር እቤቱ የሚያየው አኗኗር በጣም የወረደ መሆኑ ረብሾት ነበር።

ይህ ሁኔታና ሌሎች የሰብዕና ግጭቶች እኔን ከዚያ ማስወገድ እንዳለበት ያንን ሰው ወደ ውሳኔ አድርሶት ነበር። ወደ ዋናው ፓስተር እየሄደ እኔ ላይ እንዲቆጣ የሐሰት ክሶች ያቀርብብኝ

ነበር። ከዚያም ወደ እኔ እየመጣ፣ ዋናው ፓስተር እኔን በጣም እንደ ተቆጣና እርሱ ግን እኔን በመደገፍ እንደ ቆመ ይነግረኝ ነበር። እኔ ፊት ፈገግተኛ ይሆናል፤ ፍላጐቱ ግን እኔን ማጥፋት ነበር።

አንዳንድ ወጣቶች ወደ እኔ እየመጡ ከዚያ ቦታ ልባረር መሆኑን እንደ ሰሙ ይነግሩኝ ነበር። ያንን ወሬ እያስፋፉ የነበረው የዚያ ሰው ልጅ ሲሆን፣ ያንን የሚያደርገው እቤት የሰማውን መልሶ እያወራ እንጂ እኔን ለመጉዳት አልነበረም። በጣም ተቆጣሁ፤ ግራ ተጋባሁ። ወደዚያ ሰው ሄጄ ለምን እንደዚያ እንደያሚደርግ ጠየቅሁት፤ እርሱም እንደዚያ ማድረጉን ቢያምንም ራሱ የፈጠረው ሳይሆን፣ የተናገረው ዋናው ፓስተር ሲል የሰማውን እንደ ሆነ ነገረኝ።

በዚህ ሁኔታ ወሮች አለፉ፤ ሁኔታው ግን ምንም ዓይነት መሻሻል አያሳይም ነበር። ሌላው ቀርቶ፣ ያ ሰው በእኔና በዋናው ፓስተር መካከል የነበረ ግንኙነት እንኳ እንዲቋረጥ አደረገ። እንዲህ የሚያደርገው እኔ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ የማይፈልጋቸው ሌሎች ፓስተሮችም ላይ ነበር።

በዚያ ቤተ ክርስቲያን ማገልገሌን መቀጠል ወይም ማቋረጥ ያለብኝ መሆኑን ባለ ማወቃችን ቤተ ሰቤ ላይ ውጥረት ተፈጠረ። አዲስ ቤት ገዝተን ነበር፤ ሚስቴም እርጉዝ ነበረች፤ በወቅቱ ምንም የምንሄድት ቦታ አልነበረንም። ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን የመራኝ እግዚአብሔር መሆኑን በጣም አምን ስለ ነበር እዚያው መቆየት እንጂ፣ ጥሎ የመሄድ ዕቅድ አልነበረኝም።

ሚስቴ በሁኔታው በጣም አዝና ነበር። ‹‹ከአገልግሎት እንደሚያግዱህ አውቃለሁ፤ ሁሉም የሚነግሩኝ ያንን ነው›› አለችኝ።

‹‹እነርሱ አልቀጠሩኝም፤ እግዚአብሔር ካልፈቀደ እኔን ማባረር አይችሉም›› አልኳት። እውነታውን ለመካድ እየሞከርኩ እንደ ሆነ ስላሰበች፣ የዚያ ቤተ ክርስቲያን ሥራዬን እንዳቋርጥ አጥብቃ ለመነችኝ።

በመጨረሻ፣ እኔን ለማሰናበት ውሳኔ የመደረጉ ወሬ ተሰማ። በወጣቶቹ ቡድን ለውጥ መደረጉን ዋናው ፓስተር ለቤተ ክርስቲያኑ ሰዎች ተናገረ። ያኔም ቢሆን እኔ ላይ ከሾመው ሰው ጋር ስለ ተፈጠረው አለ መግባባት ከእርሱ ጋር አልተነጋገርኩም ነበር። ከእርሱና ከዚያ ሰው ጋር በሚቀጥለው ቀን እንድነጋገር ቀጠሮ ተያዘ። ለራሴ በመከራከር ምንም እንዳልናገር እግዚአብሔር በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ልቤ ላይ አኑሮ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ከፓስተሩ ጋር ስገናኝ፣ ብቻውን ቢሮ ውስጥ ሆኖ በማግኘቴ ገርሞኝ ነበር። ፊት ፊቴን እያዬ፣ ‹‹ጆን፣ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን የመራህ እግዚአብሔር ነው፤ ትተኸን እንድትሄድ አልፈልግም›› አለ።

እፎይታ ተሰማኝ። በመጨረሻው ሰዓት እግዚአብሔር ተከላከለልኝ።

‹‹ይኸ ሰውዬ የጠመደህ ለምንድነው?›› በማለት ጠየቀኝ። ‹‹እባክህን ወደ እርሱ ሂድና በመካከላችሁ ያለውን አለ መግባባት ፍቱ።።።››

ከዚያ ግንኙነት ጥቂት ቀን በኋላ፣ የእኔን አገልግሎት በተመለከተ ያ ሰው ስለሳለፈው ውሳኔ የሚያሳይ በጽሑፍ የሰፈረ ማስረጃ አገኘሁ። ማስረጃው እውነተኛ ዓላማውን የሚያሳይ ነበር። ያንን ለዋናው ፓስተር ለማሳየት ተዘጋጅቼ ነበር። በዚያ ቀን የነበረኝን መጥፎ ስሜት ማሸነፍ እንድችል ወዲያ ወዲህ እያልኩ ለዐርባ አምስት ደቂቃ ያህል እየጸለይኩ ነበር። ‹‹ደጋግሜ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ ሰው ቅንነት የሌለውና ክፉ ሰው ነው። ይህን አገልግሎት ለማጥፋት ታጥቆ ተነሥቷል። እውነተኛ ማንነቱን ለዋናው ፓስተር መንገር አለብኝ!›› እያልኩ ነበር።

እርሱን ለማጋለጥ የነበረኝን ፍላጐት ተገቢ ለማድረግ ብዙ ተናገርኩ። ‹‹መናገር የምፈልገው ሁሉ ትክክልና የጽሑፍ ማስረጃ ያለው እንጂ ስሜታዊ አይደለም። ቶሎ ካላስቆምነው የዚህ ሰው ክፋት ቤተ ክርስቲያኑን ሁሉ መበከሉ አይቀርም።።››

በመጨረሻ፣ ብዙም ሳላስብ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ይኸን ሰው እንዳጋልጥ አትፈልግም አይደል?›› አልኩ።

ግና እንዲህ ሲል የእግዚአብሔር ሰላም ልቤን ሞላው። በመገረም ራሴን ነቀነቅሁ። ምንም ነገር እንዳደርግ እግዚአብሔር እንደማይፈልግ በጣም እርግጠኛ ሆንኩ፤ ያንን ማስረጃ ቀዳድጄ ጣልኩ። በኋላ ላይ ረጋ ብዬ ሁኔታውን ስመለከተው አገልግሎት ውስጥ ላለ ሌላ ሰው ከመከላከል የበለጠ እኔ ራሴ የመበቀል ፍላጐት እንደ ነበረኝ ተረድቻለሁ። ዓላማዬ ራስ ወዳድነትን መሠረት ያደረገ አለመሆኑን እንደ ምክንያት በማቅረብ ራሴን አሳምኜዋለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነም፣ የነበረኝ ማስረጃ ትክክል ነበር፤ ዓላማዬ ግን ንጹሕ አልነበረም።

ጊዜ አለፈ፤ አንድ ቀን ወደ ቢሮ ከመግቢያ ሰዓት በፊት ከቤተ ክርስቲያኑ ውጪ ሆኜ እየጸለይኩ እያለ ሰውየው በመኪና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ አየሁ። ወደ እርሱ ሄጄ ራሴን በፊቱ ዝቅ እንዳደርግ እግዚአብሔር ወደ ልቤ ሐሳብ አመጣ። ወዲያውኑ ለራሴ መከራከር ጀመርኩ። ‹‹ጌታ ሆይ፣ እንደዚያማ አይሆንም፣ ይህን ሁሉ ችግር የፈጠረ እርሱ ነው፤ ወደ እኔ መምጣት ያለበት እርሱ እንጂ እኔ አይደለሁም።››

መጸለይ ቀጠልኩ፤ ይሁን እንጂ፣ ወዲያውኑ ወደ እርሱ በመሄድ ራሴን በፊቱ ዝቅ እንዳደርግ እግዚአብሔር በድጋሚ አሳሰበኝ። ያ ሐሳብ ከእግዚአብሔር እንደ ነበር ዐውቃለሁ። ቢሮዬ ሆኜ ደወልኩለትና ወደ እርሱ ቢሮ ሄድኩ። ሆኖም፣ እግዚአብሔር ባይናገረኝ ኖሮ የተናገርኩትና የተናገርኩበት መንፈስ በጣም የተለየ ይሆን ነበር።

በፍጹም ቅንነት ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁት። ‹‹ነቅፌህ ነበር፤ ከዚያም አልፎ ፈርጄብህ ነበር›› አልኩት።

እርሱም ወዲያውኑ ለስለስ አለ፤ ለአንድ ሰዓት ያህል አወራን። ምንም እንኳ በእርሱና በሌሎች ፓስተሮች መካከል የነበረው ችግር ቢቀጥልም፣ ከዚያ ቀን ወዲህ እኔን ማጥቃቱን አቆመ።

ከስድስት ወር በኋላ ከአገር ውጪ እያግለገልኩ እያለ፣ ይህ ሰው የፈጸመው በደል ሁሉ ለዋናው ፓስተር ተገለጠ። ነገሩ ከአገልግሎቱ ሌሎች ገጽታዎች ጋር እንጂ፣ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም። የሰውዬው በደል እኔ ከማውቀው የበለጠ ከባድ ነበር። ወዲያውኑ ከቤተ ክርስቲያኑ ታገደ።

ውሎ አድሮ ፍርድ መጣ፤ በእኔ እጅ ግን አልነበረም። እኔ ላይ ማድረግ የፈለገው እርሱ ላይ ተደረገበት። ይሁን እንጂ፣ በሆነው ነገር አልተደሰትኩም። ለእርሱና ለቤተ ሰቡ አዘንኩ። በእርሱ በኩል የዚያ ዓይነት ችግር ደርሶብኝ ስለ ነበር ሕመሙ ይገባኛል።

ከስድስት ወር አስቀድሞ ይቅር ብዬው ስለ ነበር አሁን እርሱን መውደድ ችያለሁ፤ እንዲህ ያለ ነገር እንዲደርስበት አልፈለግሁም ነበር። ከአንድ ዓመት በፊት በእርሱ ላይ ቂጣ አድሮብኝ በነበረ ጊዜ ታግዶ ቢሆን ኖሮ ደስ ይለኝ ነበር።

ትሕትናና (ራስን ዝቅ ማድረግ) እኔ ራሴ ለመበቀል አለመፈለጌ፣ ከበደል ወይም ከመሰናከል እስር ቤት ነጻ አውጥተውኛል።

ከአንድ ዓመት በኋላ አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ አየሁት። የእግዚአብሔር ፍቅር ውስጤ ነደደ። እርሱ ወደ ነበረበት ሮጬ ሄድኩና አቀፍኩት። ነገሮች ለእርሱ መልካም እንደ ነበሩ ሲነግረኝ ከልቤ ደስ አለኝ። ከወሮች በፊት ቢሮው ሄጄ ራሴን ዝቅ ባላደርግ ማለትም ትሑት ሆኜ ባልሆን ኖሮ፣ በዚያ ቀን ዐይኑን ማየት ይከብደኝ ነበር። እርሱን ካየሁ አሁን ጥቂት ዓመታት አልፈዋል፤ ግን ስለ እርሱ የሚሰማኝ ፍቅር ብቻ ነው፤ በእግዚአብሔር ፊቃድ ውስጥ ሆኖ እንዳየውም እውነተኛ ፍላጐት አለኝ።

እግዚአብሔር ራሱ ሳኦል ላይ ፈራጅ እንዲሆን በመምረጡ ዳዊት አስተዋይነቱን አሳይቷል። ምናልባትም፣ ‹‹በሳኦል ላይ ለመፍረድ እግዚአብሔር የተጠቀመው በማን ነበር?›› ብላችሁ ብትጠይቁኝ መልሴ - በፍልስጥኤማውያን የሚል ይሆናል።

ከእነርሱ ጋር ሲዋጉ ነበር ሳኦልና ልጆቹ የተገደሉት። ዳዊት ያንን ሲሰማ አልተደሰተም፤ ይልቁንም ምርር ብሎ አለቀሰ።

አንድ ሰው ወደ ዳዊት መጥቶ ሳኦልን የገደለ እርሱ እንደ ነበር ጉራ ነዛ። ዳዊት ጮሽ! አበጀህ! ይለኛል ብሎ ጠብቆ ነበር፤ ነገሩ ግን ከጠበቀው ውጪ ነበር የሆነው። ‹‹ዳዊትም - ታዲያ፣ እግዚአብሔር የቀባውን ለማጥፋት እጅህን ስታነሣ እንዴት አልፈራህም?›› በማለት ጠየቀው፤ ሰውየው ወዲያውኑ እንዲገደል አዘዘ (2 ሳሙኤል 1÷14-15 ይመ.)።

ከዚያም ዳዊት፣ ለሳኦልና ለልጆቹ ክብር የይሁዳ ሕዝብ የሚዘምሩት መዝሙር ደረሰ። ጠላት ደስ እንዳይሰኝ በፍልስጥኤማውያን ከተሞች ዐውራ መንገዶች ላይ የሳኦልና የልጆቹ ሞት እንዳይወራ አዘዘ። ሳኦል በተገደለበት ቦታ ዝናብ እንዳይወርድ፣ እህልም እንዳይበቅል ተናገረ። እስራኤል ሁሉ ለሳኦል እንዲያለቅሱ ጥሪ አቀረበ። ይህ ደግሞ ከተሰናከለ ወይም በደል ከሚቆጥር ሰው ልብ የሚወጣ አይደለም። የተሰናከለ ወይም አሁንም የደረሰበትን በደል እያሰበ ያለ ሰው ‹‹ጮሽ! የእጁን ነው ያገኘው!›› ነበር የሚለው።

ዳዊት ከዚያም ርቆ ሄደ። የተረፉትን የሳኦል ቤት ዘር አላጠፋም። ይልቁንም ደግ ሆነላቸው። ርስትና ምግብ ሰጣቸው፤ አንዱ የሳኦል ልጅ ከንጉሥ ማዕድ እንዲመገብ አደረገ። ታዲያ፣ የተሰናከለ ሰው እንዲህ ያደርጋል?

ምንም እንኳ ዳዊት አባት ይሆነኛል ብሎ በጠበቀው ሰው ቢከዳም፣ ከሳኦል ሞት በኋላ እንኳ ታማኝነቱን ጠብቆአል። ለሚወደንና አባት ለሚሆነን መሪ ታማኝ መሆን ቀላል ነው፤ ግን እናንተን ለማጥፋት የተነሣ ሰውን በተመለከተስ ምን ታስባላችሁ? እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው ትሆናላችሁ ወይስ እናንተ ራሳችሁ ትበቀላላችሁ?

እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ መበቀሉ ትክክል ነው።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳቸው መበቀላቸው

ግን ትክክል አይደለም።

ሚስተር ቢቭሬ፣ ዛሬ *የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኘው መጽሐፍህን እያነበብኩ ነው - ማቋረጥ ወይም መጽሐፉን ማስቀመጥ አልቻልኩም! ይኸ በሕይወት ዘመኔ ካነበብኳቸው ምርጥ መጽሐፎች አንዱ ነው።

- ፒ. ኤ. ሚዙሪ

5

መንፈሳዊ ከርታቶች

‹‹እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር ከማድረግና እግዚአብሔር የቀባው ሰለ ሆነም እጄን በእርሱ ላይ ከማንሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ›› አላቸው፡፡ ዳዊት ሰዎቹን በዚህ ቃል ገሠጻቸው፤ በሳኦል ላይ አደጋ እንዲያደርሱበትም አልፈቀደላቸውም፡፡

- 1 ሳሙኤል 24÷6-7

ባለፈው ምዕራፍ ዳዊት አባት ይሆነኛል ብሎ ተስፋ ባደረገው ሰው የደረሰበትን በደል ተመልከተናል፡፡ የእርሱ ጥፋት ምን ላይ እንደ ነበር ለማየት ብዙ ሞክሮ ነበር፡፡ የሳኦል ልብ እርሱ ላይ በጠላትነት እንዲነሣ ምክንያት የሆነ እርሱ የፈጸመው በደል ምን ነበር? የተበላሸውን ማስተካከል የሚችለው እንዴት ነው? ምንም እንኳ ሳኦል እርሱን ለመግደል እያሳደደው ቢሆንም፣ እርሱ ሳኦልን ባለመግደል ታማኝነቱን አሳይቶ ነበር፡፡

ወደ መሬት ጐንበስ ብሎ እጅ እየነሣ፤ ‹‹ክፋት ወይም ዐመፅ አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ፡፡ ተረዳልኝም፤ እኔ ክፉ አልሠራሁብህም›› በማለት ጮኸ ብሎ ለሳኦል ተናግሮ ነበር፡፡

መሪው ለነበረው ሰው ታማኝነቱን ከገለጠ በኋላ የዳዊት ልብ ተረጋግቶ ነበር፡፡ በኃላ ግን የበለጠ አስደንጋጭ ወሬ ደረሰው፤ አሁንም ሳኦል እርሱን ለማጥፋት እየፈለገ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሰራዊቱ ሁሉ እንዲያንቀላፉ ቢያደርግም፣ ሳኦልን መግደል እንዲፈቅድለት የቅርብ ጓደኛው ቢጠይቀውም፣ ዳዊት የእርሱን

ሕይወት ለማጥፋት እያሳደደው የነበረ ሰው ላይ እጁን ማንሣት አልፈለገም። በአንጻሩ ግን የሰራዊቱ ማንቀላፋት፣ የእርሱ ልብ ቅንነት የሚፈተንበት እንደ ሆነ ነበር የተረዳው። ዳዊት የራሱን መንግሥት ለመመሥረት ግድያ ይፈጽም እንደ ሆነ ወይም ደግሞ ለእርሱ በጽድቅ ዘላለማዊ መንግሥት እንዲመሠርትለት ነገሩን ለእርሱ ይተው እንደ ሆነ እንዲታወቅ እግዚአብሔር ፈልጐ ነበር።

> ወዳጆቼ ሆይ፣ ለእግዚአብሔር ቁጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ ‹‹በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ›› ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአል።
>
> - ሮሜ 12÷19

እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ መበቀሉ ትክክል ነው። የእግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳቸው መበቀላቸው ግን ትክክል አይደለም። ሳኦል እርሱ ራሱ መበቀል የሚፈልግ ሰው ነበር። የተከበረውን ሰው ዳዊትን ዐሥራ አራት ዓመት አሳደደ፤ ካህናቱንና ቤተ ሰቦቻቸውን ገደለ።

አንቀላፍቶ በነበረው ሳኦል አጠገብ ዳዊት ቆሞ በነበረ ጊዜ፣ ፊት ለፊቱ በጣም ወሳኝ ፈተና ቀርቦ ነበር። ይህ ፈተና ዳዊት ለሚጠብቃቸው በጐች የሚራራ ጨዋ ልብ ያለው መሆኑን ወይም ደግሞ የሳኦል ዐይነት ዋስትና ማጣት የሚሰማው መሆኑን ግልጥ ያደርጋል። በተነገረለት መሠረት እንደ እግዚአብሔር ልብ ሆኖ ይዘልቅ ይሆን? የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፍርድ ከመጠበቅ ይልቅ ነገሮችን በራሳችን መንገድ ስናደርግ መጀመሪያ ላይ ሁሉም ቀላል ይመስላል።

እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በመታዘዝ አለመታዘዛቸው ይፈትናቸዋል። የሃይማኖትና የማኅበረ ሰቡ መለኪያ ሚዛን የእኛን ድርጊት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ መስሎ የሚታይበት ቦታ ላይ ያኖረናል። ሌሎች፣ በተለይም ደግሞ ለእኛ በጣም ቅርብ የሆኑት ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ራሳችንን መጠበቅ እንዳለብን ምክር እንዲለግሱን ይፈቅድላቸዋል። ምናልባትም፣ ተቋዋሚ የመሰሉንን እኛ ራሳችን በመበቀል ትክክለኛ መሆናችንን የምናሳይ፣ እንደዚያ በማድረጋችንም ለራሳችን እንደ ተከላከልን እንጂ በራሱ

በደል እንዳልሆነ እናስባለን። ያ ግን፣ የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። የዓለም ጥበብ መንገድ ነው። ምድራዊና ሥጋዊ ነው።

ከእኔ በላይ የነበረውን መሪ ማጋለጥ የምችልበት ዕድል ገጥሞኝ በነበረ ጊዜ፣ ያንን ሰው ካላጋለጥኩት ሌሎችንም ሊጐዳ ይችላል ከሚል ሐሳብ ጋር ምን ያህል ትግል ገጥሞኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። እኔ'ኮ እውነቱን ብቻ ነው የምናገረው፤ እንደዚያ ካላደረግሁ ችግሩ እንዴት ማብቂያ ይኖረዋል? እያልኩ ደጋግሜ አስብ ነበር።

ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ግን፣ እግዚአብሔር ያ መረጃ እጄ እንዲገባ ያደረገበት አንዱ ምክንያት እኔን ለመፈተን ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ። እኔን ማጥፋት እንደሚፈልገው ሰውዬ እሆን ይሆን? እግዚአብሔር እንዲፈርድ፣ ሰውየው ንስሐ ካደረገ ደግሞ፣ ምሕረቱን እንዲያወርድለት ፈቃደኛ ሆኜ እገኝ ይሆን?

እግዚአብሔር እንዴት በብልሹ መሪዎች ይጠቀማል?

‹‹ሰዎች ትልልቅ ጥፋት በሚፈጽሙ መሪዎች ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለምን ይፈቅዳል?›› በማለት ብዙዎች ይጠይቃሉ።

የሳሙኤልን የልጅነት ጊዜ አስቡ (1 ሳሙኤል 2-5 ይመ.)። ወጣቱ ሳሙኤልን ብልሹ በነበረው ካህኑ ዔሊና እንደ እርሱ ካህናት በነበሩ አፍኒንና ፊንሐስ በሚባሉ ሁለት ዐመፀኛ ልጆቹ ሥልጣን ሥር ያኖረ እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አልነበረም። እነዚህ ሰዎች በጣም ክፉዎች ነበሩ። በማስገደድና ጫና በማድረግ መሥዋዕቱን ወስደው ይበሉ ነበር፤ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ከሚሰበሰቡ ሴቶች ጋር ያመነዝሩ ነበር።

እንዲህ ያለ ሕይወት ካለው አገልጋይ ሥር ብትሆኑ ኖሮ፣ ምን ይሰማችሁ እንደ ነበር ማሰብ ትችላላችሁ? እየጸለየች የነበረችውን ሴት እንደ ሰካራም እስኪቆጥር ድረስ ለመንፈሳዊ ነገር ንቃት የሌለው አገልጋይ ይታያችሁ ይሆን? ከመጠን በላይ እስኪወፍር ድረስ በሚበላው ምግብ ራሱን መቆጣጠር ያቃተው ነበር፤ አምልኮተ እግዚአብሔር በሚፈጸምበት ቦታ እያመነዘሩ

የነበሩ ወንዶች ልጆቹን እንኳ ማስተካከል ያልቻለ ነበር፤ እንዲያውም እነዚያ ዐመፀኛ ልጆቹ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲያገለግሉ አደረገ።

እንዲህ ያለ ሁኔታ ቢገጥማቸው ኖሮ ብዙ ክርስቲያኖች ይሰናከሉ ነበር፤ ያንን ቤተ ክርስቲያን ትተው የሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆኑ ነበር፤ በየሄዱበት ሁሉ የዚያን ፓስተርና አብረውት ያሉ መሪዎችን መጥፎነት ይናገሩ ነበር። በእንደዚያ ዐይነት ብልሽት መካከል ቢሆንም፣ ወጣቱ ሳሙኤል ስላደረገው የሚናገረው ጥቅስ በጣም ደስ ይለኛል፤ ‹‹ብላቴናው ሳሙኤል *ከዔሊ በታች ሆኖ* እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር›› (1 ሳሙኤል 3÷1)።

ምንጊዜም ቢሆን ዐመፅ የሚያስከትለው ውጤት ይኖረዋል፤ ‹‹በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይታይም ነበር›› (1 ሳሙኤል 3÷1)። በመላው ዕብራውያን ማኅበረ ሰብ እግዚአብሔር በጣም የራቀ ይመስል ነበር። በጌታ ቤተ መቅደስ ውስጥ የእግዚአብሔር መብራት ሊጠፋ የቀረበ ይመስል ነበር። እንዲህ ቢሆን እንኳ፣ ሳሙኤል ሌላ የአምልኮ ቦታ ፍለጋ ሄዶ ነበርን? ዔሊንና ልጆቹን ከአገልግሎት ለማባረር ኮሚቴ ማቋቋም ፈልጎ ነበርን? ሳሙኤል እንደዚያ አላደረግም፤ ይልቁን ዝም ብሎ ጌታን አገለገለ! ሳሙኤልን በዚያ ቦታ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነበር፤ ለዔሊና ለልጆቹ ዐመፅ ተጠያቂ እርሱ እንዳልነበረ ያውቃል። ከእነርሱ ሥልጣን ሥር የሆነው ሊያገለግላቸው እንጂ፣ ሊፈርድባቸው እንዳይደለ ይረዳል።።። ዔሊ የእግዚአብሔር እንጂ፣ የእርሱ አገልጋይ አልነበረም። የእርሱ በሆኑት ላይ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር በሚገባ ያውቃል።

ልጆች አባቶችን አይገሥጹም። ይልቁን ልጆችን ማስተማርና ማስተካከል የአባቶች ሥራ ነው። እንድናስተምራቸው እግዚአብሔር የሰጠንን ሰዎች ማስተካከልና ማረም ተገቢ ነው፤ ያ የእኛ ኃላፊነት ነው። በእኛ ደረጃ ያሉትን እንደ ወንድሞችና እኅቶች ማበረታታትና መምከር አለብን። በዚህና በመጨረሻው ምዕራፍ

ግን፣ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ሥልጣን ለሰጣቸው ሰዎች የእኛ ምላሽ ምን መሆን እንዳለበት መናገር እፈልጋለሁ።

ሳሙኤል እግዚአብሔር የሾመውን መሪ በሚቻለው ሁሉ አገለገለ እንጂ፣ እርሱ ላይ አልፈረደም፤ እርሱን ለማረምም አልሞከረም። ሳሙኤል የእርምት ቃል የተናገረው ባለፈው ሌሊት እግዚአብሔር ስለ ሰጠው ትንቢት እንዲነግረው ዔሊ በጠየቀው ጊዜ ብቻ ነበር። ያኔም ቢሆን የተናገረው ከእግዚአብሔር የተቀበለውን እርምት እንጂ የራሱን አልነበረም። ብዙዎች ይህን እውነት ይዘው ቢሆን ኖሮ የቤተ ክርስቲያኖቻችን ሁኔታ የተለየ ይሆን ነበር።

አብያተ ክርስቲያናት እንደ ፈለግን የምንገባባቸው፣ የምንወጣባቸው አይደሉም

በዚህ ዘመን ሰዎች አመራሩ ላይ አንዳች ስሕተት ከተመለከቱ በፍጥነት ቤተ ክርስቲያኖችን ለቅቀው ይሄዳሉ። ምናልባት፣ ፓስተሩ መባ ወይም ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰበስብበትን መንገድ በተመለከተ ላይ ላይስማሙ ይችላሉ። ገንዘቡ ጥቅም ላይ በሚውልበት ሁኔታ ጥያቄ ያድርባቸው ይሆናል። በፓስተሩ ስብከት ካልተስማሙ ለቅቀው ይሄዳሉ። ምናልባትም፣ ፓስተሩ በቀላሉ ሊቀርቡት የማይቻል የማይገኝ ወይም ደግሞ የትም የሚገኝ ተራ ዓይነት ሰው ይሆንባቸው ይሆናል። ችግሩን በትዕግሥት ከመቀበልና በተስፋ ከመጠበቅ ይልቅ ችግር የሌለበት መስሎ ወደሚታያቸው ቦታ ይሮጣሉ።

ፍጹም የሆነ ፓስተር ወይም መጋቢ ኢየሱስ ብቻ ነው። ታዲያ፣ አንድ ችግር ሲፈጠር ቆም ብለን ከማሰብና መፍትሔውን ከመፈለግ ይልቅ፣ ከችግሩ ሸሽተን ለማምለጥ የምንሞክረው ለምንድነው? ችግሩ እኛ የምንጠብቀው ዐይነት መፍትሔ ካላገኘ እንሰናከላለን፤ ከዚያም ለቅቀን እንሄዳለን። አንዳንዴ ደግሞ ነቢያዊ ነው የምንለው አገልግሎታችን ተቀባይ እንዳላገኘ እንናገራለን። ከዚያም ተቀባይነት ለማግኘት ስንል ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን እንዞራለን።

ይህን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ በዐሥራ አራት ዓመት ውስጥ፣ በተለያዩ ክፍለ አገሮች ያለ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች ብቻ አባል ነበርኩ። አምን፣ በወቅቱ መሪዎች በነበሩ ሰዎች ተሰናክዬ ነበር፤ ያንን ቦታ ለቅቄ ለመሄድ ብዙ ዕድሎች ነበሩኝ (አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው፣ አብዛኞቹ ችግሮች ከእኔ አለመብሰል የመጡ እንደ ነበሩ ተረድቻለሁ)። አመራሩን ለመንቀፍ፣ ከዚያም አልፌ ለመፍረድ ዕድሉ ነበረኝ፤ ግን ለቅቆ መሄድ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ አንድ ቀን፣ ‹‹በደስታ ትወጣላችሁ፤ በሰላምም ትሸኛላችሁ›› በሚለው ጥቅስ ጌታ ተናገረኝ፤ (ኢሳይያስ 55÷12)። ‹‹እንድትሄድ የምፈልገው በዚህ መልኩ ነው›› አለኝ።

ብዙዎች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው የሚሄዱት በዚህ መንገድ አይደለም። ለእነርሱ፣ ቤተ ክርስቲያኖች እንዳሻቸው ዘው ብለው የሚገቡባቸውና የሚወጡባቸው ይመስሏቸዋል! እዚያ መቆየት እያለባቸው ችግር እስከሌለ ድረስ ይመስላቸዋል። ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር አይስማማም። ወደ የትኛው ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንዳለባችሁ የምትመርጡ እናንተ አይደላችሁም። ያንን መወሰን ያለበት እግዚአብሔር ነው! መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹እግዚአብሔር እንደ ወደደ እያንዳንዱን በቦታው መድቦአል›› (1 ቆሮንቶስ 12÷18) ይላል እንጂ፣ ‹‹እያንዳንዱ አባል እንደ ወደደ ቤተ ክርስቲያን መቀያየር ይችላል›› አይልም።

እግዚአብሔር የሚፈልገው ቦታ ላይ ከሆናችሁ፣ እናንተን ከዚያ ለማስወጣት ሰይጣን ሊያሰናክላችሁ እንደሚሞክር አትርሱ። ወንዶችና ሴቶች ልጆችን እግዚአብሔር ከተከለበት ቦታ መንቀል ይፈልጋል። እናንተን ከዚያ ከነቀለ ደግሞ ዓላማው በደንብ ይሳካለታል። የቱንም ያህል ከባድ ችግር ቢኖር እንኳ ጸንታችሁ ከቆማችሁ ግን ዕቅዱን ታፈርሳላችሁ።

ከባድ መሳት

ለአያሌ ዓመታት አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበርኩ። የዚያ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር በአሜሪካ ከታወቁ ጥሩ ሰባኪዎች አንዱ ነበር። መጀመሪያ የዚያን ቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ስካፈል፣ ከአንደበቱ

የሚፈልቀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አፌን ከፍቼ ነበር የምሰማው።

ጊዜ እያለፈ ሄደ፤ የእኔ ሥራ ድርሻ ፓስተሩን ማገልገል ስለ ነበር፤ በጣም ከመቅረቤ የተነሣ አንዳንድ ደካማ ጐኖቹን ማየት ቻልኩ። አገልግሎትን በተመለከተ በሚያሳልፋቸው አንዳንድ ውሳኔዎች ጥያቄ አደረብኝ። ነቃፊና ፈራጅ ሆንኩ፤ መሰናከል ወደ ሕይወቴ መጣ። አሁንም እንደ ወትሮ ቢሰብክ እንኳ፣ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር ወይም ቅባት አይሰማኝም ነበር። ስብከቱ ለጥልቅ እኔነቴ አይደርስም ነበር።

የቅርብ ወዳጆቻችንና በቤተ ክርስቲያኑ ይሠሩ የነበሩ ባልና ሚስትም እኔን የተሰማኝ ዓይነት ስሜት ነበራቸው። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር መሪነት የራሳቸውን አገልግሎት ለመጀመር ቤተ ክርስቲያኑን ለቅቀው መሄድ ነበረባቸው። ከፊለግን አብረናቸው እንድንሄድ ጠይቀውን ነበር። የገጠመንን ችግር በሚገባ ያውቁ ነበር። እግዚአብሔር ለሕይወታችን ባለው ጥሪ መሠረት እንድንንቀሳቀስ ያበረታቱን ነበር። ፓስተሩ፣ ሚስቱና አመራሩ ያለባቸውን ችግር ሁሉ ይነግሩን ነበር።

ለእኔና ለአገልግሎቴ በጣም የሚያስቡ መስሎ ተሰምቶኝ ነበር። ሆኖም፣ ውይይታችን ቀድሞኑ የነበረንን ቅርታና መሰናከል ይበልጥ አቀጣጠለው እንጂ፣ መፍትሔ አልሆነንም። መጽሐፈ ምሳሌ 26÷20፣ ‹‹ዕንጨት ከሌለ እሳት ይጠፋል፤ አሾክሾኪ ከሌለም ጠብ ይበርዳል›› ይላል። እነዚህ ወገኖች የነገሩን ነገር እውነት ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ በእኛም ሆነ በእነርሱ ውስጥ የመሰናከል እሳት እያቀጣጠለ በመሆኑ፣ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል አልነበረም።

‹‹አንተ የእግዚአብሔር ሰው መሆንህን በሚገባ እናውቃለን›› አሉኝ። ‹‹በዚህ ቦታ ይህ ሁሉ ችግር እየደረሰብህ ያለው በዚህ ምክንያት እንደ ሆነም እንረዳለን።››

እኔና ሚስቴ፣ ‹‹እነዚህ ሰዎች የተናገሩት ትክክል ነው፤ ያለንበት ሁኔታ ጥሩ አይደለም፤ ይህን ቤተ ክርስቲያን መልቀቅ

አለብን። ፓስተሩና ሚስቱ በጣም ስለሚወዱን፣ ለእኛም ፓስተር ይሆኑናል። ከእነርሱ ጋር ያለ‌ት ሰዎችም፣ እኛንም ሆነ እግዚአብሔር የሰጠንን አገልግሎ‌ት ይወዳለ›› ተባባልን።

ቤተ ክርስቲያናችንን ለቅቀን፣ በእነዚህ ባልና ሚስት ቤተ ክርስቲያን መካፈል ጀመርን፤ ያ የዘለቀው ግን ለጥቂት ወሮች ብቻ ነበር። ከችግራችን ያመለጥን ቢመስለንም፣ ግን አሁንም ቢሆን ትግል መኖሩን ተረዳን። መንፈሳችን ውስጥ ደስታ አልነበረም። የምናደርገው ሁሉ ነጻነት የሌለበትና የትግል ሆነብን። ከመንፈስ ጋር አብረን መፍሰስ አልሆን አለን። ይባስ ብሎ ደግሞ፣ ከአዲሱ ፓስተርና ከሚስቱ ጋር የነበረን ግንኙነት እየሻከረ መጣ።

በመጨረሻ ትተነው ወደ መጣነው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን መመለስ እንዳለብን ዐወቅሁ። ያንን ስናደርግ፣ ከዚያ ይልቅ ሌላ ቦታ የበለጠ የምንወደድና ተቀባይነት የምናገኝ መስሎ ቢታየን እንኳ፣ እዚያ በመገኘታችን በእግዚአብሔር ፊቃድ ውስጥ እንደ ሆንን ዐወቅን።

በኃላም አንድ ቀን እግዚአብሔር፣ ‹‹ጆን፣ መጀመሪያውኑ ይህን ቤተ ክርስቲያን ለቅቀህ እንድትሄድ አልነገርኩህም። ለቅቀህ የሄድከው ከመሰናከል የተነሣ ነው!›› በማለት ሲናገረኝ በድንገት ከእንቅልፍ የመባነን ያህል ነበር የደነገጥኩት።

ጥፋቱ የእኛ የራሳችን እንጂ፣ የፓስተሩና የሚስቱ አልነበረም። እውነት ነው፣ ችግራችንን በእርግጥ ተረድተው ነበር፤ እኛን የገጠመን ችግር እነርሱንም ገጥሞአቸው ስለ ነበር ለዚያ መፍትሔ መስጠት ነበር የሞከሩት። ከእግዚአብሔር ፊቃድ ውጪ፣ ለየትኛውም ቤተ ክርስቲያን በረከት ወይም ጠቃሚ ሰው አትሆኑም። ከእግዚአብሔር ፊቃድ ውጪ ስትሆኑ ቀድሞ ጥሩ የነበረ ጎብረት ወይም ግንኙነት እንኳ ሊሻክር ይችላል። በወቅቱ እኛ ከእግዚአብሔር ፊቃድ ውጪ ሆነን ነበር።

የተሰናከለ ሰዎች ለሁኔታዎች ከረር ያለ ምላሽ ይሰጣለ፤ የእግዚአብሔር ፊቃድ ባይሆን እንኳ መልካም መስሎ የታያቸውን ነገር ያደርጋለ። የተጠራነው ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ እንድንንቀሳቀስ

እንጂ፣ በሁኔታዎች ቀስቃሽነት የአጸፋ ምላሽ እንድንሰጥ አይደለም።

ለእግዚአብሔር የምንታዘዝና እርሱንም የምንፈልግ ከሆነ፣ ያም ሆኖ ግን እርሱ እየተናገረን ካልሆነ ያ፣ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል ታውቃላችሁ? ምናልባት፣ ‹‹ባላችሁበት ቦታ ቆዩ። ምንም ለውጥ አታድርጉ›› ማለቱ ሊሆን ይችላል።

አንድ ዐይነት ጫና ውስጥ ስንሆን፣ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር እፎይታ የሚሰጥ ቃል እንጠብቃለን። ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለ ምኞት የማይሰጥ አዳጋች ሁኔታ እንዲደርስብን እግዚአብሔር የፈቀደው እኛን ለመጉዳት ሳይሆን፣ በሳሎች እንድንሆን፣ ጥራት ያለው ሕይወት እንዲኖረንና ሊያበረታን ነው!

በአንድ ወር ውስጥ ትቼው ሄጄ ከነበረ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ጋር ፊተ ለፊት የመገናኘት ዕድል አገኘሁ። እርሱን በተመለከተ ነቃፊና ዐመፀኛ እንደ ነበርኩ ነገርኩት። እርሱም በደስታ ይቅርታ አደረገልኝ። ግንኙነታችን እየተስተካከለና ደስታ ወደ ልቤ እየተመለሰ መጣ። እንደ ገና በአገልግሎቱ መባረክ ጀመርኩ፤ ወዲያ ወዲህ ሳልል ለዓመታት በዚያ ቤተ ክርስቲያን ቆየሁ።

የተተከለ ይንሰራፋል

መጽሐፍ ቅዱስ መዝሙር 92÷13 ላይ፣ ‹‹በእግዚአብሔር ቤት ተተክለዋል፤ በአምላካችንም አደባባይ ይንሰራፋሉ›› ይላል።

የሚያንሰራፋት ቀድሞኑ በእግዚአብሔር ቤት፣ ‹‹የተተከለ›› መሆናቸውን ልብ አድርጉ። አንድ ተክል በየሦስት ሳምንቱ የምትነቅሉት ከሆነ ምንድነው የሚሆነው? ሥሩ እንደሚደርቅና ፍሬ እንደማይሰጥ፣ በኃላም ማደግ እንደማይችል ብዙዎቻችሁ ታውቃላችሁ። በየጊዜው እየነቀላችሁ ሌላ ቦታ የምትተክሉት ከሆነ፣ ውሎ አድሮ ይሞታል!

የራሳቸውን አገልግሎት ለማሳደግ በማሰብ ብዙዎች ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን፣ ከአንዱ አገልግሎት

ቡድን ወደ ሌላው አገልግሎት ቡድን ይሄዳለ፡፡ ዕውቅና ወይም የሚፈልጉትን መበረታታት በማያገኙበት ቦታ እግዚአብሔር ካስቀመጣቸው በቀላሉ ይሰናከላለ፡፡ ነገሮች እየተደረጉ ባሉበት መንገድ ካልተስማሙ ይሰናከላሉና ለቅቀው ይሄዳለ፡፡ በሰላም ከመሰናበት ይልቅ አመራሩን ወይም ቤተ ክርስቲያኑን በመውቀስና በመንቀፍ ይሄዳለ፡፡ የራሳቸውን ፀባይ ጉድለት ከማየት ዐይኖቻቸው ይታወራለ፤ ባሉበት ጫናና አዳጋች ሁኔታ ውስጥ እነርሱን ለማጥራትና በሳል ለማድረግ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ መረዳት ይሳናቸዋል፡፡

ከአትክልቶችና ከዛፎች እግዚአብሔር በሚሰጠን ምሳሌ አማካይነት መማር አለብን፡፡ አንድ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ሲተከል ከባድ ዝናብ፣ የፀሐይ ግለትና ብርቱ ነፋስ ይፈራረቁበታል፡፡ የዛፉ ችግኝ መናገር ቢችል ኖሮ ምናልባት፣ ‹‹እባካችሁ ከዚህ ቦታ አውጡኝ! ከባድ ዝናብ፣ የፀሐይ ቃጠሎና ብርቱ ነፋስ የሌለበት ቦታ ወስዳችሁ ትከሉኝ›› ይል ነበር!

የተከለው ሰው ዛፉ የሚናገረውን ሰምቶ የጠየቀውን ቢያደርግ ኖሮ፣ ከመጥቀም ይልቅ ይጐዳው ነበር፡፡ ዛፎች የፀሐይ ግለትንና ነፋስ የቀላቀለ ዝናብን የሚቋቋሙት ሥራቸውን ወደ ውስጥ በመስደድ ነው፡፡ እየደረሰባቸው ያለው ችግር የኃላ ኃላ ብርቱና ፅኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በዙሪያቸው ያለ የተፈጥሮ ችግር፣ ከተፈጥሮ በላይ ያለውን የሕይወት ምንጭ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል፡፡ ውሎ አድሮም፣ ከባድ ዐውሎ ነፋስ እንኳ ፍሬ የማፍራት ችሎታቸውን ማስቆም የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳለ፡፡

ከዓመታት በፊት በሚሰጠው ፍሬ በሚታወቅ በአንድ የፍሎሪዳ አካባቢ እኖር ነበር፡፡ የክረምቱ ብርድ ለዛፎቹ በጣም ከባድ የመሆኑን ያህል፣ የሚያፈሩት ብርቱካንም ጣፋጭ እንደሚሆን አብዛኞቹ የፍሎሪዳ ነዋሪዎች ያውቃለ፡፡ ከሚገጥመን መንፈሳዊ ተቃውሞ ቶሎ የማንሸሽ ከሆነ ሥራችን ጠንካራና ጥልቀት ያለው ይሆናል፤ የምናፈራው ፍሬ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ዘንድ የበዛና ጣፋጭ ይሆናል! ፍሬ ባለማፍራቱ የኃላ ኃላ ተነቅሎ እንደሚጣለው ሳይሆን፣ ጌታ ደስ የሚሰኝበት መልካም ዛፍ እንሆናለን (ለ.ቃስ

13÷6-9)። እኛን በሳል ለማድረግ፣ እግዚአብሔር የሚፈቅድለትን አዳጋች ሁኔታ መሸሽ የለብንም።

በመንፈስ ቅዱስ ተነሳሥቶ ዳዊት መዝሙር 1 ላይ በሚደርስብን በደል፣ በእግዚአብሔር ሕግና በእኛ መንፈሳዊ ዕድገት መካከል ስለሚኖር ብርቱ ግንኙነት ይጽፋል።

ደስታው በእግዚአብሔር ሕግ የሆነ፣ ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ ሰው ብፁዕ ነው።

- መዝሙር 1÷1-2

ከዚያም መዝሙር 119÷165 ላይ የእግዚአብሔርን ሕግ ስለሚወዱ ሰዎች አስደናቂ ነገር ይናገራል።

ሕግህን የሚወዱ ብዙ ሰላም አላቸው፤

ዕንቅፋትም (መሰናክልም) የለባቸውም።

በመጨረሻም መዝሙር 1 ቁጥር 3 ስለ እንዲህ ያለው ሰው ፍጻሜ ይገልጣል።

እርሱም በወራጅ ውሃ ዳር እንደ ተተከለች፣

ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣

ቅጠሏም እንደማይጠወልግ ዛፍ ነው፤

የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።

በሌላ አነጋገር በችግሮችና አዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ ቢሆን፣ በእግዚአብሔር ቃል ደስ መሰኘትን የሚመርጥ ሰው ተሰናክሎ መውደቅን ያስወግዳል። ያ ሰው ከመንፈስ ብርታትና ምግብ ወደሚያገኝበት ጥልቅ፣ ሥሩን እንደሚሰድ ዛፍ ይሆናል። መንፈሱ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ጉድጓድ ጥልቅ፣ ሕይወትን ይቀበላል። ይህ አዳጋች ሁኔታ፣ ፍሬ ለማፍራት ጥሩ ምክንያት እስኪሆንለት ድረስ፣ በሳል ወደ መሆን ደረጃ ያሻግረዋል። ሃሌ ሉያ!

አሁን ደግሞ ዘር ዘርቶ ስለ ነበረ ሰው ለተናገረው ምሳሌ ኢየሱስ የሰጠውን ትርጉም እንመልከት።

እንዲሁም ሌሎች በጭንጫ ቦታ የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበለዋታል። ነገር ግን ሥር የሌላቸው ስለሆኑ የሚቈዩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ ይሰናከላሉ።

- ማርቆስ 4÷16-17

እግዚአብሔር ከመረጠላችሁ ቦታ ለቅቃችሁ ስትሄዱ፣ ሥራችሁ መጫጨት ይጀምራል። ቀድሞውኑ ወደ ጥልቁ ሥር ሰዳችሁ ለመተከል ፍላጐት ስላልነበራችሁ አንድ ችግር ሲመጣ ቶሎ ከዚያ ዘወር ለማለት ቀላል ይሆንላችኃል። አዳጋች ሁኔታ ወይም ስደት ሲመጣ ጸንታችሁ የምትቆሙበት ዐቅም አይኖራችሁም፤ ቢኖራችሁ እንኳ በጣም ጥቂት ነው።

ያኔ ሌሎች በደል ያደርሱብናል በሚል ጥርጣሬና ፍራቻ፣ ከቦታ ቦታ የምትንከራተቱ የቤተ ክርስቲያን ከርታቶች ትሆናላችሁ። እውነተኛ መንፈሳዊ ፍሬ የማፍራት ዐቅማችሁ ሽባና ስንኩል ስለሚሆን፣ የሌሎችን ፍሬ ልቅምቃሚ እየበላ የሚኖር ራሱን ማዕከል ያደረገ ሰው ውጣ ውረድ ይደርስባችኃል።

የአዳም ሔዋን የመጀመሪያ ወንዶች ልጆች የነበሩትን አቤልና ቃየልን ተመልከቱ። ቃየል የራሱ ጥረት ውጤት የሆነ የምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ። መሥዋዕቱ የብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ውጤት ነበር። መሬት ቆፍሮ ድንጋዮቹን ማውጣት፣ ሥራ ሥሮችንና ሌሎች የማይፈለጉ ነገሮችን ማስወገድ ነበረበት። ከዚያም ማረስና አፈሩን ማለስለስ ነበረበት። ከዚያ መትከል፣ ውሃ ማጠጣትና ተክሉን መንከባከብ ነበረበት ለእግዚአብሔር በሚያቀርበው አገልግሎት በጣም መድከምና መጣር እንዳለበት አስቦ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ያ ሁሉ ለእግዚአብሔር መንገድ በመታዘዝ የቀረበ ሳይሆን የእርሱ የራሱ መሥዋዕት ነበር። ይህ ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ፣ በገዛ ራስ ብርታትና ችሎታ እግዚአብሔርን የማምለክ ዐይነተኛ ምሳሌ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አቤል የመታዘዝን ማለትም፣ ከመንጐቹ ምርጥ የሆነውን በኩር ለእግዚአብሔር አቀረበ። ይህን ለማቅረብ እንደ ቃየል ብዙ አልደከመም፤ ሆኖም፣ መሥዋዕቱ ለእርሱ በጣም ውድ ነበር። ሁለቱ ወንድማማቾች ኃጢአታቸውን በገዛ ራሳቸው

ሥራ ውጤት የመሸፈን ምሳሌ በሆነው በለስ ዛፍ፣ ዕርቃናቸውን ለመሸፈን እናትና አባታቸው አድርገው ስለ ነበረው ሙከራ ሰምተው ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን ምንም በደል በሌለበት አንድ እንስሳ ቆዳ የአዳምና ሔዋንን ራቁትነት በመሸፈን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ምን እንደ ነበር አመለከተ። አዳምና ሔዋን ተቀባይነት ስለሌለው የኃጢአት መሸፈኛ አያውቁም ነበር። ይሁን እንጂ፣ አሁን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ተረዱ ከእንግዲህ እነርሱም ሆኑ ልጆቻቸው አለማወቅን እንደ ሰበብ ማቅረብ አይችሉም።

ቃየል ከእግዚአብሔር ሐሳብ በተለየ መልኩ፣ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ሞከረ። በእርሱ የጸጋ መስፈርት ወደ እርሱ የሚመጡትን እንደሚቀበል፣ (የአቤል መሥዋዕት)፣ ‹‹መልካሙን ክፉን›› ባገናዘበ መልኩ ወደ እርሱ የሚመጡትን ግን እንደማይቀበል በተግባር በማሳየት እግዚአብሔር መፍትሔ ሰጠ። ከዚያም፣ መልካም ካደረገ ተቀባይነት እንደሚያገኝ፣ ሕይወትን ካልመረጠ ግን ኃጢአት እንደሚገዛው እግዚአብሔር ለቃየል ተናገረ።

ቃየል በእግዚአብሔር አኮረፈ። ንስሓ ከመግባትና ትክክል የሆነውን ከማድረግ ይልቅ፣ ሁኔታው መልካም ባሕርይ እንዲያስገኝለት ከመፍቀድ ይልቅ፣ በእግዚአብሔር ላይ ካደረበት ቁጣና መሰናክል የተነሣ አቤልን ገደለው።

እግዚአብሔርም ለቃየል እንዲህ አለው፤

> እንግዲህ የተረገምህ ነህ፤ የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፏን ከከፈተችው መሬት ትሰደዳለህ። ብታርሳትም ፍሬዋን አትለግስህም፤ በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች ትሆናለህ።
>
> - ዘፍጥረት 4÷11-12

ቃየል በጣም የፈራውን በእግዚአብሔር የመናቅን ፍርድ በራሱ ላይ አመጣ። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያስገኝልኛል ባለው ነገር ተረገመ። ደም ማፍሰሱ የበለጠ መርገም ሆነበት። ከእንግዲህ ምድር ሙሉ ብርታቷን አትሰጠውም። ፍሬ የሚያገኘው በከባድ ውጣ ውረድ ይሆናል።

የተሰናከለ ክርስቲያኖችም እንዲሁ ፍሬ የማፍራት ዐቅማቸውን ያጣለ።። ስለ ዘሪው በተናገረው ምሳሌ ኢየሱስ የሰውን ልብ ከአፈር ጋር አመሳስሎታል።። ዐመፀኛው ቃየል የሚያርሰው መሬት መካን እንደሚሆን ሁሉ፣ የተሰናከለ ልብም እንዲሁ በምሬት የተመረዘና መካን ይሆናል።። የተሰናከለ ሰዎች ምናልባት የተለያዩ ተአምራት ይለማመዱ ይሆናል፤ በልሳን ይናገሩ፣ ትንቢት ይናገሩ ይሆናል፤ ጥሩ ሰባኪዎችና ለሕመማቸው ፈውስ ያገኙ ሊሆኑ ይችላለ።። እነዚህ ግን የመንፈስ ስጦታዎች እንጂ፣ የመንፈስ ፍሬዎች አይደሉም።። የሚፈረድብን በፍሬያችን እንጂ፣ ባለን መንፈሳዊ ስጦታ አይደለም።። ስጦታ ከሰጠው ይሰጣል፤ ፍሬ ግን ጊዜውን ጠብቆ ይበቅላል።።

ከክፉ ሥራው የተነሣ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እንደሚሆን እግዚአብሔር ለቃየል መናገሩን ልብ አድርጉ።። በዚህ ዘመን በየቤተ ክርስቲያኑ ብዙ መንፈሳዊ ተንከራታቾችና ተቅበዝባገሮች አለ።። የዝማሬ፣ የስብከትና ትንቢት የመናገር ስጦታቸው ቀድሞ በነበሩበት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተቀባይ ባለ ማግኘቱ ከዚያ ለቅቀው ሄደዋል።። ልባቸው ውስጥ መሰናክል ይዘው ስጦታዎቻቸውን የሚቀበልላቸውና ስብራታቸውን የሚፈውስላቸው ቤተ ክርስቲያን ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ይላለ።።

የተበደለና ስደት የደረሰባቸው ይመስላቸዋል።። የዚህ ዘመን ኤርምያስ የሆኑ ይመስላቸዋል።። ጉዳዩ ማንንም ሳይሆን፣ ‹‹እግዚአብሔርና እነርሱን›› ብቻ የሚመለከት እንደ ሆነ ያስባለ።። ለመማር ዝግጁ አይደለም።። የስደት አባዜ ስለ ተጠናወታቸው፣ ‹‹ሰዎች ሁሉ ያሳድዱኛል›› ይላለ።። የተሰደዱ ቅዱሳን ወይም የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ሆኑ ማሰብ መጽናኛቸው ይሆናል።። ሰውን ሁሉ ይጠራጠራለ።። ቃየል ላይ የደረሰው ይኸው ነበር።። እርሱ የተናገረውን ስሙ፤

> በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።።
>
> ዘፍጥረት 4÷14

ቃየል የተሰዳጅነት አባዜ የተጠናወተው እንደ ነበር ተመልከቱ - የሚያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል! አለ።። ዛሬም ይኸው ነው።። የተሰናከለ ሰዎች፣ ሌሎች ሁሉ እነርሱን መግደል እንደሚፈልጉ ያስባለ።።

ይህን ዝንባሌ እስከ ያዙ ድረስ መለወጥ የሚገባውን የሕይወታቸውን ክልል ማየት ከባድ ይሆንባቸዋል። ራሳቸውን ያገልላሉ፤ በራሳቸው ላይ ጉስቁልና በሚጋብዝ መልኩ ይኖራሉ።

> ወዳጅነትን የማይፈልግ ሰው የራሱን ፍላጐት ብቻ ይከተላል፤ ቅን የሆነውን ፍርድ ሁሉ ይቃወማል።
>
> - ምሳሌ 18÷1

እግዚአብሔር የፈጠረን ተገልለንና ከሌሎች ተነጥለን እንድንኖር አይደለም። እርሱ ልጆቹ እርስ በርስ ሲደጋገፉና ሲመጋገቡ ደስ ይሰኛል። አኩራፊዎችና በቀላሉ ተቀያሚዎች ስንሆን፣ ለእኛ ደስ አለመሰኘት ሌሎችን ምክንያት በማድረግ ለራሳችን ስንቆረቆር ያዝናል። እርሱ ንቁ የቤተ ሰቡ አባሎች እንድንሆን ይፈልጋል። ሕይወታችንን ከእርሱ እንድንቀበል ይፈልጋል። የተሰናከለ ሰው የእግዚአብሔርን ሳይሆን፣ የእርሱን ፍላጐት ብቻ ይከተላል። ምንም ዓይነት ምክር የማይቀበል በመሆኑ፣ ለበለጠ መሳት ራሱን ያጋልጣል።

እንዲህ ስል እነርሱን ለማዘጋጀትና ለማደስ ሲባል ከሰዎች እንዲለዩና ለብቻቸው እንዲሆኑ እግዚአብሔር ግለ ሰቦችን አይጠራም እያልኩ አይደለም። ራሳቸውን የራሳቸው እስረኞች ስላደረጉ ሰዎች ነው አሁን እየተናገርኩ ያለሁት። ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን፣ ከአንዱ ጎበረት ወደ ሌላው ጎበረት ይቅበዘበዛሉ፤ ራሳቸው በፈጠሩ ዓለም ውስጥ ራሳቸውን እስረኛ ያደርጋሉ። ከእነርሱ የማይስማማ ሁሉ የተሳሳተና ጠላታቸው ይመስላቸዋል። ገለልተኛ ቦታ ይዘው ለራሳቸው ይከላከላሉ፤ ምኞት የሚሰማቸው እነርሱ ራሳችው በሚቆጣጠሩት ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ብቻ ነው። እዚህ ደረጃ ላይ ከደረሱ ደግሞ የራሳቸውን ደካማነት ማየት ይሳናቸዋል። ችግሮችን ከመቋቋም ይልቅ፣ ቶሎ ሮጠው ማምለጥ ይፈልጋሉ። በመሰናከል አዙሪት ውስጥ ስለሚሽከረከሩ ከሌሎች ጋር በሚደርስባቸው ግጭት ውስጥ ሊኖር የሚችለው መልካም ባሕርይ የመግንባት ሂደት ያመልጣቸዋል።

በሌሎች መሰናከል፣

የራሳችሁን ፀባይ ድካም እንዳታዩ ያደርጋል፤

ምክንያቱም ምን ጊዜም ወቀሳውን ሌሎች ላይ ታደርጋላችሁ።

እንደ ባልና ሚስት ለብዙ ዓመታት የያዝናቸው ይቅር ያላልናቸው ብዙ ጉዳትና ስብራቶች ነበሩን። በዚያ ጊዜ እጅግ በጣም ጥቂት ወዳጆች ብቻ ነበሩን፤ በተለይም እኔ አዘውትሬ የአንድ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን በታማኝነት ብከታተልም፤ የተገለልኩና የሚወደኝ ሰው እንደሌለ ይሰማኝ ነበር። *የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኘውን መጽሐፍህን ካነበብኩ በኋላ ግን፣ ነገሮች ሁሉ ተለወጡ። በደሎቼንና ይቅር አለማለቴን ፊት ለፊት ተጋፈጥኩ፤ በእግዚአብሔር ርዳታ አሁን ፍጹም ነጻ ሰው ነኝ!

- ሲ.ጄ፣ ቤልፋስት፣ አየርላንድ

ከእውነታው መደበቅ

ሁልጊዜ ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ ሊደርሱ አይችሉም።

- 2 ጢሞቴዎስ 3÷7

ጣዙ ጊዜ፣ ‹‹አንድን ቤተ ክርስቲያን ወይም የአገልግሎት ቡድን ለቅቄ መሄድ ያለብኝ መቼ ነው?›› የሚል ጥያቄ ይቀርብልኛል። እኔም፣ ‹‹መጀመሪያውኑ አሁን ወዳላችሁበት ቤተ ክርስቲያን ያመጣችሁ ማን ነበር?›› በማለት እመልስላቸዋለሁ።

አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት መልስ፣ ‹‹እግዚአብሔር ነው›› የሚል ይሆናል። ‹‹ታዲያ፣ ወደዚያ ያመጣችሁ እግዚአብሔር ከሆነ፣ እርሱ እስኪመራችሁ ድረስ መሄድ የለባችሁም። እግዚአብሔር ዝም ቢላችሁ እንኳ፣ ምንም ለውጥ አታድርጉ። ወደ የትም አትሂዱ። እኔ ባስቀምጥኳችሁ ቦታ ሁኑ!›› ማለቱ ነው። ወደ ሌላ እንድትሄዱ እግዚአብሔር ከመራችሁ፣ የቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ሁኔታ ምንም ይሁን፣ ምን በሰላም መሄድ አለባችሁ።

በደስታ ትወጣላችሁ፤ በሰላምም ትሸኛላችሁ

- ኢሳይያስ 55÷12

ስለዚህም የምትወስዱት ርምጃ፣ በመንፈስ ምሪት መሠረት እንጂ፣ ሌሎች ሰዎች ያደረጉትን ወይም የተናገሩትን መሠረት ያደረገ አይሆንም። ያንን አገልግሎት ለቅቃችሁ የሄዳችሁት ነገሮች ስለ ተበለሻሸ አይደለም ማለት ነው።

የተሰናከለ ወይም ነቀፋ የሞላበት ልብ ይዛችሁ፣ ከአንድ ቦታ ተለይታችሁ እንድትሄዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ይህ እናንተ ለሁኔታው የምትሰጡት ምላሽ እንጂ፣ በእርሱ ምሪት ርምጃ የመውሰዳችሁ ውጤት አይደለም። ሮሜ 8÷14፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና›› ይላል እንጂ፣ ‹‹በሚገጥማቸው አዳጋች ሁኔታ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው›› አላለም።

አብዛኛውን ጊዜ አዲስ ኪዳን ውስጥ ልጅ የሚል ቃል ጥቅም ላይ ከዋለ፣ ቃሉ የሚመጣው ቴክኖን *(teknon)* እና ሁዮስ *(huios)* ከተሰኙ ሁለት ግሪክ ቃላት ነው። ቴክኖን የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም፣ ‹‹በመወለድ ልጅ የሆነ››[1] የሚለው ነው።

የመጀመሪያው ልጄ አዲሰን የተወለደ ጊዜ፣ ከሚስቴና ከእኔ በመገኘቱ ብቻ የእኛ ልጅ ሆኖአል። ከሌሎች ሕፃናት ጋር ሕፃናት ማቆያ ቦታ የነበረ ጊዜ ባሕርዩን በማየት የእኔ ልጅ መሆኑን አትለዩም። ወዳጆቻችንና ሌሎች ዘመዶቻችን ሊጐበኙን በመጡ ጊዜ አልጋው ላይ የታሰረውን ስሙን ስላዩ እንጂ፣ ለይተው ሊያውቁት አልቻሉም ነበር። ከሌሎች የተለየ የሚያደርገው ምንም ነገር አልነበረም። ከጆንና ሊዛ ቢቭሬ በመወለዱ ብቻ አዲሰን የእነርሱ ልጅ ሆኖአል።

ሮሜ 8÷15-16 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቴክኖን ነው። የልጅነትን መንፈስ ስለ ተቀበልን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች (ቴክኖን) መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል›› ይላል። አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታው አድርጐ ሲቀበል በአዲስ ልደት ልምምድ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል (ዮሐንስ 1÷12 ይመ)።

አዲስ ኪዳን ውስጥ ልጅ ተብሎ የተተረጐመ ሌላው ቃል ሁዩስ ነው። ብዙውን ጊዜ አዲስ ኪዳን ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ‹‹የወላጆቹ ባሕርይ ወይም ባሕርያት ስላለት ልጅ መሆኑ የሚታወቅ››[2] የሚለው ነው።

ልጄ አዲሰን እያደገ ሲመጣ በመልክና በተግባር አባቱን መምሰል ጀመረ። አዲሰን የስድስት ዓመት ልጅ እያለ እኔና ሊዛ ጉዞ ለማድረግ፣ ወላጆቼ ጋ አኑረነው ነበር። ከጉዞ ስንመለስ አዲሰን ቁርጥ አባቱን ነው የሚመስለው በማለት እናቴ ለሊዛ ነገረቻት። ባሕርዩ እኔ በእርሱ ዕድሜ በነበርኩ ጊዜ የነበረኝ ዓይነት ነበር። እያደገ ሲመጣ ደግሞ ይበልጥ እኔን እየመሰለ መጣ። በአሁኑ ጊዜ በመወለዱ ብቻ ሳይሆን፣ የአባቱ ዐይነት ባሕርይና ሰብዕና ያለው በመሆኑም ጭምር ማንም የጆን ቢቭሬ ልጅ መሆኑን ያውቃል።

ስለዚህ በቀላል ሁኔታ ለማስቀመጥ፣ ቴክኖን የተሰኘው የግሪክ ቃል፣ ‹‹ጨቅላ ሕፃናት›› ማለት ሲሆን፣ ሁዩስ የተሰኘው ቃል ግን፣ ‹‹ያደጉ ልጆችን›› ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል ማለት ነው[3]

እንደ ገና ሮሜ 8÷14 ስንመለከት፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች (ሁዩስ) ናቸውና›› ነው የሚለው። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩት ያደጉና በሳሎች ልጆች መሆናቸውን በግልጽ ማየት እንችላለን። ያላደጉና በሳል ያልሆኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን መንፈስ ምሪት የሚከተሉት በጣም አልፎ አልፎ ነው። ለሚገጥሟቸው ሁኔታዎች ብዙውን ጊዜ ምላሽ የሚሰጡት ስሜትን ወይም አእምሮን መሠረት በማድረግ ነው። ለእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ብቻ ምላሽ መስጠት ገና አልተማሩም።

አዲሰን እያደገ ሲሄድ በባሕርይም እየጐለመሰ ይሄዳል። የበለጠ ባደገና በሳል በሆነ መጠን፣ እኔም የበለጠ ኃላፊነት እሰጠዋለሁ። አለማደጉና በሕፃንነት ባሕርይ ተወስኖ መቅረቱ በምንም ዐይነት ትክክል አይሆንም። ሕፃን ሆነን እንድንቀር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።

የልጄ የአዲሰን ባሕርይ እያደገና እየዳበረ የመጣበት አንዱ መንገድ፣ አዳጋች ሁኔታዎችን በመጋፈጥ ነበር። ትምህርት ቤት መሄድ በጀመረ ጊዜ አንዳንድ፣ ‹‹ጉልበተኛ›› ልጆች አጋጥመውት ነበር። እነዚያ መጥፎ ልጆች፣ ልጄ ላይ እያደረጉና እየተናገሩ ስለ ነበረው ነገር ሰማሁ፤ ሂጄ ችግሩን ለመፍታት ፈልጌ ነበር። ያ ግን

ትክክል እንዳልሆነ ይገባኛል። የእኔ ጣልቃ መግባት የአዲሰንን ባሕርይ ዕድገት ሊያሰናክል ይችላል።

ስለሆነም እኔና ሚስቴ እቤት ውስጥ ለእርሱ ምክር መስጠትና ትምህርት ቤት ውስጥ እየገጠመው ላለው ችግር እርሱን ማዘጋጀት ቀጠልን። በዚህ ችግር መሐል ለእኛ ምክር በመታዘዝ በባሕርይ መገለመስና ማደግ ጀመረ።

እግዚአብሔር እኛን በተመለከተ የሚያደርገውም ይህንኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር፣ *‹‹የእግዚአብሔር ልጅ (ሁዮስ) ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ››* ይላል (ዕብራውያን 5÷8)

አካላዊ ዕድገት የጊዜ ጉዳይ ነው። ማንኛውም የሁለት ዓመት ልጅ ቁመት ስድስት ጫማ አይሆንም። አእምሮአዊ ዕድገት የመማር ጉዳይ ነው። መንፈሳዊ ዕድገት ግን የጊዜም ሆነ የመማር ጉዳይ ሳይሆን፣ የመታዘዝ ጉዳይ ነው። እስቲ ጴጥሮስ የሚናገረውን እንስማ፤

> እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ፣ እናንተም በዚሁ ዓላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአትን ትቶአል።
>
> - 1 ጴጥሮስ 4÷1

ኃጢአትን የተወ ሰው ፍጹም ታዛዥ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። አድጐአል፤ በሳል ሆኖአል። የራሱን ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንገድ ይከተላል። ከተቀበለው መከራ የተነሣ ኢየሱስ መታዘዝን እንደ ተማረ ሁሉ፣ እኛም ከሚገጥሙን አዳጋች ሁኔታዎች የተነሣ መታዘዝን እንማራለን። በመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል ስንሰማ፣ በመከራና በችግር ጊዜ እናድጋለን፣ በሳሎች እንሆናለን። ቁልፍ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀታችን ሳይሆን፣ መታዘዝ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ለሃያ ዓመታት ክርስቲያኖች ቢሆኑም፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ ቢናገሩም፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ስብከቶች ቢሰሙም፣ ብዙ መጻሕፍት ቢያነቡም፣ አሁንም መንፈሳዊ ቅዘን

ጨርቅ የሚያስፈልጋቸው ለምን እንደ ሆነ አሁን አንዱን ምክንያት ተረድተናል። እንዲህ ያለ ወገኖች አዳጋች ሁኔታ በገጠማቸው ጊዜ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ፣ በራሳቸው መንገድ ለራሳቸው መከላከል ይፈልጋሉ። ‹‹ሁሉ ጊዜ ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ ሊደርሱ አይችሉም›› (2ኛ ጢሞቴዎስ 3÷7)። በሕይወታቸው ተግባር ላይ ስለማያውሉት እውነትን ወደ ማወቅ አይደርሱም።

እንድናድግና በሳሎች እንድንሆን ከተፈለገ እውነት በሕይወታችን የራሱን መንገድ መፈጸም አለበት። መታዘዝ በሌለበት ሁኔታ በአእምሮ እውነትን መቀበል ብቻ በቂ አይደለም። እየተማርን ቢሆን እንኳ ካለ መታዘዝ የተነሣ ሳናድግና በሳሎች ሳንሆን እንቀራለን።

ለራስ መጠንቀቅ

ባለ መታዘዝ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለራሳቸው የሚጠነቀቁበት በጣም የተለመደ ሰበብ የደረሰባቸው መሰናክል ወይም በደል ነው። ያለፈ ጊዜ በደልን ማስተናገድ ሐሰተኛ ለራስ የመጠንቀቅ ስሜት ይፈጥራል። ችግሩን ሌላው ሰው ላይ ስለምታደርጉ የራሳችሁን ደካማነት ከማየት ያግዳችኃል። በድሎናል የምትሉትን ሰው ጥፋት ብቻ ስለምታዩ የራሳችሁን አለመብሰል ወይም ኃጢአት ማየት አትችሉም። ስለዚህም በገጠማችሁ ችግር አማካይነት መልካም ባሕርይ እንድታዳብሩ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ እየሠራ ያለውን ሳትቀበሉ ትቀራላችሁ። የተሰናከለ ሰው የችግሩ ምክንያት ነው የሚለውን ነገር ቶሎ ይቆርጣል፤ የኃላ ኃላም ከሰው ሁሉ ይርቅና መንፈሳዊ ከርታታ ይሆናል።

በቅርቡ አንዲት ሴት አንዱን ቤተ ክርስቲያን ትታ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እየሄደች ስለ ነበረች ጓደኛዋ ነግራኝ ነበር። አንድ ቀን አብረው ራት እንዲበሉ አዲሱን ፓስተር ወደ ቤቷ ጠርተው ነበር። እየተጨዋወቱ እያለ፣ ፓስተሩ የበፊቱ ቤተ ክርስቲያኗን የተወችው ለምን እንደ ነበር ይጠይቃታል። ሴትዬዋም በበፊቱ ቤተ ክርስቲያን አመራር የነበረውን ችግር ትነግረዋለች።

ፓስተሩ በሚገባ ካደመጣት በኃላ፤ ሁሉም ነገር እንደሚስተካከል ይነግራታል። ከልምድ እንደ ተማርኩት ሴትየዋ ጉዳትና ነቃፊ ዝንባሌዋን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንድትፈታ ቢነግራት በጣም የተሻለ ይሆን ነበር። አስፈላጊ ከሆነም፣ እግዚአብሔር ያንን ቤተ ክርስቲያን እንድትተው እስኪመራት ድረስ፤ ወደ በፊቱ ቤተ ክርስቲያንዋ እንድትመለስ ሊነግራት ይገባ ነበር።

እግዚአብሔር በሰላም ካሰናበታችሁ፣ ከዚያ መሄዳችሁ ትክክል መሆኑን ለሌሎች የማስረዳት ችግር አይገጥማችሁም። የበፊቱ ቤተ ክርስቲያናችሁ ላይ የመፍረድ፣ የመንቀፍ ወይም ችግሩን የማጋለጥ ዝንባሌ አይሰማችሁም። ያቺ ሴት ብዙም ሳትቆይ፣ ለአዲሱ ፓስተርና የመሪነት ችሎታው የሚኖራት አመለካከት፣ ለበፊቱ ቤተ ክርስቲያን የነበራት አመለካከት ዓይነት እንደሚሆን አውቃለሁ። ልባችሁ ውስጥ በደል ወይም መሰናከል ካለ፣ ማንኛውንም ነገር የምታዩት ወይም የምትቀበሉት ከዚያ አንጻር ይሆናል።

ከእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ጋር የሚስማማ አንድ የዱሮ ምሳሌ አለ። በዱሮ ጊዜ ሰፋሪዎች ወደ ምዕራቡ የአገሪቱ ክፍል በመጓዝ ላይ እያለ አንድ አስተዋይ ሰው በአዲሱ ሰፈር ያለ ኮረብታ ላይ ቆሞ ይጠብቃቸዋል። ከምሥራቅ የመጡት ሰፋሪዎች፣ እዚያ ከመስፈራቸው በፊት ያገኙት የመጀመሪያ ሰው ይህን አስተዋይ ሰው ነበር። እነርሱም የዚያ አካባቢ ሰዎች ምን ዓይነት እንደ ሆኑ በመጓጓት ጠየቁት።

የመለሰላቸው፣ ‹‹ትታችሁ በመጣችሁት ቦታ ያሉ ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው?›› በሚል ሌላ ጥያቄ ነበር።

‹‹በመጣንበት ቦታ ያሉ ሰዎችማ በጣም መጥፎዎች ናቸው። ሐሜተኞችና ንጹሐንን በመጉዳት ራሳቸውን የሚጠቅሙ ናቸው። ያ ቦታ ብዙ ሌቦችና ውሸታሞች የሞሉበት ነው›› ይሉታል።

ሰውየውም፣ ‹‹እዚህ ያሉትም ያው ትታችሁ እንደ መጣችሁት ቦታ ሰዎች ናቸው›› በማለት ይመልስላቸዋል።

እየሸሹት ከነበረው ዓይነት ችግር ስለዳናችው ሰውየውን አመስግነው ሰዎች አሁንም ወደ ምዕራቡ አቅጣጫ ጉዞዋቸውን ይቀጥላሉ።።

ከዚያም ሌሎች ሰፋሪዎች ይመጡና፣ ‹‹የዚህ ቦታ ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው?›› በማለት ይጠይቁታል።።

አስተዋዩ ሰውየም፣ ‹‹ትታችሁ በመጣችሁበት ቦታ ያለ ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው?›› የሚል ጥያቄ ያቀርብላቸዋል።።

‹‹ቦታው በጣም ጥሩ ነው! በጣም የምንቀርባቸው ወዳጆች ነበሩን።። እዚያ ያለ ሰዎች፣ ከራሳቸው ይልቅ የሌሎችን ጥቅም የሚያስቀድሙ ናቸው።። እያንዳንዱ ሰው እርስ በርስ ስለሚተሳሰብ በዚያ ቦታ ችግር ወይም እጦት የለም።። አንድ ሰው አንድ ትልቅ ሥራ ከጀመረ፣ የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው ይረዱታል።። ያንን ቦታ ትተን ለመምጣት መወሰን ለእኛ በጣም ከባድ ነበር፤ ሆኖም፣ ለወደ ፊቱ ትውልድ በማሰብ እንደ አገር መሥራቾች የግድ ወደዚህ ምዕራብ አገር መምጣት ስለ ነበረብን ነው የመጣነው›› ይሉታል አስተዋዩ ሽማግሌም፣ ‹‹እዚህ ያሉትም ያው ትታችሁ እንደ መጣችሁበት ቦታ ሰዎች ናቸው›› በማለት የበፊቱን ዓይነት መልስ ይሰጣቸዋል።።

ሰዎችም በጣም ደስ ብሎአቸው፣ ‹‹እንግዲያውስ መስፈር ያለብን እዚህ ነው!›› ይባባላሉ።።

የወደ ፊት ሕይወታቸውን የተመለከቱት ያለፈውን በተመለከቱበት ሁኔታ ነበር።።

ወደ ቀጣዩ ቤተ ክርስቲያን ወይም ከሰዎች ጋር ወደሚኖራችሁ ግንኙነት የምትገቡት ሌላውን ቤተ ክርስቲያን ወይም ግንኙነት ትታችሁ በመጣችሁበት መንገድ ነው።። ዮሐንስ 20÷23 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብትለ፣ ኃጢአታቸው ይቅር ይባልላቸዋል፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ባትለ ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም›› ብሏል።።

ሰዎች ያደረሱብንን በደል ምክንያት በማድረግ፣ በልባችን ቅርታና ምሬት የምናስተናግድ ከሆነ ኃጢአታቸውን

እንይዝባቸዋለን። አንድን ቤተ ክርስቲያን ትተን የምንሄደው ወይም ከሰዎች ጋር የነበረንን ግንኙነት የምናቋርጠው በቅርታና በምሬት መንፈስ ከሆነ፣ ወደ ቀጣዩ ቤተ ክርስቲያን የምንገባው ወይም አዲስ ግንኙነት የምንጀምረው በዚያው ዓይነት ዝንባሌ ነው የሚሆነው። ችግር ከተነሣ አዲስ የጀመርነውን ግንኙነት ማቋረጥ ወይም አዲስ የገባንበትን ቤተ ክርስቲያን ትተን መሄድ ቀላል ይሆንልናል። የሚደርስብን ጉዳት በአዲሱ ግንኙነታችን የገጠመን ብቻ ሳይሆን፣ ቀድሞ በነበረን ግንኙነት የደረሰብን ቁምር ይሆናል።

ፍቺ የፈጸሙ ሰዎች ሌላ ትዳር ቢመሠርቱ እንኳ ከ60 እስከ 65 እጅ እንደ ገና እንደሚፋቱ የተደረገው ጥናት አመልክቷል።[4] ሰዎች የመጀመሪያ ትዳራቸውን የሚያቋርጡበት ሁኔታ የሁለተኛው ትዳራቸውንም ሁኔታ ይወስናል። ለመጀመሪያ የትዳር ጓደኛቸው ያላቸው ይቅር አለማለት፣ ሁለተኛው የትዳር ግንኙነታቸውንም ያሰናክለዋል። ሌለኛውን ወገን መመወቀሳቸው ወይም ተጠያቂ ማድረጋቸው፤ የራሳቸውን ድርሻ ወይም የፀባይ ደካማነት እንዳያዩ ያሳውራቸዋል። ይባስ ብሎ ደግሞ አሁን፣ እንደ ገና እንጐዳ ይሆን? ወይም የሚል ስጋት ይጨመርበታል።

ይህ መርሐ በትዳርና በፍቺ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት ይመለከታል። አንድ ጊዜ ከአንድ ሌላ አገልግሎት ድርጅት ጋር ይሠራ የነበረ ሰው ከእኛ አገልግሎት ጋር ለመሥራት መጥቶ ነበር። በበፊቱ አገልግሎት መሪ ጉዳት ደርሶበት ነበር፤ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ ከእኛ ጋር እንዲሠራ እንድጠይቀው የጌታ ፈቃድ መሆኑ ተሰምቶኝ ነበር። ያለፈ ጊዜ ጉዳትና ስብራቱ በመፈወስ ላይ እንደ ሆነ አስቤ ነበር።

ለቀድሞው አገልግሎት መሪ ደውየ ይህ ሰው ከእኛ ጋር እንዲሠራ ያለኝን ዕቅድ ነገርኩት። እርሱም ለሁለቱም ማሰቤን ስለ ተረዳ፣ አበረታታኝ፤ ጥሩ ዕቅድ ማድረጌንም ነገረኝ። ሰውየው ከእኛ ጋር መሥራቱን ሲቀጥል የተጀመረው የፈውስ ሂደት የተሟላ ሊሆን እንደሚችል አስቤ ነበር። ግንኙነታቸው እንደ ገና እንዲታደስና እንዲፈወስ ጸሎቴ መሆኑን ለሁለቱም ነግሬአቸው ነበር።

አዲሱ ሰውየ ከአገልግሎታችን ጋር እንደ ተቀላቀለ፣ ብዙም ሳይቆይ ችግሮች መታየት ጀመሩ። ችግሩን ለመፍታት ብሞክርም የተገኘው መፍትሔ ጊዜያዊ ብቻ ነበር። ሰውየው በፊት ከደረሰበት ጉዳትና ስብራት ባሻገር ማየት ያቃተው ይመስል ነበር። ያለፈ ጉዳትና ስብራቱ እንደ ገና ብቅ እያለ ያስቸግረው ነበር። የበፊቱ መሪ ያደረሰበትን ዐይነት በደል እያደረስኩበት እንደ ሆነ እኔንም መክሰስ ጀመረ።

እንደ አንድ ሠራተኛ ለአገልግሎታችን ከሚሠራው ይልቅ የዚያ ሰው ሁኔታ በጣም ያሳስበን ስለ ነበር እኔም ተቸገርኩ። ሰውየው ተፈውሶ ለማየት ጽኑ ፍላጐት ነበረኝ፤ ለሌሎች የማላደርገውን ለእርሱ አደርግ ነበር።

ከሁለት ወር በኃላ ሥራውን ለቀቀ። የመጀመሪያው ዓይነት ችግር እንደ ገጠመው ተሰምቶት ነበር። ‹‹ጆን፣ ከእንግዲህ ወዲህ ከሌላ አገልግሎት ጋር አልሠራም›› በማለት ተሰናብቶ ሄደ።

ያንን ሰው ባረክሁት፤ ወጥቶ ሲሄድም ቅዝዝ ብዬ አየሁት። እርሱም ሆነ ሚስቱን እንወዳቸው ነበር። በጣም የሚያሳዝነው ትዶት ለሄደው አገልግሎት የእግዚአብሔር ጥሪ በሕይወቱ እንዳለ ግልጽ መሆኑ ነበር፤ ያ ማለት ግን፣ በሌላ አቅጣጫ አይሳካለትም ማለት አይደለም።

እርሱ ከሄደ በኃላ በጣም ተረብሼ ስለ ነበር አጥብቄ ጸለይኩ። ‹‹ሁለታችንም ከእኛ ጋር መሥራቱ ትክክል እንደ ነበር ብናስብም፣ እንዲህ በፍጥነት ለቅቆ የሄደው ለምንድነው?››

ከጥቂት ሳምንቶች በኃላ በአንድ አስተዋይ ፓስተር ጓደኛዬ በኩል ጌታ ለጥያቄዬ መልስ ሰጠኝ። ‹‹ሰዎች ቀድሞውኑ የመሸሽ ፍላጐት በልባቸው ካለ፣ በትዕግሥት እንዲቋቋሙት እግዚአብሔር ከሚፈልገው ሁኔታ እንኳ ቢሆን እንዲሸሹ ብዙ ጊዜ ይፈቅዳል›› በማለት ነበር የተናገረው።

ከዚያም፣ ከኤልዛቤል የሸሸው የኤልያስን ታሪክ ነገረኝ (1 ነገሥት 18-19 ይመ.)። ከጥቂት ጊዜ በፊት ኤልያስ ክፉዎቹን የበአልና የአስታሮት ነቢያት ገድሎ ነበር። እነዚህ ሰዎች ሕዝቡን

ወደ ጣያት አምልኮ የመሩና ከኤልዛቤል ማዕድ የሚበሉ ነበሩ። ኤልዛቤል ይህን ስትሰማ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ኤልያስን ለማስገደል ዛተች።

እግዚአብሔር የፈለገው እንሷን እንዲቀቅም ቢሆንም፣ ኤልያስ ግን ሸሸ። እንዲያውም ሞት እስኪመኝ ድረስ በጣም ተስፋ ቆርጦ ነበር። ኤልያስ የተሰጠውን ተልዕኮ መፈጸም የሚችልበት ሁኔታ ላይ አልነበረም። የሚበላው ምግብና የሚጠጣው ውሃ የያዘ መልአክ እግዚአብሔር ላከለት፤ ከዚያም አርባ ቀንና ሌሊት ተጉዞ ወደ ኮሬብ ተራራ እንዲሸሽ ፈቀደለት።

እዚያ ሲደርስ እግዚአብሔር ያቀረበለት የመጀመሪያ ጥያቄ፣ ‹‹ኤልያስ ሆይ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ?›› የሚል ነበር።

ይህ ጨርሶ መጠየቅ ያልነበረበት ጥያቄ ይመስላል። ለጉዞው የሚሆን ምግብ የሰጠው ጌታ ራሱ ነበር፤ እንዲሄድ የፈቀደለትም እርሱ ነበር፤ እዚያ ሲደርስ፣ ‹‹ኤልያስ ሆይ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ?›› ብሎ የጠየቀው እርሱ ነበር። ኤልያስ ከዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመሸሽ ተዘጋጅቶ እንደ ነበር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። ምንም እንኳ የመጀመሪያው ዕቅዱ ያ እንዳልነበር ካቀረበው ጥያቄ ግልጽ ቢሆንም ከዚያ እንዲሸሽ ፈቅዷል።

ከዚያም ለኤልያስ፣ ‹‹በመጣህበት መንገድ ተመልሰህ ወደ ደማስቆ ምድረ በዳ ሂድ፤ እዚያ ስትደርስ... የናምሲ ልጅ ኢዩን በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ ቅባው፤ ደግሞም ነቢይ ሆኖ በእግርህ እንዲተካ የአቤል ምሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው›› አለው (1 ነገሥት 19÷15-16)። በኤልሳዕና በኢዩ አገልግሎት ዐመፀኛዋ ንግሥትና ክፉ ሥርዐቷ ተወገደ (2 ነገሥት 9-10)። በእርሱ ቦታ ሆነው እንዲያገለግሉ በተቀቡ ሰዎች አማካይነት እንጂ፣ የተጀመረው ሥራ በኤልያስ አልተጠናቀቀም።

‹‹አዳጋች ሁኔታዎችን ላለ መጋፈጥ ልባችንን ካመቻቸን፣ ምንም እንኳ የእርሱ ፍጹማዊ ፈቃድ ባይሆንም፣ የፈለግነውን እንድናደርግ እግዚአብሔር ይተወናል›› በማለት ነበር ያ ፓስተር የነገረኝ።

በኃላም፣ ዘጉልቁ 22 ላይ ካለው ይህንኑ ነጥብ የሚያሳይ ታሪክ አስታወስኩ። ታሪኩ እንደሚነግረን ለእርሱ ትልቅ ሽልማት የሚያስገኝለት ስለ ነበር በለዓም እስራኤልን መርገም ፈልጐ ነበር።

መጀመሪያ ላይ፣ ወደዚያ እንዲሄድ የእርሱ ፈቃድ መሆን አለመሆኑን እግዚአብሔርን ጠይቆ ነበር፤ እግዚአብሔርም በለዓም ወደዚያ መሄድ እንደሌለበት ነግሮት ነበር። በዚህ ጊዜ የሞዓብ መሳፍንት ከበፊቱ የበለጠ ገንዘብ ይዘው መጡ፤ ትልቅ ከበሬታ እንደሚደረግለትም ነገሩት፤ በለዓም እንደ ገና እግዚአብሔርን ጠየቀ። ለበለዓም ብዙ ገንዘብና ከበሬታ ስለሚያስገኝለት እግዚአብሔር የበፊቱ ሐሳቡን ይለውጣል ብሎ ማሰብ በራሱ አስቂኝ ነው። ሆኖም፣ በዚህ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ እግዚአብሔር ነገረው።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሐሳቡን የለወጠው ለምንድነው? ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር፣ መልሱ—እግዚአብሔር ሐሳቡን አልለወጠም ነው። በለዓም ወደዚያ ለመሄድ ልቡን አዘጋጅቶ ስለ ነበር፣ ያንኑ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ተወው። በለዓም ወደዚያ በመሄዱ የእግዚአብሔር ቁጣ እርሱ ላይ የነደደው በዚህ ምክንያት ነበር።

ቀድሞውኑ የእርሱ ፈቃድ መሆኑን የምናውቀው ጉዳይን በተመለከተ እግዚአብሔርን መጨቅጨቅ፣ መነዝነዝ እንችላለን። ያኔ፣ ምንም እንኳ የእርሱ የመጀመሪያ ዕቅድ ባይሆንም፣ ለዘለቄታ የሚጠቅመን ባይሆን፣ እንኳ፣ የፈለግነውን እንድናደርግ ይፈቅዳል።

አንዳንዴ የእግዚአብሔር ዕቅድ ጉዳት እንዲደርስብንና መጋፈጥ ከማንፈልገው ሁኔታ ጋር እንድንጋፈጥ ሊሆን ይችላል። እኛ ግን፣ ሕይወታችንን ማሳደግና ማጠንከር ከሚችል ሁኔታ ስንሸሽ እንገኛለን። መሰናክልን ፊት ለፊት ከመጋፈጥ መሸሽ ጊዜያዊ ፋታ ከመስጠት ባሻገር ከችግር ነጻ አያደርገንም። የችግሩ ሥር ወይም ምክንያት ግን በዚያው ባለበት ሁኔታ ይቀራል።

ከዚያ ለድርጅታችን እንዲሠራ ቀጥረነው ከነበረ ወጣት ጋር የነበረን ልምምድ ቀድሞ የደረሰ በደል ወይም መሰናክል ከሰዎች ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ትምህርት ትቶልኝ አልፏል። በምሬትና

በመሰናከል ምክንያት ቀድሞ የነበረውን ግንኙነት አቋርጠ ከመጣ ሰው ጋር፣ ጤናማ ግንኙነት መመሥረት በጣም ያስቸግራል። መጀመሪያ ፈውስ መኖር አለበት። ምንም እንኳ የበፊቱ መሪውን ይቅር ማለቱን ቢናገርም፣ ያ ሰው ጉዳቱን ከአእምሮው አላወጣም ነበር።

ፍቅር በደልን ይቅር ይላል፤ ስለዚህም የወደ ፊቱን በተመለከተ ምን ጊዜም ተስፋ አለ። አንድን በደል (መሰናክል) በእውነት ይቅር ብለን ወይም አሸንፈን ከሆነ፣ አጥብቀን ሰላም ማድረግ መፈለጋችን አይቀርም። ምናልባት፣ ወዲያውኑ ያንን ማድረግ ባይቻል እንኳ፣ በልባችን ነገሮች የሚስተካከሉበትን አጋጣሚ እንጠብቃለን።

አንድ ወዳጄ፣ ‹‹በፈላ ውሃ የደነገጠ ውሻ፣ ቀዝቃዛ ውሃ እንኳ ይፈራል›› የሚል የቆየ ምሳሌ ነግሮኝ ነበር። ዛሬስ ቢሆን፣ በአንድ ወቅት ተቃጥለው የነበሩና ይቅር ማለት የከበዳቸው፣ እርካታ ሊሰጣቸው የሚችለውን ቀዝቃዛ ውሃ እንኳ የሚፈሩ ምን ያህል ሰዎች ይኖሩ ይሆን?

ኢየሱስ ቁስላችንን መፈወስ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ፣ ቀላል መንገድ ባለ መሆኑ ብዙ ጊዜ እንዲፈውሰን አንፈቅድም። ወደ ፈውስና መንፈሳዊ ብስለት የሚያደርስ የትሕትናና (ራስን ዝቅ የማድረግ) ራስን የመካድ መንገድ ነው። ሐዘን ያደረሰባችሁ ሰው ቢሆን እንኳ፣ የሌላውን ሰው ጥቅም የማስቀደም ውሳኔ ነው።

ቢናቁና ቢገለሉ እንኳ ሰላም የሚፈልጉ ሰዎች እንጂ፣ ትዕቢተኞች በዚህ መንገድ መሄድ አይችሉም። መንገዱ ዝቅ ወደ ማለት የሚመራ መንገድ ነው። ወደ ሕይወት የሚመራ መንገድ ነው።

በእግዚአብሔር ፊት በመሆን

የምንማረውን ሌሎች ሰዎች ፊት መማር አይቻልም።

የሰይጣን ሽንገላን እያነበብኩ ነበር። ከዚያ ወዲህ ለእግዚአብሔር ቃል የነበረኝ አመለካከት በጣም ተለውጧል። በጣም በሚያምም ሁኔታ አልፊ ነበር፤ ከዚያ መጽሐፍ ያገኘሁት መልእክት ባይረዳኝ ኖሮ ለዘላለሙ ተሰናክዬ እቀር ነበር።

- ኤፍ. ኤን ማሌዥያ

7

ጽኑ መሠረት

ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል - ‹‹እነሆ የተፈተነ ድንጋይ፣ የመሠረት ድንጋይ፣ ለጽኑ መሠረት የሚሆን የከበረ የማእዘን ድንጋይ፣ በጽዮን አስቀምጣለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም (በችኮላ አይሠራም)።

- ኢሳይያስ 28÷16

የሚያምን በችኮላ አይሠራም።›› የሚሠራው ነገር ጽኑ መሠረት ስለማይኖረው የሚቸኩል ሰው የረጋ የተደላደለ ሰው አይደለም። እንዲህ ያለው ሰው፣ በስደት ወይም በመከራ ማዕበል በቀላሉ ይነቀነቃል፤ ይናወጣል። ለምሳሌ ያህል ስምዖን ጴጥሮስ ላይ የደረሰውን እንመልከት።

ፊልጶስ ቂሣርያ በነበሩ ጊዜ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ነው ይላሉ?›› በማለት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠይቋቸው ነበር (ማቴዎስ 16÷13)።

ከደቀ መዛሙርቱ በርካታዎቹ፣ የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ ሰዎች የነበራቸውን አመለካከት በስሜት እየተናገሩ ነበር። ኢየሱስ እስኪጨርሱ ድረስ ጠብቆ በቀጥታ እነርሱን እየተመለከተ፣ ‹‹እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?›› በማለት ጠየቃቸው (ቁጥር 15)።

ደቀ መዛሙርቱ ግራ ተጋብተውና ምን መመለስ እንዳለባቸው እያሰላሰሉ እያለ፣ አንዳንዶቹ ፊት ላይ ፍርሃት ሳይታይ እንዳልቀረ፣ የሚናገሩትንም አጥተው ሳይቸገሩ እንዳልቀረ

አስባለሁ። መናገር የሚወዱትና ሌሎች የሚሉትን ሲያስተጋቡ የነበሩት ሰዎች በድንገት ፀጥ አሉ። ምናልባትም፣ ይህን ጥያቄ ከዚያ በፊት ከምር አስበውበት አያውቁም ነበር። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ አሁን ግን አጥጋቢ መልስ እንደሌላቸው ተግንዝበዋል።

ኢየሱስ ማድረግ የነበረበትን በሚገባ አድርጓል። በዚህ ጥያቄ አማካይነት ምን እያሰቡ እንደ ነበር ግልጽ አደረገ። የሚያውቁትንም ሆነ የማያውቁትን ነገር በትክክል መገንዘብ ወደሚችሉበት ቦታ አመጣቸው። ለኢየሱስ እውነተኛ ማንነት በልባቸው ቦታ ከመስጠት ይልቅ፣ በሌሎች ግምትና አስተሳሰብ ነበር ሲኖሩ የነበረው። አሁን ባደረጉት መልኩ ራሳቸውን መርምረው አያውቁም ነበር።

መልስ መስጠት የቻለ በጎላ ኢየሱስ ጴጥሮስ የሚል ስም የሰጠው ስምየን ብቻ ነበር። በድንገት፣ ‹‹አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ›› በማለት መለሰ (ማቴዎስ 16÷16)።

ከዚያም ኢየሱስ፣ ‹‹የዮና ልጅ ስምየን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ፣ ሥጋና ደም አይደለም›› አለው (ቁጥር 17)።

የዚህ መገለጥ ምንጭ ማን እንደ ሆነ ኢየሱስ ለጴጥሮስ እየተናገረ ነበር። ጴጥሮስ ይህን ዕውቀት ያገኘው፣ እግዚአብሔር ገልጠለት እንጂ፣ ሌሎች የተናገሩትን በመስማት ወይም በመማር አልነበረም።

ስምየን ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ነገር የተራበ ሰው ነበር። ሌላ ጊዜም ቢሆን፣ ለኢየሱስ ብዙ ጥያቄ የሚያቀርበው እርሱ ነበር። ሌሎቹ ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ቁጭ ብለው ሲመለከቱ በባሕር ላይ የተራመደ እርሱ ነበር። እርሱ ሌሎች በሚሰነዝሩት ሐሳብ ወይም በሚሰጡት ግምት አርፎ የሚቀመጥ አልነበረም! በቀጥታ ከእግዚአብሔር መስማት የሚፈልግ ሰው ነበር።

ኢየሱስን በተመለከተ በመለኮታዊ መገለጥ የተገኘ ይህ ዕውቀት መንፈሳዊ ነገርን የተራበ በመሆኑ፣ ያገኘው ስጦታ ማለትም ልቡ ውስጥ ከበራለት ብርሃን የተቀበለው እንጂ፣ ከራሱ ስሜት

የፈለቀ አልነበረም። ጴጥሮስ ያየውንና የሰማውን ብዙዎችም ዐይተውና ሰምተው ነበር፤ ይሁን እንጂ እንደ ጴጥሮስ ልባቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የተራበ አልነበረም።

አንደኛ ዮሐንስ 2÷27፣ ‹‹ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም፤ ነገር ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያስተምራችሁ፣ ያም እውነት እንጂ ሐሰት እንዳልሆነ...›› ይላል።

ይህ ቅባት ስምዖን ጴጥሮስን እያስተማረው ነበር። ጴጥሮስ ሌሎች የሚሉትን ሁሉ ሰምቶ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የገለጠለትን ለመረዳት ውስጡን ተመለከተ። ከእግዚአብሔር የሆነ እውነት ከተገለጠላችሁ ማንም ሊያናውጣችሁ አይችልም። እግዚአብሔር ለእናንተ አንድ ነገር ከገለጠላችሁ ዓለም በሙሉ የሚናገረው ደንታ አይሰጣችሁም። በልባችሁ ያለውን ማንም መለወጥ አይችልም።

ከዚያም ኢየሱስ፣ ‹‹አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም›› በማለት ለጴጥሮስና ለተቀሩት ደቀ መዛሙርት ተናገረ (ማቴዎስ 16÷18)። ስለሆነም፣ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ጽኑ መሠረት መሆኑን በግልጽ እናያለን፤ እዚህ ላይ ግን ጽኑ መሠረት የሆነው፣ ጴጥሮስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ መረዳቱ ነበር።

አብርሆት ያለው ቃል

ከማቀርበው ስብከት የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዲሰሙ ብዙ ጊዜ ለጉባኤዎችና ለግለ ሰቦች እናገራለሁ። ብዙ ጊዜ ማስታወሻ መያዝ ላይ ስለምናተኩር የተነገረውን ሁሉ በጽሑፍ እናሰፍራለን። እንዲህ ማድረጉ ቅዱሳት መጻሕፍትንና አተረጓጎማቸውን በተመለከተ ምናልባት የአእምሮ መረዳት፣ ማለትም የጭንቅላት ዕውቀት ይሰጠን ይሆናል።

የሚኖረን የጭንቅላት ዕውቀት ብቻ ከሆነ፣ ሁለት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ (1) በቀላሉ ለስሜታዊነት እንጋለጣለን ወይም (2)

በአእምሮ መረዳት በምንችለው ብቻ እንወሰናለን። ይህ ግን ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠርትበት ጽኑ መሠረት አይደለም። ቤተ ክርስቲያኑ በቃል በተጠና ጥቅስ ብዛት ሳይሆን፣ ከመለኮታዊ መገለጥ በተገኘ የእግዚአብሔር ቃል እንደምትመሠረት ነው እርሱ የተናገረው።

አንድ ስብከት ስንሰማ፣ ወይም አንድ መጽሐፍ ስናነብ፣ መንፈሳችን ውስጥ አብርሆት የሚያመጡ ቃሎች ወይም ሐረጐች መፈለግ አለብን። ይህ ለእኛ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚሆነው። ብርሃንና መንፈሳዊ መረዳት ወይም ግንዛቤ ይሰጠናል። ዘማሪው፣ ‹‹የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤ አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል›› ይላል (መዝሙር 119÷130)። የሚያበራልንና ግልጽ የሚያደርግልን ቃሉ ለልባችን እንጂ፣ ለአእምሮአችን የሚሰጠው ትርጓሜ አይደለም።

አንዳንዴ ሰባኪው እየተናገረ ያለው ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ለልቤ የሚሰጠው አብርሆት ግን ፍጹም የተለየ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ አገልጋዩ የተናገረውን ቃል ራሱን ይቀባና ልቤ ውስጥ እንዲቀጣጠል ያደርጋል። በዚህም ሆነ በዚያ፣ ለእኔ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖአል ማለት ነው። አላዋቂ (መረዳት የሌለው) ከመሆን ወደ በሳልነት (አብሮሆት ያለው) ወደ መሆን የሚለውጠን ይህ ነው። እንግዲህ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመሠርት የተናገረው በእንዲህ ዐይነቱ ልባችን ውስጥ አብርሆት በሚያገኝ ቃል ጽኑ መሠረት ነው ማለት ነው።

የተገለጠ የእግዚአብሔርን ቃል ኢየሱስ ከዐለት ጋር አመሳስሎታል። ዐለት ጽናትና ብርታትን ይወክላል። አንደኛው ዐለት ላይ ሌላው ደግሞ አሸዋ ላይ ተሠርተው ስለ ነበሩ ሁለት ቤቶች የተነገረውን ምሳሌ እናስታውሳለን። ስደትን፣ መከራንና ችግርን የመሳሰሉ አዳጋች ሁኔታዎች ሁለቱንም ቤቶች እንደ ማዕበል ሲመቷቸው፣ ዐለት ላይ የተሠራው ቤት ጸንቶ ሲቆም፣ አሸዋ ላይ የተሠራው ግን ሙሉ በሙሉ ፈረሰ።

ከእግዚአብሔር መስማት ያለብን አንዳንድ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። ለምሳሌ ያህል ማንን ነው ማግባት

ያለብኝ? የት ነው መሥራት ያለብኝ? የየትኛው ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለብኝ? የተሰጥኦትንና ሌሎችን ማንሣት ይቻላል። እነዚህን ውሳኔዎች በተመለከተም ቢሆን የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ሊኖረን ይገባል። ከዚያ ውጪ ውሳኔያችን ጽናት በሌለው መሬት ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

እግዚአብሔር በመንፈሱ የገለጠልን ከእኛ ሊወሰድ አይችልም። ይህ ለምናደርገው ማንኛውም ነገር መሠረት ሊሆነን ይገባል። እንዲህ ካላደረግን በሚገጥመን መከራና ችግር በቀላሉ እንሰናከላለን፤ እውነተኛ ማንነታችንን ከማየትም እንታወራለን።

ቃሉን ሰምተው በደስታ ቢቀበሉት እንኳ፣ ወደ ጥልቅ ልቦናቸው ገብቶ ሥር ስላልሰደደ ሰዎች፣ ኢየሱስ የተናገረውንም አስታውሱ። እነዚህ ሰዎች ቃሉን የተቀበሉት በከፍተኛ ስሜትና ደስታ ነበር።

> ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበሉታል፤ ነገር ግን ሥር የሌላቸው ስለሆኑ የሚቈዩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ ይሰናከላሉ።

- ማርቆስ 4÷16-17

ሁለቱም የሚናገሩት ለአንድ ተክል ወይም ሕንፃ ጽናትና ብርታት ስለሚሆን ነገር በመሆኑ *ሥር* እና *መሠረት* የሚሉትን ቃሎች ያለ ምንም ችግር በማለዋወጥ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። በተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ጸንቶ ያልቆመ ወይም ያልተመሠረተ ሰው በመሰናከል ማዕበል በቀላሉ ተገፍቶ ይወድቃል።

ኢየሱስ በጥያቄ ያፋጠጣቸውን ደቀ መዛሙርት የምንመስል ስንቶቻችን እንሆን ይሆን? እስከዚያ ድረስ እነዚያ ደቀ መዛሙርቱ ይኖሩ የነበረው ሌሎች ሲናገሩ ወይም ሲሰበኩ በሰሙት ላይ ነበር። የእግዚአብሔርን ምክር ወይም የመንፈስን ምስክርነት ሳይጠይቁ የሌሎችን ሐሳብና ቃል እንደ እውነት ይወስዳሉ። መኖርና መናገር

ያለብን፣ እግዚአብሔር በገለጠልን ብቻ ነው። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠርተውም በዚህ ላይ ነው።

በአንድ ወቅት ከአንድ ወጣት ጋር በጣም መቀራረብ የጀመረች ያላገባች ጸሐፊ ነበረችኝ፤ ወጣቱም የቤተ ክርስቲያኑ ሠራተኛ ነበር። እነዚህ ወጣቶች በየቀኑ በጣም እየተቀራረቡ ይሄዱ ነበር። በጣም መቀራረባቸውን የሚያይ ሰው ሁሉ እንደሚጋቡ እርግጠኛ ሆኖ ነበር። እነርሱም ቢሆኑ በጉዳዩ ተነጋግረውበት ነበር።

አንድ እሑድ ምሽት ዋናው ፓስተር ይጠራቸውና፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል - እናንተ ሁለታችሁ ትጋባላችሁ›› ይላቸዋል።

በማግሥቱ ጠዋት ጸሐፊዬ ወደ ቢሮ የመጣችው አየር ላይ እየተንሳፈፈች ነበር ማለት ይቻላል። በጣም ደስ ብሏት ነበር። የጋብቻ ሥርዓታቸውን እኔ እንድፈጽምላቸው ጠይቃኝ ነበር፤ እኔም ለእኔ ትልቅ ክብር እንደ ሆነ ነግሬአት ነበር። ለማማከር አገልግሎት ሁለቱንም እንዳገኛቸውም ቀጠሮ ይዤላቸው ነበር።

ግን ውስጤ ነጻነት አልነበረውም። በቀጠሮው ቀን ወደ ቢሮዬ ሲመጡ መንፈሴ እየታወከ ነበር። ጸሐፊዬን ፊት ለፊት እያየሁ፣ ያ ወጣት በእርግጥ እግዚአብሔር ለእርሷ የመረጠላት ሰው መሆኑን ምን ያህል እርግጠኛ እንደ ሆነች ጠየቅኃት። ቅንጣት ያህል ጥርጥር እንደሌላት እየተፍለቀለቀች መለሰች።

እንደ ገና ወጣቱን ፊት ለፊት እያየሁ፣ ‹‹ይህችን ልጃገረድ እንድታገባ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለህ ታምናለህ?›› በማለት ጠየቅሁት።

ለአፍታ ያህል በከፊል አፉን ከፍቶ ካየኝ በኃላ፣ ‹‹የለም፤ እርግጠኛ አይደለሁም›› በሚል ዓይነት ስሜት ራሱን ነቀነቀ።

ሁለቱንም ተራ በተራ ካየሁ በኃላ ለወጣቱ፣ ‹‹አላጋባችሁም። እናንተ ላይ ማን ትንቢት እንደ ተናገረ ወይም ምን እንደ ተናገረ ግድ የለኝም፤ ምን ያህል ሰው፣ ‹‹እናንተ ሁለታችሁ ጥሩ ባልና ሚስት ትሆናላችሁ›› በማለት እንደ ተናገረ ግድ የለኝም።

እግዚአብሔር ፈቃዱን ለልባችሁ ግልጽ ካላደረገ ጋብቻ የምትፈጽሙበት ምክንያት የለም።

‹‹የእርሱ ፍጹማዊ ፈቃድ መሆኑን ሳይገልጥላችሁ ብትጋቡ›› በማለት ቀጠልኩ። ‹‹ማዕበል ሲመጣ - ደግሞም መምጣቱ አይቀርም - ሌላ ሴት አግብቼ ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር? ታዲያ፣ አሁን ምን ማድረግ አለብኝ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ። የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ማረጋገጥ ነበረብኝ። አሁን ግን ወጥመድ ውስጥ ያለሁ ያህል ይሰማኛል።

‹‹ያኔ ልባችሁ ይዝላል፤ ጋብቻችሁ ላይ የሚቃጣውን ችግር መቋቋም አትችሉም። በነገራችሁ ሁሉ የምታወላውሉና የምታመነቱ ትሆናላችሁ።››

ከዚያም ሁለቱንም አሰናበትኳቸው፤ ጋብቻን በተመለከተ ከእንግዲህ የምንገናኝበት ምክንያት እንደሌለም ነገርኳቸው። እርሱ እፎይ ያለ ይመስል ነበር፤ እርሷ ግን በጣም ተረብሻ ነበር። ለቀጣዮቹ ሁለት ሳምንቶች ቢሮዋችን ውስጥ የነበረው ሁኔታ ጥሩ አልነበረም። ሆኖም፣ የተናገርኩት እውነት መሆኑን ዐውቅ ነበር። ያ ወጣት የእርሷ ባል እንደሚሆን በእውነት እግዚአብሔር ተናግሮአት ቢሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔር ለእርሱም ግልጽ እንደሚያደርግላት መተማመን ነበረባት፤ ያ ሆኖ ቢሆን ኖሮ፣ በእኔም ሆነ በእግዚአብሔር ቅር መሰኘት አይኖርም ነበር። በነገሩ ገፍታ ከመሄድ እንድትቆጠብና እርሱም ከእግዚአብሔር እስኪሰማ ጊዜ ልትሰጠው እንደሚገባ ነገርኳት፤ የነገርኳትንም አደረገች።

ሦስት ሳምንት ካለፈ በኃላ እንደ ገና እንዳናግራቸው ጠየቁኝ። ወዲያውኑ የደስታ ስሜት ተሰማኝ፡ በቀጠሮው ጊዜ ወደ ቢሮዬ ሲመጡ፣ የእርሱ ዓይኖች እንደ ፊርጥ እያበሩ፣ ‹‹የወደ ፊት ሚስቴ እንድትሆን ይህችን ልጃገረድ እግዚአብሔር እንደ ሰጠኝ አሁን በጣም እርግጠኛ ሆኜአለሁ›› አለ። በሰባት ወሮች ውስጥ ተጋቡ።

እግዚአብሔር አንድ ግንኙነት ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳኖራችሁ የምታውቁ ከሆነ ጠላት በቀላሉ እናንተን ከዚያ

ማውጣት አይችልም። በተገለጠ የእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ላይ ተመሥርታችኃል፤ ስለሆነም የማይቻል ቢመስል እንኳ፣ በግጭቶች መካከል በሰላም ታልፋላችሁ።

ሌላ አማራጭ የለም

የእኔና የሚስቴ የመጀመሪያዎቹ አምስት የትዳር ዓመቶች በጣም አስቸጋሪ ነበሩ። ቀድሞ የነበረንን ፍቅር ማደስ የማይቻል እስኪመስል ድረስ እርስ በርስ እንነታረክ ነበር።

በዚያ ሁሉ መሐል በአንድነት ያቆየን አንድ ነገር ብቻ ነበር – የተጋባነው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት እንደ ነበር ሁለታችንም በሚገባ እናውቅ ነበር። ስለሆነም መፋታትን እንደ አንድ ምርጫ አልወሰድንም። የነበረን ምርጫ እርሱ እንደሚፈውሰንና እንደሚለውጠን ማመን ብቻ ነበር። የቱንም ያህል የሚያምም ቢሆን እንኳ፣ ሁለታችንም በዚህ ሂደት ማለፍ ነበረብን።

ነገሩን ሁሉ እርግፍ አድርጌ ለመተው ባሰብኩ ጊዜ ሁሉ፣ ትዳራችንን በተመለከተ እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ ቃል አስታውስ ነበር። ለአብሮነታችን እግዚአብሔር ያቀደውንና እያደረገ ያለውን ማጨናገፍ አልፈለግሁም።

እግዚአብሔር የሰጠን አንዱ ተስፋ ቃል፣ እኔና ሚስቴ አንድ ላይ ሆነን እንደምናገለግለው ነበር። ተስፋውን በሰጠን ጊዜ ያንን በቀላሉ ማየት ይቻላል ለአገልግሎት የሚያነሣሣ የእግዚአብሔር እጅ በሁለታችንም ላይ ነው በማለት አስቤ ነበር።

ትዳራችን ማዕበል መካከል ሲሆን ግን፣ የተስፋ ቃሉ ግልጽ ሆኖ አልታየኝም ነበር። ያም ሆኖ ግን፣ ተስፋ መቁረጥ አልፈለግሁም። ትዳራችን ውስጥ ከገባው ፀብና ትዕቢት የተነሣ ተፈጥሮአዊው ተስፋ እንኳ ጠፍቶ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ያኔም ቢሆን ልቤ ውስጥ ልዕለ ተፈጥሮአዊው የሕይወት ዘር ነበር። ያ ተስፋ በሚያስፈልገኝ ጊዜ መልሕቅ ወይም መሠረት ሆኖኝ ነበር።

ጊዜ እያለፈ ሲሄድ እግዚአብሔር ግንኙነታችንን መፈወሱ ብቻ ሳይሆን፣ ቀድሞ ከነበረው የበለጠ መጽናት መጠንከሩ ግልጽ

መሆን ጀመረ። እርስ በርስ ይቅር በመባባልና ካለፈ ጥፋት በመማር በግጭቶች መሐል ተያይዘን አደግን። አሁን ሁለታችንም አብረን እያገለገልን ነው። ከእንግዲህ ሚስቴን፣ እንደ ወዳጄና ምርጥ ጓደኛዬ ብቻ ሳይሆን፣ በጣም የምተማመንባት አገልጋይ አድርጌ ነው የምመለከታት። ከማንኛውም ሰው ይልቅ ምስጢሬን የማካፍለው ለእርሷ ነው።

እነዚያን አስቸጋሪ አምስት ዓመቶች ካሳለፍኩ በኃላ እግዚአብሔር በሁለታችንም ውስጥ ያለውን ደካማነት ዐይቶ እንደ ነበርና እርስ በርስ የነበረን የሻከረ ግንኙነት ያንን ወደ ብርሃን እንዳወጣው እረዳለሁ።

እንደ ባልና ሚስት አብረን መሆናችን ምን ያህል መልካም መሆኑን ሳስብ በጣም እደነቃለሁ። ከሊዛ ጋር ከመተዋወቄ በፊት እግዚአብሔር ሚስት እንዲሰጠኝ አጥብቄ ስጸልይ ነበር። ያ ምርጫ በሕይወቴ ካደረግሁት በጣም ጠቃሚ ውሳኔ ማለትም፣ ለወንጌል ከመታዘዝ ቀጥሎ ሁለተኛው ነው። እየጸለይኩና እግዚአብሔር ለሚስትነት የሚመርጥልኝን ሴት እየጠበቅሁ ስለ ነበር ሌሎች በትዳር ውስጥ የገጠማቸው ዐይነት ችግር እኔን እንደማይገጥመኝ አስብ ነበር። ምንኛ ተሳስቻለሁ!

እግዚአብሔር የመረጠልኝ ሚስት ልቤ በጣም የሚፈልጋትን ነበር። ይሁን እንጂ፣ እኔ ውስጥ ለነበረው ራስ ወዳድነትና አለመብሰል ተጋልጣ ነበር። ፍቺን በመምረጥ ወይም እርሷን በደለኛ በማድረግ ከግጭት ባመልጥ ኖሮ የእኔ ጮርቃነት ግልጽ አይሆንም ነበር፤ በደል ደርሶብኛል በሚል ሽፋን እንደ ተሸፈነ ይቀር ነበር። ጋብቻን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቄ እርሷን ትቼ ከመሄድ ጠበቀኝ።

ምናልባትም ይህን በማንበብ ላይ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁ፣ ትዳር በመሠረትኩ ጊዜ እኔ አልዳንኩ እንደነበር ታስቡ ይሆናል።

ለእናንተ እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኃል፤ ‹‹ላገቡት ይህን ትእዛዝ እሰጣለሁ፤ ይህም ትእዛዝ የጌታ እንጂ፣ የእኔ አይደለም። ሚስት ከባሏ አትለያይ፤ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር፤ አለዚያ ከባሏ

ጋር ትታረቅ፤ ባልም ሚስቱን አይተዋት… ወንድሞች ሆይ፣ እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ጸንቶ ይኑር›› (1 ቆሮንቶስ 7÷10-11፣ 24)።

በመሰናከል ወጥመድ አማካይነት ከጽናታችሁ እንዳትናወጡ ይህ የጋብቻ ቃል ኪዳን ልባችሁ ውስጥ ዘልቆ ይግባ። በነገር ሁሉ ፈቃዱን እንዲገልጥላችሁ እግዚአብሔር ለምኑ።

ምናልባትም አንዳንዶቻችሁ አማኞች ብትሆኑም፣ ትዳር የመሠረታችሁት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ላይሆን ይችላል። ትዳራችሁን በተመለከተ ወደ እግዚአብሔር በረከት እንድትገቡ ከፈለጋችሁ ከማግባታችሁ በፊት የእርሱን ምክር ባለ መፈለጋችሁ ንስሐ አድርጉ፤ እርሱም ይቅር ይላችኃል። ሁለቴ መሳሳት አንድ ትክክለኛ ነገር እንደማያስገኝ ምን ጊዜም በልባችሁ ያዙ - ከመሰናከል የተነሣ ቃል ኪዳን ማፍረስ የችግሩ መፍትሔ አይሆንም። ጋብቻችሁን በተመለከተ ቃል እንዲሰጣችሁ ጌታን ፈልጉ።

ጽኑ መሠረት

የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትና አገልግሎታችንን ልንመሠረትበት የሚገባ ጽኑ መሠረት ነው። ለአጭር ጊዜ ብቻ ተሳታፊዎች ስለ ነበሩባቸው ቤተ ክርስቲያኖችና የአገልግሎት ተቋሞች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ነግረውኛል። እነዚህ ሰዎች የሚንቀሳቀሱት ወይም ርምጃ የሚወስዱት በሚገጥሟቸው ችግሮች እንጂ፣ በእግዚአብሔር ምሪት አለ መሆኑን ሳስብ ልቤ በጣም ያዝናል። ችግሮቹ ምን ያህል ትልልቅ እንደ ነበሩ፤ እነርሱና ሌሎች ወገኖች ላይ የደረሰው በደል እጅግ ከባድ እንደ ነበር እያጋነኑ ይናገራሉ። በውሳኔያቸው ትክክል እንደ ነበሩ ያስባሉ። ይሁን እንጂ፣ የማያቀርቡት አጉል ምክንያት የራሳቸውን ደካማነት እንዳያዩ ግርዶሽ ይሆንባቸዋል።

ከአገልግሎት ተቋሞች ወይም ከቤተ ክርስቲያኖች ጋር አሁን ያላቸውን ግንኙነት፣ ‹‹ጊዜያዊ›› ይሉታል፤ ወይም ደግሞ፣ ‹‹ለጊዜው እግዚአብሔር ያስቀመጠኝ ቦታ›› ይሉታል። እንዲውም፣ አንድ ጊዜ

አንድ ሰው፣ ‹‹እዚህ ቤተ ክርስቲያን ያለሁት በውሰት ነው›› ሲል ሰምቻለሁ። እንዲህ በማለት የሚናገሩት፣ ነገሮች አስቸጋሪ ሲሆኑባቸው ወዲያውኑ ለመሸሽ ማምለጫ መንገድ እንዲሆንላቸው ነው። በሚሄዱባቸው አዳዲስ ቦታዎች ሁሉ መሠረት የሚሆናቸው ነገር የለም፣ ማዕበል በቀላሉ እየነዳ፣ ቀጣዩ ወደብ ላይ ይጥላቸዋል።

ወደ ማን እንሄዳለን?

እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ? በማለት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ካቀረበው ጥያቄ፣ የተገለጠ የእግዚአብሔርን ፊቃድ ስናውቅ ስለሚመጣ ጽናትና እርግጠኝነት እንመለከታለን። ስምዖን ጴጥሮስን ተመልከቱ።

እግዚአብሔር አባት ለልቡ የገለጠለትን ስምዖን ከተናገረ በኃላ ኢየሱስ፣ ‹‹አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም›› አለ (ማቴዎስ 16÷18)

የስምዖንን ስም ኢየሱስ ጴጥሮስ ወደሚል ለወጠው። ይህ ትኩረት የሚያሻው ፋይዳ አለው፤ ምክንያቱም ስምዖን፣ ‹‹መስማት››[1] ማለት ነው። ጴጥሮስ ደግሞ፣ ‹‹ድንጋይ››[2] ማለት ነው። ለልቡ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቱ ጠንካራ ድንጋይ ሆነ። በዐለት መሠረት ላይ በድንጋይ የተሠራ ቤት፣ ዐውሎ ነፋስና ማዕበል ቢመታው እንኳ ጸንቶ ይቆማል።

እዚህ ላይ ዐለት የሚለው ቃል ፔትራ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ‹‹ትልቅ ዐለት››[3] ማለት ነው። ከእንግዲህ እርሱ ቤቱ የሚሠራበት ትልቅ ድንጋይ መሆኑን ኢየሱስ ለስምዖን ጴጥሮስ እየተናገረ ነበር።

በኃላም 1 ጴጥሮስ 2÷5 ላይ ጴጥሮስ፣ ‹‹እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ›› በማለት ጽፎአል። አንድ ድንጋይ የትልቅ ዐለት ትንሽ ክፋይ ነው። በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብርታት፣ ጽናትና ኃይል አለ፤ ያንን የሚቀበል ሰው ሕይወቱ ፍሬ ያፈራል። ያ ሰው፣ ሕያው

የእግዚአብሔር ቃል በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብርታት ብርቱ ይሆናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ 1 ቆሮንቶስ 3÷11 ላይ እንደ ጻፈው፣ ‹‹አንድ ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ መሠረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።›› ሕያው የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ስንፈልገው እርሱ ይገለጣል፤ ደግሞም መሠረት ይሆናል።

የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማብቂያ ላይ አብረውት እያገለገሉ ለነበሩት ሰዎች፣ ሕይወት አስቸጋሪ ሆኖባቸው እንደ ነበር ከዮሐንስ 5÷16 እንመለከታለን። የሃይማኖት መሪዎቹና አይሁድ እርሱን ለመግደል በመፈለግ ኢየሱስን እያሳደዱ ነበር። አንዳንድ ነገሮች ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ፣ እርሱን በግድ ወስደው ንጉሥ ሊያደርጉት ፈልገው ነበር፤ እርሱ ግን ያንን ስላልፈለገ ትቷቸው ሄደ (ዮሐንስ 6÷15 ይመ.)።

ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ፣ ‹‹እንደዚያ የሚያደርገው ለምንድነው?›› በማለት ሳይጠይቁ አይቀርም። ‹‹ይህ'ኮ ለእርሱም ሆነ ለእኛ ጥሩ አጋጣሚ ነው።›› ንጉሥ መሆንን አለመፈለጉ ረብሿቸው ነበር። ማንነታቸውን የሚያናውጥ ነፋስና ማዕበል እየመጣ ነበር።

‹‹ይህን ሰው ለመከተል ቤተ ሰባችንንና ሥራችንን ጥለን መጥተናል። እርሱ ይመጣል የተባለው መሲሕ ነው። ይህን መጥምቁ ዮሐንስ ተናግሮአል፤ በፊልጶስ ቂሣርያ በነበርን ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስም ይህን ሲናገር ሰምተናል። እነዚህ ሁለት ምስክሮች ናቸው፤ ታዲያ፣ አሁን ያሉትን መሪዎች ክፉ የሚናገራቸው ለምንድነው? የገዛ ራሱን መቃብር የሚቆፍረው ለምንድነው? ሌላው ቢቀር፣ የእርሱ ደቀመዛሙርት የሆንነው እኛን እንኳ፣ ‹‹እናንተ እምነት የሌላችሁ ጠማማ ትውልድ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ›› የሚለውን የመሰለ ጠንካራ ቃል የሚናገረው ለምንድነው?››

ኢየሱስ ለመከተል ሁሉን እርግፍ አድርገው ትተው ለመጡ ለእነዚያ ሰዎች የመሰናከል ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች እየመጡ ነበር።።

አንድ ቀን ደግሞ ኢየሱስ፣ ‹‹እውነት እላችኃለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ፣ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም›› በማለት ለእነርሱ በጣም እንግዳ የሆነ ትምህርት አስተምሮ ነበር (ዮሐንስ 6÷53)።

‹‹ምንድነው እየተናገረ ያለው?›› በማለት ግራ ተጋቡ።። ‹‹ይህ በበኩሌ መቀበል ከምችለው በላይ ነው!›› ያም ብቻ አይደለም፤ ይህን የተናገረው ደግሞ በቅፍርናሆም ያለው ምኩራብ መሪዎች ፊት ነበር።። እንዲህ እንዲህ ያለ ነገሮች ተፈጠማምረው ደቀ መዛሙርቱ መቀበል ከሚችሉት በላይ ሆኑባቸው።።

> ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣ ‹‹ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀበለው ይችላል?›› አሉ።።
>
> - ዮሐንስ 6÷60

የኢየሱስ ምላሽ ስሙ፤

ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር ማጉረምረማቸውን ኢየሱስ በገዛ ራሱ ተረድቶ እንዲህ አላቸው፤ ‹‹ይህ ዕንቅፋት (መሰናክል) ይሆንባችኃልን?››

- ዮሐንስ 6÷61

እነዚህ የገዛ ራሱ ደቀመዛሙርት ነበሩ! እውነትን ከማድበስበስ ይልቅ፣ እውነቱን ፊት ለፊት ነገራቸው።። አንዳንዶቹ ደካማ መሠረት ላይ ተመሥርተው እንደ ነበር ያውቃል።። ደካማ መሠረታቸውን በማጋለጥ ልባቸው ውስጥ ያለውን ማየት የሚችለበት ዕድል ሰጣቸው።። እነርሱ ግን እንደ ሰምያን ጴጥሮስ ወይም እንደ ሌሎቹ ደቀመዛሙርት እውነትን የተራቡ አልነበሩም።። ያደረጉትን ተመልከቱ፤

ከዚህም በኃላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኃላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ አልተከተሉትም።

- ዮሐንስ 6÷66

ወደ ኃላ የተመለሱት፣ ‹‹ብዙዎች›› እንጂ፣ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ልብ አድርጉ። ከእነዚህ መሐል ቀደም ሲል በፊልጶስ ቂሣርያ በነበሩ ጊዜ፣ ‹‹አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ይሉሃል፤ አንዳንዶች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል›› በማለት በፍጥነት መልስ ሰጥተው የነበሩ ሰዎች እንደሚገኙ አይጠረጠርም (ማቴዎስ 16÷14)። እነዚህ ሰዎች መጀመሪያውኑ በተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል የተመሠረቱ አልነበሩም።

መሰናክለ በዚህ ዘመን ብዙዎች የሚያደርጉትን እንዲያደርጉ ገፋፋቸው - ትተው ሄዱ። የተታለሉና በደል የደረሰባቸው መስሏቸው ነበር፤ ግን እንደዚያ አልነበረም። ዐይኖቻቸው ራስ ወዳድ ፍላጐታቸው ላይ አትኩሮ ስለ ነበር፣ እውነቱን ማየት አልቻሉም።

ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ፊት ለፊት በተናገረ ጊዜ፣ ጴጥሮስ የተናገረውን ተመልከቱ።

ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን፣ እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ? አላቸው ስምዖንም ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ አንተ አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ አምነናል፤ ዐውቀናልም››

- ዮሐንስ 6÷67-69

ኢየሱስ እነዚያን ሰዎች፣ ‹‹እባካችሁ አትሂዱ፤ እንደምታውቁት ብዙዎች ትተውኝ ሄደዋል። አሁን እናንተም ትታችሁን ስትሄዱ ብቻዬን እንዴት እሆናለሁ!›› በማለት አልለመናቸውም። በፍጹም! ይልቁን፣ ‹‹እናንተም መሄድ ትፈልጋላችሁ?›› ነበር ያላቸው።

ምንም እንኳ እርሱም እንደ ሌሎቹ መሰናከል የሚችልበት አጋጣሚ ቢኖርም፣ ስምየን ጴጥሮስ የሰጠውን መልስ ስሙ።

‹‹ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሂዳለን?›› ነበር ያለው።

የሰማው ነገር እርሱንም ግራ ሳያጋባው አልቀረም፤ ይሁን እንጂ፣ እርሱ ውስጥ ሌሎች ዘንድ የሌለ ማወቅ ነበር። ፊልጶስ ቂሣርያ በነበሩ ጊዜ ጴጥሮስ ኢየሱስ፣ ‹‹የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ›› እንደ ሆነ እውነተኛ መገለጥ ተቀብሎ ነበር (ማቴዎስ 16÷16)።

አሁን ደግሞ በዚህ ፈተና ግለት መሐል፣ ልቡ ውስጥ የተተከለውን እውነት ተናገረ፤ ‹‹አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል ዐውቀናልም›› አለ። ይህ በትክክል ፊልጶስ ቂሣርያ በነበሩ ጊዜ የተናገረው ነበር። እርሱ በሕያው የእግዚአብሔር ቃል ዐለት ላይ የተመሠረተ ድንጋይ ነበር። ስለዚህ እንደ ሌሎች ተሰናክሎ ትቶት አይሄድም።

መከራ ማንነትን ይገልጣል

መከራና ችግር አንድ ሰው ያለበትን ሁኔታ ይገልጣሉ በማለት ብዙ ጊዜ እናገራለሁ። በሌላ አነጋገር በመንፈሳዊ ደረጃ የት እንዳለን ይወስናሉ ማለት ነው። እውነተኛ የልባችሁን ሁኔታ ይገልጣሉ። ለተጽዕኖ የምትሰጡት ምላሽ፣ እውነተኛ ማንነታችሁ የሚሰጠው ምላሽ ነው።

አሸዋ ላይ በጣም የሚያምር፣ በጣም ውድ በሆነ ነገሮች የተሠራና ከፍተኛ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ባለ አምስት ፎቅ ሕንፃ መሥራት ትችላላችሁ። ሁሉም ነገር መልካም እስከ ሆነ ድረስ፣ ውብና ጠንካራ መስሎ ይታያል።

እዚያ ሕንፃ ጐን ተራ የሚመስል ባለ አንድ ፎቅ ሕንፃ መሥራት ትችላላችሁ። አጠገቡ ካለው ያማረ ሕንፃ ጋር ሲነጻጸር ትኩረት የማይስብ፣ እንዲያውም መኖሩን እንኳ ማንም ልብ የማይለው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ሰዎች ማየት ያልቻሉት ነገር - ዐለት ላይ መመሥረቱን ነው።

ጐርፍና ዐውሎ ነፋስ እስካልተነሣ ድረስ፣ ያ ባለ አምስት ፎቅ ሕንፃ ያለበት ሁኔታ ጥሩ ይመስላል። ከባድ ጐርፍ ከመጣ ግን ባለ አምስት ፎቁ ቤት ይፈርሳል፤ በቀላሉ እንዳልነበር ይሆናል። አነስተኛ ዐቅም ያላቸው ነፋሶችን መቋቋም ቢችል እንኳ፣ ዐውሎ ነፋስን መቋቋም አይችልም። ለተመልካች ተራ የሚመስለው ባለ አንዱ ፎቅ ሕንፃ ግን ጸንቶ ይቆማል። ሕንፃው ትልቅ የመሆኑን ያህል አወዳደቁም የዚያኑ ያህል ከባድ ይሆናል።

በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች በፊልጶስ ቂሣርያ እንደ ነበሩት ለመናገር ችኩሎች እንደ ነበሩትና በኃላ ግን ማንነታቸው እንደ ተገለጠባቸው ደቀ መዛሙርት ናቸው። እንደዚያ ባለ አምስት ፎቅ ሕንፃ – የጽናት፣ የብርታትና የውበት ምሳሌዎች መስለው ይታያሉ። ጥቃቅንና ተራ የሆኑ ማዕበሎችን ይቋቋሙ ይሆናል። ከባድ ጐርፍና ማዕበል ሲመጣ ግን ምንነታቸው ይገለጣል።

ሌሎች በሚናገሩት ላይ ሳይሆን፣ ሕይወታችሁን በተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረታችሁን እርግጠኞች ሁኑ። ጌታን መፈለጋችሁንና በልባችሁ እርሱን ማድመጣችሁን ቀጥሉ። ሰዎች ስላደረጉት ብቻ አንድን ነገር አታድርጉ፤ ሰዎች ስለ ተናገሩት ብቻ አንድን ነገር አትናገሩ። እርሱን ፈልጉ፤ ልባችሁ ውስጥ በበራላችሁ ብርሃን ጸንታችሁ ቁሙ!

ጠላት ነውጥ የሚያመጣው ለማጥፋት ነው።

እግዚአብሔር ግን ከዚያ የተለየ ዓላማ አለው።

የሰይጣን ሸንገላ በተሰኘው መጽሐፍ በኩል ስለ ተላለፈው መልእክት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በሕይወቴ ታላቅ ለውጥ እንዲመጣ እየጸምኩና እየጸለይኩ ነበር። በታላም እግዚአብሔር ወደዚህ መልእክት መራኝ፤ በአስደናቂ ሁኔታ ሕይወቴን ለውጦታል። ይህ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ፣ ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ ነው።

- ሲ. ፒ ኒው ዚላንድ

8

የሚናወጥ ነገር ሁሉ ይናወጣል

በዚያን ጊዜ ድምፁ ያናወጠው ምድርን ነበር፤ አሁን ግን፥ ‹‹ምድርን ብቻ ሳይሆን፣ ሰማያትንም አንድ ጊዜ ደግሜ አናውጣለሁ›› ብሎ ቃል ገብቶአል። አንድ ጊዜ ‹‹ደግሜ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማይናወጡት ጸንተው ይኖሩ ዘንድ የማይናወጡት ይኸውም – የተፈጠሩት የሚወገዱ መሆናቸውን ነው።

- ዕብራውያን 12÷26-27

የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠራበት መሠረት መሆኑን ባለፈው ምዕራፍ ተመልክተናል። ሌሎች ደቀ መዛሙርት ተሰናክለው ኢየሱስን ትተው ቢሄዱም፣ ጴጥሮስ ግን እንደዚያ አለማድረጉን ዐይተናል። እርሱም እንደ ሌሎች ትቶ መሄድ እንደሚችል ኢየሱስ ቢፈቅድለት እንኳ፣ ስምዖን ጴጥሮስ ልቡ ውስጥ የነበረውን እውነት አውጥቶ ተናግሮአል።

አሁን ደግሞ ኢየሱስ ተላልፎ በተሰጠበት ሌሊት ለስምዖን ጴጥሮስ ቀርቦ የነበረ ሌላ ፈተና እንመልከት።

ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር ተቀምጦ ነበር፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ የጌታ ራት የሚባለውን ሥርዐት እያዘጋጀ እያለ፣ ‹‹አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ በማእድ ከእኔ ጋር ናት። የሰው ልጅስ አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ይሄዳል፤ ነገር ግን እርሱን አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት›› በማለት አስደንጋጭ ነገር ተናገረ (ሉቃስ 22÷21-22)። እንዴት ከባድ ነው፤

በዚህ ዘመን አገላለጽ ፊሊጥ ኢየሱስ፣ ‹‹ቦንቡን አፈነዳ›› የምንለው ዐይነት ንግግር ነው።።

ምንም እንኳ ተላልፎ እንደሚሰጥ ኢየሱስ ገና ከመጀመሪያው ቢያውቅም፣ ደቀ መዛሙርቱ ስለዚያ ጉዳይ ሲሰሙ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር።። ከመጀመሪያ አንሥቶ ከእርሱ ጋር ከነበሩት አንዱ፣ በጣም ይቀርበው የነበረ ወዳጁ፣ አሳልፎ እንደሚሰጠው በተናገረ ጊዜ ክፍለ ውስጥ የነበረውን የመሸማቀቅ ስሜት መገመት ትችላላችሁ?

በአንጻሩ እነርሱ፣ ‹‹ከመካከላቸው ይህን የሚያደርግ ማን ሊሆን እንደሚችል እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር›› (ቁ.23)።። ከእነርሱ አንዱ እንዲህ ያለ ከባድ ወንጀል የሚያደርግ መሆኑ በጣም አስደንግጦአቸው ነበር።። ሆኖም፣ የመጠያየቃቸው ዓላማ ንጹሕ አልነበረም።። ውይይታቸው ከተቋጨበት ሁኔታ ይህን ማወቅ እንችላለን።። የተጠያየቁበት መንፈስ ራስ ወዳድና ትዕቢት የሞላበት ነበር።። እስቲ ቀጥሎ ያለውን ጥቅስ ተመልከቱ፣

> ደግሞም ከመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ በእነርሱ ዘንድ ክርክር ተነሣ።።
>
> - ሉቃስ 22÷24

ስዕሉን ማየት ሞክሩ፤ የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ለካህናት አለቆች ተላልፎ እንደሚሰጥ፣ በሮማውያን እንዲፌዝበት፣ እንዲገረፍና በኃላም እንዲገደል ተላልፎ አንደሚሰጥ ኢየሱስ ነግሮአቸው ነበር።። ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሚሆነውም ሰው ከእርሱ ጋር ማእድ ተቀምጧል።። ያ ሰው ማን ሊሆን እንደሚችል ደቀ መዛሙርቱ ተጠያይቀው ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ መጠያየቃቸው ያበቃው ከእነርሱ ማን ታላቅ እንደ ሆነ በመከራከር ነበር።። ነገሩ በርስት የሚጣሉ ልጆችን ያህል አስፈሪ ነበር።። እነዚያ ደቀ መዛሙርት ለኢየሱስ አላስቡም ነበር፤ እነርሱን ያሳሰባቸው የደረጃና የሥልጣን ጉዳይ ነበር።። ምንኛ አሳዛኝ ራስ ወዳድነት ነው!

እኔ ኢየሱስ የነበረበት ቦታ ብሆን ኖሮ፣ የነገርኳቸውን በደንብ ሰምተው እንደ ሆነ ወይም ለእኔ ያስቡ እንደ ሆነ እጠይቃቸው ነበር።። ከዚህ አጋጣሚ ጌታ ምን ያህል በፍቅርና በትዕግሥት እንደ

ተመላለሰ እናያለን። አብዛኞቻችን ኢየሱስ የነበረበት ሁኔታ ላይ ብንሆን ኖሮ፣ ‹‹ሁላችሁም ከፊቴ ጥፉ፤ እኔ ከባድ ችግር ውስጥ ነኝ፤ እናንተ ግን የምታስቡት ስለ ራሳችሁ ጉዳይ ነው!›› እል ነበር። ለመሰናከል ጥሩ አጋጣሚ ይሆነኝ ነበር።

በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያንን ክርክር ያስነሣው ማን እንደ ነበር መገመት እንችላለን፤ ስምዖን ጴጥሮስ ነው፤ በቡድኑ መካከል ተሰሚነት የነበረውና ሁሌም መጀመሪያ የሚናገር እርሱ ነበር።

ምናልባትም፣ በባሕር ላይ ለመራመድ እርሱ የመጀመሪያ ሰው መሆኑን ሌሎቹን ማሳመን ችሎ ይሆናል። ወይም ደግሞ ምናልባት፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛ ማንነት የመጀመሪያውን መገለጥ እንዴት እንዳገኘ አስታውሶአቸው ይሆናል። ኢየሱስ፣ ሙሴና ኤልያስ በነበሩበት የመለውጥ ተራራ እርሱ ስለ ነበረው ልምምድ አጫውቶአቸውም ይሆናል።

ከዐሥራ ሁለቱ መካከል የበለጠው እርሱ እንደ ነበር ጴጥሮስ በጣም እርግጠኛ ነበር። ይህ እርግጠኝነት ግን ፍቅርን ሳይሆን ትዕቢትን መሠረት ያደረገ ነበር።

ኢየሱስ ሁለንም አያቸውና፣ እርስ በርስ መፎካከራቸው ተራ ሰዎች እንጂ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ልጆች መሆናቸውን እንደማያመለክት ሲናገር፣ ‹‹የአሕዛብ ነገሥታት ሕዝቦቻቸውን በኃይል ይገዛሉ፤ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውም በጐ አድራጊዎች ተብለው ይጠራሉ። በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን፤ ይልቁን ከእናንተ ታላቅ የሆነ እንደ ታናሽ፣ ገዥ የሆነም እንደ አገልጋይ ይሁን። ለመሆኑ በማእድ ከተቀመጠና ቆሞ ከሚያስተናግድ ማን ይበልጣል? በማእድ የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ ያለሁት እንደ አንድ አገልጋይ ነው አለ›› (ሉቃስ 22÷25-27)።

የመበጠሩ ዓላማ

ምንም እንኳ ስምዖን ጴጥሮስ፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛ ማንነት የላቀ መገለጥ ቢቀበልም፣ በክርስቶስ ፀባይና ትሕትና እየተመላለሰ አልነበረም። ባለፈው ድል እና ትዕቢት መሠረት ላይ፣ የራሱን

ሕይወትና አገልግሎት እየገነባ ነበር። 1 ቆሮንቶስ 3÷10 ላይ ጳውሎስ በክርስቶስ መሠረትነት ላይ እንዴ መገንባት እንዳለብን መጠንቀቅ እንደሚገባ ይመክረናል።

ስምዖን ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት በሚያስፈልጉ ነገሮች ሳይሆን፣ በራሱ ፈቃድ ጥንካሬና በራስ የመተማመን መንፈስ ነበር እየገነባ የነበረው። ምንም እንኳ እርሱ ባያውቀውም፣ የባሕርይ ለውጥ የሚያደርግበት ጊዜ እየመጣ ነበር። የነበረው፣ ‹‹የኑሮ ትምክህት›› መለወጥ ነበረበት (1 ዮሐንስ 2÷16)

በክርስቶስ ወደ ተዘጋጀለት ፍጻሜ እንዲደርስ ከተፈለገ፣ ትዕቢት ለዚያ ብቃት አይሰጠውም። ቶሎ ካልተቀጨ ይህ ትዕቢት የኃላ ኃላ እርሱን ራሱን ያጠፋዋል። ከሕዝቅኤል 28÷11-19 በእግዚአብሔር የተቀባ ኪሩብ የነበረው ለሲፈር ባሕርይ ውስጥ የነበረውና ለውድቀት ያበቃው ደካማ ጐን ይኸው ትዕቢት እንደ ነበር እንመለከታለን።

አሁን ደግሞ ኢየሱስ ለስምዖን ጴጥሮስ የነገረውን ተመልከቱ -

> ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ ‹‹ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፣ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤

- ለቃስ 22÷31

ጠላት ወደ ውስጥ ገብቶ የጴጥሮስን እምነት እንዲያበጥር ትዕቢት በሩን ከፈተ። ማበጠር የሚለው ቃል ሲኒያዞ *(Siniazo)* ከሚለው ግሪክ ቃል የተተረጐመ ነው። ‹‹መንፋት፣ (እህልን) በወንፊት ማንቀርቀብ፣ የአንድ ሰው እምነት ወደ መጥፋት እስኪቃረብ ድረስ ውስጣዊ ቀውስ መፍጠር››[1] ማለት ነው። ኢየሱስ በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ብዙዎች ያለን ዐይነት ዝንባሌ ቢኖረው ኖሮ፣ ‹‹ወዳጆቼ፣ አጥብቀን እንጸልይ፤ ይህን የሰይጣን ጥቃት እንዋጋ፤ ሰይጣን ስምዖን ላይ እንዲህ ያለ ነገር ሲያደርስ ዝም ብለን ማየት የለብንም!›› ይል ነበር። ግን እርሱ እንዲህ ነበር ያለው፣

እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤

አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ።

- ሉቃስ 22÷32

ኢየሱስ የጸለየው ጴጥሮስ ምንም ችግር እንዳይገጥመው አልነበረም። እርሱ የጸለየው በዚያ ሂደት ውስጥ እምነቱ እንዳይጠፋ ነበር። ከዚያ ከባድ መከራ በኃላ ስምዖን ጴጥሮስ ፍጻሜውን ለማሟላትና ወንድሞቹንም የሚያበረታበት አዲስ ባሕርይ እንደሚያዳብር ኢየሱስ ያውቅ ነበር።

የስምዖን ጴጥሮስን እምነት ለማጥፋት ክፉኛ ለማናወጥ ሰይጣን ፈቃድ ጠይቆ ነበር። የጠላት ፍላጐት ያንን ታላቅ መገለጥ የተቀበለውን፣ ያንን ታላቅ ዕምቅ ዐቅም የነበረውን ሰው ማጥፋት ነበር። እግዚአብሔር ግን ለዚያ ነውጥ የተለየ ዓላማ ነበረው፤ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ እግዚአብሔር ሰይጣንን ቀድሞ ነበር። ጠላት ይህን እንዲያደርግ የፈቀደው፣ በስምዖን ጴጥሮስ ውስጥ ያለ ማንኛውም መናወጥ ያለበት ነገር እንዲናወጥ ነበር።

አንድን ነገር ማናወጥ አምስት ዓላማዎች አንዳለት አንድ ወቅት ላይ ሚስቴ ሊዛ ተምራ ነበር።

1. የበለጠ ወደ መሠረቱ እንዲመጣ ለማድረግ
2. የሞተውን ለማስወገድ
3. የበሰለውን ለመሰብሰብ
4. ለማንቃት፣ ለመቀስቀስ
5. ከእንግዲህ መለያየት እንዳይችል ለማዋሐድ ወይም ለመቀላቀል

ራስ ወዳድነት ወይም ትዕቢት ላይ የተመሠረተ ማንኛውም የአስተሳሰብ ሂደት፣ ወይም የልብ ዝንባሌ መጥራት፣ ተቆርጦ መጣል አለበት። ከዚህ ከባድ ነውጥ የተነሣ የስምዖን ጴጥሮስ በራስ መተማመን ሁሉ ይወገዳል፤ የሚቀረው ሁሉ በእግዚአብሔር ጽኑ መሠረት ላይ የተመሠረተው ብቻ ይሆናል። ያለበትን ትክክለኛ

ሁኔታ ለማወቅ ይነቃል፣ የሞተው ይወገዳል፤ የበሰለው ይሰበሰባል። እርሱንም ወደ እውነተኛ መሠረት ያመጣዋል። ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ብቻ ይተማመናል እንጂ፣ በራሱ መንገድና ሐሳብ አይንቀሳቀስም።

እርሱን እንደሚክድ በነገረው ጊዜ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ እኔ ከአንተ ጋር ወህኒ ለመውረድም፣ ለመሞትም ዝግጁ ነኝ›› በማለት ጴጥሮስ በድፍረት ኢየሱስን ተከራክሮ ነበር። ይህ ቃል በገዛ ራሱ ከነበረው እምነት እንጂ፣ ከመንፈስ የመጣ አልነበረም። ይህ ነውጥ የሚያስከትለውን ሁኔታ ገና ማየት አልቻለም ነበር።

ይሁዳና ስምየን

አንዳድ ሰዎች ጴጥሮስ ብዙ የሚናገርና ፈሪ ነበር ይላሉ። ሆኖም፣ በአትክልቱ ቦታ የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ጓዶች ኢየሱስን ለመያዝ በመጡ ጊዜ፣ ጴጥሮስ ሰይፍ በመሰንዘር የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ ቆርጦ ነበር (ዮሐንስ 18÷10)። መቼም ፈሪ ሰው፣ በቁጥር በጣም የሚበልጡ የጠላት ወታደሮች ባሉበት እንዲህ አያደርግም። እንደ እውነቱ ከሆነ ጴጥሮስ ብርቱ ሰው ነበር፤ ብርታቱ ግን በራሱ ሰብዕና ነበር፤ ምክንያቱም የመበጠሩ ሥራ ገና ስላልተጀመረ፣ በትሕትና በእግዚአብሔር በመደገፍ የተገኘ ባሕርይ አልነበረም።

ልክ ኢየሱስ አስቀድሞ እንደ ተናገረው ነበር የሆነው። ደፋሩ፣ ብርቱውና ለኢየሱስ ለመሞት ዝግጁ መሆኑን የተናገረው ጴጥሮስ፣ ብዙ ወታደሮች በነበሩበት አትክልት ቦታ ሰይፍ የመዘዘው ይኸው ስምየን ጴጥሮስ፣ በአንዲት ትንሽ የቤት ሠራተኛ ፊት ፈራ። በጣም ከመደንገጡ የተነሣ ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ የሚባል ሰው እንኳ እንደማያውቅ ካደ።

አንዳንዶች ሰዎችን የሚያሰናክሉ ትልልቅ ነገሮች ብቻ እንደ ሆኑ ያስባሉ። ሆኖም፣ ብዙ ጊዜ ሲያናውጡን የሚታዩት ትንንሽ ነገሮች ናቸው። ይህም በራስ የመተማመንን ከንቱነት ያመለክታል።

ከዚያም ጴጥሮስ ለሁለት ተጨማሪ ጊዜ ኢየሱስን ካደ። ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ፤ ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ አምርሮ

አለቀሰ። በራሱ የመተማመን ስሜቱ ሁሉ ተናወጠ፣ ከእንግዲህ እንደ ገና መነሣት የሚችልም አልመሰለውም። ምንም እንኳ እርሱ ባይገነዘበውም፣ የቀሩለት ነገሮች ሁሉ በመንፈስ የተገለጡለት ነገሮች ብቻ ነበሩ።

ስምዖን ጴጥሮስና ይሁዳ በብዙ መንገድ ተመሳሳይ ናቸው፤ በጣም መራራ በነበሩት የኢየሱስ መራራ ቀኖች፣ እርሱን መካዳቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። ያም ሆኖ ግን ሁለቱ ሰዎች መሠረታዊ ልዩነትም ነበራቸው።

ስምዖን ኢየሱስን ባወቀበት ሁኔታ፣ እርሱን ለማወቅ ይሁዳ ምንም ፍላጐት አልነበረውም። ይሁዳ ኢየሱስ ላይ የተመሠረተ አልነበረም። እርሱን ለመከተል ሁሉንም ትቶ መምጣቱ፣ ከኢየሱስ ጋር አብሮ ወደ ተለያየ ቦታ መጓዙ፣ ሌላው ቀርቶ ስደት በበረታበት ጊዜ ይሁዳ አብሮ መሆኑ ኢየሱስን የሚወድ አስመስሎት ነበር።

እርሱም እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት አጋንንት አስወጥቶአል፤ ሕመማንን ፈውሶአል፤ ወንጌልንም ሰብኮአል። (እንዲሰብኩ፣ እንዲፈውሱና አጋንንት እንዲያስወጡ ሁለት ሁለት እያደረገ ኢየሱስ የላከው ዐሥራ ሁለት ሐዋርያት እንጂ፣ ዐሥራ አንድ እንዳልነበረ አስታውሱ።) ያም ሆኖ፣ የከፈለው መሥዋዕት ኢየሱስን ከመውደዱ ወይም ስለ ማንነቱ ካገኘው መለኮታዊ መገለጥ የተነሣ አልነበረም።

ገና ከመጀመሪያውኑ ይሁዳ የራሱ አጀንዳ ነበረው። ለራሱ ጥቅም ከማሳደድ ዝንባሌው ንስሐ አልገባም። ‹‹እንዲህ ባደርግ እናንተስ ምን ትሰጡኛላችሁ?...›› የሚለው ዝንባሌ በቀጥታ ይሁዳን ይገልጠዋል (ማቴዎስ 26÷14)። ጥቅም ለማግኘት ሲል ዋሸቶአል፤ አታልሎአል (ማቴዎስ 26÷25)። ለኢየሱስ አገልግሎት ከሚሰበሰበው ገንዘብ ለግል ጥቅሙ ይወስድ ነበር (ዮሐንስ 12÷4-6)። ምንም እንኳ ከእርሱ ጋር ሦስት ዓመት ተኩል ቢያሳልፍም፣ በፍጹም ጌታን አላወቀውም ነበር።

ሁለቱም ሰዎች በፈጸሙት በደል ተጸጽተው ነበር። ሆኖም፣ ይሁዳ ጴጥሮስ የነበረው መሠረት አልነበረውም። ኢየሱስን ለማወቅ

ምንም ፍላጐት ስላልነበረው፣ ኢየሱስ በእውነተኛ ማንነቱ ለእርሱ አልተገለጠለትም ነበር። ይሁዳ እውነተኛ የኢየሱስ ማንነት ተገልጦለት ቢሆን ኖሮ፣ አሳልፎ አይሰጠውም ነበር። ሕይወቱ ላይ ኃይለኛ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ ሁሉም ነገሩ ተናወጠበት፣ ተበተነበት! የሆነውን ተመልከቱ፣

> አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውንም ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፤ ‹‹ንጹሕ ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ›› አለ። እነርሱም፣ ‹‹ታዲያ እኛ ምን አገባን፤ የራስህ ጉዳይ ነው!›› አሉት። ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ ወርውሮ ወጣ፤ ሄዶም ራሱን ሰቅሎ ሞተ።
>
> - ማቴዎስ 27÷3-5

ኃጢአት እንዳደረገ ዐውቆ ነበር፤ በኃጢአቱ ተጸጽቶም ነበር፤ ያም ሆኖ ግን ክርስቶስን አላወቀም ነበር። አሳልፎ የሰጠውን ሰው እውነተኛ ማንነትና ታላቅነት ጨርሶ አልተረዳም ነበር። እንዲሁ በደፈናው፣ ‹‹ንጹሕ ሰው አሳልፌ ሰጥቻለሁ›› ነበር ያለው። እንደ ስምዖን ጴጥሮስ እርሱም በትክክል ክርስቶስን ዐውቆ ቢሆን ኖሮ፣ የጌታን መልካምነት በማወቅ ወደ እርሱ ሄዶ ንስሐ ይገባ ነበር። ራስን ማጥፋት፣ ያለ እግዚአብሔር ጸጋ የመኖር ሌላ መገለጫ ነው። ለሦስት ዓመት ጌታን ከተከተለ በኃላ የሆነው ነውጥ እውነተኛ የይሁዳን ማንነት ገለጠ። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች በተለምዶ፣ ‹‹የኃጢአተኛ ጸሎት›› በመባል የሚታወቀውን ጸሎት ጸልየዋል፤ አዘውትረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል፤ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል፤ መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን አጥንተዋል። ምንም እንኳ እርሱን እንደሚያውቁ በአንደበታቸው ቢናገሩም፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያደረጉት የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ ትክክለኛ መገለጥ ሳይኖራቸው ነበር። አዳጋች ሁኔታ ሲመጣ በእግዚአብሔር ይሰናከላሉ፤ ከእርሱ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖራቸው አይፈልጉም።

እንዲህ ያሉ ሰዎች፣ ‹‹እግዚአብሔር ለእኔ ምንም አላደረገልኝም›› ሲሉ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ። ‹‹ምናልባት ይረዳኝ

እንደሁ በማለት ክርስትናን ሞከርኩ፤ ግን ሕይወት የበለጠ ከባድ ሆነብኝ›› ወይም፣ ‹‹እንዲህ እንዲያደርግልኝ ወደ እግዚአብሔር ጸለይኩ፣ ግን የለመንኩትን አላደረገልኝም!›› ይላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እርሱን ተከተሉ እንጂ፣ ሕይወታቸውን በእውነት ለእርሱ የሰጡ አልነበሩም፡፡ ከእርሱ እንደሚያገኙ ተስፋ ላደረጉት ነገር ነበር እርሱን ሲያገለግሉ የነበረው፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች በቀላሉ ይሰናከላሉ፡፡ እነርሱን በተመለከተ ኢየሱስ የሰጠው ገለጻ እንዲህ ይላል፤

> ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበሉታል፤ ነገር ግን ሥር የሌላቸው ስለሆኑ የሚቆዩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ፡፡

- ማርቆስ 4÷16-17

መሠረት ወይም ሥር ስለሌላቸው ወዲያው ይሰናከላሉ ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ለመሆኑ መመሥረት ያለብን ወይም ሥር መስደድ ያለብን ምን ላይ ነው? መልሱን ኤፌሶን 3÷16-18 ላይ እናገኛለን፤ መመሥረት ወይም ሥር መስደድ ያለብን ፍቅር ላይ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር መሠረታችን ነው፡፡

ኢየሱስ፣ ‹‹ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም›› ብሏል (ዮሐንስ 15÷13)፡፡ ለማንወደው ወይም ለማንተማመንበት ሰው ሕይወታችንን መስጠት አንችልም፡፡ በሚገባ ካላወቅነውና ካልተማመንበት በቀር ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር መስጠት አንችልም፡፡ የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕርይ ማወቅና መረዳት ይኖርብናል፡፡ እርሱ እኛን የሚጐዳ ምንም እንደማያደርግ ሙሉ መተማመን ሊኖረን ይገባል፡፡

ምንጊዜም ቢሆን እርሱ ለዘለቄታ ጥቅማችን የሚሆነውን ነው የሚያደርገው፡፡ ከእምነታችን ካልተናወጥን፣ አዳጋችና ተስፋ አስቆራጭ የመሰለን ሁሌም ለእኛ መልካም ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በእርሱ ዘንድ ክፋት ወይም ዐመፃ የለም፡፡ እኛን ማጥፋት የሚፈልግ ሰይጣን ነው፡፡

ብዙ ጊዜ በሕይወታችን የሚሆኑ ነገሮችን የምናየው፣ የቅርቡን ብቻ በሚያሳይ መነጽር ነው። ይህ ደግሞ የነገሩን ትክክለኛ ገጽታ ያዛባል። እግዚአብሔር ግን እያለፍን ያለንበትን ሁኔታ ከዘላለማዊ ጠቀሜታው አንጻር ነው የሚያየው። ሁኔታዎችን ውሱን ከሆነ ዕይታችን አንጻር ብቻ የምናይ ከሆነ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ።

በመጀመሪያ እኛን ለማጥራትና አላስፈላጊ ነገሮችን ከሕይወታችን ቆርጦ ለመጣል እግዚአብሔር በሚያደርገው ሥራ፣ በራሱ በእግዚአብሔር፣ ወይም ከአገልጋዮቹ በአንዱ በቀላሉ እንሰናከላለን። ሁለተኛ፣ በቀላሉ በጠላት እንታለላለን። ሰይጣን ለጊዜው ትክክል በሚመስል ነገር ይጠቀማል፤ የመጨረሻ ግቡ ግን በዚያ ትክክል በሚመስል ነገር ተጠቅሞ እኛን ማጥፋት ወይም መግደል ነው። በእግዚአብሔር ተማምነን ካረፍን፣ ምንም ነገር ከአባታችን ጥበቃ ውጪ አያደርገንም። ከሚገባ በላይ ለራሳችን የማሰብና የመጠንቀቅ አባዜ ተጠቂዎች አንሆንም።

በእግዚአብሔር ባሕርይ መደገፍ

ጠላት በእግዚአብሔር እንዳንተማመን ለማድረግ ከሚሞክርበት መንገድ አንዱ፣ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያለንን ምልከታ ማዛባት ነው። ‹‹በእርግጥ እግዚአብሔር በአትክልቱ ስፍራ ካለ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ ብሎአልን?›› በማለት ለሔዋን ጥያቄ ያቀረበ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነበር (ዘፍጥረት 3÷1)። የእርሱን ባሕርይ ለማጠልሸትና ለማዛበት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አጣመመ።

እግዚአብሔር የተናገረው፣ ‹‹በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ›› በማለት ነበር (ዘፍጥረት 2÷16-17)።

ያለ ጥርጥር እባቡ ለሔዋን፣ ‹‹እግዚአብሔር ከማንኛውም መልካም ነገር ከልክሏችኃል›› ማለቱ ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እግዚአብሔር፣ ‹‹ከ… በቀር ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ በነጻነት ትበላለህ›› ነበር ያለው። የአትክልት ቦታውን ሁሉ፣ ከአንዱ በቀር በአትክልት ቦታው ያለ ዛፎችን ፍሬ ሁሉ እንዲበላ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሰጥቶ ነበር።

‹‹በእርግጥ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ አያስብም። የሚያስብላችሁ ቢሆንማ ኖሮ እንዳትበሉ አይከለክላችሁም ነበር። እናንተ እንደምታስቡት እርሱ አይወዳችሁም። እንዲያውም እርሱ መልካም አምላክ አይደለም›› የሚል ትርጉም ያለው ሐሳብ በማቅረብ እባቡ ሴቲቱ ለእግዚአብሔር የነበራትን አመለካከት አጣመመ። በመጨረሻም ተታለለች፤ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በተመለከተ ሐሰቱን አመነች። ያኔ ኃጢአት የማድረግ ፍላጐት ተነሣሣ፤ ምክንያቱም ከዚያ በኃላ የእግዚአብሔር ቃል ለእርሷ ሕይወት ሳይሆን፣ ሕግ ሆኖባት ነበር። ‹‹የኃጢአት ኃይል ሕግ ነው›› (1 ቆሮንቶስ 15÷56)።

ዛሬም ቢሆን ጠላት በዚህ መንገድ ይሠራል። የአባታችን የእግዚአብሔርን ባሕርይ በተመለከተ ልጆቹ ጠማማ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ማንኛችንም አባቶችን፣ አስተማሪዎችን፣ የመሥሪያ ቤት አለቆችንና የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችን የመሳሰሉ ራስ ወዳድና ክፉ ሰዎች እናውቃለን። እነዚህ ሰዎች ሥልጣንን የሚወክለ በመሆናቸው፣ እግዚአብሔርንም እነርሱን ባየንበት ዐይን እናየዋለን፤ ምክንያቱም የመጨረሻው ባለ ሥልጣን እርሱ ነው።

ለምድራዊ አባቶቻችን ያለንን አመለካከት በማጣመም፣ ጠላት በዘዴ ለአባታችን ለእግዚአብሔር ያለንን አመለካከትም አዛብቶአል። ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት የአባቶች ልብ ወደ ልጆች እንደሚመለስ እግዚአብሔር ይናገራል (ሚልክያስ 4÷6)። የእርሱ ባሕርይ ወይም ማንነት የእርሱ በሆኑ መሪዎች ይታያል፤ ያ ደግሞ የፈውስ መተላለፊያ ይሆናል።

እግዚአብሔር እናንተን ለመጉዳት ምንም እንደማያደርግና በሕይወታችሁ የሚያደርገው ወይም የማያደርገው ማንኛውም ነገር ለእናንተ ዘላቂ ጥቅም እንደ ሆነ ካወቃችሁ፣ በነጻነት ራሳችሁን ትሰጡታላችሁ። ለጌታ ሞትን እንኳ ለመቀበል ዝግጁ ትሆናላችሁ።

ሙለ በሙለ ራሳችሁን ለኢየሱስ ከሰጣችሁና በእርሱ ጥበቃ ከተማመናችሁ በፍጹም አትሰናከሉም፤ ምክንያቱም ከእንግዲህ እናንተ የራሳችሁ አይደላችሁም። የሚጐዱትና ተስፋ የሚቆርጡት፣ በማንነቱ በመታመን ሳይሆን አንዳች ነገር ጠብቀው ወይም ፈልገው ወደ እርሱ የመጡት ናቸው።

የዚያ ዐይነት ዝንባሌ ካለን በቀላሉ ተስፋ እንቆርጣለን። ራስን ማዕከል ያደረገ ሕይወት በቅርብ ያለውን ብቻ እንድናይ ያደርገናል። አሁን ያለንበትን ሁኔታ በእምነት ዐይን አናይም። ሕይወታችን በእውነት በክርስቶስ የተዋጠ ከሆነ ባሕርዩን እናውቃለን፤ የደስታው ተካፋዮችም እንሆናለን። ከእንግዲህ ጨርሶ አንናወጥም ወይም ተስፋ አንቆርጥም።

ነገሮችን የምንመዝነው አካባቢውን ወይም ሁኔታውን በማየት ከሆነ፣ በቀላሉ እንሰናከላለን። በመንፈስ ዐይን ማየት ግን እንዲህ አይደለም። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር መልስ የሚሰጠኝ እኔ በጣም አስፈላጊ ነው ባልኩት ጊዜ፣ ሁኔታና መጠን አይደለም። ሆኖም፣ ወደ ኃላ ዘወር ብዬ እያንዳንዱን ነገር ስመለከት የእርሱን ጥበብ አያለሁ።

ብዙ ጊዜ ልጆቻችን እነርሱን የምናስተምርበትን ዘዴ፣ ወይም ከዚያ ጀርባ ያለውን ዓላማ ምክንያት አይረዱልንም። ከዚያ እንዲጠቀሙ በማሰብ ለታላላቆቹ ልጆች ገለጻ መስጠት እንሞክራለን። አልፎ አልፎ ግን እነርሱም ቢሆኑ፣ ካለመብሰላቸው የተነሣ ላይረዱ ወይም ላይስማሙ ይችላሉ፤ የኃላ ኃላ ግን መረዳታቸው አይቀርም። አንዳንዴ ዓላማው ታዛዥነታቸውን፣ ፍቅራቸውንና ብስለታቸውን ለመፈተን ሊሆን ይችላል። በሰማይ ያለው አባታችንም እንደዚህ ያደርጋል። እንዲህ ባለ ሁኔታዎች ውስጥ እምነት፣ ‹‹ምንም እንኳ መረዳት ባልችልም፣ እተማመንብሃለሁ›› ይላል።

ዕብራውያን 11÷35-39 ላይ እግዚአብሔር የሰጣቸው የተስፋ ቃል ሲፈጸም ባያዩ እንኳ፣ ሳይናወጡ ጸንተው ስለ ቆሙ ሰዎች ሲናገር፣ ‹‹ሌሎቹ ደግሞ የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚያም

ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም። አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣለ፤ በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤ እየተጐሳቆለ፣ እየተሰደዱና እተንገላቱ የበግና የፍየል ቆዳ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሐውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተንከራተቱ። እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም፣ ከእነርሱም ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም።›› የሚለውን ጽሑፍ እናያለን።

የሚከፈለው ዋጋ ምንም ይሁን ምን፣ እነርሱ የፈለጉት ራሱ እግዚአብሔርን ነበር። የተገባላቸው ተስፋ ቃል ሲፈጸም ባያዩ እንኳ፣ አምነውበታል። እንዲህ ያለ ሰዎች አይሰናከሉም!

በእንዲህ ያለ ሁኔታ እግዚአብሔርን ከወደድንና ከተማመንንበት፣ በእርግጥ በእርሱ ሥር ሰደናል፤ በእርሱ ተመሥተናል። የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን፣ ማንኛውም ማዕበል ሊያናውጠን አይችልም። ይህ ደግሞ በእኛ ቆራጥ ውሳኔ ወይም ሰብዕና ጥንካሬ የሚመጣ አይደለም። በራስ መተማመናቸውን ሁሉ እርግፍ አድርገው ጥለው፣ እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ላደረጉ ሁሉ የሚሰጥ ጸጋ ነው። ይሁን እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ ለመሰጠት፣ በመጀመሪያ ሕይወታችሁን የያዘው ማን መሆኑን ማወቅ ይገባችኃል።

ለትሑታን ጸጋ ይሰጣቸዋል

ከእንግዲህ ወዲህ ስምያን በራሱ ብርታት መኩራራት አይችልም። በተፈጥሮ የነበረውን በራስ መተማመን አጥቷል። በገዛ ራሱ ጥንካሬ የመተማመንን ከንቱነት በሚገባ ማየት ችሎአል። ይህ ደግሞ ዝቅ እንዲል፣ ትሑት እንዲሆን አስችሎታል። ከእንግዲህ እርሱ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል ትክክለኛው ሰው ይሆናል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል ትሕትና ቅድመ ግዴታ ነው። ‹‹ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ትዕቢተኞን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል›› በማለት ሲጽፍ ይህ ጉዳይ በጴጥሮስ ልቦና ውስጥ ምን ያህል ከብዶ እንደ ነበር መመልከት ይቻላል (1 ጴጥሮስ 5÷5)።

ተስፋ ወደ መቁረጥ እስኪደርስ ድረስ ጴጥሮስ ክፉኛ ተናውጦ ነበር። ይህንን በመቃብሩ ቦታ የጌታ መልአክ፣ ‹‹ነገር ግን ሂዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ፣ ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤ እንደ ነገራችሁ እዚያ ታገኙታላችሁ ብላችሁ ንገሯቸው›› በማለት ለሴቶቹ ከተናገረው መረዳት ይቻላል (ማርቆስ 16÷7)። መልአኩ እርሱን ነጥሎ ነበር የተናገረው። ጴጥሮስ ክፉኛ ተናውጦ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ እግዚአብሔር መሠረት አኑሮለታል። ነውጥ የበለጠ ያጠነክረዋል እንጂ፣ ሊያፈርሰው አይችልም።

ኢየሱስ ጴጥሮስን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ገና መልሶ አቆመ። በነውጥ ውስጥ ያለፈ በመሆኑ ከእንግዲህ በቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና ከሆኑት ሰዎች አንዱ ሊሆን ነው።ለመሰቀለ ዋና ተጠያቂ በሆኑ ሰዎች ፊት፣ የክርስቶስን ትንሣኤ በድፍረት ተናገረ። በአንዲት ትንሽ የቤት ሠራተኛ ፊት ፈርቶ የተንቀጠቀጠው ሰውዬ አሁን በአይሁድ ሸንጎ ፊት ሳይናወጥ መቆም ችሎአል። በታላቅ ሥልጣንና ድፍረት ተሞልቶ እውነቱን ተናገረ።

ብዙ ዓመት በታማኝነት ካገለገለ በኃላ፣ ጴጥሮስ ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ እንደ ተገደለ ታሪክ ይናገራል።[2] ጌታው በሞተበት መንገድ ለመሞት ብቁ አለመሆኑን አጠንክሮ በመናገሩ ነበር ተዘቅዝቆ እንዲሰቀል የተፈረደበት። ከእንግዲህ እርሱ ፈሪና ድንጉጥ አይደለም። እርሱ ጽኑ ዐለት ላይ የተመሠረተ ድንጋይ ነው።

በዚህ ሕይወት የሚገጥሙ ፈተናዎች፣ የተሰናከላችሁት በእግዚአብሔር ወይም በሌሎች መሆን አለመሆኑን በልባችሁ ያለውን ይገልጣሉ። ፈተናዎች በእግዚአብሔርና በሌሎች ላይ መራራ ያደርጓችኃል ወይም ደግሞ ያጠነክሯችኃል። ፈተናውን ካለፋችሁ፣ ሥራችሁ የበለጠ እየጠለቀ ይሄዳል፤ ለወደ ፊት ሕይወታችሁም የተረጋጋችሁና ጽኑዎች ያደርጋችኋል። ፈተናውን ካላለፋችሁ ትሰናከላላችሁ፤ ይህም ወደ ርኩሰትና መራራነት ይመራችኃል።

ጌታ ሆይ፣ በሚገባ አገልግዬሃለሁ
ታዲያ፣ ለምን...?

ፓስተር በነበርኩ ጊዜ በጓደኞቹና በመሪዎቹ በጣም የተከበረ አንድ ባለ ብሩኅ አእምሮ የዐሥራ አራት ዓመት ልጅ ወጣቶች ቡድን ውስጥ ነበር። ጥሩ ተማሪና የተዋጣለት አትሌትም ነበር። ለእግዚአብሔር ነገር ከፍ ያለ ቅንዓት ስለ ነበረው በታማኝነት ያገለግል ነበር፤ በእያንዳንዱም ፕሮጀክት በፈቃደኝነት ይሳተፍ ነበር። ከእኛ ጋር ለሚሲዮን ሥራ ወጥቶ በነበረ ጊዜ ለሚያገኘው ሰው ሁሉ ይመሰክር ነበር።

በሕይወቱ አንድ ወቅት ላይ በቀን አራት ሰዓት በጸሎት የሚያሳልፍበት ጊዜ ነበር። ከጌታ ብዙ ነገሮች ተቀብሎ ነበር፤ ያንንም ለሌሎች አካፍሎ ነበር። ለሰዎች የሚያካፍለው ሰሚዎቹን በጣም የሚባርክ ነበር። ለአገልግሎት የመጣለትን ጥሪ ተቀብሎ ስለ ነበር፤ ሃያ ዓመት ከመሙላቱ በፊት ፓስተር ለመሆን ፍላጐት ነበረው። ምንም የማይነቀንቀው ዐለት ይመስል ነበር።

ያንን ወጣት በጣም ነበር የምወደው፤ በሕይወቱ የእግዚአብሔር ጥሪ መኖሩን በመረዳቴ እርሱ ላይ ሰፊ ጊዜ አሳልፍ ነበር። ግን አንድ ነገር በጣም ያሳስበኝ ነበር – ከሚገባ በላይ በራሱ ይተማመን ነበር። ያን በተመለከተ ላናግረው እፈልግ ነበር፤ ያን ለማድረግ ግን ነጻነት አልተሰማኝም። አንድ ደረጃ ላይ ለውጥ መምጣቱ እንደማይቀር ይገባኝ ነበር። ያ ወጣት በአንዳንድ አዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ ቢያልፍም፣ የነበረው ጥንካሬ እንደ ተጠበቀ ነበር። አንዳንድ አዳጋች ሁኔታዎችን ተቋቁሞ ሲያልፍ በማየቴ ቀደም ሲል ስለ እርሱ የነበረኝን ግምት እንድጠይቅ አድርጐኝ ነበር።

ጥቂት ዓመታት አለፉ። እኔም ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ ለማገልገል ሙሉ ጊዜ ሰጠሁ። ያም ሆኖ ግን በየጊዜው አገኘው ነበር። በአንድ ዐይነት ስብራት ውስጥ እንደሚያልፍ አውቅ ነበር። ምን ሊሆን እንደሚችል ባላውቅም፣ የታቀደለት ፍጻሜ ላይ ለመድረስ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ አውቅ ነበር። ይህ ስምዖን ጴጥሮስ ካለፈበት መበጠር ሂደት ጋር ተመሳሳይ ነበር።

ያ ወጣት ዐሥራ ስምንት ዓመት በሞላው ጊዜ አባቱ በካንሰር ታመመ። አባቱ እንደሚፈወስ በማመን እርሱና እናቱ መጸም መጸለይ ጀመሩ፤ ሌሎችም እንዲሁ በመጸም በመጸለይ ከጐናቸው ቆመው ነበር። በጥቂት ወሮች ውስጥ አባቱ ለኢየሱስ ጌትነትና አዳኝነት ሕይወቱን ሰጠ።

የጤንነቱ ሁኔታ ግን እየባሰ መጣ። ሚስቴ ስልክ ደውላ ያንን ወጣት እንዳገኘው አጥብቃ ስትነግረኝ፣ በአላባማ ሌላ ከተማ እያገለገልኩ ነበር። ደውዬ አገኘሁት አጠገቡ ሆኖ የሚያጽናናው ሰው እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነበር።

እዚያ የነበረኝ አገልግሎት ካበቃ በኃላ ሌሊቱን በሙሉ ስነዳ አድሬ፣ ከጠዋቱ አራት ሰዓት እቤት ደረስኩ። የአባቱ ሁኔታ ከምንጊዜውም ይበልጥ እየባሰ በመምጣቱ በሕይወት የሚቆየው ለጥቂት ቀኖች ብቻ መሆኑን ዶክተሮች ተናገሩ። ሌላው ቀርቶ፣ ሰው እንኳ የማይለይበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

አባቱ ተፈውሶ ከአልጋ ቁራኛነት እንደሚነሣ ወጣቱ በጣም ልበ ሙሉ ነበር። ቤተ ሰቡን ካገለገልኩ በኃላ ብዙ ሰዓት ቆይቼ ከዚያ ሄድኩ። በማግሥቱ ተደውሎ ሁኔታው የበለጠ እየከፋ መምጣቱ ተነገረን።

እኔና ሊዛ ወዲያውኑ ጸለይን። ያንን ሰው ወደ ራሱ ለመውሰድ አልጋው አጠገብ ዝግጁ ሆኖ ኢየሱስ እየጠበቀ መሆኑን እግዚአብሔር ለሚስቴ ራእይ ሰጣት። ከሰላሣ ደቂቃ በኃላ ወጣቱ ደውሎ አባቱ መሞቱን ነገረን። ያኔም ቢሆን፣ እንደ ቀድሞ ጠንካራ ይመስል ነበር። ግን ያ፣ ጅማሬ ነበር።

አባቱ መሞቱን ለመናገር በጣም ለሚቀርቡት ወዳጆቹ በዚያው ሌሊት ስልክ ደወለ። ቴሌፎኑን ሲያነሡ አንዳንዶቹ እያለቀሱ ነበር። ወሬውን እንዴት ቀደም ሲል እንደ ሰሙ ገረመው። ሆኖም ለእርሱ እንደ መሰለው የእርሱን አባት መሞት አልሰሙም ነበር። እያለቀሱ የነበረው በአደጋ ለሞተው በጣም የቅርብ ከሆኑ ወዳጆቹ ለአንዱ ነበር። ያ ወጣት በአንድ ቀን አባቱንና በጣም የሚወደው ጓደኛውን አጣ። ነውጡ ጀመረ። ግራ

ተጋባ፣ ተስፋ ቆረጠ፤ ፍዝዝ አለ። የእግዚአብሔር አብሮነት ከእርሱ እጅግ የራቀ መስሎ ተሰማው።

ከአንድ ወር በኃላ እየነዳ ወደ ቤት እየሄደ እያለ፣ ያ ወጣት አደጋ ደርሶ ወደ ነበረበት ቦታ ይደርሳል። የድንገተኛ ጊዜ አደጋ ሕክምና ሥልጠና ስለ ነበረው ርዳታ ለማድረግ ይቆማል። ተጋጭተው በነበሩት ሁለት መኪኖች ውስጥ የቅርብ ጓደኞቹ ነበሩ። ርዳታ እያደረገ እያለ ሁለቱ እርሱ ክንድ ላይ ሞቱ።

ወጣቱ ወዳጄ፣ የመጨረሻ ነጥብ ላይ ደረሰ። ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ ሦስት ሰዓት ሙሉ በጸሎት አሳለፈ። ‹‹እግዚአብሔር ሆይ ወዴት ነህ? የምታጽናና መሆንህን ተናግረሃል፤ አሁን ግን እኔ መጽናናት አልቻልኩም!›› አለ።

እግዚአብሔር ጀርባውን ያዞረበት መሰለ። የገዛ ራሱ ብርቱነት ጥሎት ሲሄድ፣ በእርግጥም ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር ላይ ተቆጣ። ለምን እንዲህ እንዲሆን ይፈቅዳል? የተናደደው ማንም ላይ ሳይሆን፣ ራሱ እግዚአብሔር ላይ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ተሰናከለ። ረዳት በሚያስፈልገው ሰዓት እግዚአብሔር የተወው መሰለው።

‹‹ጌታ ሆይ፣ በሚገባ አገልግየሃለሁ፤ አንተን ለመከተል ብዙ ነገር ትቻለሁ፤ አሁን ግን አንተ ራስህ እኔን ተውከኝ!›› በማለት ጸለየ። እርሱን ለማገልገል ለተዋቸው ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ባለ ዕዳ ቆጠረ።

ብዙ ሰዎች ከዚህ ያነሰ፣ አንዳንዴም ከዚህ የከፋ ጉዳትና ተስፋ መቁረጥ ደርሶባቸዋል። ብዙዎችም በራሱ በጌታ ላይ ተሰናክለዋል። ለእርሱ አደረግን የሚሉትን ሁሉ፣ ግምት ውስጥ የማስገባት ግዴታ ያለበት ይመስላቸዋል።

እነዚህ ሰዎች ሲያገለግሉ የነበረው በተሳሳተ ምክንያት ነበር። እግዚአብሔርን ማገልገል ያለብን ስለ ማንነቱና አስቀድሞ ስላደረገልን እንጂ፣ ግና ወደ ፊት ያደርግልናል ብለን ስለምንጠብቀው ነገር መሆን የለበትም። በእርሱ የተሰናከሉ ወገኖች እነርሱ ነጻ እንዲሆኑ ምን ያህል ከባድ ዕዳ እንደ ተከፈለላቸው ግና

በሚገባ አልተረዱም። ከእንዴት ዐይነት ሞትና ጥፋት እንደ ታደጋቸው ዘንግተዋል። እነዚህ ሰዎች የሚያዩት በጊዜያዊው እንጂ በዘላለማዊው ዐይን አይደለም።

ያ ወጣት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አቆመ፤ ከአጉል ጓደኞች ጋር ቡና ቤቶችና ፓርቲዎች ማዘውተር ጀመረ። በጣም ተስፋ ቆርጦና ተናድዶ ስለ ነበር፣ ከእግዚአብሔር ነገር ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖረው አልፈለገም።

ሆኖም፣ በዚህ ዐይነት አኗኗር ከሁለት ሳምንት በላይ መቀጠል አልቻለም፤ ልቡ በጣም ተወቅሶ ነበር። በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ሆኖ፣ ለስድስት ወር ያህል ወደ ጌታ መቅረብ አልፈለገም ነበር። ያኔም ቢሆን ሰማይ የነሐስ ያህል ሆኖበት ነበር፤ የእግዚአብሔር መገኘት በጣም ርቆት ነበር።

ከአንድ ዓመት በላይ አለፈ። በተለያዩ አጋጣሚዎች እግዚአብሔር አሁንም በሕይወቱ ሥራ ላይ መሆኑን ማየት ቻለ። እርሱም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ጀመረ፤ በዚህ ጊዜ ሁኔታው ከበፊቱ በጣም የተለየ ነበር። አሁን ትሑት ሆኖአል። የፈተናው ጊዜ ካለፈ በኃላ፣ በፍጹም እርሱን እንዳልጣለው እግዚአብሔር አሳየው። መንፈሳዊ ሕይወቱ እየታደሰ ሲመጣ በራሱ ብርታት ሳይሆን ትምክህቱን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ማድረግን ተማረ።

እኔም በየጊዜው አገኘው ነበር። ከአንድ ዓመት ተኩል በኃላ ይኖራለ ብሎ ያላሰባቸው ነገሮች በሕይወቱ መኖራቸውን ማየት እንደ ቻለ አጫወተኝ። ‹‹መልካም ምግባር የጐደለኝና ከሰዎችም ጋር ጥሩ ግንኙነት ያልነበረኝ ነበርኩ። በሰዎች ዓይን ብርቱ ሆኜ መታየት እንዳለብኝ እየነገረ ነበር አባቴ ያሳደገኝ፤ ይህ አስተዳደጌ እግዚአብሔር የሚፈልገው ዐይነት አልነበረም። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ስላልተወኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

‹‹ልቤን በጣም ያሳዘነው በየቡና ቤቱ መዞሬና መጠጣቴ አልነበረም፤ በጣም ያሳዘነኝ ለመንፈስ ቅዱስ ጀርባዬን ማዞሬ ነበር። አሁን በጣም ነው የምወደው፤ ከእርሱ ጋር የነበረኝ ጎብረት የአሁኑን ያህል ጣፋጭ ሆኖ አያውቅም።››

በሕይወቱ ብዙ ነውጥ ደረሰ። በዚያ ውስጥ በራሱ የመተማመን ዝንባሌው ጥሎት ጠፋ። አሁን ያ ወጣት፣ ስምዖን ጴጥሮስ የነበረው ዐይነት መሠረት አለው፤ ያ በፍጹም አይወሰድበትም። ሕይወትና አገልግሎቱን ትዕቢት ላይ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መሥርቶአል። መሰናክል በሕይወታችን ያለውን ድካምና የምንሰበርበትን ነጥብ ግልጽ ያደርጋል። ብዙ ጊዜ ብርቱዎች እንደ ሆንን ያሰብነው ደካማነታችን የተሸፈነበት ቦታ ነው። ከባድ ዐውሎ ነፋስ መጥቶ እስኪገልጠው ድረስ እንደ ተደበቀ ይቀራል። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹እኛ በእውነት የተገረዝን በእግዚአብሔር መንፈስ የምናመልክ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የምንመካ፣ በሥጋም የማንታመን ነንና›› በማለት ይጽፋል (ፊልጵስዩስ 3÷3)።

በራሳችን ችሎታ ዘላላማዊ ዋጋ ያለው ነገር ማድረግ አንችልም። እንዲህ ማለት ቀላል ነው፤ ይህ እውነት በጥልቅ እኛነታችን ውስጥ ሥር መሰደዱ ግን የተለየ ነገር ነው።

ሰዎች እንዳይሰናከሉ

በማለት ኢየሱስ እውነትን አልሸፋፈነም።

የሰይጣን ሽንገላ የተሰኘው መጽሐፍህ ዐይኖቼን ገልጦልኛል። እኔና ባሌ አገልግሎት ውስጥ ነው ያለነው፤ ከጌታ ጋር ያለኝ ግንኙነት በሙሉ ትክክል እንደ ሆነ አስብ ነበር። ለዐሥራ አምስት ዓመት ያህል አክስቴ ላይ ይዤው የነበረ ቂም ማንኛውንም ዋጋ ሊያስከፍለኝ ነበር። እንደ ክርስቲያኖች ይቅር ማለት እንዳለብን ብዙ ጊዜ እንማራለን፤ ይሁን እንጂ፣ መልእክትህ ያለፈ ዘመን ጉዳቴን ፊት ለፊት እንድጋፈጥ እስካደረገኝ ጊዜ ድረስ ይህን ያህል ወደ ልቤ አልገባም ነበር።

- አር ኤም ቴኔሲ

9

የመሰናከያ ዐለት

‹‹እነሆ የተመረጠና ክቡር የማእዘን ድንጋይ፣ በጽዮን አኖራለሁ፤ በእርሱ የሚያምን ከቶ አያፍርም፡፡›› እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ ድንጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን፣ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፡፡ ደግሞም፣ ‹‹ሰዎችን የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ፡፡›› የሚሰናከሉት ቃሉን ባለ መታዘዛቸው ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና፡፡

- 1 ጴጥሮስ 2÷6-8

በዚህ ዘመን ማመን የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙን እያጣ መጥቷል፡፡ ብዙዎች የሚገምቱት አንድን እውነት ወይም ሐቅ መቀበል መሆኑን ነው፡፡ ለብዙዎች ከመታዘዝ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ከላይ ባለው ምንባብ ግን ማመንና አለመታዘዝ ተቃራኒ መሆናቸው ነበር የቀረበው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው እንጂ አይጠፋም›› ይላል (ዮሐንስ 3÷16)፡፡ ማመን ለሚለው ቃል ካለን የተሳሳተ አስተሳሰብ የተነሣ፣ ማድረግ ያለባቸው ኢየሱስ የሚባል ሰው በዚህ ምድር እንደ ነበርና በታላም መስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደ ሞተ ማመን ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ፤ ይህን ካደረጉም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንደሚስተካከል ያስባሉ፡፡ የሚያስፈልገው ይኸው ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ አጋንንትም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ይስተካከል ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም

ይንቀጠቀጣለ›› ይላል (ያዕቆብ 2÷19)። ያም ሆኖ ግን ድነት ለእነርሱ አልተሰጠም።

በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ማመን የተሰኘው ቃል፣ የአንድን ነገር መኖር ከመቀበል ወይም አንድ ነገር እውነት መሆኑን በአእምሮ ከመስማማት የበለጠ ትርጉም አለው። እንግዲህ ከላይ ያለውን ጥቅስ በዐውዱ መሠረት ስንመለከተው፣ የማመን ዋናው ጉዳይ መታዘዝ መሆኑን ነው የምንረዳው። ስለዚህም፣ ‹‹እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት እርሱ ክቡር ነው፤ ለማይታዘዙት ግን፣ ‹‹ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ።›› ደግሞም፣ ‹‹ሰዎችን የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ›› በሚል መልኩ ማንበብ እንችላለን።

ራሳችሁን የሰጣችሁትን አምላክ ባሕርይና ፍቅር በሚገባ ካወቃችሁ ለእርሱ መታዘዝ አይከብዳችሁም። ከጌታ ጋር የሚኖረን መቀራረብ መሠረቱ ፍቅር ነው፤ እዚህ ላይ ፍቅር ስንል የእርሱን መርሐዎች ወይም ትምህርቶች መወደድ ማለት ሳይሆን፣ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ ማለት ነው። ፍቅር በጽናት ቦታውን ካልያዘ፣ ለመሰናከልና ተፍገምግሞ ለመውደቅ የተጋለጥን እንሆናለን።

እግዚአብሔር ‹‹ግንበኞች›› በማለት የጠራቸው እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የማእዘን ድንጋይ የሆነውን ንቀውት ነበር። የብሉይ ኪዳን ትምህርታቸውን ወድደዋል። የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቂያና ሌሎችን መቆጣጠሪያ አድርገው ሊጠቀሙበት ስለሚችሉም፣ በቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎማቸው ረክተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ አጥብቀው የያዙትንና በጣም የሚወዱትን ወግኝነት ሁሉ ኢየሱስ ሞግቶባቸው ነበር። ‹‹በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤ እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው›› በማለትም ዕቅጩን ነግሮአቸው ነበር (ዮሐንስ 5÷39)።

ግና ከጅማሬው አንሥቶ እግዚአብሔር ይፈልግ የነበረው፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት የሚያደርጉ ወንዶችና ሴቶችን እንደ ነበር መቀበል ጨርሶ ሊዋጥላቸው አልቻለም። ይልቁንም እነርሱ ገዥችና

የበላይ መሆንን ነበር የፈለጉት። ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖር ይገባው ከነበረ ቀረቤታ የበለጠ በእነርሱ ዐይን ሕጉ ከፍ ያለውን ቦታ ይዞ ነበር። በነጻ የተሰጣቸውን ንቀዋል። እነርሱ የሚፈልጉት ዋጋ የከፈለበትንና በልፋታቸው ማግኘት የሚችሉትን ነበር። ስለሆነም የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ የሆነው፣ የሕይወታቸውና የድነታቸው ተስፋ የሆነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ‹‹የሚያሰናክልና የሚጥል ዐለት ሆነባቸው።››

በቤተ መቅደስ ውስጥ ስምዖን ሕፃኑ ኢየሱስን በክንዶቹ ይዞ በነበረ ጊዜ፣ ‹‹ይህ ሕፃን በእስራኤል ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ምክንያት ይሆናል›› የሚል ትንቢት ተናግሮ ነበር (ሉቃስ 2÷34)። መውደቅና መነሣት የሚሉትን ቃሎች ልብ አድርጉ። ለዓለም ሰላም እንዲያመጣ የመጣው ኢየሱስ፣ የእርሱ ለነበሩ ወገኖች መለያየትን የሚያመጣ ሰይፍ ሆነ (ማቴዎስ 10÷34) በግንበኞቹ (በዚያ ዘመን የሃይማኖት መሪዎች የነበሩት) ሲጠቁ ለነበሩትም ሕይወት ሆነላቸው።

ኢየሱስና መሰናከያዎች

እሑድ ትምህርት ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ የሚቀርብልን ምስል፣ እረኛው አንድ ጠፍቶ የነበረ በግ በትከሻው ተሸክሞ ወደ በረቱ ሲመልሰው የሚያመለክት ነው። ወይም ደግሞ ሕፃናትን ለመባረክ እጆቹን በእነርሱ ዙሪያ በማድረግ ፈገግ ብሎ፣ ‹‹እወዳችኃለሁ›› የሚል ሰው ምስል ነው። እነዚህ ሁሉ እውነት ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ ሙሉውን ስዕል አይሰጡንም።

ይኸው ኢየሱስ ራሱ፣ ‹‹እናንተ እባቦች፣ የእፉኝት ልጆች! ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትችላላችሁ?›› በማለት ራሳቸውን ጻድቅ የሚያደርጉ ፈሪሳውያንን አውግዞ ነበር (ማቴዎስ 23÷33)። ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበሩ ገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛ ገልብጦ ነበር፤ ከዚያም ቦታ አባርሮአቸው ነበር (ዮሐንስ 2÷13-22)። እርሱን ከመከተሉ በፊት ሄዶ አባቱን ቀብሮ እንዲመጣ ለጠየቀው ሰው፣ ‹‹ሙታን ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው፤ አንተ ግን ሂደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ›› ብሎት ነበር (ሉቃስ 9÷59-60)። ይህን የመሳሰሉ ብዙ ጥቅሶች ማቅረብ ይቻላል።

ቀረብ ብለን የኢየሱስን አገልግሎት ብንመለከት፣ በአገልግሎቱ አንዳንድ ሰዎች ተሰናክለው እንደ ነበር እንረዳለን። እስቲ ጥቂት ምሳሌዎች እንመልከት።

ኢየሱስ ፈሪሳውያንን አሰናከለ።

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ እነዚህ መሪዎችን ተጋፍጦ ነበር፣ አሰናክሎአቸውም ነበር። በእርሱ በመሰናከላቸውም መስቀል ላይ እንዲገደል ፈለጉ። በጣም ነበር የጠሉት። ኢየሱስ ግን እነርሱን በጣም ስለ ወደደ፣ ‹‹እናንተ ግብዞች! ኢሳይያስ ስለ እናንተ እንዲህ ብሎ በትንቢት የተናገረው ትክክል ነው፤ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ በከንቱ ያመልከኛል›› በማለት እውነቱን ነገራቸው (ማቴዎስ 15÷7-9)። ይህ አባባሉ አሰናከላቸው።

ከዚያ በኃላ ወዲያውኑ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያቀረቡትን ጥያቄ ተመልከቱ

> ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፣ ፈሪሳውያን ያልኸውን ሰምተው እንደ ተሰናከሉ (እንደ ተቆጡ) አወቅህ? አሉት።
>
> - ማቴዎስ 15÷12

የሰጣቸውን መልስ ልብ አድርጋችሁ አንብቡ።

> የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል። ተዉአቸው፤ እነርሱ ዕውሮችን የሚመሩ ዕውር መሪዎች ናቸው፤ ዕውር ዕውርን ቢመራ ሁለቱም ተያይዘው ገደል ይገባሉ።
>
> - ማቴዎስ 15÷13-14

መሰናከል በእውነት በእግዚአብሔር ያልተተከሉ ሰዎችን እንደሚያስወግድ ኢየሱስ ያመለክታል። አንዳንድ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አባሎች፣ የአገልግሎት ቡድን ተባባሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ያ ማለት ግን የግድ ከእግዚአብሔር ወገን ናቸው ማለት አይደለም። እውነት ሲሰበክ ሊኖር የሚችለው መሰናክል፣ እውነተኛ ዓላማቸውን ይገልጣል፤ እነርሱም ይነቀላሉ።

በአገልግሎት በተዘዋወርኩባቸው ቤተ ክርስቲያኖች፣ ከቤተ ክርስቲያን ሥራ ወይም ከማኅበረ ምዕመናኑ ተለይተው በሄዱ ሰዎች፣ ፓስተሮች እያዘኑ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች ደስ ያልተሰኙት እውነት በመሰበኩና፣ የአኗኗር መንገዳቸውን ፊት ለፊት የሚጋፈጥ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከዚያ በኋላ፣ ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ገጽታ መንቀፍና መተቸት ይጀምራሉ፤ በመጨረሻም ትተው ይሄዳሉ።

አንዳንድ ፓስተሮች ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው የሚመጣ ሁሉ ተመልሶ እንዳይሄድ አጥብቀው ስለሚፈልጉ እውነትን ያመቻምቻሉ። እንዲህ ያሉ ፓስተሮችን፣ ‹‹እውነትን ከተናገራችሁ፣ ሰዎችን ታስቆጡ ይሆናል፤ ምናልባትም ትተው ይሄዱ (ይነቀሉ) ይሆናል፤ ይህን በማድረጋችሁ በፍጹም አትዘኑባቸው፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ወደ እናንተ ለሚያመጣቸው ሰዎች እውነትን መናገራችሁን ቀጥሉ›› እላቸዋለሁ።

አንዳንድ መሪዎች ሰዎችን እንዳያጡ ስለሚፈሩ ፊት ለፊት መጋፈጥ አይፈልጉም። በተለይ ደግሞ ፊት ለፊት መጋፈጥ የሚገባቸው ሰዎች ጠቀም ያለ ገንዘብ የሚሰጡ ወይም በማኅበረ ሰቡም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ተሰሚነት ያላቸው ከሆነ የበለጠ ወደ ኋላ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ለረጅም ጊዜ ከእነርሱ ጋር የኖሩ ሰዎችን ስሜት እንዳይጐዱ ይፈራሉ። ከዚህም የተነሣ ፓስተሮቹ እግዚአብሔር በአደራ የሰጣቸውን መንጋ የመጠበቅና የመመገብ ሥልጣናቸውን ያጣሉ።

ፓስተር በሆንኩባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ አንድ አስተዋይ ሰው፣ ‹‹ሥልጣንህን ጠብቅ፤ አለበለዚያ ሌላው ከአንተ ወስዶ አንተ ላይ ይጠቀምበታል›› በማለት አስጠንቅቆኝ ነበር።

ሳሙኤል፤ ለማንም ሰው እውነትን ከመናገር ወደ ኋላ የማይል ሰው ነበር፤ ሌላው ቀርቶ ለንጉሡ እንኳ እውነትን ለመናገር አልፈራም። ሳኦል ሳይታዘዝ በቀረ ጊዜ ፊት ለፊት እንዲጋፈጠው እግዚአብሔር ለሳሙኤል ነግሮት ነበር። እርሱም እንደ ተነገረው አደረገ። በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ ሳኦል ለእግዚአብሔር ቃል የሰጠው ምላሽ እውነተኛ ንስሐ በማድረግ አልነበረም። ሳሙኤል

ተለይቶት ለመሄድ ሲነሣ፣ ሳኦል ልብሱን ጨምድዶ ይዞ ስለ ነበር የሳሙኤል ልብስ ጫፍ ተቀደደ። ከዚያም፣ ‹‹እግዚአብሔር እስራኤልን መንግሥት ዛሬ ከአንተ ቀድዶታል›› በማለት አስደነገጠው (1 ሳሙኤል 15÷28)።

ሳሙኤል ለሳኦል የፈለገው ይህን አልነበረም። በሆነው ነገር በጣም አዝኖለታል። ሳኦልን ለንጉሥነት ቀብቶት ነበር፤ ስለ መልካም አመራር ሥልጠና ሰጥቶት ነበር፤ የንግሥና ሥርዐቱን የፈጸመውም እርሱ ነበር። ሳሙኤል የሳኦል የቅርብ ወዳጅ ነበር። ሆኖም፣ ሳሙኤል ለሳኦል በማዘኑ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ምላሽ ስሙ፤ ‹‹በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው? ወደ ቤተልሔሙ ሰው ወደ እሴይ ስለምልክህ ዘይት በቀንድ ሞልተህ ሂድ›› ነበር ያለው (1 ሳሙኤል 16÷1)።

ሳሙኤል ትኩስ ዘይት ወይም ቅባት ይዞ እንዲሄድ ከተፈለገ፣ የእግዚአብሔር ፍቅርና ፍርድ ሁሌም ትክክል መሆኑን መገንዘብ እንዳለበት ነበር እግዚአብሔር የነገረው። አንዴ እግዚአብሔር ከናቀው በኃላ ወደ ሳኦል ተመልሶ የሚሄድ ከሆነ፣ አዲስ ወይም ትኩስ ዘይት ይዞ መሄድ አይኖርበትም። ለሳኦል ማዘንና ማልቀሱን የሚቀጥል ከሆነ ከነበረበት ቦታ ወደ የትም አይንቀሳቀስም።

ቤተ ክርስቲያንን ትተው ለሚሄዱ ሰዎች ማዘንና ማልቀስ የሚቀጥለው፣ ወይም ወዳጆቻቸው ስለሆኑ ብቻ አባሎችን የማይገሥጹ ፓስተሮች በሕይወታቸው ያለው ዘይት ወይም ቅባት ይደርቃል። እንዲህ የሚያደርጉ የአገልግሎት ተቋሞች ይሞታሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሙት ቢሆኑ እንኳ፣ በሕይወት እንዳሉ ማስመሰል ይሞክራሉ። እንዲህ ያሉ አገልጋዮች ሳያውቁት ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ቀረቤታ ይልቅ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ቀረቤታ ያስበልጣሉ።

ከእርሱ በመለየት ትተውት ስለ ሄዱ ሰዎች ኢየሱስ እንደ ተቆጨ ወይም እንዳዘነ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም። የእርሱ ዋነኛ ደስታ የአባቱን ፈቃድ ማድረግ ብቻ ነበር። ይህን በማድረጉም የበለጠ ብዛት ያላቸው ሰዎችን ጠቅሟል።

በአንድ ወቅት በአንድ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሚያምን ቤተ ክርስቲያን ስሰብክ የሆነውን አልረሳውም። በመጀመሪያው እሑድ ቀለል ያለ የንስሐና ወደ ቀድሞ ፍቅር መመለስ እንደሚገባ ነበር የሰበክሁት። አንድ ዓይነት ተቃውሞ መኖሩ ቢሰማኝም፣ ያን መልእክት ማቅረብ እንደ ነበረብኝ አውቅ ነበር።

ከአገልግሎት በኃላ ፓስተሩ፣ ‹‹ዛሬ ጠዋት የሰበክኸው እግዚአብሔር አሳይቶኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ሕዝቡ ያንን ለመቀበል ዝግጁ እንደ ነበሩ አላስብም›› አለ።

በዚህ ጊዜ ሚስቴ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ የዚህ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ፓስተር ማነው፣ አንተ ነህ ወይስ ኢየሱስ?›› በማለት እንድትጠይቅ መንፈስ ቅዱስ ቃል ልቧ ውስጥ አኖረ።

ፓስተሩም ራሱን ጣል በማድረግ፣ ‹‹ከአንድ ወር በፊት እግዚአብሔር የነገረኝም ይህንኑ ነበር። እነዚህ ሰዎች መውሰድ ወይም መቀበል የሚችሉትን እንደሚያውቅ ነግሮኝ ነበር›› አለ። በማያያዝም ከቤተ ክርስቲያኑ ሰዎች ሦስት እጅ፣ በአገልግሎቱም ሆነ በአዘማመር ወይም በአሰባበክ ምንም ለውጥ እንዲኖር የማይፈልጉ፣ ‹‹የዱሮውን አጥባቂዎች›› እንደ ሆኑ አጫወተን። እኛም፣ እርሱ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንዲበረታ መከርነው።

በዚያ ቤተ ክርስቲያን አራት ጊዜ አገለገልን፤ እያንዳንዱ ጊዜ፣ ከበፊቱ የበለጠ ከባድና ደስ የማይል ነበር። ብዙ ጊዜ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግዬ ስሄድ፣ ደስታ ልቤን ይሞላው ነበር። አሁን ግን ችግሩ ምን እንደ ሆነ ሊገባኝ አልቻለም።

በኃላ ለጸሎት ብቻዬን ስሆን፣ ‹‹አባት ሆይ፣ ያደረግሁት ስሕተት ምንድነው? መንፈሴ ውስጥ ይህ ከባድ ሸክም ያለው ለምንድነው? ምናልባት የፓስተሩን ሥልጣንና ኃላፊነት ተጋፍቼ ይሆን?›› በማለት ጠየቅሁ።

‹‹የእግርህን አቧራ አራግፍ›› ብቻ ነበር ያለኝ (ሉቃስ 9÷5 ይመ.)።

ያንን ሲነግረኝ በጣም ደነገጥኩ። መጸለይና መጠየቄን ቀጠልኩ፤ ሆኖም፣ ያንኑ

‹‹የእግርህን አቧራ አራግፍ›› የሚል ቃል ነበር የሰማሁት።

በመጨረሻ መታዘዝ ነበረብኝ። ግና ሁለተኛውን እግሬን አራግፌ ሳልጨርስ ሽክሙ ከላዬ ተነሣ፤ ልቤም በደስታ ተሞላ። በኃላም በመደነቅ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ሰዎች እኮ አልበደሉኝም፤ ከአገራቸውም አላባረሩኝም፤ ታዲያ፣ ለምን?›› አልኩ።

አመራሩና ሕዝቡ ለእነርሱ የመጣው ቃሉን እንደ ናቁ አሳየኝ።

‹‹ጌታ ሆይ፣ እባክህ ተጨማሪ ጊዜ ስጣቸው›› በማለት ለመንኩ።

‹‹ተጨማሪ ሃምሳ ዓመታት ብሰጣቸውም አይለወጡም፤ ልባቸውን አጠንክረዋል።››

ይህ መሪ ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ፣ ተመሳስሎ በመኖር ሰላም እንዲፈጠር ማድረግን መርጧል። ቀንዱ የተሞላው በትኩስ ዘይት አይደለም። መልክ አለው፤ ይዘት ግን የለውም። በሌላ አነጋገር፤ በመንፈስ የተሞላ ሰው መስሎ ይታያል፤ ሆኖም፣ ኃይልና የእግዚአብሔር መገኘት ጐድሎታል። በኃላ ላይ፣ ይህ ሰው ፓስተርነቱን እንደ ተወ ሰማሁ፤ ቤተ ክርስቲያኑም ከበፊቱ በከፋ ሁኔታ ተከፋፍሎ ነበር።

ምን ጊዜም ቢሆን ኢየሱስ፣ በሰዎች ቁጥጥር ሥር ሆኖ አያውቅም። አደጋ ወይም ተቃውሞ እንደሚስከትልበት ወይም ሌሎች ሊሰናከሉ እንደሚችሉ ግልጽ ቢሆንም፣ እውነትን ከመናገር ወደ ኃላ አላለም። የምትፈልጉት የሰዎችን ምስጋናና ይሁንታ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ቅባት እናንተ ላይ አያርፍም። ሌሎችን የሚያሰናክል መስሎ ቢታይ እንኳ፣ የልባችሁ ዓላማ የእግዚአብሔርን ቃል መናገርና የእርሱን ፈቃድ መፈጸም መሆን አለበት።

የገዛ አገሩ ሰዎች በኢየሱስ ተሰናከሉ።

ኢየሱስ ለአግልግሎት ወደ ገዛ አገሩ መጣ። ይሁን እንጂ፣ ለሌሎች ብዙ ሰዎች ያመጣውን ነጻነትና ፈውስ ሊያመጣላቸው አልቻለም። በዚያ የነበሩ ሰዎች የተናገሩን ተመልከቱ፤

‹‹ይህ የአናጢው ልጅ አይደለምን? የእናቱስ ስም ማርያም አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳ አይደለሙን? እኅቶቹስ ከእኛው ጋር አይደለሙን? ታዲያ ይህ ሰው ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ስለዚህም ሳይቀበለት ቀሩ፡፡ ኢየሱስ ግን፣ ‹‹ነቢይ የማይከበረው በራሱ አገርና በራሱ ቤት ነው እንጂ በሌላ ቦታ ይከበራል አላቸው፡፡››

- ማቴዎስ 13÷55-57

እነዚያ የናዝሬት ሰዎች የተናገሩትን ሰማችሁ? ‹‹ለመሆኑ፣ ማን ነኝ ብሎ ነው የሚያስበው? እኛን በሥልጣን ለማስተማር ምን መብት አለው? አናውቀውም እንዴ! እዚሁ እኛው ሰፈር'ኮ ነው ያደገው፡፡ በዕድሜም ሆነ በትምህርት እንበልጠዋለን፡፡ እርሱ'ኮ ተራ የአናጢ ልጅ ነው፡፡ መደበኛ ትምህርቱን እንኳ አላጠናቀቀም፡፡››

እንዳይሰናከሉ ለማድረግ ሲል፣ አሁንም ቢሆን ኢየሱስ እውነትን ከመናገር አላፈገፈገም፡፡ የአገሩ ሰዎች በጣም ስለ ተናደዱ ከገደል አፋፍ ሊወረውሩት ሞክረው ነበር (ሉቃስ 4÷28-30)፡፡ ሕይወቱ ላይ አደጋ እያንጣበበ ቢሆንም፣ እውነትን መናገር ቀጠለ፡፡ በዚህ ዘመን ምን ያህል የዚህ ዓይነት ሰዎች ያስፈልጉን ይሆን!

የገዛ ቤተ ሰቡ በኢየሱስ ተሰናከሉ፡፡

ሌላው ቀርቶ የገዛ ራሱ ቤተ ሰቦች እንኳ ተሰናክለውበታል፡፡ እርሱ እያደረገ ከነበረው ነገር የተነሣ እየደረሰባቸው በነበረው ጫና ደስተኞች አልነበሩም፡፡ እየተናገረ ወይም እያደረገ የነበረው ሁሉ፣ እነርሱ ከሚያውቁት ማንነቱ ጋር እንደማይጣጣም ነበር ያሰቡት፡፡

ሁኔታውን የሰሙ ዘመዶቹም፣ ‹‹አእምሮውን ስቶአል›› በማለት ይዘውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ፡፡ ...እናቱና ወንድሞቹ መጡ፤ በውጭ ቆመውም ሰው ልከውበት አስጠሩት፡፡ በዙሪያው የተቀመጡ ብዙ ሰዎችም፣ ‹‹እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ውጭ ይፈልጉሃል›› አሉት፡፡ እርሱም መልሶ፣ ‹‹እናቴ ማን ናት ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?›› አላቸው፡፡ በዙሪያው ወደ ተቀመጡትም በመመልከት እንዲህ አለ፤ ‹‹እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣ እኅቴ፣ እናቴም ነውና፡፡››

- ማርቆስ 3÷21, 31-35

የገዛ ቤተ ሰቡ ሰዎች አእምሮውን ስቶአል በማለት ነበር ያሰቡት። ዘመዶቹ ወደ ነበረበት ቦታ የመጡት ይዘው ሊወስዱት እንደ ነበር መናገሩን ልብ አድርጉ። እነዚህ ሰዎች እነማን እንደ ነበሩ ማርቆስ ሲያመለክት እናቱና፣ ወንድሞቹ ነበሩ ይላል፤ በኃላም አንድ ሰው ቤት ውስጥ ሲሰብክ አግኝተውት ነበር። የዮሐንስ ወንጌል፣ ‹‹የገዛ ወንድሞቹ እንኳ አላመኑበትም ነበር›› ይላል (ዮሐንስ 7÷5)።

ኢየሱስ በጣም ይቀርቡት በነበሩ ሰዎች መናቁን ብዙዎች አልተረዱም። ይሁን እንጂ፣ እርሱ ይፈልግ የነበረው፣ የቤተ ሰቡን ወይም በጣም ይቀርቡት የነበሩ ሰዎችን ይሁንታ አልነበረም። ሰዎች መስማት በሚፈልጉት መሠረት አልነበረም ይንቀሳቀስ የነበረው። እነርሱ ቢወዱትም ቢጠሉትም የአባቱን ዕቅድ መፈጸም ነበር ዓላማው።

ኢየሱስን ከተከተልን ጓደኞችን ወይም ቤተ ሰባችን ይሰናከለብናል በማለት የሚያስቡ ብዙ ሰዎችን በተለይም፣ ባለ ትዳር ወገኖችን አይቻለሁ። ከዚህም የተነሣ ከእምት ወደ ኃላ ብለዋል ወይም በጥሪያቸው መሠረት መኖር አልፈለጉም።

እኔ ዳግም የተወለድኩ ጊዜ ቤተ ሰቦቼ በሙሉ ካቶሊኮች ነበሩ፤ አዲስ በተቀበልኩት እምነት የነበረኝን ደስታ አልተጋሩኝም ነበር። በተለይም እናቴ እኔን ያሳደገችበትን ቤተ ክርስቲያን ትቼ በመሄዴ በጣም ከፍቷት ነበር። እግዚአብሔርን በጣም የሚወዱ ካቶሊኮች እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ፤ እኔን በተመለከተ ግን ከዚያ ቤተ ክርስቲያን መውጣት እንደ ነበረብን አውቃለሁ።

ሁለተኛው አስደንጋጭ ነገር የተሰማው፣ ወደ አገልግሎት ለመግባት የወሰንኩ ገዜ ነበር። ከጥርዱ ዩኒቨርስቲ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ዲግሪዬን ያገኘሁት በቅርቡ ነበር፤ ወላጆቼ በእኔ ላይ ከፍተኛ ተስፋ ጥለው ነበር። በበኩሌ ግን ለእኔ እግዚአብሔር የሚፈልገውን አውቅ ነበር፤ ያንን ማድረጌ የቅርቤ የሆኑትን እንደሚያሰናክልም አውቅ ነበር። ይህም ለዓመታት ዘልቆ ነበር። በመካከላችን ብዙ አለ መግባባት ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ የቱንም ያህል ሊቆጡ ቢችሉም፣ ኢየሱስን መከተል ነበረብኝ።

መጀመሪያ ላይ በወንጌል ፀጥ ላሰኛቸው ሞክሬ ነበር። በማስቀደሳቸው ወይም ቅዱስ ቁርባን በመቀበላቸው ብቻ ድነት እንደማያገኙ ነግሬአቸው ነበር። በየጊዜው እየተከራከርኩ ወደ ትዕግሥታቸው ጫፍ አድርሻቸው ነበር። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው፣ ያደረግሁት ትክክል እንዳልነበረ ተረድቻለሁ። በኃላ ግን በእነርሱ ፊት እውነተኛ ክርስትና ሕይወት መኖር እንዳለብኝና መልካም ሥራዬን እንዲያዩ ማድረግ እንዳለብኝ እግዚአብሔር አመለከተኝ። ያም ሆኖ፣ አሁንም ቢሆን እነርሱን ደስ ለማሰኘት ስል እውነትን ማመቻመች አልፈልግም።

አሁን ወላጆቼ በአገልግሎቴ በጣም እየደገፉኝ ነው፤ በጣም ይከራከረኝ የነበረው ወንድ አያቴ፣ በሰማንያ ዘጠኝ ዓመቱ ማለትም ከመሞቱ ሁለት ዓመት ቀደም ሲል በአስደናቂ ሁኔታ ድነት አግኝቷል።

የኢየሱስ እናትና ወንድሞች አእምሮውን ስቶአል በማለት አስበው ነበር። ሆኖም፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዙ በበዓለ ሃምሳ ቀን በሰገነቱ በነበሩ ጊዜ ሁሉም ድነዋል። በአንድ በኩል ወንዱሙ የነበረው ያዕቆብ፣ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ዋና ሐዋርያ ሆኗል።

የቤተ ሰባችንን ሰዎች ደስ ለማሰኘት በማሰብ፣ እግዚአብሔር የነገረንን ከማድረግ ወደ ኃላ የምንል ከሆነ፣ በሕይወታችን ሊኖር የሚገባውን ትኩስ ዘይት እናጣለን፤ እነርሱም ነጻ እንዳይሆኑ እናግዳቸዋለን።

ኢየሱስ አብረውት እያገለገሉ የነበሩትን አሰናክሏል።

ባለፈው ምዕራፍ ኢየሱስ ባሰናከላቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይዘው ስለ ነበረው ዐቋም በሰፊው ተመልክተን ነበር። እስቲ እንደ ገና እንይ፤ ጉዳዩን ከኢየሱስ አንጻር ለመመልከት እንሞክር።

> ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ነገር ማጉረምረማቸውን ኢየሱስ በገዛ ራሱ ተረድቶ እንዲህ አላቸው፤ ‹‹ይህ ዕንቅፋት (መሰናከያ) ይሆንባችኃልን? ታዲያ፣ የሰው ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ

> ብታዩ ምን ልትሉ ነው... ከዚህም በኃላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኃላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ አልተከተሉትም።

- ዮሐንስ 6÷60-61,66

በዚያ ጊዜ ነገሮች በጣም ተካርረው ነበር። የሃይማኖት መሪዎቹ እርሱን ለመግደል ዐድማ እያደረጉ ነበር። የገዛ አገሩ ሰዎች ንቀውታል። ቤተ ሰቦቹ አእምሮውን ስቶአል በማለት አስበው ነበር። ከቅርብ ተከታዮቹ ብዙዎች ተሰናክለው፣ እርሱን ከመከተል ወደ ኃላ ማለታቸው ነገሩን የበለጠ አሳሳቢ አድርጐታል። ያም ሁሉ ሆኖ ግን፣ ኢየሱስ አለመቻመቸም። እንዲያውም እነርሱም ከፈለጉ መሄድ እንደሚችሉ ከእርሱ ጋር ቀርተው ለነበሩት ነግራቸው።

ኢየሱስን በጣም ያሳስበው የነበረ አንድ ነገር የአባትን ዕቅድ መፈጸም ብቻ ነበር። በዚያ ቀን ብቻውን ቀርቶ ቢሆን እንኳ፣ በልቡ የነበረውን የሚያስለውጠው አልነበረም። አባቱን ለመከተል ቁጥጥ ውሳኔ አድርጓል።

ኢየሱስ የቅርብ ወዳጆቹን አሰናክሏል።

> በማርያምና በእኅቷ በማርታ መንደር በቢታንያ ይኖር የነበረው አልዓዛር ታሞ ነበር። ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት ማርያም፣ በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ እግሩን በጠጉሯ ያበሰችው ነበረች። እኅትማማቾቹ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፤ የምትወደው ሰው ታሞአል›› ብለው መልእክት ላኩበት።

- ዮሐንስ 11÷1-3

ኢየሱስ ማርታን፣ ማርያምንና አልዓዛርን በጣም ይወድ ነበር። እነዚህ ሰዎች ለእርሱ በጣም የቀረቡ ነበሩ። ከእርሱ ጋር ጊዜ ያሳልፉ ነበር። ሆኖም፣ አልዓዛር መታመሙን ኢየሱስ ሲሰማ የሰጠውን ምላሽ ስሙ።

> ሆኖም፣ አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ።

- ዮሐንስ 11÷6

የአልዓዛር ሕመም ለሞት የሚያደርስ እንደ ነበር ኢየሱስ በመግለጥ ተረድቶ ነበር። ነገሩ በጣም አሳሳቢ ነበር። ያም ሆኖ ግን በነበረበት ቦታ ሁለት ተጨማሪ ቀን ቆየ። በመጨረሻ ወደ ቢታንያ ሲመጣ አልዓዛር ከሞተ ዋል አደር ብሎ ነበር።

ማርያምም ሆነች ማርታ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተ ነበር›› አሉት (ዮሐንስ 11÷21,32)። በሌላ አነጋገር፣ ‹‹ለምን ቶሎ አልመጣህም? እንደዚያ ሆኖ ቢሆን ኖሮ፣ ልታድነው ትችል ነበር!›› ማለታቸው ነበር።

ሁለቱ እኅትማማቾች በመጠኑም ቢሆን ቅር ሳይሰኙ፣ ሳይሰናከሉ እንደማይቀር በጣም ግልጽ ነው። መልእክተኞች ወደ እርሱ ልከው ነበር፤ እርሱ ግን ሁለት ቀን ሙሉ ሳይመጣ ቆየ። ኢየሱስ እነርሱ በጠበቁት መንገድ ምላሽ አልሰጠም። የጀመረውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተው ወዲያውኑ ጉዞ አልጀመረም፤ ይልቁን፣ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ነበር እየተከተለ የነበረው። ይህ ለማንኛችንም ቢሆን ተመራጭ ነው። በዚህ እንዲመጣ መልዕክተኛ በተላከበት ጊዜ ግን ኢየሱስ ደንታ ቢስ የሆነና ጨርሶ የማይገደው መስሎ ታየ።

ብዙ ጊዜ አገልጋዮች በሕዝባቸው ተፅዕኖ ሥር ሲሆኑ ይታያል። ሰዎች የሚጠይቋቸውን ሁሉ ማድረግ ያለባቸው ይመስላቸዋል።

አንድ ጊዜ ፓስተሩን ከሥራ አሰናብቶ የነበረ አንድ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያምን ቤተ ክርስቲያን የቦርድ አባል ሰው፣ ‹‹ፓስተሩ እኛ የምንነግረውን ሁሉ እንዲያደርግ እንፈልጋለን፤ በበኩሌ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ቢሮዬ መጥቶ ቡና እየጠጣን እንድንነጋገር እፈልጋለሁ›› በማለት ነግሮኝ ነበር።

መቼም፣ ሁሉን ማስደሰት የሚፈልግን ሰው መቆጣጠር ትችል ይሆናል፤ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሠረት የሚንቀሳቀስን ሰው ግን፣ በዚያ መልኩ መቆጣጠር አትችልም አልኩት። ይህ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ዓመት ተኩል ውስጥ፣ አራት ፓስተሮች ተፈራርቀውበት እንደ ነበር በኋላ ላይ ሰማሁ።

የወጣቶች ፓስተር በነበርኩ ዘመን፣ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ስድስት ወር በፓስተርነት ካገለገልኩ በኋላ አንድ ወጣት ወደ እኔ

መጥቶ፣ ‹‹በፊት የነበረው ፖስተር የእኔ የቅርብ ጓደኛ ነበር፤ አንተስ የቅርብ ጓደኛዬ ትሆናለህ ወይ?›› አለኝ፡፡

በፊት የነበረው ፖስተር ከወጣቶቹ ጋር ተለሳልሶ የሚኖርና ሁለንም ሰው ደስ ማሰኘት የሚፈልግ ሰው ነበር፡፡ ያ ወጣት ከእኔ ምን እየጠበቀ እንደ ነበር ወዲያውኑ ነበር ግልጽ የሆነልኝ፡፡ በመሠረቱ፣ ከላይ የነገርኳችሁ ቤተ ክርስቲያን፣ ከፖስተሩ የጠበቀው ይህንኑ ነበር፡፡

‹‹ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል›› በማለት ኢየሱስ የተናገረበትን ማቴዎስ 10÷41 ለወጣቱ ጠቀስኩለትና፣

‹‹ብዙ የቅርብ ጓደኞች አለህ አይደል?›› በማለት ጠየቅሁት፡፡

‹‹በጣም እንጂ›› አለ፡፡

‹‹ግን ያለህ አንድ ፖስተር ብቻ ነው አይደል?››

‹‹አዎን››

‹‹ታዲያ፣ አንተ የምትፈልገው የአንድ የወጣቶችን ፖስተር ዋጋ ነው ወይስ የቅርብ ጓደኛህን ዋጋ? ምክንያቱም እኔን የምትቀበልበት መንገድ ከእግዚአብሔር የምትቀበለውን ይወስናል፡፡››

ልነግረው የፈለግሁት በትክክል ገባው፡፡

‹‹የወጣቶችን ፖስተር ዋጋ ነው መቀበል የምፈልገው›› አለ፡፡

የሚያገለግለዋቸው ሰዎች የሚጠብቁባቸውን ሁሉ ካላሟለ፣ ስሜታቸውን እንዳይጐዱና ድጋፋቸውን እንዳያጡ ብዙ አገልጋዮች ይፈራሉ፡፡ ሌሎችን እንዳያሰናክሉ በመፍራት ወጥመድ ተይዘዋል፡፡ የሚቆጣጠራቸው እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ነው፡፡ ስለሆነም በቤተ ክርስቲያናቸው ወይም በማኅበረ ምዕመናቸው ውስጥ ዘላለማዊ ውጤት ያለው ሥራ የሚሠራው እጅግ በጣም በጥቂቱ ነው፡፡

ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስን አሰናከለ፡፡

ሌላው ቀርቶ መጥምቁ ዮሐንስን እንኳ በኢየሱስ የመሰናከል ፈተና ገጥሞት ነበር፡፡

> የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ይህንን ሁሉ ለዮሐንስ ነገሩት፡፡ እርሱም ከመካከላቸው ሁለቱን ጠርቶ፣ ‹‹ይመጣል የተባለልህ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? በሉት›› ብሎ ወደ ጌታ ላካቸው፡፡ ሰዎቹም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ ‹‹መጥምቁ ዮሐንስ ይመጣል የተባለልህ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ብሎ ወደ አንተ ልኮናል›› አሉት፡፡
>
> - ሉቃስ 7÷18-20

ኢየሱስ እንደሚመጣ የተነገረለት መሲሕ መሆን አለመሆኑን ዮሐንስ የጠየቀው ለምን ነበር? መንገዱን ያዘጋጀለት ዮሐንስ ራሱ ነበር፤ በኋላም፣ ‹‹እነሆ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!›› በማለት የእርሱን መምጣት የተናገረ ራሱ ዮሐንስ ነበር (ዮሐንስ 1÷29)፡፡ ‹‹በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው እርሱ ነው›› በማለት ተናግሮ ነበር (ቁ.33)፡፡ ሌላው ቀርቶ፣ ‹‹እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል›› ብሎ ነበር (ዮሐንስ 3÷30)፡፡ በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ማን መሆኑን በትክክል የሚያውቅ ዮሐንስ ብቻ ነበር፡፡ (ለስምየን ጴጥሮስ ግና አልተገለጠም ነበር፡፡)

ታዲያ፣ ‹‹ኢየሱስ መሲሕ ነው ወይስ ሌላ ሰው እንጠብቅ›› በማለት ለምን ጠየቀ?

እስቲ፣ ራሳችሁን በዮሐንስ ቦታ አድርጉ፡፡ እግዚአብሔር ማድረግ የፈለገውን ተናግሯችሁ ነበር እንበል፡፡ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች በአገልግሎታችሁ ተነክተው እንደ ነበር አስቡ፡፡ አገልግሎታችሁን በተመለከተ የብዙዎች መወያያ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖችኃል፡፡ ራስን የመካድ ሕይወት እየኖራችሁ ነበር፡፡ የተቀበላችሁትን ጥሪ በሚገባ መፈጸም እንዲያስችላችሁ ሌላው ቀርቶ ትዳር እንኳ አልመሠረታችሁም፡፡ አንበጣና የበረሐ ማር እየበላችሁ በምድረ በዳ ትኖሩ ነበር፤ በዚህ ላይ ደግሞ ብዙ ቀኖችን በጸም ታሳልፋላችሁ፡፡ ከፈሪሳውያን ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጣችኃል፤

አጋንንት እንዳለባችሁም ተናግረውባችኃል። መላው ሕይወታችሁን ያሳለፋችሁት ለሚመጣው መሲሕ መንገድ በማዘጋጀት ነበር።

አሁን ግን እስር ቤት ተጥላችኃል። ስታስተምሩና ስታሠለጥኑዋቸው የነበሩ ሰዎች ሁሉ ትኩረታቸውን ኢየሱስ ላይ በማድረጋቸው እስር ቤት እየመጡ የሚጠይቋችሁ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ የእናንተ የነበሩ ደቀ መዛሙርት አሁን የዚህ ሰው ተከታዮች ሆነዋል። እናንተን ለማገልገል የቀሩ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነርሱም ቢሆን ወደ እናንተ በመጡ ጊዜ ሁሉ የሚነግሯችሁ ስለዚህ ሰውየና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ከእናንተ ደቀ መዛሙርት በጣም የተለየ ሕይወት እንደሚኖሩ ነበር እንበል። የእርሱ ደቀ መዛሙርት ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኃጢአተኞች ጋር ይበላሉ፤ ይጠጣሉ። ሰንበትን ይሽራሉ፤ እንዲያውም አይጸሙም።

ታዲያ፣ በዚህ ጊዜ፣ ‹‹መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ ሲያርፍበት ተመልክቼ ነበር፤ ግን ይህ የአንድ መሲሕ መለያ ምልክት ነው እንዴ?›› በማለት ከራሳችሁ ጋር ትሟገታላችሁ።

እስር ቤት ውስጥ በቆያችሁ መጠን የሚደርስባችሁም መሰናከል በዚያው መጠን ይጨምራል። ‹‹ዕድሜዬን በሙሉ የእርሱን መንገድ ሳዘጋጅለት የነበረ ይህ ሰው፣ ሌላው ቢቀር እስር ቤት መጥቶ እንኳ አልጠየቀኝም! መሲሕ ከሆነ ለምን ከዚህ እስር ቤት አያወጣኝም? እኔ'ኮ ምንም የበደልኩት ነገር የለም።›››

ስለዚህም ለኢየሱስ ጥያቄ እንዲያቀርቡ በጣም የምታምኑዋቸው ሁለት ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ እንደ ላካችሁ አስቡ። ‹‹ይመጣል የተባለልህ አንተ ነህ ወይስ ሌላ ሰው እንጠብቅ?››

ኢየሱስ ለዮሐንስ የሰጠውን መልስ እንመልከት፤

በዚያኑ ጊዜ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ከበሽታ፣ ከደዌና ከርኩሳን መናፍስት ፈውሳቸው፤ የብዙ ዐይነ ስውራንንም ዐይን አበራ። ከዮሐንስ ተልከው የመጡትንም እንዲህ አላቸው፤ ‹‹ሂዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዐይነ ስውራን ያያሉ፤ ዐንካሶች በትክክል ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች ነጽተዋል፤

> ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ተነሥተዋል፤ ለድኾችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔ የማይሰናከል ሰው ሁሉ የተባረከ ነው።

- ሉቃስ 7÷21-23

ይህ የኢየሱስ አነጋገር ትንቢታዊ ነው። ዮሐንስ በጣም ከሚያውቀው ከኢሳይያስ ትንቢት ነበር የጠቀሰው። ኢሳይያስ 29÷18, 35÷4-6 እና 61÷1 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ለመጠየቅ የመጡ ጊዜ የተመለከቱትን ሁሉ ይመለከታል። እነዚህ ነገሮች መሲሕ መሆኑን ይመሰክራሉ። ሆኖም፣ እዚያ ላይ አያበቃም። ‹‹በእኔ የማይሰናከል ሰው ሁሉ የተባረከ ነው›› የሚል ጨምሮበታል።

በሌላ አነጋገር፣ ‹‹ዮሐንስ፣ እየደረሰብህ ያለውንና አብዛኞቹ መንገዶቼን መረዳት እንዳቃተህ አውቃለሁ፤ ሆኖም፣ አንተ የምትጠብቀውን ባለ ማድረጌ በእኔ አትሰናከልብኝ›› ማለቱ ነበር። በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ባለፈው ጊዜ እግዚአብሔር የተጠቀመበትን መንገድ በገዛ ራሱ መረዳት መመዘን እንደሌለበት ለዮሐንስ እየመከረው ነበር። በዚህ ዘመን ያለን እኛ የተሟላውን የእግዚአብሔር ሐሳብ መረዳት እንደማንችል ሁሉ፣ ዮሐንስም ሙሉውን የእግዚአብሔር ዕቅድ መረዳት አልቻለም ነበር። ‹‹እንድታደርግ የታዘዝከውን አድርገሃል፤ የምትቀበለው ዋጋ ታላቅ ነው፤ ግን በእኔ እንዳትሰናከል ተጠንቀቅ!›› በማለት ኢየሱስ እያበረታታው ነበር።

ይቅርታ የማይጠየቅበት በደል

እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ሁሉ፣ አብዛኞቹን የእግዚአብሔር መንገዶች የተማራችሁ ብትሆኑ እንኳ፣ አሁንም ቢሆን በኢየሱስ የመሰናከል ሁኔታ ሊያጋጥማችሁ ይችላል። በእውነት እርሱን የምትወዱና የምታምኑበት ከሆነ፣ ሁሌም የእርሱ መንገድ ከእናንተ መንገድ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን በመገንዘብ ከመሰናከል መራቅ ይኖርባችኃል።

ከዚህም ሌላ ለእግዚአብሔር መንፈስ የምትታዘዙ ከሆናችሁ፣ ሰዎች ሊሰናከሉባችሁ ይችላሉ። ዮሐንስ 3÷8 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹ነፋስ

ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው›› ብሏል፡፡

ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ወይም በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ስትንቀሳቀሱ አንዳንዶች መረዳት ያቅታቸው ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የእነርሱ ደስ አለመሰኘት፣ እውነት መሆኑን በልባችሁ የምታውቁትን ነገር ከማድረግ ወደ ኃላ እንዲይዛችሁ መፍቀድ የለባችሁም፡፡ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት በማሰብ የመንፈስን እንቅስቃሴ አታጨናግፉ፡፡ ይህን ጴጥሮስ በአጭሩ ገልጠታል፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዓላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአትን ትቶአል፡፡ ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ በሚቀረው ምድራዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ፣ እንደ ሥጋ ምኞት አይኖርም፡፡

- 1 ጴጥሮስ 4÷1-2

የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም የምትሮጡ ከሆነ፣ ሰዎች የፈለጉትን አታደርጉም፡፡ ስለዚህም ስደት ሊደርስባችሁ ይችላል፡፡ ኢየሱስን ከባድ ተቃውሞ የገጠመው ከሃይማኖት መሪዎች ነበር፡፡ አንዳንድ ሃይማኖተኛ ሰዎች እግዚአብሔር የሚሠራው ወይም የሚንቀሳቀሰው በእነርሱ መለኪያ መስፈርት ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ፡፡ እነርሱ ለእግዚአብሔር በጣም የቀረቡ እንደ ሆኑ ያምናሉ፡፡ እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሠረት በመንቀሳቀስ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ሃይማኖተኛ ሰዎችን ካሰናከለ፣ የእርሱ ተከታዮች የሆኑት ዛሬም እነርሱን ማሰናከላቸው የማይቀር ነው፡፡

የሐዋርያው ጳውሎስ ስደት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ በገላትያ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ግርዛት ለድነት አስፈላጊ ነው ከሚሉ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመወገን፣ ጳውሎስ የመሰቀሉን ወንጌል አመቻምቾል የሚል የተሳሳተ ወሬ ሰምተው ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን ወዲያውኑ ያንን ስሕተት አስተካከለ፡፡ ‹‹እስቲ እኔን ተመልከቱ፤ በየቦታው ከሃይማኖት መሪዎች ስደትና ተቃውሞ እየደረሰብኝ ነው፡፡ እነርሱ እንደሚፈልጉት ግርዛትን ሰብኬ ቢሆን

ኖሮ ይህን ያደርሱብኝ ነበር? ሐቁ፣ ወደ መዳን የሚያደርስ መንገድ መስቀሉ ብቻ መሆኑ፣ ሰዎችን የሚያሰናክል መሆኑ ነው፤ ሆኖም፣ ያ እውነት ነው፤ ከዚያ የተለየ ሌላ ነገር የምሰብክበት ምንም ምክንያት የለም!›› (ገላትያ 5÷11 ይመ)።

አንድ ሰው የወንጌልን እውነት ከተቃወመ፣ ይቅርታ የሌለው ምላሽ መስጠት አለብን። የሚስከፍለው ዋጋ የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን ለእግዚአብሔር መንፈስ ለመታዘዝ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ማድረግ አለብን። እንዲህ ያለ ውሳኔ ካደረግን፣ በሰዎች ተፅዕኖ የምናደርገው ውሳኔ ወይም ምርጫ አይኖረንም።

ኢየሱስ ለአባት በመታዘዝ

አንዳንድ ሰዎችን አሰናክሏል፤

ይሁን እንጂ፣ የራሱን መብት

የሙጥኝ ብሎ በመያዝ ማንንም አላሰናከለም።

በቅርቡ *የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኘውን መጽሐፍህን አንብቤ በፍጹም ነጻ እወጣለሁ ብዬ አስቤ ከማላውቀው የተለያየ የሕይወቴ ገጽታ ነጻ እንደ ወጣሁ ልነግርህ እፈልጋለሁ። ሕይወቴን የለወጠ በመሆኑ፣ ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀትህ በጣም አመሰግንሃለሁ።

- ሲ. አር፣ ቴኔሲ

10

እንዳናሰናክላቸው

ስለዚህ እርስ በርሳችን፣ አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ እንቆጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናክያ ድንጋይ ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቁርጥ ሐሳብ አድርግ።

- ሮሜ 14÷13

በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ኢየሱስ ብዙዎችን ማሰናከሉን ያደረግነውን ምልከታ ገና ማብቃታችን ነው። እንዲያውም በየሄደበት ቦታ ሁሉ፣ ሰዎች በእርሱ ሲሰናከሉ የነበረ ይመስላል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የዚህን ሌላ ጐን ወይም ገጽታ እንመለከታለን።

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከቅፍርናሆም ገና መመሳቸው ነበር። በአገልግሎት ወዲያ ወዲህ ሲሉ ከቆዩ በኃላ ጥቂት ዕረፍት ለማድረግ ነበር የመጡት።

ለአገልግሎቱ እንደ መነሻ ጣቢያ የሚወስደው ቦታ ቢኖር ያ ቦታ ወይም ከተማ ነው። እዚያ እያሉ የቤተ መቅደስ ግብር እየሰበሰቡ የነበሩ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ መጥተው፣ ‹‹መምህራችሁ፣ የቤተ መቅደሱን ግብር አይከፍልምን?›› አሉት (ማቴዎስ 17÷24)።

እርሱም፣ ‹‹ይከፍላል እንጂ›› ካለ በኃላ፣ ስለ ጉዳዩ ከኢየሱስ ጋር ለመነጋገር ወደ ቤት ሄደ።

ግብር ሰብሳቢዎቹ እንደዚያ ዐይነት ጥያቄ ሊያነሡ እንደሚችሉ ኢየሱስ ጠብቆ ነበር፤ ስለሆነም፣ ‹‹ስምዖን፣ ለመሆኑ ምን ትላለህ? የምድር ነገሥታት ግብር ወይም ቀረጥ የሚቀበሉት

ከራሳቸው ልጆች ነው ወይስ ከሌሎች?›› በማለት ስምዖን ጴጥሮስን ጠየቀው፡፡

‹‹ከሌሎች ነው የሚቀበለው›› አለ ጴጥሮስ፡፡

‹‹እንግዲያው ልጆች ነጻ ናቸው›› (ማቴዎስ 17÷25-26)፡፡

‹‹ልጆች ነጻ›› መሆናቸውን ኢየሱስ ለጴጥሮስ ግልጽ አደረገለት፡፡ ልጆች ግብር ወይም ቀረጥ መክፈል የለባቸውም፡፡ ይልቁንም፣ እነርሱ ከግብር ወይም ከቀረጥ የሚገኘው ጥቅም ተካፋዮች ናቸው፡፡ በማንኛውም ግብር ወይም ቀረጥ የመጠቀም መብት በነበረው ቤተ መንግሥት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ልጆች ከነገሥታት ማዕድ ይመገባሉ፤ ልብሰ መንግሥት ይለብሳሉ፤ ይህ ሁሉ የሚገኘው ከሚሰበሰበው ግብር ነው፡፡ በነጻነት ይኖራሉ፤ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በነጻ ያገኛሉ፡፡

እነዚያ ሰዎች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ግብር ይሰበስባሉ፡፡ ግን የቤተ መቅደሱ ንጉሥ ወይም ባለቤት ማን ነው? ለመሆኑ፣ ቤተ መቅደስ የተሠራው ለማን ክብር ነው? መልሱ ለእግዚአብሔር አባታችን ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሲሕ›› መሆኑን ጴጥሮስ፣ በመገለጥ ተረድቶ ነበር፡፡

ከዚህ አንጻር ኢየሱስ፣ ‹‹እንግዲህ እኔ የቤተ መቅደሱ ባለቤት ልጅ ከሆንኩ፣ ግብር ከመክፈል ነጻ መሆን የለብኝምን?›› በማለት ጴጥሮስን መጠየቁ ነበር፡፡ በእርግጥ እርሱ ያንን ግብር ከመክፈል ነጻ ነበር፡፡ ግብር አለመክፈሉ ተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ያም ሆኖ ግን ለስምዖን ጴጥሮስ የተናገረውን እንመልከት፤

> ሆኖም፣ እንዳናስቀይማቸው (እንዳናሰናክላቸው) ሂደህ መንጠቆህን ወደ ባሕር ጣል፤ መጀመሪያ የምትይዘውን ዓሣ አፉን ስትከፍት የምታገኘውን አንድ እስታቴር በእኔና በአንተ ስም ክፈል፡፡
>
> - ማቴዎስ 17÷27

ነጻ መሆኑን አስረግጦ ተናግሮአል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዳናስቀይማቸው ወይም እንዳናሰናክላቸው፣ ‹‹መክፈል አለብን!›› አለ፡፡ ወደ ባሕሩ ሂዶ የሚይዘውን የመጀመሪያ ዓሣ አፍ ሲከፍት፣

እዚያ ውስጥ ገንዘብ እንደሚያገኝ ለጴጥሮስ መናገሩ አንድ ተጨማሪ የነጻነቱ ማረጋገጫ ነበር። እግዚአብሔር አባት ሌላው ቀርቶ ለግብር የሚከፈል ገንዘብ እንኳ ይሰጣል።

ኢየሱስ የምድር ሁሉ ጌታ ነው፤ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ምድርና በእርሷ ላይ ያለ‌ት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል፤ ለእርሱም ይገዛለ‌ል። ስለሆነም የሚፈለገው ገንዘብ እዚያ ዓሣ አፍ ውስጥ መኖሩን አወቋል። እርሱ ልጅ በመሆኑ ያንን ገንዘብ ለማግኘት ላይ ታች ማለት የለበትም። ያም ሆኖ ግን ማንንም ማስቀየም ወይም ማሰናከል ስላልፈለገ ግብር መክፈልን መረጠ።

ያለፈው ምዕራፍ ላይ ሰዎችን ሲያስቀይም ወይም ሲያሰናክልና ለዚያም ምንም ይቅርታ እንዳልጠየቀ የተመለከትነው ይኸው ኢየሱስ ራሱ አይደለምን? የቤተ መቅደስን ግብር መክፈል እንደማይመለከተው አስረግጦ ተናግሮ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ ‹‹እንዳናስቀይማቸው (እንዳናሰናክላቸው) ሂድና ክፈል!›› ብሎአል። ይህ እርስ በርሱ የሚጋጭ ሐሳብ አይመስልም? መልሱን ቀጥሎ ያለው ቁጥር ላይ እናገኘዋለን፤

> በዚያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው? ብለው ጠየቁት። ኢየሱስ አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከላቸው አቆመና እንዲህ አላቸው፤ እውነት እላችኃለሁ፣ ካልተለወጣችሁ እንደ ሕፃን ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም። ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው።
>
> - ማቴዎስ 18÷1-4

እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ነጥብ፣ ‹‹ራሱን ትሑት የሚያደርግ›› የሚለው ሲሆን፣ ቀጥሎ ደግሞ በሚከተለው ቃሉ ይህን የበለጠ አጉልቶታል።

> ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን... የሰው ልጅ እንዲያገለግለ‌ት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና።
>
> - ማቴዎስ 20÷26-28

ምንኛ የሚገርም ንግግር ነው! እርሱ የመጣው ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል ነው። እርሱ ልጅ ነው፤ ስለዚህም ነጻ ነው። የማንም ዕዳ የለበትም። የማንም ተገዥ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ነጻነቱን ሌሎችን ለማገልገል ተጠቀመበት።

ለማገልገል ነጻ መሆን

እንደ የእግዚአብሔር ልጆች ወንድማችንን እንድንመስል፣ ኢየሱስ የነበረው ዐይነት ዝንባሌ እንዲኖረን አዲስ ኪዳን ይመክረናል።

> ወንድሞቼ ሆይ፣ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኃል፤ ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት።
>
> - ገላትያ 5÷13

ነጻነትን የሚተካ ሌላ ቃል መብት ነው። እንደ ሕያው እግዚአብሔር ልጆች ነጻነታችንን ወይም መብታችንን ራሳችንን ለማገልገል ልንጠቀምበት አይገባም። ነጻነት ሌሎችን ለማገልገል ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ማገልገል ውስጥ ነጻነት አለ፤ ባርነት ውስጥ ግን ቀንበር አለ። ባሪያ የግድ ማገልገል አለበት፤ አገልጋይ ግን ለማገልገል ይኖራል። በአንድ ባሪያና በአንድ አገልጋይ መካከል ያለውን ልዩነት እንመልከት።

- ባሪያ ግዴታ አለበት፤ አገልጋይ ግን ፈቅዶ ያገለግላል።
- ባሪያ ዝቅ ያለ ኃላፊነት አለው፤ አገልጋይ ግን የላቀና የበለጠ ኃላፊነት አለው።
- ባሪያ አንድ ኪሎ ሜትር ይሄዳል፤ አገልጋይ ግን ተጨማሪ ኪሎ ሜትር ሄዶ የማገልገል መብት አለው።
- ባሪያ እንደ ተበዘበዘ ያስባል፤ አገልጋይ ግን በደስታ ይሰጣል።
- ባሪያ እስረኛ ነው፤ አገልጋይ ግን ነጻ ነው።
- ባሪያ መብቱን ለማግኘት ይታገላል፤ አገልጋይ ግን ወዶና ፈቅዶ መብቱን ይተዋል።

ቅር በመሰኘት ዝንባሌ የሚያገለግለ ብዙ ክርስቲያኖች አይቻለሁ። በንፍገት ይሰጣለ፤ እየተነጫነጩ ግብር ይከፍላለ። እነዚህ ወገኖች ዛሬም በሕግ ባርነት ውስጥ አለ፤ በመሠረቱ ግን፣ ከዚያ ነጻ ወጥተው ነበር። ሆኖም በልባቸው ዝንባሌ አሁንም ባሪያዎች እንደ ሆኑ ናቸው።

በጣም አስደንጋጩ ነገር ደግሞ፣ ይህን ሕግ የሚፈጥሩት የአዲስ ኪዳንን ጥቅሶች መሠረት በማድረግ ነው። ኢየሱስ ትእዛዞቹን የሰጠበት፣ ‹‹መንፈስ›› የላቸውም። እነዚህ ሰዎች ለማገልገል ነጻ መውጣታቸውን አልተገነዘቡም። ስለሆነም፣ ከሌሎች ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ይታገላለ።

በሮሜና በቆሮንቶስ መልእክቶች ይህን ዝንባሌ ለመጋፈጥ ጳውሎስ በጣም ግልጽ ምሳሌዎች አቅርቧል። ለእነዚህ ሰዎች ነጻነት ከምግብ ነክ ጥያቄዎች ያለፈ አልነበረም። ጳውሎስ ግን፣ ‹‹በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በዐቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት። የአንድ ሰው እምነቱ ማንኛውንም ነገር እንዲበላ ይፈቅድለታል፤ በእምነቱ ያልጠነከረው ሌላው ሰው ግን አትክልት ብቻ ይበላል›› አለ (ሮሜ 14÷1-2)።

ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ ሳይሆን፣ ከአፍ የሚወጣ መሆኑን ኢየሱስ በሚገባ አሳይቷል። እንዲህ ሲል ማንኛውንም ምግብ ለአማኝ ንጹሕ አድርጓል (ማርቆስ 7÷18-19)።

በእምነታቸው ደካሞች የሆኑ አማኞች እንዳሉና እነዚህ ሰዎች ለጣዖት የተሠዋውን እንዳይበሉ በመፍራት ሥጋ መብላት እንደማይፈልጉ ጳውሎስ ይናገራል። ይህን አስመልክቶ ኢየሱስ ቢናገርም፣ እነዚህ ሰዎች በንጹሕ ሕሊና መመገብ አልቻሉም።

እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ስለ መብላት እንዲህ እላለሁ፤ በዚህ ዓለም ጣዖት ከንቱ እንደ ሆነና ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን... ለእኛ ግን ሁሉም ነገር ከእርሱ የሆነ፣ እኛም ለእርሱ የሆን አንድ አምላክ አብ አለን፤ ደግሞም ሁሉም ነገር በእርሱ አማካይነት የሆነ፣ እኛም በእርሱ አማካይነት የሆን፣ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። ነገር ግን ይህን የሚያውቁ ሁሉም አይደሉም፤ አንዳንድ ሰዎች እስከ አሁን

> ድረስ ጣዖትን ማምለክ ስለ ለመዱ እንዲህ ያለውን ሥጋ ሲበሉ በእርግጥ ለጣዖት እንደ ተሠዋ ያስባሉ፤ ኅሊናቸውም ደካማ ስለሆነ ይረክሳል

- 1 ቆሮንቶስ 8÷4,6-7

በእነዚያ ቤተ ክርስቲያኖች የነበሩ በእምነታቸው ብርቱ የሆኑ ወገኖች፣ በደካሞቹ ቅዱሳን ፊት ከየት እንደ መጣ የሚያጠራጥር ሥጋ ይበሉ ነበር። እነዚህ ምግቦች ንጹሕ እንደ ሆኑ ኢየሱስ ቢናገርም፣ አንዳንድ አለመግባባቶችን ፈጥሮ ነበር። ደካሞቹ አማኞች በጣዖት መሠዊያ ላይ የቀረበ ሥጋን ስዕል ከአእምሮአቸው አውጥተው መጣል አልቻሉም። ብርቱዎች ግን ጣዖት ከንቱ ነገር እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ ያንን በመብላታቸውም ኅሊናቸው አይወቅሳቸውም።

ይሁን እንጂ፣ የበለጠ የሚያሳስባቸው እንደ አዲስ ኪዳን አማኞች መብታቸውን አጥብቀው መያዝ እንጂ፣ ወንድሞቻቸውን ማሰናከላቸው አልነበረም። እነርሱ ሳያውቁት በደካሞቹ ወንድሞቻቸው መንገድ ላይ የመሰናከያ ድንጋይ እያኖሩ ነበር። በእውነተኛ አገልጋይ ልብ ውስጥ እንዲህ ያለ ዝንባሌ የለም። ይህን በተመለከተ ጳውሎስ የሚለውን ተመልከቱ።

> ስለዚህ እርስ በርሳችን አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ እንቆጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቁርጥ ሐሳብ አድርግ።... የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት ነው እንጂ፣ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም።

- ሮሜ 14÷13,17

‹‹የእግዚአብሔር መንግስት በእውነት ምን እንደ ሆነ አንርሣ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት'ኮ - ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ ነው›› እያለ ነው። አዳዲሶቹ አማኞች እነዚህን ሁሉ ጥቅሞች አልተረዱም ነበር። ብርቱዎቹ አማኞች ደግሞ ነጻነታቸውን፣ ‹‹መብታቸውን›› እንደ ማስከበሪያ መድረክ እንጂ፣ ሌሎችን ለማገልገል እየተጠቀሙበት አልነበረም። የአዲስ ኪዳን

ነጻነታቸውን በተመለከተ በቂ ዕውቀት ነበራቸው። ሆኖም፣ ፍቅር የሌለበት ዕውቀት አጥፊ ነው።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ የኢየሱስ ዐይነት ልብ አልነበራቸውም። ሌሎችን ለማገልገል ሕይወታችንን የመስጠት አስፈላጊነት ምሳሌ እንዲሆነን ኢየሱስ የቤተ መቅደሱን ግብር ላለ መክፈል የነበረውን መብት ለጴጥሮስና ለሌሎች ደቀ መዛሙርት አረጋግጠላቸው ነበር። ነጻነታችን የመብት ማስከበሪያ እንዲሆንና ከዚህም የተነሣ ሌሎችን ለማሰናከያነት እንድንጠቀምበት አይፈልግም።

በክርስቶስ ስላላቸው ነጻነት በቂ ዕውቀት ላላቸውና፣ የእርሱ የማገልገል ልብ ግን ለሌላቸው ወገኖች፣ ጳውሎስ ይህን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

> ስለዚህ ክርስቶስ የሞተለት ይህ ደካማ ወንድም በአንተ ዕውቀት ምክንያት ጠፋ ማለት ነው። በዚህ መንገድ ወንድሞቻችሁን በመበደልና ደካማ ኅሊናቸውን በማቁሰል ክርስቶስን ትበድላላችሁ።
>
> - 1 ቆሮንቶስ 8÷11-12

ነጻነታችንን ኃጢአት ለማድረግ ልንጠቀምት እንችላለን። እንዴት? ደካማ ኅሊና ያላቸው ወገኖችን በማቁሰል፣ የክርስቶስ ከሆኑት ታናናሾች አንዱን በማሰናከል እንዲወድቅ በማድረግ።

መብታችንን መተው

የቤተ መቅደሱን ግብር ከመክፈል አንጻር ኢየሱስ የነበረውን ነጻነት ካሳየ በኃላ፣ ወዲያውኑ የደቀ መዛሙርቱን ትኩረት ወደ ትሕትና አስፈላጊነት ነበር የወሰደው።

> በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሰው ከባድ የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል። ይህች ዓለም የመሰናከል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት! መሰናክል መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር ግን የመሰናከሉ ምክንያት ለሚሆን ሰው ወዮለት። እጅህ ወይም እግርህ ለመሰናከል ምክንያት ቢሆንብህ ቆርጠህ ጣለው፤ ሁለት እጅ

ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል፣ አንካሳ ወይም ሽባ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። እንዲሁም ዐይንህ ለመሰናክል ምክንያት ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ጣለው፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃነም እሳት ከምትጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። ከእነዚህ ከታናናሾች መካከል አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ እላችኋለሁና፤ በሰማይ ያሉት መላእክቶቻቸው በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ሁልጊዜ ያያሉ።

- ማቴዎስ 18÷6-10

ይህ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሙሉ በሙሉ የሚናገረው ስለ መሰናክል ነው። ሌላው ቀርቶ፣ አዲስ ኪዳን የሰጠን መብት ቢሆን እንኳ፣ በምንም መልኩ የኃጢአት ምክንያት መሆን እንደሌለብን ኢየሱስ በጣም ግልጽ አድርጐአል። ወንድማችሁን የሚያሰናክል ወይም ኃጢአት እንዲያደርግ ምክንያት የሆነ ማንኛውንም ነገራችሁን ቆርጣችሁ ጣሉት።

ምናልባት፣ ቀደም ሲል ከነበረው ምዕራፍ ከተመለከትነው በመነሣት እንዲህ ከሆነ፣ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ለምን አሰናከለ በማለት ግራ እንጋባ ይሆናል። መልሱ በጣም ቀላል ነው። ኢየሱስ አንዳንድ ሰዎችን ያሰናከለው ለአባት ከመታዘዙና ሌሎችን ከማገልገሉ የተነሣ ነበር። እርሱ ሌሎችን ያሰናከለው የገዛ ራሱን መብት ለማስከበር ሲል አልነበረም።

በሰንበት ዕለት በመፈወሱ ፈሪሳውያን ተሰናክለው ማለትም፣ ተቀይመው ነበር። ደቀ መዛሙርቱ የተሰናከሉት አባቱ የሰጠውን እውነት በመናገሩ ነበር። ማርያምና ማርታ የተሰናከሉት አልዓዛርን ለመፈወስ ቶሎ ባለ መምጣቱ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ራሱን ለማገልገል ወይም ለመጥቀም ሲል ኢየሱስ ማንንም ሲያሰናክል አናይም።

ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ጳውሎስ ይህን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ የምታደርጉት ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ።

- 1 ቆሮንቶስ 8÷9

ነጻነታችን የተሰጠን ሌሎችን እንድናገለግልና ሕይወታችንንም እንድንሰጥ ነው። መግንባት እንጂ ማፍረስ የለብንም። ይህ ነጻነት የተሰጠን ነገሮችን እንድናጠራቅም አይደለም። ይሁን እንጂ፣ በዚህ መንገድ ስለ ተጠቀምንበት፣ በክርስቲያኖች አኗኗር ብዙዎች ተሰናክለዋል።

1 ቆሮንቶስ 8÷9 ላይ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ እንደ ገና ስሙ፤ ‹‹ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ የምታደርጉት፣ ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ።››

ይህን ትእዛዝ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ልናፈርስ እንደምንችል አንድ ምሳሌ ይኸውላችሁ። ለሁለተኛ አገልግሎት ወደ ኢንዶኔዥያ በሄድኩ ጊዜ ሚስቴ ሊዛን፣ ልጆቼንና ሞግዚታቸውን ይዤ ነበር የሄድከት። የመዝናኛ ደሴት ወደ ሆነችው ዴንፓሳር ባሊ መጣን።

እኛ የምናገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የነበረ ሰው በጣም ጨኸት በበዛበት የከተማው ክልል ውስጥ አንድ መጠነኛ ሆቴል ነበረው። ረጅም ርቀት ነበር የተጓዝነው፤ በዚህ ላይ ደግሞ በቂ እንቅልፍ አላገኘንም ነበር። በጣም ደካክሞን ነበር። እዚያ ባሳለፍነው ሌሊት በሰዎች ጫጫታና በውሾች ጨኸት ብዙ ጊዜ እንባንን ነበር። እዚያ ያሳለፍነው አንድ ሌሊት ቢሆንም፣ የምንፈልገውን እንቅልፍ አላገኘንም ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ወደ ጃቫ ሄደን በጣም በተጨናነቀ ፕሮግራም ውስጥ ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንቶች አገለገልን። በእነዚያ ሁለት ሳምንቶች ውስጥ የነበረን ነጻ ቀን አንድ ብቻ ነበር፤ ያም ቢሆን ለጉዞ የምናውለው ነበር። በቀኑ ውስጥ ባሉት ሃያ አራት ሰዓቶች ውስጥ ሰላሣ ሺህ አባሎች በነበሩት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቀን አምስት ጊዜ አገልግለን ነበር።

ጉዞአችን መጨረሻ ላይ በባሊ በኩል እንድንመለስ ነበር ያሰብነው። እንደ ገና በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌው ሆቴል እንድናርፍ ፓስተሩ ነገረን። ሁለት ሳምንት ሙሉ ያለ በቂ ዕረፍት

በአገልግሎት ካሳለፍን በኃላ በድጋሚ እዚያ ቦታ ማረፍ ደስ አላለንም።

ጃቫን ለቅቀን በምንሄድበት ቀን ጠዋት ቁርስ ላይ እያለን፣ ባሊ ውስጥ ካሉት በጣም ምርጥ ሆቴሎች በአንዱ እንድናርፍ አንዲት ደግ ሴት ሙሉ ወጪያችንን እንደምትሸፍንልን ነገረችን። የምንፈልገውን ዕረፍት ማግኘት የምንችልበትና በዚያ ውብ ቦታ ጊዜ ማሳለፍ ስለምንችል በጣም ነበር ደስ ያለኝ።

ከነበርንበት ሬስቶራንት ለመነሣት ዕቃዎቻችንን እያዘገጃጀን እያለ ሴትዮዋ ባቀረበችው ሐሳብ ደስ አለመሰኘትዋን ሊዛ ነገረችኝ። እኔና አስተርጓሚው ግን፣ ብትከፍልልን ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ልናሳምናት ሞከርን። ከጃቫ ወደ ባሊ ለመሄድ አውሮፕላን ውስጥ እያለን ሊዛ ትክክለኛ ነገር እያደረግን እንዳይደለ በድጋሚ ነገረችኝ።

የነገረችኝን ባለ መስማቴ ሞኝነቴ የታወቀኝ በኃላ ነበር። ቤተ ክርስቲያኑን፣ ምንም ገንዘብ የማያስወጣ በመሆኑ እያደረግን ያለው ጥሩ እንደ ሆነ ነገርኳት። ባሊ ስንደርስ ዕቃችን እየተፈተሸ እያለ ከልመና ባላነሰ ሁኔታ እንደ ገና ነገረችኝ፤ እኔ ግን ችላ አልኳት።

ፓስተሩን ሳገኘው ሴትየዋ ስለምትከፍልልን እዚያ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆቴል ውስጥ እንደማናርፍ ነገርኩ። በነገርኩት ቅር የተሰኘ መስሎ ስለ ታየኝ ችግሩ ምን እንደ ሆነ ጠየቅሁት።

‹‹ጆን፣ ይህ ሽማግሌውንና ቤተ ሰቡን በጣም ያሳዝናቸዋል (ያሰናክላቸዋል)። እነዚህ ሰዎች ለእናንተ ሲሉ ሆቴል ውስጥ ክፍሎች ይዘዋል፤ ስለዚህ እነዚያ ክፍሎች በዚያ ሌሊት ማንም አይዛቸውም›› በማለት በግልጽ ነገረኝ።

ከዚያም ባለፈ እነርሱ ያዘጋጁልንን ባለ መቀበላችን ፓስተሩን ሳላሳዝነው እንዳልቀረሁም አስባለሁ። በመጨረሻ እዚያ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆቴል ውስጥ እንደምናርፍና የሴትዮዋን ግብዣ እንደማንቀበል ነገርነው።

የነበረኝን ዝንባሌ በተመለከተ ጌታ አስተማረኝ። በሁኔታዬ ፓስተሩ መሞዳቱን አውቃለሁ። የእኔን ሐሳብ (መብት) ብቻ መከተሌ ያንን ወንድም እንዳሰናከለው ማየት ቻልኩ፤ ያ ደግሞ ኃጢአት ነው። ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁት፤ እርሱም ይቅርታ አደረገልኝ። ያንን ትምህርት ድጋሚ እንደማልማር ተስፋ አደርጋለሁ።

መተናነጽን የሚመለከት ፈተና

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ፣ በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ ያለውን ቁልፍ አድርጎ አስቀምጧል።

> ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ።
>
> - ሮሜ 14÷19

በግል እኛ ካለን ነጻነት የተነሣ ሌሎች እንዲሰናከሉ አለማድረግ ዓላማችን ሊሆን ይገባል። እያደረግን ወይም እየተናገርን ያለው የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ ያለው ሊሆን ይችላል። ያም ቢሆን እንኳ፣ የማደርገው ወይም የምናገረው ሌላውን ሰው ያንጻል ወይስ የእኔን መንገድ ብቻ ነው እየተከተልኩ ያለሁት? በማለት ራሳችንን እንጠይቅ።

> ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ ሁሉም ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር አያንጽም፤ እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ የራሱን ብቻ አይፈልግ።... እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። ለአይሁድም ሆነ ለግሪኮች ወይም ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሰናክል አትሁኑ። እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር እናንተም እንዲሁ አድርጉ፤ ብዙዎች ይድኑ ዘንድ፣ ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለእነርሱ የሚጠቅመውን እሻለሁና።
>
> - 1 ቆሮንቶስ 10÷23-24,31-33

በዚህ ምንባብ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም የሕይወታችሁን ገጽታ እንዲመዝን ፈቃዳችሁ ይሁን። ለሌሎች ሳይሆን ለራሳችሁ ጥቅም ብቻ ለማዋል ያሰባችሁትን ማንኛውንም ድብቅ ዓላማ ወይም አጀንዳ እንዲያሳያችሁ ፍቀዱለት። የትኛውንም የሕይወት ገጽታችሁን የሚመለከት ቢሆን፣ የሁሉም አገልጋይ ሆናችሁ ለመኖር የእርሱን ምሪት ተከተሉ።

በክርስቶስ ያላችሁን ነጻነት የራሳችሁን መብት ለማስጠበቅ ሳይሆን፣ ሌሎችን ነጻ ለማውጣት ተጠቀሙበት። ‹‹አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ፣ ለማንም ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም›› በማለት የጻፈው የጳውሎስ አገልግሎት መመሪያ ይኸው ነበር (2 ቆሮንቶስ 6÷3)።

ይቅር የማይል ሰው

እግዚአብሔር የእርሱን ትልቅ

ዕዳ ይቅር እንዳለለት ዘንግቶአል።

ለአንድ ዓመት ያህል *የሰይጣን ሽንገላ* መጽሐፍ መደርደሪያዬ ላይ ነበር፤ በታላ ግን ማንበብ ጀመርኩ። ብዙም ሳልቆይ በሕይወቴ እየሠራ የነበረው መንፈስ ምንነትና ማንነት በጣም ግልጽ ሆነልኝ። ይህን መጽሐፍ እንዳነብ የመራኝ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ነበር ቅንጣት ጥርጥር የለኝም። ብዙ ባነበብኩ መጠን፣ በዚያ ልክ እየተወቀስኩ መጣሁ። ሌሎችን ይቅር ማለት የሚፈልጉ ሰዎች ወደ ፊት እንዲመጡ በቤተ ክርስቲያን ፓስተሩ አጥብቆ እየጠየቀ ነበር። በድለውኛል ብዬ የማስባቸውን ሁሉ፣ በተለይም ደግሞ አባቴን ይቅር ለማለት ምንም ሳላመነታ ወደ ፊት ሄድኩ። ከዚያ ይቅር እንዲለኝ አባቴን ጠየቅሁት። ይቅር ስላለኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፤ አሁን ነጻ ሰው ነኝ! ስለዚህ መጽሐፍ በጣም ነው የማመሰግንህ!

- አር. ፒ. ቨርጂኒያ

11

ይቅር ካላላችሁ – ይቅር አትባሉም

ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል። እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ። ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

- ማርቆስ 11÷24-26

በተቀረው የዚህ መጽሐፍ ክፍል ሁሉ፣ ትኩረታችንን መሰናክልን ወይም በደልን አለ መተው የሚያስከትለውን ውጤትና እንዴት ነጻ መሆን እንደሚቻል ማሳየት ላይ እንዲሆን እፈልጋለሁ።

‹‹ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም›› በማለት ኢየሱስ የተናገረው በእርግጠኝነት ነበር። ለምንናገረው ነገር ሁሉ ይህን ያህል ትኩረት በማንሰጥበት ባሕልና ዘመን ውስጥ ነው ያለነው። ከዚህም የተነሣ ሌሎች ሰዎችም የሚናገሩት የምራቸውን እንደ ሆነ አናስብም። በዚህ ዘመን አንድ ሰው ለሚናገረው ያን ያህል ግምት አይሰጥም።

ይህ ሁሉ የሚጀምረው በልጅነት ጊዜ ነው። ለምሳሌ አንድ ወላጅ ለልጁ፣ ‹‹ሁለተኛ እንደዚያ ካደረግህ እቀጣሃለሁ›› ይለዋል እንበል። ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ልጁ ደግሞ ደጋግሞ ያንኑ ጥፋት ይፈጽማል። ጥፋቱን በፈጸመ ጊዜ ሁሉ ልጁ ከወላጁ ያንኑ ማስጠንቀቂያ ይሰማል። ሁሌም ግን የእርምት ርምጃ ሲወሰድበት አያይም። የእርምት ርምጃ ቢወሰድበት እንኳ፣ እንደ ተባለው

ሳይሆን በጣም ቀላል፣ ወይም ደግሞ ወላጁ በጣም ከመናደዱ የተነሣ ከመጠን ያለፈ ሊሆን ይችላል።

ሁለቱም የምትናገሩት ከልባችሁ እንዳይደለ ወይም የምትናገሩት የውሸት እንደ ሆነ ለልጁ መልእክት ያስተላልፋሉ። ከዚያም ልጁ ሥልጣን ያለው አካል ሁሉ የሚናገረው እውነት እንዳይደለ ማሰብ ይጀምራል። ስለሆነም፣ ልጁ ማንኛውም ሥልጣን ያለው ሰው የሚናገረውን ከልቡ መውሰድ ያለበት መቼ ሊሆን እንደሚችል ግራ ይጋባል። ይህ ዝንባሌ በሌሎች የሕይወት ገጽታዎቹም ይንጸባረቃል። ለአስተማሪዎቹ፣ ለጓደኞቹ፣ ለመሪዎቹና ለአለቆቹ ያለው አመለካከት ሁሉ ከዚህ አንጻር ይሆናል። በኃላም ጐልማሳ ሲሆን፣ ይህን እንደ እውነትና መደበኛ ነገር ይቀበላል። አሁን እርሱም ከልቡ ያላሰበበትን ቃል ይገባል፤ እርሱ ራሱ በእውነት የማያምንበትን ነገር ይናገራል።

እስቲ በጣም የተለመደ ንግግርን አስመልክቶ መላ ምታዊ ምሳሌ ልስጣችሁ።

ከበደ አበበን አንድ ቦታ ያየዋል፤ በጣም የሚያውቀው ጓደኛው ቢሆንም፣ ከረጅም ጊዜ ወዲህ አግኝቶት አያውቅም እንበል። በጣም ቸኩሎ ነበር፤ ስለዚህም፣ በዚህ ሁኔታ አበበን ማናገር የለብኝም፤ በዚህ ላይ ደግሞ እርሱን ለማናገር ጊዜ የለኝም ብሎ ያስባል።

ከዚያ ሁለቱ ሰዎች ዐይን ለዐይን ይገናኛሉ።

‹‹እንደምንድነህ ወዳጄ፣ ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ጌታ ይመስገን›› ይላል ከበደ።

ለአጭር ጊዜ ያወራሉ። ከበደ በጣም ቸኩሎ ስለ ነበር፣ ‹‹አንድ ቀን ተገናኝተን፤ አብረን ምሳ መብላት አለብን›› በማለት ወሬውን ይቋጫል።

በመጀመሪያ፣ ከበደ አበበን በማግኘቱ ደስተኛ አልነበረም፤ ምክንያቱም፣ በሌላ ጉዳይ ቸኩሎ ነበር። ሁለተኛ፣ አበበን በማግኘቱ በጣም ደስ ብሎኛል ‹‹ጌታ ይመስገን›› ያለው የእውነት አልነበረም። ሦስተኛ አንድ ቀን አብረው ምሳ እንደሚበሉ ቢናገርም፣ ያንን ያለው

ከልቡ አይደለም። እንዲሁ ቶሎ ከእርሱ ለመለየትና፣ ያንን በማለቱ ጎሊናውን ቀለል ለማሰኘት ብቻ ነበር። እንግዲህ በዚያ ንግግር ውስጥ ከበደ የተናገረው አንዱ እንኳ የምሩን አልነበረም ማለት ነው።

ይህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች በገሃዱ ዓለም በየዕለቱ ይፈጸማለ። በዚህ ዘመን ሰዎች ከሚናገሩት አንድ አራተኛው የምራቸውን አይደለም ማለት ይቻላል። ታዲያ፣ አንድ ሰው የሚናገረው የትኛው የምር፣ የትኛው እንዲሁ ለወሬ ብቻ መሆኑን፣ ለይተን ለመቀበል ብንችገር ያስገርማል?

ኢየሱስ ሲናገር ግን፣ የሚናገረው ትኩረት ሰጥተን እንድንቀበለው ነው። እርሱ የሚነግረንን ሌሎች ባለ ሥልጣኖች ወይም በሕይወት ዘመናችን የሚገጥሙን ሰዎች የሚናገሩትን በምንመለከትበት መንገድ መውሰድ አንችልም። አንድ ነገር ከተናገረ፣ ያንን የተናገረው ከልቡ ወይም የምሩን ነው። እኛ ታማኝ ባንሆንም፣ እርሱ ታማኝ ነው። ከእኛ ባሕል ወይም ማኅበረ ሰብ እጅግ በላቀ መልኩ እርሱ የሚመላለሰው በእውነትና በታማኝነት ደረጃ ነው። ስለሆነም ኢየሱስ፣ ‹‹ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም›› ሲል ያንን የተናገረው ከልቡ ወይም የምሩን ነው።

አንድ ርምጃ ወደ ፊት ለመሄድ ያህል፣ በወንጌሎቹ ውስጥ እርሱ ይህን የተናገረው አንዴ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ጊዜ ነው። ይህ ማስጠንቀቂያ በጣም አስፈላጊ ለመሆኑ አጽንዖት እየሰጠ ነው የተናገረው። ይህ አስመልክቶ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ የተናገራቸው ጥቂቶችን እንይ።

እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ፣ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላችኃል። ነገር ግን የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

- ማቴዎስ 6÷14-15

እንደ ገና፣

ይቅር በለ፤ ይቅር ትባላላችሁ።

- ሉቃስ 6÷37

እንደ ገና በጌታ ጸሎት፣

እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን - የሚል እናነባለን።

- ማቴዎስ 6÷12

የበደሉዋቸውን ሰዎች ይቅር በሚሉበት መንገድ እግዚአብሔርም እነርሱን ይቅር እንዲላቸው የሚፈልጉ ምን ያህል ክርስቲያኖች ሊሆኑ እንደሚችል ራሴን እጠይቃለሁ። ያም ሆኖ ግን፣ እነርሱ ራሳቸው ይቅር የሚባሉት በትክክል በዚህ መንገድ ነው። በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ይቅር አለመባባል በጣም ከመስፋፋቱ የተነሣ፣ ይህን የኢየሱስን ቃል የምራችንን ወይም ከልባችን መውሰድ አንፈልግም። እንዲህ ወይም እንዲያ መሆኑ ግን እውነቱን አይለውጠውም። ይቅር የምንባለው ሌላውን ሰው ይቅር በምንልበት፣ በምንፈታበትና ወደ ቀድሞ ሁኔታ በምንመልስበት መንገድ ነው።

በፊልጲንስ ስላለ አንድ አገልጋይ ያልተለመደ ዐይነት ምስክርነት ሰምቻለሁ። በበፊቱ አገልግሎቱ እርሱን የሚያውቁ ወዳጆቼ ስለ ልምምዱ የሚናገር አንድ መጣጥፍ አሳይተውኛል።

በነበረው የንግድ ሥራ እጅግ እየተሳካለት ስለ ነበር፣ ለሕይወቱ ከእግዚአብሔር የመጣውን ጥሪ ሰውየው መቀበል ተቸግሮ ነበር። እጅግ በጣም ብዙ ገንዘብ እያገኘ ነበር። አልታዘዝም ማለቱ የኃላ ኃላ ባስከተለው መዘዝ በከፍተኛ የልብ ሕመም በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ።

እዚያው ኦፕራሲዮን የሚደረግበት ጠረጴዛ ላይ እያለ፣ ይሞትና ራሱን የመንግሥተ ሰማይ ደጅች ላይ ያገኘዋል። በዚያ ቦታ ኢየሱስ ቆሞ ነበር፤ አለ መታዘዙን በተመለከተ ያናግረዋል። ተጨማሪ ዕድሜ ከሰጠው፣ በሙሉ ልቡ እንደሚገለግለው ቃል

በመግባት ሰውየው ጌታን ይለምነዋል። ጌታም ልመናውን ይቀበላል።

ወደ አካለ ከመመለሱ በፊት ጌታ ገሃነምን ያሳየዋል። የሚስቱ እናት ገሃነም እሳት ነበልባል ውስጥ ስትቃጠል ይመለከታል።

ያንን በማየቱ በጣም ተገረመ። ኃጢአተኛ ሰው የሚጸልየውን ጸሎት ጸልያ ነበር፤ ክርስቲያን እንደ ሆነች ስትናገር ነበር፤ ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን ትመጣ ነበር።

‹‹ወደ ገሃነም የተጣለችው ለምንድነው?›› በማለት ሰውየው ጌታን ይጠይቀዋል።

ጌታም፣ አንድ ዘመዷን ይቅር እንዳላለችና ስለዚህ እርሷም ይቅር እንዳልተባለች ይነግረዋል።

ይቅር ማለትና መንፈሳዊ ዕድገት

እኔና ሊዛም እንዲሁ ይቅር ያለ ማለት ወጥመድን አስመልክቶ በአገልግሎታችን ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ጉዳዮች ተመልክተናል። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንዶኔዥያ ሳገለግል ያረፍኩት አንድ በጣም ሀብታም የንግድ ሰው ቤት ውስጥ ነበር። እርሱም ሆነ ቤተ ሰቡ እኔ እያገለገልኩ ወደ ነበረበት ቤተ ክርስቲያን ቢሄዱም፤ ጌታን በመቀበል አልዳኑም ነበር።

እዚያ ባሳለፍኩት ሳምንት ውስጥ ሚስቱ ዳነች፣ እርሱ ቀጠለ፤ ከዚያም ሦስቱም ልጆቹ ድነት አገኙ። ነጻ መውጣትም ነበር፤ መላው የቤተ ሰቡ ከባቢ ተለወጠ። ቤታቸው በታላቅ ደስታ ተሞላ።

ከሚስቴ ጋር በድጋሚ ወደ ኢንዶኔዥያ እንደምመለስ ሲረዱ፣ እነርሱ ቤት እንድናርፍ ጋበዙን፤ ለሦስቱ ልጆቼና ለሞግዚቷ የአውሮፕላን ቲኬት እንደሚከፍሉም ቃል ገቡ።

በድጋሚ ስንመለስ ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ዐሥር ጊዜ ያህል አገልግለናል። ስለ ንስሐና የእግዚአብሔር መገኘት ነበር

የሰበክሁት። ጉባኤው ውስጥ የእርሱ መገኘት ይሰማን ነበር፤ በዚያ ውስጥ ብዙዎች ያለቅሱና ከተለያየ እስራት ነጻ ይወጡ ነበር።

በድጋሚ መላው ቤተ ሰብ የአገልግሎታችን ተጠቃሚ ሆነ። በዚያው ከተማ ውስጥ ትኖር የነበረች የሰውየው እናት በእያንዳንዱ ስብሰባ ተገኝታ ነበር። ለልጆቹ የአውሮፕላን ትኬት መግዣ ከፍ ያለውን ገንዘብ የሰጠች እርሷ ነበረች።

የሳምንቱ መገባደጃ ላይ የሰውየው ሚስት በቀጥታ ዐይኖቼን እያየች፣ ‹‹ጆን፣ ለእኔ የእግዚአብሔር መገኘት ያልተሰማኝ ለምንድነው?›› በማለት ጠየቀችኝ።

ገና ቁርስ በልተን መጨረሳችን ስለ ነበር፣ ሁሉም ከገበታው ተነሥተው ነበር።

‹‹እያንዳንዱን ስብሰባ ተካፍያለሁ፤ የተናገርከውን ሁሉ ሰምቻለሁ፤ ንስሐ ለማድረግ ወደ ፊት መጥቼ ነበር፤ ግን አንዴ እንኳ የእግዚአብሔር መገኘት አልተሰማኝም። ያም ብቻ ሳይሆን፣ ሌላ ጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር መገኘት ተሰምቶኝ አያውቅም›› አለች።

ጥቂት ከተነጋገርን በኋላ፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ እንድትሞዪ እንጸልይ›› አልኳት። እጄን እርሷ ላይ ጭኜ መንፈስ ቅዱስን እንድትቀበል ጸለይኩላት፤ ግን ጨርሶ የእግዚአብሔር መገኘት አልተሰማንም።

ከዚያም ጌታ፣ ‹‹ባልዋን ይቅር አላለችም፤ ውስጧ ይቅር ያለ ማለት አለ፤ ይቅር እንድትለው ንገራት›› በማለት ለመንፈሴ ተናገረኝ።

እጄን፣ ከእርሷ ላይ አነሣሁ። ባሏ መሞቱን አውቃለሁ፤ ያም ሆኖ፣ ፊት ፊቷን እየተመለከትኩ፣ ‹‹ባልሽን ይቅር ያላልሽው ነገር መኖሩን ጌታ አሳይቶኛል›› አልኳት።

‹‹አዎን፣ እውነት ነው›› አለች በነገርኳት እየተስማማች። ‹‹ግን'ኮ እርሱን ይቅር ለማለት የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ።››

ከዚያም፣ እርሷ ላይ ስለ ፈጸመው በጣም ዘግናኝ ነገር አጫወተችን። እኔም፣ እርሱን ይቅር ለማለት ለምን እንዳዳገታት መረዳት ቻልኩ።

ይሁን እንጂ፣ ‹‹አንቺ ከእግዚአብሔር እንድትቀበዪ ይቅር ማለት ይኖርብሻል›› አልኳት። ከዚያም፣ ይቅር ማለትን በተመለከተ ኢየሱስ ያስተማረውን ገለጽኩላት። ‹‹በራስሽ ብርታት ይቅር ልትዪው አትችዪም። ይህን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቢና በመጀመሪያ አንቺ ራስሽን ይቅር እንዲልሽ ለምኚው። ከዚያ ባልሽን ይቅር ማለት ትችያለሽ። ይቅር ካለ ማለት እስራት ባልሽን ለመፍታት ፈቃደኛ ነሽ?›› በማለት ጠየቅኳት።

‹‹አዎን›› በማለት መለሰች።

ከዚያም፣ ‹‹በሰማይ የምትኖር አባት ሆይ፣ ባሌ ላይ በያዝኩት ይቅር ያለ ማለት ይቅር እንድትለኝ በኢየሱስ ስም እጠይቅሃለሁ፤ በራሴ ብርታት ይቅር ልለው እንደማልችል አውቃለሁ። ብዙ ሞክሬ አልሆነልኝም። አሁን ግን፣ አሁን ግን በአንተ ፊት ባሌን ይቅር ካለ መባል እስራት ከልቤ እፈታዋለሁ። ይቅር ብየዋለሁ›› የሚል አጭር ጸሎት እንድታደርግ መራሁዋት።

እነዚህን ቃሎች ገና ተናግራ ሳትጨርስ፣ እንባዋ በጉንጮቿ ኮለል ብሎ መፍሰስ ጀመረ።

‹‹እጆችሽን ወደ ላይ አንሺና በልሳን ተናገሪ›› አልኳት።

በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ውብ በሆነ ሰማያዊ ቋንቋ ጸለየች። እዚያ ቁርስ ለመብላት ተቀምጠን በነበረበት ማዕድ እንዳለን፤ በጣም ብርቱ የሆነ የእግዚአብሔር መገኘት ተሰማን። በግምት ለአምስት ደቂቃ ያህል ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ጥቂት ከተነጋገርን በኃላ፣ ከእንግዲህ የእግዚአብሔር መገኘት ሁሌም ከአንቺ ጋር ነው አልኳት። እግዚአብሔርን ማምለክ ቀጠለች፤ እኔ ግን ትቻት ሄድኩ።

ወሬው ለልጇና ለሚስቱ ሲደርስ፣ በጣም ነበር የተገረሙት። እናቱ ስታለቅስ አንዴ እንኳ ዐይቶ እንደማያውቅ ልጁ ተናገረ።

እርሷ ራሷም ብትሆን ያለቀሰችበትን ጊዜ አታስታውስም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ ባሌ የሞተ ጊዜ እንኳ አላለቀስኩም›› ነበር ያለችኝ።

በዚያ ምሽት በነበረው አገልግሎት ውሃ ጥምቀት ፈጸመች። በቀጣዮቹ ሦስት ቀኖች ፊቷ ላይ ደስ የሚልና ውብ ፈገግታ ይታይ ነበር። ከዚያ በፊት ግን በፈገግታ ሆና እንዳየኋት አላስታውስም። ይቅር ባለ ማለቷ፣ ይቅር ያለ ማለት እስረኛ ሆና ነበር። ይቅር ካለ መባል እስራት፣ ባልዋን ከፈታች በኃላ ግን በሕይወቷ የእግዚአብሔርን ኃይል አገኘች፤ መገኘቱም ይሰማት ጀመር።

ይቅር ያላለው አገልጋይ

ማቴዎስ 18 ላይ ይቅር ያለ ማለትንና የበደልን ቀንበር አስመልክቶ ኢየሱስ ተጨማሪ ትምህርት ሰጥቷል። በደል ካደረሰባቸው ወንድም ጋር መታረቅ እንዳለባቸው ደቀ መዛሙርቱን እያስተማረ ነበር። (ዕርቅን በተመለከተ በኃላ በምናገኘው ምዕራፍ እንነጋገራለን።)

ጴጥሮስ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?›› በማለት ጠየቀ (ማቴዎስ 18÷21)። በጣም ቸር እንደ ሆነ ነበር ያሰበው።

ጴጥሮስ ነገሮችን እስከ ጽንፍ መውሰድ የሚወድ ሰው ነበር። በመለወጥ ተራራ ላይ፣ ‹‹አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ ሦስት ዳሶች ልሥራ›› በማለት የጠየቀ እርሱ ነበር (ማቴዎስ 17÷4)። አሁንም ቢሆን በጣም ቸር ወይም ለጋስ እንደ ሆነ ሳያስብ አልቀረም። ሰባት ጊዜ ይቅር ለማለት ፈቃደኛ በመሆን፣ ጌታን ላስገርመው በማለት ሳያስብ አልቀረም።

ግን፣ ያልጠበቀው መልስ ነበር ያገኘው። ቸርነቴን ወይም ለጋስነቴን አሳይበታለሁ ብሎ ጴጥሮስ ያሰበውን ኢየሱስ ከንቱ አደረገበት፤ ‹‹እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፣ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም›› (ማቴዎስ 18÷21-22)። በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር ይቅር በሚልበት መንገድ ማለትም ያለ ምንም ገደብ ይቅር በል ማለት ነው።

ከዚያም ኢየሱስ ይህን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ አንድ ምሳሌ ተናገረ፡፡

> ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ የፈለገውን ንጉሥ ትመስላለች፡፡ ሂሳቡን ማጣራት እንደ ጀመረም ዐሥር ሺህ ታላንት ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ አቀረቡለት፡፡
>
> - ማቴዎስ 18÷23-24

ኢየሱስ የጠቀሰው ግንዘብ መጠን ምን ያህል ብዙ እንደ ነበር ለመረዳት፣ አንድ ታላንት ምን ያህል እንደ ነበር ማወቅ አለብን፡፡ ታላንት አንድ ዓይነት መለኪያ ሲሆን ወርቅን (2 ሳሙኤል 12÷30)፣ ብርን፣ (1 ነገሥት 20÷39) እና ሌሎች ዋጋ ያላቸው ነገሮችን ለመለካት ይጠቅማል፡፡ በዚህ ምሳሌ የሚናገረው ስለ ዕዳ ሲሆን፣ የገንዘቡ ዓይነት ወርቅ ወይም ብር ነበር ቢባል ከሐቁ አንርቅም፡፡ ለማንኛውም ወርቅ ነው የሚለውን እንያዝ፡፡

በጣም የተለመደው ታላንት ሰባ አምስት ፓውንድ ያህል ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ሰው መሸከም የሚችለውን ያህል ይከብዳል (2 ነገሥት 5÷23 ይመ.)፡፡ በዚህ ሂሳብ መሠረት ዐሥር ሺህ ታላንት 750,000 ፓውንድ ወይም 375 ቶን ሲሆን፣ አገልጋዩ የነበረበት ዕዳ 375 ቶን ወርቅ ነበር ማለት ነው፡፡

በአሁን ጊዜ የወርቅ ዋጋ ለአንድ አውንስ 375 ዶላር ነው፡፡ አሁን ባለው ገበያ አንድ ታላንት ወርቅ 450,000 ዶላር ይሆናል፡፡ ስለሆነም ዐሥር ሺህ ታላንት 4.5 ቢሊዮን ዶላር ያወጣል ማለቱ ነው፡፡ ያ አገልጋይ 4.5 ቢሊዮን ዶላር የንጉሡ ዕዳ ነበረበት!

እዚህ ላይ ኢየሱስ ያ አገልጋይ መክፈል የማይችለው ዕዳ መጠን እንደ ነበረበት አጽንዖት ይሰጣል፡፡ እስቲ እናንብብ፡፡

> አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ መክፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ላይ ወድቆ - ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ ሲል ለመነው፡፡ ጌታውም አዘነለትና ማረው ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው፡፡
>
> - ማቴዎስ 18÷25-27

አሁን ደግሞ፣ ይህ ምሳሌ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ከበደል ወይም ከመሰናከል ጋር እንደሚያያዝ እንመልከት። አንድ በደል ሲፈጸም ዕዳ እየተገባ ነው። ምናልባትም፣ ‹‹ለዚህ ተግባሩ ዋጋ ይከፍላል›› ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል። ስለ ሆነም ይቅር ማለት ዕዳ የመሰረዝ ያህል ነው ማለት ነው።

ንጉሡ፣ አገልጋዩ መክፈል ያልቻለውን ዕዳ ይቅር ያለውን እግዚአብሔርን ይወክላል። ቈላስይስ 2÷13-14 ላይ፣ ‹‹እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን ኃጢአታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኃጢአታችንንም ሁሉ ይቅር አለን፤ ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት (የዕዳ ሰርቲፊኬት) ከነሕግጋቱ በመደምሰስ በመስቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው››[1] የሚል እናነባለን።

ይቅር የተባለልን ዕዳ መክፈል የምንችለው አልነበረም። በደል፣ ኃጢአታችን እጅግ ብዙ ነበር። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር እንዲሁ በነጻ ድነት ሰጠን። ኢየሱስ ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የዕዳ ሰርቲፊኬት ሻረ። ይህ አገልጋይ ከጌታው ጋር በነበረው ግንኙነትና፣ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረን ግንኙነት መካከል ያለውን ተያያዥነት ማየት እንችላለን።

> ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ አንድ መቶ ዲናር የእርሱ ዕዳ ያለበትን አገልጋይ ባልንጀራውን አግኝቶ እንቅ አድርጐ በመያዝ፣ ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ አለው።
>
> - ማቴዎስ 18÷28

አንድ ዲናር የአንድ የጉልበት ሠራተኛ የቀን ደመወዝ ያህል ነው።[2] ስለሆነም አሁን ባለው ደመወዝ አንድ መቶ ዲናር አራት ሺህ ዶላር ያህል ይሆናል ማለት ነው አሁን ማንበባችንን እንቀጥል፤

> ባልንጀራው አገልጋይ ከፊቱ ወድቆ - ታገሠኝ፤ እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነበረ፣ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ ወህኒ አስገባው።
>
> - ማቴዎስ 18÷29-30

እንደ እርሱ አገልጋይ የነበረ ጓደኛው፣ መጠነኛ ገንዘብ ማለት የአንድ ዓመት ደመወዝ አንድ ሦስተኛ ያህል የእርሱ ዕዳ ነበረበት። የደመወዛችሁን አንድ ሦስተኛ ብታጡ ምን ይሰማችኃል? ሆኖም፣ ያ ሰው 4.5 ቢሊዮን ዶላር ዕዳ ተሰርዞለት እንደ ነበር አስታውሱ። ያ ገንዘብ ዕድሜ ልኩን ሠርቶ ማግኘት የማይችለው ነው!

ሌሎች ላይ የምንይዘው በደል እኛ እግዚአብሔር ላይ ከፈጸምነው በደል ጋር ሲነጻጸር፣ 4,000 ዶላርን ከ4.5 ቢሊዮን ዶላር ጋር የማነጻጸር ያህል ይሆናል። ምናልባት አንድ ሰው ከባድ በደል አድርሶብን ይሆናል፤ ሆኖም፣ ያ እግዚአብሔር ላይ ከፈጸምነው በደል ጋር አይወዳደርም።

እናንተ ላይ የደረሰው በደል፣ ማንም ላይ ደርሶ የማያውቅ ይመስላችሁ ይሆናል። ሆኖም፣ ኢየሱስ ላይ የደረሰው በደል ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር መገንዘብ አትችሉም። እርሱ ንጹሕ ነበር፤ እንከን የሌለበት የታረደ በግ ነበር።

ይቅር ማለት የማይችል ሰው፣ እርሱ ራሱ ይቅር የተባለለትን ታላቅ ዕዳ ዘንግቶአል። ኢየሱስ ከዘላለም ሞትና ስቃይ እንዳዳናችሁ ከተገነዘባችሁ፣ እናንተም ሌሎችን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይቅር ትላላችሁ። (ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት ላይ በዚህ ሁኔታ እንዴት መመላለስ እንደምንችል እንነጋገራለን)።

ለዘላለም የእሳት ባሕር ውስጥ ከመጣል የከፋ ነገር የለም። በዚያ ዕረፍት የለም፤ እሳቱ አይጠፋም፤ ትሉ አያንቀላፋም። በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እግዚአብሔር ይቅር እስካለን ጊዜ ድረስ፣ የእኛ መጨረሻ ያ ነበር። ሃሌ ሉያ! ይቅር ማለት ከከበዳችሁ የገሃነምን እውነተኝነትና ከዚያ ያዳናችሁን የእግዚአብሔርን ፍቅር አስቡ።

ለአማኞች የሚሆን ትምህርት

ምሳሌውን ማንበብ እንቀጥል፤

> የሆነውን ነገር ያዩ ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤ ሄደውም ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው ነገሩት። በዚህ ጊዜ ጌታው

> አገልጋዩን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ አንተ ክፉ አገልጋይ፣ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልትምረው አይገባህም ነበርን?
>
> - ማቴዎስ 18÷31-33

በዚህ ምሳሌ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ለማያምኑ ሰዎች አይደለም። ስለ አንድ ንጉሥ አገልጋዮች ነው እየተናገረ ያለው። በጣም ብዙ ዕዳ ይቅር የተባለለት ሰውዬ፣ የጌታው፣ ‹‹አገልጋይ›› ተብሎአል። እርሱ ይቅር ያላለው ሰውየም፣ ‹‹አገልጋይ ባልንጀራው›› ተብሎአል። ስለሆነም ይህ የሚያሳየው ይቅር ማለት የማይፈልግ አማኝን ዕጣ ፈንታ ነው ማለት ነው።

> በቁጣም ያለበትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ፣ ለአሳሪዎች አሳልፎ ሰጠው። ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኃል።
>
> - ማቴዎስ 18÷34-35

እነዚህ ጥቅሶች ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ይዘዋል።

1. ይቅር ያላለው አገልጋይ፣ ለስቃይ ተላልፎ ተሰጠ።
2. የመጀመሪውን ዕዳ፣ ማለት 375 ቶን ወርቅ መክፈል አለበት።
3. የወንድሙን በደል ይቅር በማይል ሰው ላይ፣ እግዚአብሔር አባት ተመሳሳይ ነገር ያደርግበታል።

1. ይቅር ያላለው አገልጋይ ለስቃይ ተላልፎ ተሰጠ።

የዌብስተር መዝገበ ቃላት፣ ስቃይን፣ ‹‹የአካልና የአእምሮ ሕመም›› ወይም፣ ‹‹ለመቅጣት፣ እሺ ለማሰኘት›› ወይም፣ ‹‹በሌላው ስቃይ ለመደሰት ሲባል፣ ሌላው ወገን ላይ የሚፈጸም ከባድ ጉዳት››[3] በማለት ይገልጸዋል።

ይህን ስቃይ የሚያደርሱ አጋንንታዊ መናፍስት ናቸው። አማኞች ብንሆን እንኳ፣ የአካልና የአእምሮ ሕመምና ስቃይ እንዲያደርሱብን እግዚአብሔር፣ ‹‹ለአሰቃዮቹ›› ፈቃድ አሳልፎ

ይሰጠናል። ፈውስን፣ መጽናናትን ወይም ነጻ መውጣትን መቀበል ላቃታቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ በየስብሰባው ጸልዬ አውቃለሁ፤ ይህ የሆነው፣ ሌሎች ሰዎችን መፍታትና ከልባቸው ይቅር ባለ ማለታቸው ነበር።

የሕክምና ዶክተሮችና ሳይንቲስቶች ይቅር አለማለትንና መራራነትን፣ ቁርጥማትና ካንሰርን ከመሳሰሉ በሽታዎች ጋር ያያይዙታል። አብዛኞቹ የአእምሮ በሽታዎች፣ ከመራራ ይቅር ያለ ማለት መንፈስ ጋር ተሳስረዋል።

ብዙ ጊዜ ይቅር የማንለው ሌሎችን ቢሆንም፣ አንዳንዴ ራሳችንንም እንኳ ይቅር ማለት ያቅተናል። ኢየሱስ፣ ‹‹ይቅር ያላልከው ሰው ካለ፣ ይቅር በል...›› ብሎአል (ማቴዎስ 5÷24 ይመ.)። ይህ ደግሞ ራስንም ይጨምራል! እግዚአብሔር ይቅር ብሎህ ከሆነ፣ ታዲያ፣ ሌላው ቀርቶ ራስህን እንኳ ቢሆን፣ እርሱ ይቅር ያለውን ይቅር ላለማለት ለመሆኑ አንተ ማን ነህ?

2. ይቅር የማይል አገልጋይ፣ ያተከፈለውን የመጀመሪያ ዕዳ መክፈል አለበት።

ማድረግ የማይቻለውን እንዲያደርግ ይጠየቃል። ይህ ኢየሱስ መስቀል ላይ የከፈለውን ዕዳ ለመክፈል የመጠየቅ ያህል ነው። እንደዚያ ከተባልን ደግሞ ድነታችንን ማጣታችን ነው።

ምናልባትም፣ ‹‹እስቲ ቆይ፤ አንድ ሰው የንስሐ ጸሎት ካደረግና ሕይወቱን ለኢየሱስ ከሰጠ በፍጹም እንደማይጠፋ ነው የማምነው›› ትለኝ ይሆናል።

የምታምኑት እንደዚያ ከሆነ፣ ታዲያ ጴጥሮስ የሚከተለውን ለምን እንደ ጻፈ እስቲ ንገሩኝ።

> ጌታችንንና አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ በኃላ እንደ ገና ተጠላልፈው ቢሸነፉ፣ ከመጀመሪያው ይልቅ የኃለኛው ሁኔታቸው የከፋ ይሆንባቸዋል። የጽድቅን መንገድ ካወቁ በኃላ ከተሰጣቸው ቅዱስ ትእዛዝ ወደ ኃላ ከሚመለሱ ቀድሞኑ የጽድቅን መንገድ ባላወቁት ይሻላቸው ነበር።
>
> 2 ጴጥሮስ 2÷20-21

ጴጥሮስ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሚገኘው ድነት አማካይነት ከኃጢአት (ከዓለም ርኩሰት) አምልጠው ስለ ነበሩ ሰዎች ነው የሚናገረው። በኃላ ግን፣ እንደ ገና በኃጢአት ተጠላልፈዋል (ምናልባትም ይቅር ያለ ማለት ሊሆን ይችላል) በእርሱም ተሸንፈዋል። ተሸንፈዋል ማለት፣ ወደ ጌታ አልተመለሱም፤ ፈቅደው ባደረጉት ኃጢአት ንስሐ አልገቡም ማለት ነው። ከጽድቅ መንገድ ወደ ኃላ መመለስ ቀድሞውኑ ያንን ካለማወቅ የከፋ እንደ ሆነ ጴጥሮስ ተናግሮአል። በሌላ አነጋገር፣ የዘላለምን ሕይወት ከተቀበለ በኃላ ለዘለቄታው ሳይመለሱ መቅረት ቀድሞውኑ ድነት ካለማግኘት የከፋ እንደ ሆነ እግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ሐዋርያው ይሁዳም እንዲሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለ፣ ‹‹ሁለት ጊዜ የሞቱ›› ሰዎች ይናገራል (ይሁዳ 12-13)። ሁለት ጊዜ መሞት ማለት፣ በአንድ ወቅት ያለ ክርስቶስ የሞታችሁ ነበራችሁ፤ ከዚያም እርሱን በመቀበል ሕያው ሆናችሁ፤ ከዚያ በኃላ ግን ከእርሱ መንገድ ለዘለቄታው ተለያችሁ ማለት ነው።

አያችሁ፣ ብዙዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?›› እያሉ ራሳቸውን ጻድቅ ማድረግ ይሞክራሉ፤ እርሱ ግን፣ ‹‹ከቶ አላወቅኃችሁም፤ እናንተ ክፉዎች ከእኔ ራቁ›› ይላቸዋል (ማቴዎስ 7÷22-23)። አንድ ወቅት ላይ ያውቁት ነበር። ‹‹ጌታ›› ብለውታል፤ በስሙ ታምራት አድርገው ነበር። እርሱ ግን አላወቃቸውም።

ኢየሱስ የማያውቀው ማንን ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው›› በማለት ጽፎአል (1 ቆሮንቶስ 8÷3)። እግዚአብሔር የሚያውቀው እርሱን የሚወዱትን ነው።

ምናልባትም፣ ‹‹እኔም'ኮ እግዚአብሔርን እወዳለሁ፤ የማልወደው ይህን በጣም የበደለኝን ወንድም ነው›› ትሉ ይሆናል። እንደዚያ ከሆነ ተሳስታችኃል፤ እግዚአብሔርን አትወዱም፤ ምክንያቱም፣ ‹‹ማንም እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ እርሱ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን

እግዚአብሔርን መውደድ አይችልምና›› ተብሎ ተጽፎአል (1 ዮሐንስ 4÷20)። መሳት ከባድ ነገር ነው፤ ምክንያቱም የሳተ ሰው ከልቡ ትክክል ነኝ ብሎ ያምናል። እርሱ እየሄደ ያለው በዚያኛው መንገድ ቢሆንም፣ በዚህኛው መንገድ እየሄደ እንደ ሆነ ያምናል። ቃሉን የማያምን ሰው የገዛ ልቡን ያስታል።

‹‹ብዙዎች›› መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡ ቢያምኑም፣ እንዳይገቡ መከልከላቸው፣ ኢየሱስም በመጨረሻ ቀን ብዙዎች እንደሚያሰናክለ መናገሩ ትኩረት የሚያሻው አይደለም? (ማቴዎስ 24÷10)። ሁለቱ ምድቦች ውስጥ ያሉት ተመሳሳይ ዐይነት ሰዎች ይሆኑ ይሆን?

አንዳንድ ሰዎች ይቅር ባለ ማለት ይሰቃያሉ፤ ምናልባትም ሞት እንዲገላግላቸው ተስፋ ያደርጉ ይሆናል። ይህ ግን እውነት አይደለም። ይቅር ያለ ማለትን፣ አሁን መፍትሔ ልንፈልግለት ይገባል፤ አለበለዚያ መክፈል የማይቻለውን እንድንከፍል እንገደዳለን።

3. የደረሰበት ጉዳት ወይም በደል የቱንም ያህል ትልቅ ቢሆንም፣ ከልቡ ይቅር በማይል ማንኛውም አማኝ ላይ እግዚአብሔር አባት ያንኑ ያደርጋል።

ኢየሱስ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ ተናግሮአል፤ ይህን ምሳሌ በትክክል እንድንረዳ አድርጐአል። ደቀ መዛሙርቱ እንዲያብራራላቸው ካልጠየቁት በቀር፣ ኢየሱስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች ለአንዱ እንኳ ማብራሪ አልሰጠም። ይሁን እንጂ፣ ይቅር ማለት በማይፈልጉ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ከባድ ፍርድ በተመለከተ፣ ምንም ጥያቄ እንዲቀርብለት አልፈለገም።

ከሌሎች አያሌ ሁኔታዎች እንደምንመለከተው ይቅር የማንል ከሆነ፣ እኛም ይቅር እንደማንባል ኢየሱስ በጣም ግልጽ አድርጓል። እርሱ እንደ እኛ አለመሆኑን አትርሱ፤ እርሱ ሲናገር የምሩን ነው የሚናገረው።

ይህ ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይገኝም። ይልቁንም ይቅር ላለማለት ሰዎች የተለያዩ ሰበቦች ይሰጣሉ። ይቅር አለማለት

– ከግብረ ሰዶማዊነት፣ ከዝሙት፣ ከስርቆት፣ ከስካርና ከመሳሰሉት ያነሰ ኃጢአት ተደርጐ ይታሰባል። ይሁን እንጂ፣ ይቅር የማይሉ ወገኖች እነዚህ ኃጢአቶችን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አብረው የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

አንዳንድ ሰዎች ይህ በጣም ጨካኝ መልእክት እንደ ሆነ ያስቡ ይሆናል፤ እኔ ግን እንደ ጨካኝ ፍርድ ሳይሆን፣ የምሕረትና የማስጠንቀቂያ መልእክት መሆኑን ነው የማየው። ይልቁንስ አሁኑኑ በመንፈስ ቅዱስ ተነክታችሁ እውነተኛ ንስሐና ይቅር መባልን ብትለማመዱ አይሻልም? ወይስ ይቅር ማለትን እምቢ ብላችሁ፣ ከእንግዲህ ንስሐ ማድረግ በማትችሉበት ሁኔታ ጌታ፣ ‹‹ከእኔ ራቁ›› ሲላችሁ መስማት ትፈልጋላችሁ?

እንደ ገና መጐዳትን በፈቃደኝነት እስከ መቀበል ድረስ እንኳ ቢሆን፣

እኛ ራሳችን ከመበቀል መራቅ አለብን።

የሰይጣን ሽንገላን ለመጻፍ ለእግዚአብሔር በመታዘዝህ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ይህ መጽሐፍ የተቀባ በመሆኑ እያነበብኩ ባለሁበት ጊዜ ሁሉ በጌታ መንፈስ ተነክቼ ነበር፤ መጽሐፉን አንብቤ ለመጨረስ በጣም ጥቂት ቀኖች ብቻ ነበር የወሰደብኝ። ይህ መጽሐፍ ሕይወቴን ፍጹም ለውጦታል። ከመሰናከል ሰንሰለት ተላቅቄአለሁ፤ በቀረው ሕይወት ዘመኔ በሙሉ — ልቤ፣ አእምሮዬና ስሜቴ ነጻ ሆኖ እንዲቀጥል በእኔ በኩል ማንኛውንም ጥንቃቄ አደርጋለሁ።

- ኤል.ኤም. ደቡብ ካሮላይና

በቀል – አደገኛው ወጥመድ

ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት በጐ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ፡፡

- ሮሜ 12÷17

ከለፈው ምዕራፍ በግልጽ እንደ ተመለከትነው ይቅር ያለ ማለትን በደል መያዝ፣ ሌላው ሰው ላይ ዕዳ የማኖር ያህል ነው፡፡ አንድ ሰው በሌላው ሰው ከተበደለ፣ በዳዩ የእርሱ ባለ ዕዳ እንደ ሆነ ያስባል፡፡ በግንዘብም ይሁን በሌላ፣ አንድ ዐይነት ክፍያ እንዲደረግለት ይጠብቃል፡፡

ፍርድ ቤቶቻችን የተቋቋሙት የበደለ ወይም ጥፋት የፈጸመ ወገኖችን ለመበቀል ነው፡፡ ክስ መመሥረት ዕዳ እንዲከፈላቸው ሰዎች ያላቸውን ፍላጐት ለማርካት መሞከር ነው፡፡ አንድ ሰው በሌላው ሰው ጉዳት ከደረሰበት ሰው ሠራሽ ፍትሕ፣ ‹‹በዳዩ ሰው ለፍርድ መቅረብ አለበት፤ በደል ማድረሱ ከተረጋገጠም ዋጋ መክፈል አለበት›› ይላል፡፡ ይቅር ማለት ያልፈለገው አገልጋይ፣ እንደ እርሱ አገልጋይ የሆነው ባልንጀራው ያለበትን ዕዳ እንዲከፍለው ፈለገ፤ ያንን ክፍያ እንዲያስፈጽምለት ፍርድ ቤትን ጠየቀ፡፡ ይህ ግን የጽድቅ መንገድ አይደለም፡፡

> ወዳጆቼ ሆይ፣ ለእግዚአብሔር ቁጣ ፈንታ ስጡ እንጂ፣ አትበቀሉ፤ ‹‹በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ›› ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአል፡፡
>
> - ሮሜ 12÷19

የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን እኛ፣ ራሳችን መበቀል ጽድቅ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ሳንሆን በቀረን ጊዜ ሁሉ፣ ያንኑ እያደረግን ነው። በቀልን እናስባለን፣ እናቅዳለን፤ እናውጠነጥናለን፤ በመጨረሻም ተግባር ላይ እናውለዋለን። ዕዳው በሙሉ እስካልተከፈለ ድረስ ይቅር ማለት አንፈልግም፤ የካሣው መጠን ምን ያህል መሆን እንዳለበት የምንወስን እኛ ብቻ ነን። እኛ ላይ የደረሰውን በደል ለማስተካከል ራሳችን የፈራጅነቱን ቦታ እንይዛለን። ይሁን እንጂ፣

> ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ሊያድንና ሊያጠፋ የሚችል ነው፤ ነገር ግን በባልንጀራህ ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? ወንድሞች ሆይ፣ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤ ያለዚያ ይፈረድባችኃል፤ እነሆ ፈራጁ በበር ላይ ቆሞአል።
>
> - ያዕቆብ 4÷12÷5÷9

እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው፤ እርሱ ጻድቅ ፍርድ ይፈርዳል። ሆኖም፣ እርሱ ለሰው እንደ ሥራው የሚከፍለው በጽድቅ ነው። አንድ ሰው በፈጸመው በደል በእውነት ንስሐ ካደረገ፣ ኢየሱስ መስቀል ላይ ከፈጸመው ሥራ የተነሣ ዕዳው ይሰረዝለታል።

ምናልባት፣ ‹‹የተበደልኩ እኔ እንጂ፣ ኢየሱስ አይደለም!›› ትሉኝ ይሆናል። እናንተ ግን እርሱ ላይ የፈፀማችሁትን በደል አልተገነዘባችሁም። ሰው ሁሉ ኃጢአት ቢያደርግም፣ እርሱ ምንም በደል የሌለበት ንጹሕ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን ለሞት ተላልፎ ተሰጠ። እያንዳንዳችን ከምድራዊው ሕግ እጅግ ከፍ ያለውን፣ የእግዚአብሔር ሕግ ተላልፈናል። እንግዲህ ፍትሕ መደረግ ካለበት፣ ሁላችንም በአጽናፈ ዓለሙ ሁሉ እጅግ ከፍተኛ በሆነው ዳኛ፣ ሞት ሊፈረድብን ይገባ ነበር።

በሌላው ሰው ግፍ የተፈጸመባችሁ፣ እናንተ ምንም በደል ሳታደርጉ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣ እናንተ ላይ የደረሰውን በደል፣ ራሳችሁ ይቅር ከተባላችሁት ጋር ብታነጻጽሩት በፍጹም እንደማይመጣጠን ትረዳላችሁ። እናንተ ካላባችሁ ዕዳ ጥቂት ቅናሽ እንኳ አያመጣም! ምናልባት እንደ ተታለላችሁ ተሰምቷችሁ ከሆነ፣ የተደረገላችሁን ምሕረት ብዛት አልተረዳችሁትም ማለት ነው።

ለበቀል ቦታ የለም

በአሮጌው ኪዳን መሠረት እኔ ላይ በደል ካደረሳችሁ፣ ያንኑ እናንተ ላይ እንዳደርግ ሕጉ ድጋፍ ይሰጠኝ ነበር። ማንኛውንም ዕዳ በወቅቱ መቀበል፣ ክፉን በክፉ መመለስ ይፈቀድ ነበር (ዘሌዋውያን 24÷19፤ ዘፀአት 21÷23-25 ይመ.)። ሕጉ የማይገሥሥ ሥልጣን ነበረው፤ በዚያ ዘመን እነርሱን ነጻ ለማውጣት ኢየሱስ ገና አልሞተም ነበር።

የአዲሱ ኪዳን አማኞችን በተመለከተ ግን የተነገረውን ተመልከቱ።

> ‹‹ዐይን ስለ ዐይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኃል። እኔ ግን እላችኃለሁ፤ ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወሙት፤ ነገር ግን ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ አዙርለት። አንድ ሰው እጀ ጠባብህን ሊወስድ ቢከስህ፣ ካባህን ጨምረህ ስጠው። አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል የሚያህል ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድድህ፣ ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ። ለሚለምንህ ስጥ፤ ከአንተም ሊበደር የሚሻውን ፊት አትንሣው።

- ማቴዎስ 5÷38-42

ኢየሱስ ለበቀል ምንም ቦታ አልሰጠም። እንዲያውም፣ ሌላ በደል ሊደርስብን ቢችል እንኳ፣ ያንን ለመቀበል ፈቃደኛ እስከ መሆን ድረስ፣ ዝንባሌያችን እኛ ራሳችን ከመበቀል መታቀብ እንዳለብን ነው የተናገረው።

የደረሰብንን በደል በዐይነት ለመመለስ በፈለግን ጊዜ ሁሉ፣ ራሳችንን ዳኝነት ወንበር ላይ ማስቀመጣችን ነው። ማቴዎስ 18 ላይ የተመለከትነው ይቅር ማለት ያልፈለገው አገልጋይ፣ እንደ እርሱ አገልጋይ የነበረ ባልንጀራውን እስር ቤት ሲያስገባው ይህን ማድረጉ ነበር። በምላሹ ይህ ይቅር ማለት ያልፈለገ አገልጋይ፣ ለማያሰቃዩት ተላልፎ ተሰጠ፤ ዕዳውን በሙሉ ለመክፈል ቤተ ሰቡ መሸጥ ነበረባቸው።

እኛ ግን ጻድቅ ለሆነው ዳኛ ቦታና ዕድል መስጠት አለብን። እርሱ በጽድቅ ዋጋ ይከፍላል። በጽድቅ የሚበቀል እርሱ ብቻ ነው።

አንድ ጊዜ መሰናክልን በተመለከተ ቴምፓ ፍሎሪዳ ባለ አንድ ቤተ ክርስቲያን እያግለገልኩ እያለ አንዲት ሴት ወደ እኔ መጥታ፣ የቀድሞ ባሏ ያደረሰባትን በደል ሁሉ ይቅር ብላው እንደ ነበር ነገረችኝ። ሆኖም፣ የበደልን እስራት ስለ መፍታት እያደረግሁ የነበረውን ንግግር ከሰማች በኃላ አሁንም ቢሆን፣ ውስጧ ሰላም እንደሌላትና ጥሩ ያልሆነ ስሜት እንደሚሰማት ተረዳች።

‹‹አሁንም ቢሆን፣ ገና ይቅር አላልሽውም›› አልኳት በጨዋነት።

‹‹እንዴ፣ ይቅር ብየዋለሁ እንጂ›› አለች ኮስተር ብላ፣ ‹‹እንዲያውም እያለቀስኩ ነው ይቅር ያልኩት።››

‹‹አልቅሰሽ ሊሆን ይችላል፤ ግን ከበደል እስራት አልፈታሽውም።››

እኔ እንደ ተሳሳትኩና እርሷ ግን ይቅር እንዳለችው አጥብቃ ተከራከረች።

‹‹ከእርሱ ምንም አልፈልግም፤ ከበደል እስራትም ፈትቼዋለሁ።››

‹‹እስቲ፣ አንቺ ላይ ያደረገው ምን እንደ ነበር ንገሪኝ›› በማለት ጠየቅሁ።

‹‹እኔና ባሌ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ፓስተሮች ነበርን። እኔና ሦስት ወንዶች ልጆቻችንን ትቶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበረች አንዲት ታዋቂ ሴት ጋር ተወዳጀ።›› ይህን ስትነግረኝ ዐይኖቿ እንባ አቅርረው ነበር።

‹‹እኔን በማግባቱ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ወጣና አሁን የተወዳጃትን ሴት ማግባቱ ግን ትክክለኛ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ነገረኝ። ከእኔ የበለጠ በጣም ተባባሪው በመሆንዋ እርሷ ለአገልግሎቱ ታላቅ ቅርስ እንደ ሆነችና እኔ ግን ዕንቅፋት እንደ ሆንኩበት ነገረኝ። ነቃፊና ተቺ መሆኔን ነገረኝ። ለትዳራችን መፍረስ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂዋ እኔ እንደ ሆንኩ ነገረኝ። ከዚያ

በኃላ ተመልሶ አልመጣም፤ አንድ በደል እንኳ ማድረሱንም አልተቀበለም፡፡››

ይህ ሰው ከባድ ስሕተት መፈጸሙና ሚስትና ልጆቹን በጣም መጉዳቱ ግልጽ ነው፡፡ በፈጸመው በደል በጣም ተጐድታለች፤ ለበደሉ ተመጣጣኝ ክፍያ፣ እንዲያደርግ እየጠበቀች ነበር፡፡ ከእርሱ እየጠበቀች የነበረው የፍቺ ገንዘብ ወይም ለልጆቿ ማሳደጊያ እንዲሰጣት አልነበረም፤ አዲሱ ባሏ ይህን ሁሉ እያደረገላት ነበር፡፡ እንዲከፍላት የምትጠብቀው ክፍያ፣ እርሱ በደል መፈጸሙንና እርሷ ግን ትክክል እንደ ነበረች እንዲያምን ብቻ ነበር፡፡

‹‹ወደ አንቺ መጥቶ በደል ማድረሱንና ጥፋቱ የእርሱ እንጂ፣ የአንቺ አለመሆኑን ካልተናገረ፣ ከዚያም ይቅር እንድትዪው ካልጠየቀ ይቅር ልትዪው አልፈለግሽም፡፡ ያለበትን ዕዳ እንዲከፍልሽ እየጠበቅሽ ነው፡፡ እስረኛ ያደረገሽ ይህ ያልተከፈለሽ ዕዳ ነው፡፡›› በማለት እውነቱን ነገርኳት፡፡

ወደ እርሱ መጥተን፣ ‹‹እኛ ተሳስተናል፤ አንተ ግን ትክክል ነህ፤ ስለዚህ ይቅርታ አድርግልን›› በማለት እስክንጠይቀው ድረስ ኢየሱስ ቢጠብቅ ኖሮ፣ መስቀል ላይ የሞተ ጊዜ ይቅር አይለንም ነበር፡፡ መስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ፣ ‹‹አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› በማለት ፈጽሽ (ሉቃስ 23÷34)፡፡ ወደ እርሱ መጥተን እርሱን እንደ በደልን ከመናዘዛችን በፊት ነበር እርሱ ይቅር ያለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም፣ ‹‹ጌታ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ሌላውን ይቅር በሉ›› (ቈላስይስ 3÷13)፣ እንደ ገና፣ ‹‹እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ›› በማለት ይመክረናል (ኤፌሶን 4÷32)

‹‹ታዲያ፣ እኔ በድያለሁ፤ አንቺ ግን ትክክል ነሽ? ካላለ በቀር ይቅር አትዪውም ማለት ነው?›› ስላት እንባዋ መፍሰስ ጀመረ፡፡ እርሷና ልጆቿ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር ሲነጻጸር፣ እርሷ የምትፈልገው ግምት ውስጥ የማይገባ መሰላት፡፡ ሆኖም፣ የሰው ልጅ ፍትሕ ሥርዓት ቀንበር ተጭኖአት ነበር፡፡ ዕዳውን የመቀበል መብት እንዳላትና ያ፣ እስኪ ከፈላት እየጠበቀች ስለ ነበር፣ ራስዋን

ዳኛ አድርጋለች። ይህ መሰናክል በእርሷና በአዲሱ ባሏ መካከልም ዕንቅፋት ሆኖ ነበር። የቀድሞ ባልዋ ለእርሷ ፖስተርዋም ጭምር ስለ ነበር፣ ሥልጣን ካላቸው ወንዶች ሁሉ ጋር የነበራትን ቀረቤታ አውኮት ነበር።

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ልባችንን ከአፈር ጋር አመሳስሎታል። በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እንድንተክልና እንድንመሠረትም ተመክረናል። ያኔ የእግዚአብሔር ቃል ዘር ልባችን ውስጥ ያድጋል፤ ውሎ አድሮም የጽድቅ ፍሬ ያፈራል። ይህ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው (ገላትያ 5÷22-23 ይመ.)።

ማንኛውም አፈር ወይም መሬት የሚያበቅለው የተዘራበትን ወይም የተተከለበትን ብቻ ነው። የባለ ዕዳነትን፣ ይቅር ያለ ማለትንና የበደልን ዘር ከዘራን ከእግዚአብሔር ፍቅር የተለየ ሌላ ሥር ብቅ ይላል። ይህም የመራራነት ሥር ይባላል።

መራራነትን አስመልክቶ ፍራንሲስ ፍራንጂፓን አንድ በጣም ጥሩ ገለጻ ሰጥቷል። ‹‹መራራነት፣ የሚፈልገውን ያላገኘ በቀል ነው›› [1] ነበር ያለው። በቀል የሚፈልገውን ነገር ካላገኘ መራርነት ይፈጠራል።

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ይህን አስመልክቶ በግልጽ ተናግሮአል።

> ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን አድርጉ፤ ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም፤ ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል ተጠንቀቁ።
>
> - ዕብራውያን 12÷14-15

‹‹ብዙዎችን እንዳይበክል›› የሚለውን ሐረግ ልብ አድርጉ። ‹‹ብዙዎች›› የሚለው በመጨረሻው ቀን እንደሚሰናከሉ ኢየሱስ የተናገረላቸው ይሆኑ ይሆን? በማለት በድጋሚ እጠይቃለሁ (ማቴዎስ 24÷10 ይመ.)።

መራራነት አንድ ዐይነት ሥር ነው። ከተንከባከቡዋቸው፣ ውሃ ካጠጡዋቸው - ከጠበቁዋቸው፣ ከመግቡዋቸውና ትኩረት ከሰጧቸው ሥሮች ጥልቀትና ጥንካሬያቸውም እንደዚያው ያድጋል። ወዲያውኑ ካልተነቀሉ – ሥሮች ለመንቀል በጣም ከባድ ይሆናሉ። የበደል ወይም የመሰናከል ጥንካሬና ብርታት ማደግ ይቀጥላል። በቁጣችን ላይ ፀሐይ መግባት እንደሌለበት የተመከርነው በዚህ ምክንያት ነው። (ኤፌሶን 4÷26 ይመ.)። እንደዚያ ካልሆነ የጽድቅ ፍሬ ሳይሆን የቁጣ፣ የቅርታ፣ የቅንዓት፣ የጥላቻ፣ የመከፋፈልና የፀብ ፍሬ ይፈራል። እነዚህን ኢየሱስ መጥፎ ፍሬ ብሏቸዋል። (ማቴዎስ 7÷19-20 ይመ.)።

የበደል እስራትን በመፍታት ሰላም የማይፈጥር፣ ሰላምን የማይከታተል ሰው የኃላ ኃላ እንደሚረክስ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይቅር ካለ ማለት ዐመፅ የተነሣ ክቡርና ውድ የነበረው ይበላሻል።

ንጉሥ ሊሆን የታሰበው ረከሰ

ምንም እንኳ ሳኦል ለዳዊት ታማኝ ባይሆንም፣ ዳዊት ግን ለሳኦል ታማኝ ሆኖ እንደ ኖረ ቀደም ሲል ከዚህ መጽሐፍ ተመልክተን ነበር። ከአንዴም ሁለቴ አጋጣሚውን ቢያገኝም እንኳ ዳዊት መበቀል አልፈለገም። ዳዊት እንደ የእግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው ነበር። በእርሱና በሳኦል መካከል እግዚአብሔር እንዲፈርድ ነገሩን ሁሉ ለእርሱ ተወ። የእግዚአብሔር ፍርድ ሳኦል ላይ በመጣ ጊዜ፣ ዳዊት በደስታ አልፈነደቀም። በእርሱ ላይ ሥር የሰደደ ምሬት ስላልነበረው ሳኦል ላይ በደረሰው መጥፎ ነገር በጣም አዘነ።

ከሳኦል ሞት በኃላ ዳዊት ንጉሥ ሆነ። መንግሥቱን አበረታ፣ የጦር ኃይሉንና የኢኮኖሚ ዐቅሙን አጠነከረ፤ ዙፋኑን አደላደለ። ብዙ ሚስቶች አገባ፤ እነርሱም የመጀመሪያ ልጁ አምኖንን፣ ሦስተኛ ልጁ አቤሴሎምን ጨምሮ ብዙ ልጆች ወለዱለት።

የዳዊት ልጅ አምኖን ከፊል እኅቱ በነበረችውና ለአቤሴሎም ግን ሙሉ እኅቱ በነበረችው ትዕማር ላይ ፀያፍ ተግባር ፈጸመ።

በጣም የታመመ በመምሰል መጥታ ምግብ እንድታዘጋጅለት ትዕማርን እንዲልክላት አባቱን ጠየቀ። ወደ እርሱ ስትመጣ ሌሎች አገልጋዮች ከክፍሉ እንዲወጡ በማድረግ ደፈራት። ከዚያም በጣም ጠላት፤ ከፊቱ ዘወር እንድትልም አባረራት። ድንግል የነበረችውን ንግሥት አዋረደ፤ የወደ ፊት ሕይወቷን ተሳቅቃ እንድትኖር አደረገ። (2 ሳሙኤል 13 ይመ.)።

ከፊል ወንድሙ ለነበረው ለአምኖን አንድ ቃል እንኳ ሳይናገር፣ አቤሴሎም እኅቱን ወደ ቤቱ አምጥቶ የሚያስፈልጋትን አደረገላት። ሆኖም፣ ትዕማር ላይ ባደረገው አምኖንን በጣም ጠላው።

አቤሴሎም ከፊል ወንድሙ የሆነውን አምኖንን አባቱ ይቀጣዋል ብሎ ጠብቆ ነበር። የአምኖንን ወንጀል ንጉሡ ሲሰማ በጣም ተቆጣ፤ ሆኖም ምንም ርምጃ አልወሰደም። አቤሴሎም በአባቱ ፍትሕ አለማድረግ በጣም ተናደደ።

በአንድ ወቅት ትዕማር የንጉሡ ደናግል ልጆች የሚለብሱትን ልብሰ መንግሥት ትለብስ ነበር፤ አሁን ግን ልብሷ ዕፍረት ሆነ። በጣም ውብ ድንግል ስለ ነበረች ሰዎች ለእርሷ ላቅ ያለ አመለካከት ነበራቸው። አሁን ተገልላ ትኖር ጀመር፤ ከእንግዲህ፣ ድንግል ባለ መሆንዋም ማንም አያገባትም።

የተደረገው በጣም አሳዛኝ ነበር። ንጉሡ ባዘዛት መሠረት ለአምኖን ጥሩ ነገር አድርጋለት ነበር፤ እርሱ ግን ደፈራት። ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ምንም ያላደረገ ይመስል ተንደላቅቆ ሲኖር፣ የእርሷ ሕይወት ግን ተመሰቃቀለ። ከእንግዲህ ዕድሜ ዘመንዋን በሙሉ በዕፍረትና በውርደት ማሳለፍ ሊኖርባት ነው።

አቤሴሎም በሀዘን የተሸማቀቀች እኅቱን በየቀኑ ይመለከት ነበር። ከእንግዲህ የእርሷ እንደ ልዕልት መኖር ቅዠት ሆኖአል። አባቱ አንድ ነገር አስኪያደርግ በመጠበቅ፣ አቤሴሎም አንድ ዓመት ቆየ፤ ዳዊት ግን ምንም አላደረገም። አቤሴሎም በአባቱ ተከፋ (ተሰናከለ)፤ ለበደለኛው አምኖን የነበረው ጥላቻም እየበረታ ሄደ።

ከሁለት ዓመት በኃላ ጥላቻው፣ አምኖንን የመግደል ሤራ ወለደ። ምናልባትም አቤሴሎም፣ ተገቢው ባለ ሥልጣን ምንም ባለማድረጉ፣ እኔ ራሴ ለእንቴ እበቀልላታለሁ በማለት ሳያስብ አልቀረም።

ግብጣ አዘጋጅቶ የንጉሡን ልጆች ሁሉ ጠራ። አምኖን ምንም ባልጠረጠረበት ሁኔታ አቤሴሎም ገደለው። አቤሴሎም ወደ ጌሹር ሸሸ፤ አምኖን ላይ የነበረው የበቀል ጥማት አበቃ። ግን፣ በተለይ ከቤተ መንግሥት ርቆ በነበረ ጊዜ፣ አባቱ ላይ የነበረው ቅርታ ይበልጥ መንደድ ጀመረ።

የአቤሴሎም ሐሳብ በምሬት የተመረዘ ነበር። የዳዊትን ደካማነት በመንቀፍ ረገድ የተዋጣለት ተቃዋሚ ሆነ። ያም ሆኖ ግን፣ አንድ ቀን አባቱ እንደሚያስጠራው ጠብቆ ነበር። ዳዊት ግን እንደዚያ አላደረገም። ይህ ደግሞ የአቤሴሎምን ቅርታ የበለጠ አቀጣጠለው።

ምናልባትም እንዲህ በማለት ሳያስብ አልቀረም፤ *አባቴን ብዙ ሰዎች ያደንቁታል፤ እውነተኛ ማንነቱን ግን በሚገባ አላዩም። እግዚአብሔርን ሸፍን በማድረግ የራሱን ጥቅም የሚያሳድድ ሰው ነው። እርሱ'ኮ ከንጉሥ ሳኦል የባሰ ሰው ነው። የአማሌቃውያንን ንጉሥ ባለ መግደሉና ምርጥ ከሆኑ በጐቻቸውና በሬዎቻቸው ጥቂቶቹን ለራሱ በማስቀረቱ፣ ሳኦል ዙፋኑን አጣ። አባቴ ግን ለእርሱ በጣም ታማኝ የነበረውን ሰው በማስገደል ኃጢአቱን ሸፍኖአል። አምኖንን ያልቀጣው እርሱ ራሱ ነፍሰ ገዳና ዘማዊ ስለ ነበር ነው! ይህን ሁሉ ደግሞ እግዚአብሔርን አመልካለሁ በሚል አስመሳይነት ሸፍኖታል።*

አቤሴሎም በጌሹር ሦስት ዓመት ቆዬ። ዳዊት ከአምኖን ሞት ተጽናንቶ ነበር፤ አቤሴሎም ወደ አገሩ እንዲመለስ ኢዮአብ ንጉሡን አሳመነ። ያም ሆኖ ግን፣ አሁንም ቢሆን ዳዊት አቤሴሎምን ፊት ለፊት ለማግኘት አልፈለገም። በዚህ ሁኔታ ሁለት ተጨማሪ ዓመት አለፈ፤ በመጨረሻ ዳዊት አቤሴሎምን ወደ ቀድሞ ሙሉ መብቱ መለሰው። ይሁን እንጂ፣ አቤሴሎም ልብ ውስጥ የነበረው ጥላቻ አሁንም እንዳለ ነበር።

አቤሴሎም የተዋጣለት አስመሳይ ነበር። አምኖንን ከመግደሉ በፊት፣ ‹‹አቤሴሎም አምኖንን ክፉም ሆነ ደግ አንዳች ቃል አልተናገረውም፤ ምክንያቱም አምኖን እኅቱ ትዕማርን ስላስነወራት ጠልቶት ነበር›› (2 ሳሙኤል 13÷22)። እንደ አቤሴሎም ሁሉ ብዙ ሰዎች ጥላቻቸውና መከፋታቸውን ደብቀው ይይዛሉ።

በአባቱ ላይ ከነበረው ቂምና ጥላቻ የተነሣ፣ በዳዊት አስተዳደር ቅር የተሰኙ ሰዎችን መሰብሰብ ጀመረ። ማንኛውም እስራኤላዊ እርሱን እንዲያገኘውና ቅር የተሰኘበትን እንዲነግረው ምቹ ሁኔታ ፈጠረ። በሰማው ነገር ማዘኑን እየገለጠ እርሱ ንጉሥ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሮች አሁን ባሉበት መልኩ መጥፎ አይሆኑ እንደ ነበር ይናገር ነበር። ንጉሡ ለእነርሱ የሚሆን ጊዜ ስላልነበረው የአንዳንዶቹን ጉዳይ አቤሴሎም እርሱ ራሱ ይወስን ነበር። አቤሴሎም ጉዳያቸውን ያይላቸው የነበረው፣ እርሱ ራሱ የጠበቀውን ፍትሕ ባለ ማግኘቱ ሊሆን ይችላል።

ለሕዝቡ በጣም የሚያስብና የሚቆረቆር መስሎ ታየ። መጽሐፍ ቅዱስ አቤሴሎም ከአባቱ ከዳዊት የእስራኤልን ልብ እንደ ሰረቀ ይናገራል። ግን፣ ከልቡ እያሰበላቸው ነበር ወይስ፣ ቅር የተሰኘበት ዳዊትን ከዙፋኑ ለመጣል ምቹ አጋጣሚ እየጠበቀ ነበር?

የተዋጣለት ስሕተት ለቃሚ

አቤሴሎም የእስራኤልን ልብ ወደ ራሱ ሳበ፤ ዳዊትም ላይ ተነሣ። ንጉሥ ዳዊት ሕይወቱን ለማዳን ከኢየሩሳሌም መሸሽ ነበረበት። አቤሴሎም የራሱን መንግሥት ያቋቋመ መስሎ ታይቶ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እርሱ ላይ ክፉ ነገር እንዳያደርሱበት ዳዊት አዝዞ የነበረ ቢሆንም፣ ዳዊትን በማሳደድ ላይ እያለ አቤሴሎም ተገደለ።

አቤሴሎምን የገደለው የገዛ ራሱ ጥላቻና መራራነት ነበር ማለት ይቻላል። ብዙ መሥራት ይችል የነበረና የዙፋኑ ወራሽ እንደሚሆን ታስቦ የነበረ ሰው አባቱ ላይ አለኝ የሚለውን ዕዳ

መፍታት ባለ መፈለጉ በወጣትነት ዕድሜው ተቀጨ። ውስጡ በነበረው ምሬትና ጥላቻ ረከሰ።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎችን የሚረዱ ሰዎች ብዙ ጊዜ በሚያገለግሉዋቸው ሰዎች ይሰናከላሉ። ብዙም ሳይቆዩ ነቃፊዎች፣ ተቺዎችና በመሪዎቹ ወይም እነርሱ በሾሟቸው ሰዎች ላይ የሚያዩትን ስሕተት መለቃቀምን ሥራዬ ብለው ይይዙታል። ይሰናከላሉ። አመለካከታቸው ይዛባል። እግዚአብሔር ነገሮችን በሚያይበት ሳይሆን፣ ፍጹም በተለየ ሁኔታ ነገሮችን ያያሉ።

የሕይወታቸው ተልዕኮ፣ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን እነርሱ መልካም መሪ አይደለም ከሚሉት ሰው ማዳን እንደ ሆነ ያምናሉ። የተገዱትን፣ ቅር የተሰኙትንና ማስተዋል የሌላቸው ሰዎችን ልብ ያሸፍታሉ፤ እነርሱ ራሳቸው እንኳ ሳያውቁት መጨረሻ ላይ፣ ቤተ ክርስቲያንን ወይም የአገልግሎት ተቋምን ይከፋፍላሉ ወይም ይለያያሉ። ልክ እንደ አቤሴሎም ማለት ነው።

አንዳንዴ፣ ምልከታቸው ትክክል ሊሆን ይችላል። አዎን፣ ዳዊት አምኖን ላይ ርምጃ መውሰድ ነበረበት። አዎን፣ መሪው የተሳሳተባቸው ገጽታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ታዲያ ዳኛው ማን መሆን ነው ያለበት - እነርሱ ወይስ እግዚአብሔር? መለያየትና መከፋፈልን የምትዘሩ ከሆነ፣ ያንኑ እንደምታጭዱ ልብ አድርጉ።

አቤሴሎም ላይ የደረሰውና በዘመናችን ባሉ አገልግሎቶች ላይ እየሆነ ያለው ጊዜ የሚጠይቅ ሂደት ነው። ብዙ ጊዜ ልባችን ውስጥ ቅርታ፣ መራራነት ወይም መሰናክል መግባቱን እንኳ ላናውቀው እንችላለን። በማደግ ላይ እያለ የመራራነት ሥር የሚታወቀው በጣም አልፎ አልፎ ነው። በኃላ ግን ሙሉ ዕድገት ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ በብዛትም ሆነ በጥንካሬ ይበረታል። የዕብራውያን ጸሐፊ እንደሚመክረን፣ ‹‹መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል - መጠንቀቅ አለብን›› (ዕብራውያን 12÷15)።

ልባችንን መመርመርና ለእግዚአብሔር እርምት ሕይወታችንን መክፈት አለብን - ምክንያቱም የልባችንን ሐሳብና

ዝንባሌ መለየት የሚችል የእርሱ ቃል ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለሰው ልብ በመናገር ይወቅሳል፤ በደልን ያሳያል። የእርሱን ወቀሳ ችላ በማለት፣ እርሱን ማሳዘን የለብንም። እንዲህ ካደረግን በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ እንግባ፤ ለእርሱ እርምት ልባችንን እንክፈት።

አንድ ጊዜ አንድ አገልጋይ ቀደም ሲል አድርጐ የነበረውን ነገር አስመልክቶ፣ ተግባሩ ከአቤሴሎም ወይም ከዳዊት ማንኛውን እንደሚመስል ጠይቆኝ ነበር። ይህ ሰው ከተማው ውስጥ ለነበረ አንድ ፓስተር ረዳት ሆኖ ይሠራ ነበር፤ በኃላ ግን ፓስተሩ ከሥራው ያባረረዋል። የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር፤ ዋናው ፓስተር ይህን ወጣት ይመቀኘውና ይፈራው ነበር።

ከአንድ ዓመት በኃላ ያ የተባረረ አገልጋይ በዚያው ከተማ ሌላ ሰፊር ቤተ ክርስቲያን እንዲመሠርት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያምናል። ያንንም ያደርጋል፤ ትቶት ከመጣው ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ሰዎች መጥተው ከእርሱ ጋር ሆኑ። አቤሴሎም እንዳደረገው እርሱም እንዳያደርግ ይፈልግ ስለ ነበር በነገሩ ስጋት ገብቶት ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ሰው በቀድሞ ፓስተሩ ላይ ጥላቻ ወይም ምሬት አልነበረበትም። አዲሱን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተው፣ የቀድሞውን ቤተ ክርስቲያንን ለመጋፋት አልነበረም እንደዚያ እንዲያደርግ ከእግዚአብሔር ምሪት በመቀበሉ ብቻ ነበር።

በአቤሴሎምና በዳዊት መካከል የነበረውን ልዩነት አሳየሁት። መሪው የነበረው ሰው ላይ ካደረበት ጥላቻ የተነሣ አቤሴሎም የሌሎችን ልብ አሸፈተ። ምንም እንኳ ሳኦል እርሱን እያሳደደው ቢሆንም፣ ለሳኦል ታማኝ እንዲሆኑለት ዳዊት ሌሎችን ሲመክር ነበር። አቤሴሎም ሰዎችን ለራሱ ወሰደ፤ ዳዊት በነበሩበት ተዋቸው። ‹‹ታዲያ፣ አንተ ሰዎቹን ባለህበት ቦታ ትተህ ነው የሄድከው አይደል?›› በማለት ጠየቅሁት። ‹‹ወይስ፣ ወደ አንተ እንዲመጡና ከአንተ ጋር እንዲሆኑ አባብለሃቸዋል?።›› ‹‹ብቻዬን እንጂ ማንንም ይዤ አልወጣሁም፣ ማንንም አላባበልሁም›› አለ።

‹‹መልካም፤ እንግዲያው ያደረግኸው ዳዊት ያደረገውን ነው፡፡ አብረውህ ያሉት ሰዎች በቀድሞ ፓስተራቸው ጥላቻ እንዳያድርባቸው እርግጠኛ ሁን፤ ምናልባት ጥላቻ አድሮባቸው ቢሆን እንኳ፣ ወደ ነጻነትና ወደ ፈውስ ምራቸው፡፡››

በአሁኑ ጊዜ የዚያ ሰው ቤተ ክርስቲያን በጣም እያደገ ነው፡፡ ያንን ወዳጄን በጣም ያደነቅሁት ልቡን ለመመርመር ባለ መፍራቱ ነው፡፡ ያም፣ ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች መንፈሳዊ ሰዎች ምክር በመጠየቁ ነው፡፡ ‹‹ትክክለኛነቱ›› እንዲረጋገጥለት ከማድረግ ይልቅ፣ ለእግዚአብሔር መንገድ መገዛት ለእርሱ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡

ልባችሁ ውስጥ ያለውን ቂም ወይም መራራነት መንፈስ ቅዱስ እንዲያሳያችሁ ለመጠየቅ አትፍሩ፡፡ የበለጠ በደበቃችሁት መጠን፣ ልባችሁ የበለጠ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ ልባችሁ ልክ እንደ መልካም ዐፈር የለሰለሰ ይሁን፡፡ እንዴት?

> መራራነትን ሁለ፣ ቁጣንና ንዴትን፣ ጭቅጭቅንና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁለ፡፡
>
> - ኤፌሶን 4÷31-32

ሥልጠና ካልወሰዳችሁባቸው በደሎች እንኳ ቢሆን፣

ከሚደርሱባችሁ እጅግ ከባድ በደሎች

በሚገጥማችሁ ተግዳሮት የበለጠ ታድጋላችሁ።

የሰይጣን ሽንገላ የተሰኘውን መጽሐፍ አገኘሁ! መጽሐፉ እጅግ በጣም ነው የባረከኝ። እንዲያነቡትም ለብዙዎች ተናግሬአለሁ። በሕይወቴ በእርግጥ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። በጣም አመሰግናለሁ!

- ኤስ ቲ ጆርጂያ

13

ከወጥመዱ ማምለጥ

ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ።

- ሐዋርያት ሥራ 24÷16

ከበደል ወይም ከመሰናክል ነጻ ሆኖ መኖር ጥረት ይጠይቃል። ጳውሎስ ከልምምድ ጋር ያመሳስዋል። ሰውነታችንን ካለማመድነው ለጉዳት የመጋለጥ ዕድሉ በጣም ያንሳል። ሐዋይ በነበርኩ ጊዜ ፎቶግራፍ ለማንሣት አንድ ግንብ ላይ ወጥቼ እያለሁ፣ የጉልበቴ ጡንቻ በመወጣጠሩ ለአራት ቀን ያህል መራመድ አልቻልኩም ነበር።

‹‹ዘወትር ልምምድ ብታደርግ ኖሮ፣ ይህ ችግር አይደርስብህም ነበር። ልምምድ ባለ ማድረግህ ጡንቻዎችህ ተኮማትረዋል፤ አንተም በቀላሉ ለጉዳት የምትጋለጥ ሆነሃል›› በማለት የነገረኝ ፊዚዮ ቴራፒስቱ ነበር።

ጉልበቴ ድኖ መራመድ ከቻልኩ በኃላ አንድ ሌላ ባለ ሙያ፣ ‹‹የጉልበትህን ጡንቻዎች ወደ መደበኛ ቦታቸው ለመመለስ፣ ይህን ልምምድ ማድረግ አለብህ›› አለኝ። ጉልበቴ ሙሉ በሙሉ እስኪድን ድረስ ጥቂት ወሮች ወስዶ ነበር።

ሐዋርያት ሥራ 24÷16 ላይ እጥራለሁ ወይም ልምምድ አደርጋለሁ የሚለውን ቃል ግሪኩ *አሰኪዎ (askeo)* ይለዋል። ቫይንስ ኤክስፓዚቶሪ መዝገበ ቃላት ደግሞ ልምምድ የሚለውን፣

‹‹ለማሠልጠን ወይም ሥርዐት ለማስያዝ ሲባል መድከም፣ ጥረት ማድረግ ወይም መለማመድ››[1] በማለት ያብራራዋል።

አንዳንዴ ሰዎች ሲበድሉን ይቅር ማለት ከባድ አይሆንብንም። የደረሰብንን በደል በሚገባ በማስተናገድ ረገድ ልባችንን ስላሠለጠንነው ወይም ሁኔታውን ለመቀበል ስላለማመድነው፣ ይህን ያህል ጉዳት አያስከትልብንም ወይም ዘላቂ ቁስል ትቶ አያልፍም።

በቂ ልምምድ ያደረጉ ሰዎች፣ ያንን እኔ ሐዋይ እያለሁ የወጣሁበትን ግንብ ቢወጡ ኖሮ ምንም አይጐዱም ነበር። በተመሳሳይ መልኩ፣ አንዳንድ ሰዎች ልባቸውን ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለማምደውታል። የዕድገት ወይም የብስለት ደረጃችን የሚለካው፣ ጉዳት በማያደርስብን ሁኔታ በደልን ወይም መሰናከልን ማስተናገድ ስንችል ነው።

አንዳንድ በደሎች ወይም መሰናክሎች እኛ ከተለማመድናቸው በተለየ መልኩ በጣም ከባድ ናቸው። የምናደርገው ተጨማሪ ጥረት ቁስል ወይም የበለጠ ጉዳት ሊያስከትልብን ስለሚችል፣ ነጻ ለመሆንና እንደ ገና ለመፈወስ መንፈሳዊ ልምምድ ማድረግ ይኖርብናል። ሆኖም፣ የዚያ ጥረት ውጤት ዋጋ ይኖረዋል።

በዚህ ምዕራፍ ጉዳትን መፈወስ ተጨማሪ ጥረት ስለሚጠይቁ ከባድና ጽኑ በደሎች መናገር እፈልጋለሁ።

አገልግሎት ውስጥ ከነበረ ሰው አንድ ከባድ ጉዳት ደርሶብኝ ነበር። በመሠረቱ፣ የደረሰብኝ ጉዳት ይኸኛው ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ዓመት ተኩል ሙሉ እየተባባሱ ከመጡ በርካታ ጉዳቶች አንዱ ነበር። አብረውን የነበሩ ሱቆች ሁሉ እየሆነ የነበረውን ያውቁ ነበር። ‹‹ለመሆኑ፣ ጉዳቱ ይህን ያህል አልተሰማህም?›› በማለት ይጠይቁኝም ነበር። ‹‹ምን ለማድረግ አስበሃል? ወይስ ሌላ ጉዳት እስኪደርስብህ ትጠብቃለህ?››

‹‹ምንም አይደለም፤ ምንም የደረሰብኝ ጉዳት የለም፤ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ያለውን ጥሪ በመፈጸም ረገድ እየተጋሁ ነው›› በማለት እመልስላቸው ነበር።

ሆኖም፣ መልሴ ትዕቢት እንጂ ሌላ አልነበረም። እንደ እውነቱ ከሆነ እጅግ ሲበዛ ተጐድቼ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ ምንም እንዳልተደረገ ለመቁጠር ነበር የሞከርኩት፤ ሌላው ቀርቶ፣ ጉዳቴን በልቤ ውስጥ እንኳ መቀበል አልፈለግሁም ነበር። ይህ ሁሉ እንዴት ሊደርስብኝ እንደ ቻለ በማውጣት በማውረድ፣ ሰዓቶች አሳልፍ ነበር። አንዳንዴ እደነግጣለሁ፤ አንዳንዴ ፍዝዝ እላለሁ፤ አንዳንዴ ደግሞ እገረማለሁ። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሐሳቦችን ሁሉ ዐምቄ ይገፍኣቸው ነበር፤ ፊት ለፊት ስታይ ብርቱ ብመስል እንኳ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ደካማ ነበርኩ፤ ጥልቅ እኔነቴም ተጐድቶ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ወሮች አለፉ። ሁሉም ነገር ደረቅ ሆኖብኝም ነበር፤ አገልግሎቴም አታክቶኝ ነበር፤ በጸሎት ክፍሌ ውስጥ እያለሁ ብቸኝነት ነበር የሚሰማኝ፤ ሕይወት ራሱ ስቃይ ሆኖብኝ ነበር። በየዕለቱ ክፉ ሐሳቦችን መዋጋት ነበረብኝ። ይህ ሁሉ የደረሰብኝ በሕይወቴ የእግዚአብሔር ጥሪ ስላለ ነው በማለት አሳቤ ነበር፤ እውነቱን ለመናገር ግን፣ ያ ሁሉ ስቃይ ይቅር ያለ ማለቴ ውጤት ነበር። ያ ሰው ባለበት ቦታ በተገኘሁ ጊዜ ሁሉ፣ መንፈሳዊ ሽንፈት ተሰምቶኝ ነበር የምመለሰው።

ውሎ አድሮ፣ አንድ በፍጹም የማልረሳው ጠዋት መጣ። ከቤቴ ጀርባ ባለ ቦታ ሆኜ እየጸለይኩ ነበር። ‹‹ጌታ ሆይ፣ እውነት ተጐድቻለሁ እንዴ?›› በማለት ጠየቅሁ። ቃሎቹ ገና ከአፌ ወጥተው ሳያበቁ፣ ጥልቅ መንፈሴ ውስጥ፣ አዎን! የሚል ቃል ሰማሁ።

እግዚአብሔር በእውነት መጐዳቴን እንድቀበል ፈለጓል።

‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ከዚህ ጉዳትና መሰናክል እንድወጣ እባክህ ርዳኝ፤ ከእንግዲህ ይህን መሸከም አልችልም›› በማለት ጸለይኩ።

እግዚአብሔር የፈለገውም እዚህ ቦታ እንድደርስ ነበር - የገዛ ራሴ ዐቅም ወደሚያበቃበት ደረጃ እንድደርስ ነበር። ብዙ ጊዜ በገዛ ራሳችን ጉልበት ነገሮችን ማድረግ እንሞክራን። ይህ መንፈሳዊ ዕድገታችንን ያደናቅፋል፤ ለተደጋጋሚ ውድቀትና ሽንፈት ያጋልጠናል።

ወደ ፈውስና ነጻነት የሚያደርስ የመጀመሪያ ርምጃ መጐዳታችንን መቀበል ነው። ብዙ ጊዜ ግን ትዕቢት መጐዳታችንንና መሰናከላችንን እንድንቀበል አይፈልግም። ያለሁበትን እውነተኛ ቦታ ከተቀበልኩ በኃላ አጥብቄ እግዚአብሔርን መፈለግ ያዝኩ፤ ለሚሰጠኝም እርምት ራሴን ክፍት አደረግሁ።

ለጥቂት ቀኖች ያህል እንድጸም እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ተሰማኝ። ጸም፣ እኔን ለመንፈሱ ድምፅ ንቁ የምሆንበት ሁኔታ ላይ ከማድረጉ በተጨማሪ ሌላ ሌሎች ጥቅሞች እንደሚሰጠኝም አውቃለሁ።

> እንግዲህ እኔ የመረጥሁት ጸም የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፤ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ አይደለምን?
>
> - ኢሳይያስ 58÷6

እነዚህ የዐመፃ እስራቶች እንዲበጠሱና፣ ከጭቆና ነጻ ለመሆን ዝግጁ ነበርኩ። ከጥቂት ቀኖች በኃላ የቀብር ሥርዐት ላይ ተገኝቼ ነበር። ያ በድሎኛል ወይም አሰናክሎኛል የምለው ሰውዬም እዚያ ነበር። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ጀርባ ባለው ቦታ ሳየው ልቤ ተነክቶ ማልቀስ ጀመርኩ።

‹‹ጌታ ሆይ፣ ይቅር እለዋለሁ። እኔ ላይ ካደረገው ክፉ ነገር ሁሉ እፈታዋለሁ›› አልኩ፤ ወዲያውኑ ሸክም የተነሣልኝ መሰለኝ። ይቅር ብዬዋለሁ፤ ስለዚህ ነፍሴ በእፎይታ ተጥለቀለቀች።

ሆኖም፣ ይህ ወደ ፈውስ ለማደርገው ጉዞ የመጀመሪያው ነበር። አዎን፣ በልቤ ይቅር ብየዋለሁ፤ ግን ቁስሉ ምን ያህል ሥር የሰደደ እንደ ነበር ገና አላወቅሁም ነበር። አሁንም ለጥቃት እንደ ተጋለጥኩ ነበር፤ ምናልባትም ድጋሚ ልጐዳ እችላለሁ። ነገሩ

ከአካላዊ ጉዳት የመዳን ወይም የመፈወስ ያህል ነው። ልምምድ ወይም ጥረት ያስፈልገኛል፤ ወደ ፊት ተመሳሳይ ዐይነት ጉዳት እንዳይገጥመኝ ልቤን፣ አእምሮዬንና ስሜቶቼን ማበርታት ይኖርብኛል።

ምናልባት ተመልሶ ቢመጣስ?

ጥቂት ወሮች አለፉ። አልፎ አልፎ፣ ይቅር ከማለቴ በፊት የነበሩኝን ሐሳቦች መዋጋት ነበረብኝ። እንደ እኔው በዚያ ሰው የተጐዳ ሌላ ወንድም ይመጣና በዚያ ሰው ላይ ያማርራል፤ ሰውዬውን ሳየው ወይም ድምፁን ስሰማ ሕመሙ ያገረሽብኝ ነበር። እነዚህ ሐሳቦች ሲመጡ ወዲያውኑ እቋቋማቸው ነበር፤ ምሽግ የሆናቸውን ነገር አፈርሶ ነበር (2 ቆሮንቶስ 10÷5) ይህ እንግዲህ፣ ነጻ እንደ ሆንኩ ለመዝለቅ ማድረግ የነበረብኝ ልምምድ ወይም ጥረት ነበር።

በመጨረሻ እነዚህ ሐሳቦች ወደ በፊቱ ይቅር አለማለት መልሰው እንዳያገቡኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጌታን ጠየቅሁ። እግዚአብሔር ለእኔ የሚፈልገው የላቀ ነጻነት መሆኑን አውቃለሁ፤ እኔም ብሆን በቀረው ዘመኔ በቅርብ ርቀት መሰናክልን ይዤ መዝለቅ አልፈልግም። ለጐዳኝ ሰውዬ አጥብቄ መጸለይ እንዳለብኝ ጌታ ሐሳቡን ልቤ ውስጥ አኖረ፤ የሚከተለው ቃሉንም አስታወሰኝ።

> እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ።
>
> - ማቴዎስ 5÷44

እንደ ገና ጸለይኩ። መጀመሪያ ላይ ጸሎቴ፣ ምንም የጋለ መሻት የሌለበት ደረቅና አታካች ነበር። ግዴታ ተጥሎበት እንደሚጸልይ ሰው፣ ‹‹ጌታ ሆይ ባርከው። ደስ የሚል ቀን እንዲኖረው ርዳው። በሚያደርገው ሁሉ ርዳው። በኢየሱስ ስም አሜን›› እያልኩ ነበር የምጸልየው።

ይህ ለጥቂት ሳምንቶች ቀጠለ። ያም ሆኖ ግን የትም አላደረሰኝም። ከዚያ አንድ ጠዋት ጌታ መዝሙር 35 ወደ ልቤ አመጣ። መዝሙር 35 ላይ ያለው ምን እንደ ነበር፣ ይህን ያህል

ሐሳቡ አልነበረኝም፤ ከዚያ ያንን ክፍል አውጥቼ ማንበብ ጀመርኩ። ግና ግማሽ ያህሉን እንዳነበብኩ ያለሁበት ሁኔታ ታየኝ።

> ጨካኝ ምስክሮች ተነሡ፤ ስለማላውቀውም ነገር ጠየቁኝ። በበጐ ፈንታ ክፉ መለሱልኝ፤ ነፍሴንም ብቸኛ አደረጓት።
>
> - መዝሙር 35÷11-12

ራሴን ዳዊት የነበረበት ቦታ አደረግሁ። በእኔ አመለካከት፣ ያ ሰውየና ግብረ አበሮቹ ለመልካም ተግባሬ ክፉ መልሰውልኝ ነበር። በእርግጥም ነፍሴ ሐዘንተኛና ብቸኛ ሆና ነበር። በመጨረሻዎቹ ጥቂት ዓመታት የነበርኩበትን ውጊያ ለማመልከት፣ እግዚአብሔር በዚህ መዝሙር እየተጠቀመ ነበር። በተለይም አንዱ ክፍል በጣም ነበር የገረመኝ።

> እኔ ግን እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፤ ነፍሴንም በጾም አደከምኋት፤ ጸሎቴም መልስ አጥቶ ወደ ጉያዬ ተመለሰ። ለወዳጄ ወይም ለወንድሜ እንደማደርግ እየተንቀራጠጥሁ አለቀስሁ፤ ለእናቴም እንደማለቅስ በሐዘን ዐንገቴን ደፋሁ።
>
> - መዝሙር 35÷13-14

እነዚያ ሰዎች እርሱን ለማጥፋት እየሞከሩ እንደ ነበር ዳዊት ይናገራል። ምንም የፈጸመው በደል ባይኖርም፣ በክፋት እያጠቁት ነበር።

ለእኔ መልስ የሆነኝ፣ ‹‹እኔ ግን...›› የሚለው ነበር።

የዳዊት ምላሽ ሌሎች እርሱ ላይ ያደረሱትን መሠረት ያደረገ አልነበረም። መልካም የሆነውን ለማድረግ ቁርጥ ውሳኔ በማድረጉ፣ የሥጋ ወንድሞቹ ለሆኑ ሰዎች እንደሚጸልይ ሰው ጸለየላቸው፤ ለእናቱ እንደሚያለቅስ አለቀሰ። ለዚያ ሰው እንዴት መጸለይ እንዳለብኝ እግዚአብሔር አመለከተኝ። ‹‹ልክ ለአንተ እንዳደርግ እንደምትፈልገው ሆነህ ለእርሱ ጸልይለት!››

በዚህ ጊዜ ጸሎቴ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። ከእንግዲህ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ባርከው፤ ጥሩ ቀን እንዲኖረው ርዳው›› የሚል ዐይነት አልሆነም፤ ጸሎቴ ራሱ በሕይወት ተሞላ። ‹‹እግዚአብሔር

ሆይ፣ የበለጠ ራስህን ግለጥለት። በመገኘትህ ባርከው። የበለጠ በቅርብ ይወቅህ። አንተን ደስ የሚያሰኝና ለስምህም ክብር የሚያመጣ ይሁን›› በማለት ጸለይኩ። እግዚአብሔር ለእኔ እንዲያደርግልኝ እንደምፈልገው ዐይነት ለእርሱ ጸለይኩ።

በዚህ መልኩ በከፍተኛ ተነሳሽነት አንድ ወር ከጸለይኩለት በኃላ በከፍተኛ ድምፅ፣ ‹እባርክሃለሁ! በኢየሱስ ስም እወድሃለሁ!›› አልኩ። ከውስጥ መንፈሴ የወጣ ጩኸት ነበር። ለእኔ ለራሴ ስል ለእርሱ ከመጸለይ ወጥቼ፣ ለእርሱ ለራሱ ስል ወደ መጸለይ ተሻገርኩ። ፈውሴ ሙሉ በሙሉ እውን እንደ ሆነም አመንሁ።

ፊት ለፊት በመገናኘት መፈወስ

ተጨማሪ ጥቂት ሳምንቶች ካለፉ በኃላ ሰውየውን እንደ ገና አየሁት። ልቤ ውስጥ የቀረ መራራ ስሜት ነበር። አሁንም ነቃፊነትን እየተዋጋሁ ነበር።

‹‹ጆን፣ ሂደህ ሰውየውን ማግኘት አለብህ›› በማለት ሚስቴ አበረታታችኝ።

‹‹የለም፣ አልሄድም - አሁን'ኮ ተፈውሻለሁ›› አልኩ ጥቂት ጠንከር ብዬ።

ሆኖም፣ የተናገርኩት እውነት ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ እየመሰከረልኝ አልነበረም። ስለሆነም፣ ወደ እርሱ መሄድ ያስፈልገኝ እንደሆነ ጌታን ጠየቅሁ። - አምን አለኝ።

ከሰውየው ጋር ቀጠሮ ያዝኩ፤ ወደ እርሱ ስሄድ ስጠታ ይገፍለት ነበር። ራሴን ዝቅ አደረግሁ፤ ስለ ነበረኝ መጥፎ ዝንባሌ ተናዘዝኩና ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁት። ዕርቅ ወረደ፤ ይቅር ባይነትና ፈውስ ወደ ልቤ ይፈስስ ጀመር።

ከቢሮው የወጣሁት ሙሉ በሙሉ ተፈውሼና ብርቱ ሆኜ ነበር። ከእንግዲህ ጥርሴን ነክሼ ሕመሙን መቋቋም አልነበረብኝም፤ የነቃፊነቴና የተቺነት ስሜቴም አብሮኝ አልነበረም። ከዚያ ወዲህ ግንኙነታችን ተስተካክሎአል፤ ከዚያ

ወዲህ፣ ሌላ ችግር አልገጠመንም። እንዲያውም እርስ በርስ መደጋገፍ ጀምረናል።

‹‹ሰውየውን መጀመሪያ ያገኘሁት ጊዜ፣ ምንም ያላደረገኝ መስሎ ነበር የታየኝ፤ በደል እንዳልሠራ ስላሰብኩ ልወደው ችዬአለሁ። ያደረሰብኝን ጉዳት እያሰላሰልኩ በነበረ ጊዜ ግን፣ እርሱን መውደድ ከብዶኝ ነበር። ያን ለማድረግ በጣም እምነት ጠይቆኝ ነበር። በዚህ መታደስ ሂደት ውስጥ ካለፍኩ በኃላ ግን ተፈውሻለሁ፤ አሁን በደሉን ግምት ውስጥ ሳላስገባ መጀመሪያ ያገኘሁት ጊዜ እወደው እንደ ነበር እርሱን መውደድ ችያለሁ›› በማለት ለሊዛ ነግሬአት እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ይህ ደግሞ በሳል ፍቅር ነው። ቀጥሎ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ወደ አእምሮዬ መጣ።

> ፍቅር ብዙ ኃጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ።

- 1 ጴጥሮስ 4÷8

በእኛ ፊት ምንም በደል ያልፈጸሙ ሰዎችን መውደድ ቀላል ነው። ይህ ዓይነቱ ፍቅር የጫጉላ ፍቅር ነው። በደላቸውን በግልጽ እያየን፣ በተለይም የበደላቸው ተጠቂዎች እኛ ራሳችን ከሆንን ሰዎችን መውደድ መቻል ግን የተለየ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በሳል እያደረገኝ ነበር፤ ልቤን እያበረታና እየጠገነ ነበር።

ከዚያም ወዲህ ተመሳሳይ ነገሮች ደርሰውብኝ ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ፣ የበደልን እስራት ለመፍታት ጊዜ አይወስድብኝም። ምክንያቱ – ከበደል ወይም ከመሰናክል ነጻ እንደ ሆንኩ ለመዝለቅ ልምምድ ወይም ጥረት አድርጌ ስለ ነበር ነው።

ከቤቴ በስተ ጀርባ ባለ ቦታ እያለሁ እግዚአብሔር ከተናገረኝ ጀምሮ፣ ከሰውየው ቢሮ ነጻ ሆኜ እስከ ወጣሁበት ጊዜ ድረስ በርካታ ወሮች አልፈው ነበር። ያ ልቤ እየበረታና እየተጠገነ የሄደበት የልምምድ ወይም የጥረት ወቅት ነበር። በእነዚያ ወሮች ውስጥ አንዳንዴ የትም መድረስ እንዳልቻልኩ ይሰማኝ ነበር። እንዲያውም ሁኔታዬ ሁሉ እየተባባሰ በመሄድ ላይ እንዳለ ነበር የሚሰማኝ።

ይሁን እንጂ፣ ወደ ፊውስ የሚያደርስ አስተማማኝ መንገድ ላይ ነበርኩ። የእግዚአብሔር መንፈስ መራመድ በምችለው ልክ እየመራኝ ነበር። ያ ወደ ብስለት ደረጃ የመምጣቴ ሂደት ነበር። ያንን ልምምድ በምንም አልለውጠውም፤ ለሕይወቴ ባመጣው ዕድገት በጣም አመስጋኝ ነኝ።

በአዳጋች ሁኔታዎች አማካይነት በሳል መሆን

የምናድገው በአዳጋች ጊዜዎች እንጂ፣ በምቾት ጊዜዎች አይደለም። ከጌታ ጋር በምናደርገው ጉዞ አንዳንዴ ከባድ ቦታዎች ይገጥሙናል። ሆኖም፣ በእርሱ ፍጹማን ሆኖ የመገኘት ሂደት አካል በመሆናቸው ፊት ለፊት መጋፈጥ እንጂ፣ ሸሽተን ማምለጥ አንችልም። ሸሽተን ማምለጥን ከመረጥን ግን፣ ዕድገታችን ይጫጫል፤ ይገታል።

የተለያዩ ዕንቅፋቶችን እያሸነፋችሁ ስትሄዱ፣ ብርቱዎችና ርኅሩኆች ትሆናላችሁ። ኢየሱስን የበለጠ ትወዱታላችሁ። በአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ ካለፋችሁ በኃላ ይህ ግንዛቤ ከሌላችሁ ግን፣ ምናልባትም የተፈጸመባችሁ በደል ካደረሰባችሁ ቁስል ገና አልተፈወሳችሁም ይሆናል። መፈወስ የእናንተ ምርጫ ነው። አንዳንድ ሰዎች ጉዳት ቢደርስባቸውም፣ ጨርሶ አይፈወሱም። ይህ ጭካኔ ቢመስል እንኳ፣ ያ የሆነው በእነርሱ ምርጫ ነው ማለት ይቻላል።

ኢየሱስ ከተቀበለው መከራ የተነሣ መታዘዝን ተማረ። ጴጥሮስ ከተቀበለው መከራ የተነሣ መታዘዝን ተማረ፤ ጳውሎስ ከተቀበለው መከራ የተነሣ መታዘዝ ተማረ። እናንተስ? ተምራችሁ ይሆን? ወይስ አሁንም፣ ጠንካሮች፣ ግትሮች፣ ቀዝቃዞችና በቅርታ እንደ ተሞላችሁ ነው ያላችሁት? እንደዚያ ከሆነ፣ ገና መታዘዝን አልተማራችሁም።

አምን፣ አንዳንድ በደሎች ወይም መሰናክሎች፣ በአጭር ጊዜ ብን ብለው አይጠፉም። ነጻ ለመሆን የራሳችሁን ጥረት፣ የራሳችሁን ልምምድ ይጠይቃሉ። ሆኖም፣ በዚያ ሂደት ውስጥ ታድጋላችሁ፤ በሳሎችም ትሆናላችሁ።

ብስለት በቀላሉ አይመጣም። እንደዚያ ቢሆንማ ኖሮ፣ ሁሉም በሳሎች ይሆኑ ነበር። ከሚገጥማቸው ተቃውሞ የተነሣ፣ እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርሱ በጣም ጥቂቶች ናቸው። የማጎበረ ሰባችን አኗኗር መንገድ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት ሳይሆን፣ ራስ ወዳድ በመሆኑ ተቃውሞ ይኖራል። ዓለም፣ ‹‹በአየር ላይ ላሉት ኃይላት ገዥ›› በሆነው ሥልጣን ሥር ነው (ኤፌሶን 2÷2)። ከዚህም የተነሣ በክርስቶስ ወዳለው ብስለት ለመግባት ራስ ወዳድ ከሆነው ሥርዐት የሚመጣ ተቃውሞ ይኖራል። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኖችን መሥርቶ ወደ ነበረባቸው ሦስት ከተሞች ተመልሶ ነበር። ዓላማው እዚያ ያሉ ደቀ መዛሙርትን ነፍስ ማበረታታት ነበር። ይሁን እንጂ፣ እነርሱን ያበረታታው እንዴት እንደ ነበር መረዳቱ ይጠቅማል።

> ...በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን›› - በማለት ነበር ያበረታታቸው።
>
> - ሐዋርያት ሥራ 14÷22

የተመቸና የተደላደለ ሕይወት እንደሚኖራቸው ቃል አልገባላቸውም። በዓለም መለኪያ መስፈርት መሠረት፣ ነገር ሁሉ እንደሚሳካላቸውና እንደሚከናወንላቸው ቃል አልገባላቸውም። የጀመሩትን ጉዞ በደስታ እንዲፈጽሙ ከተፈለገ፣ እርሱ መከራ በማለት የጠራው ተቃውሞ ይገጥማቸዋል።

አንድ ወንዝ ላይ ከወራጁ ውሃ በተቃራኒ የምትቀዝፉ ከሆነ፣ ወደ ፊት ለመሄድ ሳታቋርጡ መቅዘፍ ይኖርባችኃል። መቅዘፋችሁን አቋርጣችሁ ዘና ካላችሁ፣ በወራጁ ውሃ ቁልቁል ተወሰዳላችሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በእግዚአብሔር መንገድ ለመጓዝ ቁርጥ ውሳኔ ካደረጋችሁ፣ የተለያዩ ችግሮች ይገጥሟችኃል። መከራዎቹ የአንድ ዋነኛ ጥያቄን መልስ ግልጽ ያደርጋሉ – በዓለም መለኪያ መስፈርት መሠረት የራሳችሁን ትፈልጋላችሁ ወይስ ራስን የመካድ ሕይወት ትኖራላችሁ?

ለኢየሱስ ስንል የራሳችንን ሕይወት የምናጣ ከሆነ፣ የእርሱን ሕይወት እንደምናገኝ አትርሱ። ትኩረታችሁን የመጨረሻው ውጤት ላይ እንጂ፣ ትግሉ ላይ አታድርጉ።

ጴጥሮስ ይህን በሚገባ አስቀምጧል።

ወዳጆች ሆይ፣ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።

- 1 ጴጥሮስ 4÷12-13

የመከራውን ልክ ከሚገኘው ደስታ ልክ ጋር ማስተካከሉን ልብ አድርጉ። ለመሆኑ፣ በዚያ ልክ ደስ የምትሰኙት እንዴት ነው? የእርሱ ክብር ሲገለጥ፣ እናንተም ከእርሱ ጋር ትከብራላችሁ። የምታገኙት ክብር፣ እርሱ የራሱን ባሕርይ እናንተ ውስጥ እንዲፈጽም በምትፈቅዱለት መጠን ነው። ስለሆነም፣ የደረሰባችሁን በደል ሳይሆን፣ የሚመጣውን ክብር ተመልከቱ። ሃሌ ሉያ!

እናንተ ትክክል መሆናችሁን ከማሳየት ይልቅ

የተሰናከለውን ወንድም መርዳት ይበልጣል።

ዐሥራ ስምንት ዓመቴ ነው። የእኔ መንታ ከሆነች እኅቴ ጋር አንድ ወላጅ ብቻ ባለበት ቤት ውስጥ ነበር ያደግሁት፤ በጣም ደስ የሚሉ የሩቅ ዘመዶችም አሉን። ወላጅ አባቴን በፍጹም አግኝቼው አላውቅም፤ ሕይወቴ ላይ ለደረሰው ሁሉ እርሱ ላይ ቂምና ጥላቻ ነበረኝ። ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የሆነው ወንዱ አያቴ፣ *የሰይጣን ሽንገላን እንዳነብ* ሰጠኝ። ካነበብኩ በኋላ አባቴን ሙሉ በሙሉ ይቅር ማለት ችዬአለሁ።

- ኤን. ኤም ኒው ሜክሲኮ

14

የመጨረሻው ግብ – ዕርቅ

ለቀደሙት ሰዎች፣ አትግደል፣ የገደለ ይፈረድበታል እንደ ተባለ ሰምታችኃል፣ እኔ ግን እላችኃለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን ‹ጅል› የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ ‹ደደብ› የሚል ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል። ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣ መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤ በመጀመሪያ ሂደህ ከወንድምህ ጋር ተሰማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ።

- ማቴዎስ 5÷21-24

ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከተራራው ስብከት ነው። ኢየሱስ የጀመረው፣ ‹‹ለቀደሙት ሰዎች… እንደ ተባለ ሰምታችኃል›› በማለት ነበር፤ ከዚያ በኃላ ደግሞ፣ ‹‹እኔ ግን እላችኃለሁ…›› አለ።

በዚህ የመልእክቱ ክፍል ኢየሱስ እንዲህ ዐይነቱን ንጽጽር ደጋግሞ ተጠቅሞአል። በመጀመሪያ ውጫዊ ድርጊታችንን ከሚቆጣጠረው ሕግ ጠቀሰ። ከዚያም ያንኑ ወደ ልብ በማምጣት ዓላማው ምን እንደ ሆነ አሳየ። ስለሆነም፣ መግደል ሌላውን ሰው በመግደል ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ ወንድሙን የሚጠላ ሰውም እንዲሁ ነፍሰ ገዳይ ነው። እናንተ የምትሆኑት፣ በእርግጥ ልባችሁ ውስጥ ባለው መሠረት ነው!

በዚህ የስብከቱ ክፍል ኢየሱስ በደልን ተከትሎ የሚመጡ ውጤቶችን በጉልህ አሳይቶአል። ቁጣ ወይም ምሬት የመያዝን አደገኛነት አብራርቶአል። አንድ ሰው ያለ በቂ ምክንያት ወንድሙ ላይ ከተቆጣ ፍርድ ይጠብቀዋል። ያ ቁጣ እያደገ ሄዶ፣ ወንድሙን ‹‹ራካ›› [1] ካለው፣ በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል።

ራካ የሚለው ቃል፣ ‹‹ባዶ ራስ›› ወይም ሞኝ ማለት ነው። ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ዘመን፣ በአይሁድ የተለመደ የንቀት አነጋገር ነበር። እንግዲህ ያ ቁጣ እያደገ ሄዶ፣ ወንድሙን ሞኝ ወይም ባደራስ የሚልበት ደረጃ ላይ ከደረሰ ለገሃነም ፍርድ ያበቃዋል ማለት ነው። ሞኝ የሚለው ቃል፣ አምላክ የለሽ ማለት ነው።[2] ሞኝ በልቡ አምላክ የለም ይላል (መዝሙር 14÷1 ይመ.)። በዚያ ዘመን አንድን ሰው ሞኝ ማለት ከባድ ስድብ ነበር። ውስጡ የነበረው ቁጣ ወደ ጥላቻ ተለውጦ ካልሆነ በቀር፣ ማንም ይህን የመሰለ ነገር አይናገርም ነበር። በዚህ ዘመን አባባሉ፣ ‹‹ገሃነም ግባ›› ከማለት ጋር ሊመሳሰል ይችላል።

በጊዜ መፍትሔ ካልተገኘለት፣ ቁጣ ወደ ጥላቻ እንደሚመራ ኢየሱስ አሳያቸው። በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ ጥላቻ ለገሃነም ፍርድ ያደርሳል። ከዚያም ወንድማቸው እነርሱ ላይ ያዘነበት ነገር መኖሩ ትዝ ካላቸው፣ እርሱን አግኝቶ ዕርቅ ማድረግ ተቀዳሚ ሥራቸው መሆን እንደሚገባው ነገራቸው።

ለመሆኑ፣ በእንዲህ ያለ ችኮላ ዕርቅ ማድረግ ያለብን ለምንድነው - ለራሳችን ስንል ወይስ ለወንድማችን ስንል? ከዚያ በደል መወጣት እንዲችል፣ እርሱን ለመርዳት ሲባል ወደ እርሱ መሄድ አለብን። ምንም እንኳ እኛ በእርሱ ባንሰናከልበትም እንኳ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ሰውየው ከነቁጣው ውሎ እንዲያድር አይፈልግም። ምንም ያደረስነው በደል ላይኖር ይችላል። ትክክል ወይም ስሕተት መሆኑ ምንም ማለት አይደለም። ለእኛ በጣም አስፈላጊው ነገር፣ የእኛን ትክክለኛነት ከማሳየት ይልቅ ያንን የተሰናከለ ወንድም መርዳት ነው።

በደል ወይም መሰናክል የሚፈጠርባቸው ሁኔታዎች በጣም በርካታ ናቸው።

ምንም እንኳ በእውነት እርሱን ባንሞዳውም፣ አንዳንዴ በደል ደርሶብኛል ባዩ ሰው ጥሩ ሰዎች እንዳልሆንን ሊያስብ ይችላል። የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ያደረገው፣ የተሳሳተ መረጃ ደርሶት ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ትክክል ወዳልሆነ ድምዳሜ እንዲደርስ ያደረገው፣ ትክክለኛ መረጃ ደርሶት ሊሆን ይችላል። እኛ የተናገርነው በተለያየ መገናኛ መንገድ ሲተላለፍ፣ ሊጣመምና ከታሰበበት ዓላማ ውጪ ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ ፍላጐታችን ሰውን መጉዳት ባይሆንም፣ ቃልና ተግባራችን የተለያየ መልእክት አስተላልፈው ይሆናል።

ብዙ ጊዜ ራሳችንን የምንዳኘው ልባችን ውስጥ ባለው ሐሳብ ሲሆን፣ ሌሎችን የምንዳኘው ግን በተግባራቸው ነው። አንድ ነገር አስቦ፣ ፍጹም የተለየ ነገር ማስተላለፍ ይቻላል። አንዳንዴ እውነተኛ ዓላማችን በጣም በረቀቀ ሁኔታ፣ ከእኛ ከራሳችን እንኳ ሊሰወር ይችላል። ፍጹም ንጹሕ እንደሆነም እናምን ይሆናል። ሆኖም፣ በእግዚአብሔር ቃል ማጥለያነት ስናጠልለው ግን በተለየ ዓይን እንመለከተዋለን።

በመጨረሻም፣ ምናልባት ሰውየው ላይ ምንም በደል አልፈጸምን ይሆናል። ከመናደዳችን የተነሣ ተቆጥተን ሊሆን ይችላል፤ የቁጣው ወላፈን እርሱን ተሰምቶት ይሆናል። ወይም ደግሞ ያ ሰው ሆን ብሎ እና አዘውትሮ እኛን የሚያስቆጣ ነገር በማድረጉ፣ እኛም ያንን የሚመስል ምላሽ ሰጥተን ይሆናል።

ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ተበድያለሁ የሚለውን ሰው መረዳት ያጨልማል፤ ምንም እንኳ እውነተኛውን የእኛን ዓላማ እንደ ተረዳ ቢያምንም፣ እንዲሁ በግምት፣ ወይም ከሰዎች በሰማው፣ ወይም መስሎ በታየው መሠረት ራሱን ያስታል። ለመሆኑ፣ ትክክለኛ መረጃ ሳይኖረን፣ እንዴት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት እንችላለን? በደል እንደ ደረሰበት በሙሉ ልቡ እንደሚምን ያደረገው ምን እንደ ሆነ ለመረዳት ንቁ መሆን አለብን። እንዲህ ሊያስብ የቻለው በምንም ምክንያት ይሁን በምን፣ እኛ ግን ራሳችንን ዝቅ ለማድረግና ይቅርታ ለመጠየቅ ፈቃደኛ መሆን አለብን።

ምንም እንኳ በደለኞቹ እኛ ባንሆን እንኳ፣ ኢየሱስ ዕርቅ እንድናደርግ መክሮናል። ዕርቅ እንዲመጣ በማድረግ ረገድ በትሕትና መመላለስ በሳልነት ይጠይቃል። ይሁን እንጂ፣ በደል ለደረሰበት ወገን የመጀመሪውን ርምጃ መውሰድ ምንጊዜም አዳጋች ነው በደል አድራሹ ወደ እርሱ ሄዶ ነገሩን እንዲያስተካክል ኢየሱስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነው።

የተበደለው ወገን ይቅርታ መጠየቅ

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤

> ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ።
>
> - ሮሜ 14÷19

ይህ የበደልነው ሰው እንዴት መቅረብ እንዳለብን ያሳያል። ወደ እርሱ የምንሄደው በንዴትና በብስጭት ከሆነ ሰላም ማምጣት አንችልም። እንዲህ ማድረግ ለተጐዳው ሰው ሁኔታውን አስቸጋሪ ያደርግበታል። ትዕቢታችንን ዋጥ አድርገን፣ ሰላም ፈጣሪ የመሆን ትሕትና ሊኖረን ይገባል። ዕውነተኛ ዕርቅ ለማስገኘት ብቸኛው መንገድ ይኸው ነው።

የበደልኳቸውን ወይም በእኔ ላይ የተቆጡ ሰዎችን ይቅርታ ብጠይቅም፣ መልሰው እኔኑ የነቀፉበት ጊዜ ነበር። ራስ ወዳድ፣ ደንታ ቢስ፣ ትዕቢተኛና፣ ተሳዳቢ፣ ወይም ቁጡ መሆኔን ነግረውኝ ነበር።

የተለመደ ምላሼ፣ ‹‹የለም፣ እንደዚያ አይደለሁም፤ በፍጹም አልተረዳችሁኝም!›› የሚል ይሆን ነበር። ሆኖም፣ ለራሴ መከላከል የእነርሱን ተበድለናል የማለት እልህ የበለጠ ያቀጣጥለዋል እንጂ፣ ምንም አይጠቅምም። ሰላም የመፍጠር መንገድም አይደለም። ለራሳችንና ‹‹ለመብታችን›› መከራከር እውነተኛ ሰላም አያመጣም።

ከዚያ ይልቅ፣ መናገር የሚፈልጉትን ሁሉ ተናግረው እስኪጨርሱ ድረስ ማድመጥ እንጂ፣ እኔ ምንም መናገር እንደማይገባኝ ተረድቻለሁ። በተናገሩት ነገር ባልስማማ እንኳ፣ የተናገሩትን

እንደማከብርና እኔ ግን፣ ልቤንና ዝንባሌዬን እንደምመረምር እንዲያውቁ አደርጋለሁ። ከዚያም፣ እነርሱን በመጉዳቴ ማዘኔን እነግራቸዋለሁ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ እኔን በተመለከተ የተናገሩት ትክክል ሆኖ ይገኛል። እንዲህ ከሆነ፣ ‹‹አዎን፣ ትክክል ናችሁ፤ ይቅርታ አድርጉልኝ›› እላቸዋለሁ።

አሁንም ቢሆን፣ ዕርቅን ለማውረድ ሲባል፣ ራስን ዝቅ ማድረግ ተገቢ መሆኑን መገንዘብ አለብን ማለት ነው። ምናልባትም ቀጥሎ ያለውን ኢየሱስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

> የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ፣ ዳኛውም ለአሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ፣ በወህኒም እንዳትጣል፤ በመንገድ ላይ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ። እውነት እልሃለሁ፤ ካስፈረደብህ ግን የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወጣም።
>
> - ማቴዎስ 5÷25-26

ትዕቢት እውነት ቢሆን እንኳ ራሱን ይከላከላል። ትሕትና ግን በመስማማት፣ ‹‹አዎን፣ ልክ ነህ፤ እንዲህ በማድረጌ አጥፍቻለሁ፤ እባክህን ይቅርታ አድርግልኝ›› ይላል።

> ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፤ በኋላም ሰላም ወዳድ፣ ታጋሽ፣ እሺ ባይ፣ ምሕረትና መልካም ፍሬ የሞላባት፣ አድልዎና ግብዝነት የሌለባት ናት።
>
> - ያዕቆብ 3÷17

ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብ እሺ ባይና ሰላም ወዳድ ነው። በግል ከሰዎች ጋር የሚኖረውን ግጭት በተመለከተ፣ አንገተ ደንዳና ወይም ግትር አይደለም። በመንፈሳዊ ጥበብ የሚመራ ሰው አጥፍቻለሁ ማለትን ወይም እውነትን እስካልተጻረረ ድረስ፣ ሌሎች ከሚያቀርቡት ሐሳብ መለየትን አይፈራም።

የበደላችሁን ሰው መቅረብ

እስከ አሁን ወንድማችንን ስንበድል ወይም ስናሰናክል ምን ማድረግ እንዳለብን ተመልክተናል፤ አሁን ደግሞ፣ ወንድማችን

እኛን ሲበድለን ወይም ሲያሰናክለን ምን ማድረግ እንዳለብን እንመለከታለን፡፡

> ወንድምህ ቢበድልህ ሂደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው፡፡ ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ፡፡
>
> - ማቴዎስ 18÷15

ብዙዎች ይህን ጥቅስ የሚጠቀሙበት ኢየሱስ ማስተላለፍ ከፈለገው መልእክት በተለየ ዝንባሌ ነው፡፡ በደል ደርሶባቸው ከሆነ ወደ በዳዩ ወገን ሂደው በበቀልና በቁጣ መንፈስ ይጋፈጡታል፡፡ የበደላቸው ሰው ላይ ለመፍረድ ይህን ጥቅስ እንደ ድጋፍ ይወስዱታል፡፡

ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ይህን የተናገረበትን ዓላማ ስተዋል፡፡ ዓላማው ፍርድ ሳይሆን ዕርቅ ነው፡፡ ወንድማችን ምን ያህል እንደ በደለንና በዚህም ምክንያት ሊፈረድበት እንደሚገባ እንድንነግረው አይደለም ኢየሱስ የፈለገው፡፡ ከእርሱ ጋር የነበረን ግንኙነት እንዳይታደስ ዕንቅፋት የሆነ ነገርን ለማስወገድ ነው ወደ እርሱ መሄድ ያለብን፡፡

ይህ እግዚአብሔር እኛን ወደ ራሱ ከሚመጣበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እኛ እግዚአብሔርን በድለናል፣ ‹‹ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል›› (ሮሜ 5÷8)፡፡ ታዲያ እኛ፣ ለራሳችን መከራከርን ለመተውና ከበደለን ሰው ጋር ሰላም ለመፍጠር ሲባል ለትዕቢት ለመሞት ፈቃደኞች ነን? እግዚአብሔር እኛን የረዳን ይቅርታ ከመጠየቃችን በፊት ነበር፡፡ ኢየሱስ እኛን ይቅር ለማለት የወሰነው ኃጢአት ማድረጋችንን እንኳ ሳናውቅ ነበር፡፡

ምንም እንኳ እርሱ ወደ እኛ ቢመጣም፣ የእርሱን ዕርቅ ቃል እስካልተቀበልን ድረስ፣ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ዕርቅ አይኖረንም፡፡

> ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤ እግዚአብሔር

> በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር፤ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን። ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኃለን።
>
> - 2 ቆሮንቶስ 5÷18-20

የማስታረቁ ቃል የሚጀምረው ሁላችንም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ያደረግን መሆኑን ከመገንዘብ በመነሣት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር መለያየታችንን ካላወቅን፣ ከእርሱ ጋር ዕርቅ ማድረግን ወይም ድነት መቀበልን አንፈልግም።

ከአዲስ ኪዳን እንደምንመለከተው ደቀ መዛሙርት ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ማድረጋቸውን ሰብከዋል። ግን፣ ኃጢአት ማድረጋቸውን ለሰዎች መናገር የነበረባቸው ለምን ነበር? በእነርሱ ላይ ለመፍረድ ነው? እግዚአብሔር ግን እንደዚያ አያደርግም፣ ‹‹እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው›› (ዮሐንስ 3÷17)። ወይስ ኃጢአተኝነታቸውን ለሰዎች የምንናገረው፣ ያለበትን ሁኔታ ተገንዝበው በኃጢአታቸው ንስሐ እንዲያደርጉና ይቅርታ እንዲጠይቁ ነው?

ሰዎችን ወደ ንስሐ የሚያመጣ ምንድነው? መልሱን ሮሜ 2÷4 ላይ እናገኛለን።

> ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ የሚመራ መሆኑን ሳትገነዘብ የቸርነቱን፣ የቻይነቱን፣ *የትዕግሥቱን ባለ ጠግነት ትንቃለህ?*

ወደ ንስሐ የሚመራን የእግዚአብሔር ቸርነት ነው። የእርሱ ፍቅር እኛ በገሃነም እንዲፈረድብን አይተወንም። ለእኛ መስቀል ላይ እንዲሞት ብቸኛ ልጁን ኢየሱስን በመላክ ፍቅሩን ገልጧል። ምንም እንኳ፣ እርሱን የበደልንና ያሳዘንን ቢሆንም፣ መጀመሪያ ወደ እኛ የመጣ እግዚአብሔር ነበር። ወደ እኛ የመጣው ሊፈርድብን ሳይሆን፣ እኛን ወደ ራሱ ለመመለስና ለማዳን ነበር።

እግዚአብሔርን መምሰል ስላለብን የበደለንን ወንድም ይቅር ማለት ይኖርብናል (ኤፌሶን 5÷1)። ኢየሱስ ያመለከተው አሠራር - ወደ እርሱ ሂድ፣ በሁለታችሁ መካከል ያለውን ማንኛውንም ተገቢ ያልሆነ ነገር ለማስወገድ ዕርቅና መታደስ ለመፍጠር እንጂ፣ እርሱ ላይ ለመፍረድ ሳይሆን ኃጢአቱን አሳየው። እኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ወንድማችንን ወደ ንስሐና ግንኙነታችንን ወደ ማደስ ይመራዋል።

> እንግዲህ በጌታ እስረኛ የሆንሁ እኔ፣ ለተቀበላችሁት ጥሪ የሚገባ ኑሮ ትኖሩ ዘንድ እለምናችኃለሁ። ፍጹም ትሑታንና ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች ሁኑ። በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።
>
> - ኤፌሶን 4÷1-3

ይህን የመንፈስ ማሰሪያ የምንጠብቀው፣ በትሕትና፣ በጨዋነት፣ በትዕግሥትና በፍቅር አንዳችን የሌላውን ደካማ ጐን በመቻል ነው። እንዲህ ሲሆን፣ የፍቅር ማሰሪያ ይጠነክራል።

አንዳንድ የበደልኳቸው ሰዎች ወደ እኔ መጥተው ፊርደውብኝ ነበር። ከዚህ የተነሣ ከእነርሱ ጋር የመታረቅ ፍላጐቴ ጠፍቶ ነበር። እንዲያውም እነርሱ የፈለጉት ምን ያህል መናደዳቸውን እንዳውቅላቸው እንጂ፣ ዕርቅ ፍለጋ አይደለም በማለት አስቤ ነበር።

ሌሎች የበደልኳቸው ሰዎች ደግሞ በቅንነትና በጨዋነት ወደ እኔ መጥተው ነበር። እኔም ለእነርሱ የነበረኝን አመለካከት ወዲያውኑ በመለወጥ ይቅርታ ጠይቄአቸዋለሁ፤ አንዳንዴ ተናግረው አስኪጨርሱ እንኳ አያስችለኝም ነበር።

አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ፣ ‹‹ጥሩ ጓደኛ ባለ መሆንህ፣ ለእኔ ይህን ወይም ያንን ባለ ማድረግህ ይቅርታ እንዳደረግሁልህ እንድታውቅ እፈልጋለሁ›› ብሏችሁ ያውቃል?

እንዲህ ያሉ ሰዎች የቻሉትን ያህል ከፊኹባችሁ በኃላ፣ ‹‹ይቅርታ ልትጠይቀኝ›› ይገባል በሚል ዐይን ይገረሙዋችኃል።

በዚህ ሁኔታችሑ በጣም ትገረማላችሁ፤ ምን እንደምታደርጉ ግራ ይገባችኃል። እነዚህ ሰዎች ወደ እናንተ የመጡት ዕርቅ ለመፈለግና ሻክሮ የነበረ ግንኙነታችሁን ለማስተካከል ሳይሆን፣ ሊያስደነግጧችሁና ሊቆጣጠሩዋችሁ ነው።

የሚሰጠን ምላሽ ምንም ይሁን ምን፣ ከልባችን ይቅር ለማለት ቁርጥ ውሳኔ ሳናደርግ የበደለንን ወንድም ለማግኘት መሄድ የለብንም። እርሱን ከማግኘታችን በፊት፣ እርሱ ላይ ከነበረን የጥላቻ ስሜት ነጻ መሆን አለብን። እንደዚያ ካልሆነ ፈውስ ሳይሆን፣ ከእነዚህ አለታዊ ስሜቶች የተነሣ አጉል ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን።

ትክክለኛ ዝንባሌ ይዘን ስንነሣና ከበደለን ወንድም ጋር ዕርቅ ለማድረግ ስንሞክር፣ እርሱ ግን እኛን ለመስማት ፈቃደኛ ካልሆነ ምንድነው ማድረግ ያለብን?

> ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው።እነርሱን ባይሰማ፣ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ፣ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቁጠረው።
>
> - ማቴዎስ 18÷16-17

እነዚህ ሂደቶች ዓላማቸው አንድ ነው - ዕርቅ። ይህን ሲናገር ኢየሱስ፣ ‹‹ሙከራህን ቀጥል›› ማለቱ ነበር። በደል ፈጻሚው ሰው በእያንዳንዱ ርምጃ የነበረውን ድርሻ ልብ አድርጉ። ኢየሱስ በነገረን መሠረት፣ በመጀመሪያ በደል ወዳደረሰብን ወንድም ሂደን፣ ለእርሱ ከመንገራችን በፊት መበደላችንን ላገኘናቸው ሰዎች ሁሉ የምንናገረው ምን ያህል ጊዜ ይሆን? እንዲህ የምናደርገው ነገሩን ከልባችን ባለ መያዛችን ነው። እኛ ላይ የደረሰውን በደል ላገኘነው ሁሉ በመናገራችን እውነተኞች መሆናችንን የምናሳይ ይመስለናል። ምን ያህል እንደ ተበደልን ሌሎች ከእኛ ጋር ሲስማሙ፣ ዐቋማችን እውነት መሆኑን ያሳየንና የተጽናናን ይመስለናል። እንዲህ ያለው ዝንባሌ የሚያሳየው ራስ ወዳዳነትን ብቻ ነው።

አንኳሩ እውነት

መነሻ ሐሳባችን የእግዚአብሔር ፍቅር ከሆነ፣ በፍጹም አናፍርም። ፍቅር በፍጹም አይከስርም። ኢየሱስ እኛን እንደ ወደደ፣ እኛም ሌሎችን የምንወድ ከሆነ፣ ሰዎች ከእኛ ጋር መታረቅ ባይፈልጉ እንኳ፣ የተሟላ ነጻነት ይኖረናል። የሚከተለውን ጥቅስ በጥንቃቄ ተመልከቱ። የእግዚአብሔር ጥበብ ለማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋል ይችላል።

ቢቻላችሁ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።

- ሮሜ 12÷18

አንዳንዴ ሌሎች ከእኛ ጋር በሰላም መኖር የማይፈልጉበት ጊዜ ሊኖር ስለሚችል፣ ‹‹ቢቻላችሁስ›› ነው ያለው። ምናልባትም አንዳንዶች ለዕርቅ የሚያቀርቡት ቅድመ ሁኔታ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንድናመቻምች የሚያደርግ ሊሆን ይችላል። በሁለቱም መንገድ የሻከረውን ግንኙነት ማስተካከል አይቻልም።

‹‹በበኩላችሁ...›› መባሉንም ልብ አድርጉ። ለእውነት ያለንን ታማኝነት እስከ ጠበቅን ድረስ፣ ከሌላው ሰው ጋር ዕርቅ ለማድረግ በእኛ በኩል የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። ብዙ ጊዜ ግንኙነታችንን ለማስተካከል በምናደርገው ጥረት በቀላሉ ተስፋ እንቆርጣለን።

አንድ ጊዜ ከነበርኩበትበጣም ከባድ ሁኔታ በራሴ መንገድ እንዳልወጣ አንድ ወዳጄ፣ የሰጠኝን ምክር በፍጹም አልረሳውም። ‹‹ጆን፣ በራስህ መንገድ ከዚህ ሁኔታ ለመውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች ማቅረብ እንደምትችል አውቃለሁ። ግን ያንን ከማድረግህ በፊት በሚገባ መጸለይህንና ወደ ሁኔታው የእግዚአብሔር ሰላም ለማምጣት የሚቻልህን ሁሉ ማድረግህን እርግጠኛ ሁን›› ነበር ያለኝ።

ከዚያም በመቀጠል፣ ‹‹አንድ ቀን ወደ ኃላ ዘወር ብለህ ስትመለከትና ይህ ግንኙነት እንዳይሻክር የሚቻለኝን ሁሉ አድርጌ ነበር ወይ? ብለህ ራስህን ስትጠይቅ ይቆጭሃል። እውነትን

ሳታመቻምች የሚቻልህን ሁለ ማድረግህንና ያንን ያደረግኸው ሌላ አማራጭ ስላልነበረህ መሆኑን ማስረገጥ መልካም ነው።።›› አለ።።

ስለ ምክሩ ያንን ወዳጄን በጣም ነው የማመሰግነው፤ ምክሩ የእግዚአብሔር ጥበብ እንዳለበትም እረዳለሁ።።

ኢየሱስ እንዲህ ማለቱን አስታውሱ፣

ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና።።

- ማቴዎስ 5÷9

‹‹ምንም ግጭት እንዳይኖር የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው›› አይደለም ያለው።። ምንም ግጭት እንዳይኖር የሚፈልግ ሰው፣ እውነትን በማመቻመች እንኳ ቢሆን ሰላም እንዲኖር በማሰብ ፊት ለፊት መጋፈጥ አይፈልግም።። ሆኖም፣ ይህ እውነተኛ ሰላም አይደለም።። ዘለቄታ የሌለው፣ አርቲፊሻልና አስመሳይ ሰላም ነው።።

ሰላም የሚያወርድ ሰው ግን፣ የሚገኘው ዕርቅ ዘላቂነት እንዲኖረው በፍቅር ሄዶ እውነትን ይናገራል።። ይህ ሰው አርቲፊሻልና አስመሳይ ወዳጅነት እንዲኖር አይፈልግም።። ግልጽነትን፣ እውነትንና ፍቅርን ነው የሚፈልገው።። የሽንገላ ፈገግታ በማሳየት መበደሉን አይደብቅም።። ዘላቂነት ባለው ደፋር ፍቅር መሠረት ላይ ሰላምን ይገነባል።።

እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ እንዲሁ ነው።። እርሱ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም።። ይሁን እንጂ፣ ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተ እውነትን አያመቻምችም።። እንዲሁ ላይ ላዩን በሚደረግ ስምምነት ሳይሆን፣ በእውነተኛ መሰጠት ዕርቅ እንዲኖር ነው የሚፈልገው።። ይህ የትኛውም የክፋት ኃይል መበጠስ በማይችልበት ሁኔታ የፍቅርን ማሰሪያ ያጠነክራል።። እርሱ ለእኛ ሕይወቱን ሰጥቶናል።። እኛም እንደዚያ ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅብን።።

እዚህ ላይ አንኳሩ እውነት የእግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ልብ አድርጉ።። የእግዚአብሔር ፍቅር አይጠፋም፤ አይደበዝዝም፣

ማለቂያ ማብቂያም የለውም። የራሱን አይፈልግም። በቀላሉ አይበሳጭም (1 ቆሮንቶስ 13÷5)።

የእግዚአብሔር ፍቅር ማንኛውንም ዐይነት ኃጢአት እንደሚያሸንፍ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ጽፎአል።

> ፍቅራችሁ በጥልቅ ዕውቀትና በማስተዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እጸልያለሁ። ይኸውም ከሁሉ የሚሻለውን ለይታችሁ እንድታውቁ፣ እስከ ክርስቶስም ቀን ድረስ ንጹሐንና ነቀፋ የሌለባችሁ እንድትሆኑ፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሚገኘው የጽድቅ ፍሬ እንድትሞሉ ነው።
>
> - ፊልጵስዩስ 1÷9-11

ከመሰናክል ወጥመድ ነጻ በመሆን ረገድ ቁልፉ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር ሞልቶ የተትረፈረፈ ፍቅር፣ በየጊዜው ልባችን ውስጥ እያደገና እየተነከረ የሚሄድ ፍቅር መሆን አለበት።

በዚህ ዘመን ማኅበረ ሰባችን ውስጥ ያሉ ብዙዎች መናገር እንጂ፣ መሥራት በማይፈልግ ላይ ላዩን በሆነ ፍቅር ተታልለዋል። ከመሰናክል የሚጠብቀን ፍቅር፣ ሌላው ቀርቶ ለጠላቱ እንኳ መልካም እንዲሆን ያለ ስስት ራሱን ይሰጣል። በዚህ ዐይነቱ ፍቅር ስንመላለስ በሰይጣን ሽንገላ አንጠመድም።

መደምደሚያ

ርምጃ መውሰድ

ይህን መጽሐፍ በማንበባችሁ ባለፈው ጊዜ፣ ወይም በአሁኑ ጊዜ፣ ባላችሁ ግንኙነት አንዳች ነገር የያዛችሁባቸው ሰዎችን የእግዚአብሔር መንፈስ አሳስቦአችሁ ይሆናል። እንደዚያ ከሆነ፣ የሚከተለውን አጭር የመፈታት ጸሎት አብረን እንድንጸልይ እጠይቃችኃለሁ።

ሆኖም፣ ከመጸለያችሁ በፊት ከእናንተ ጋር አብሮ ወዳለፈው ጊዜ ልምምምችሁ እንዲመለስና አንዳች ነገር የያዛችሁባቸው ሰዎችን ወደ ልባችሁ እንዲያመጣ መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት። እነዚያ ሰዎች እነማን እንደ ሆኑ እያሳያችሁ እያለ፣ በፊቱ ፀጥ በሉ። በመሠረቱ፣ በቦታው የሌለ ነገርን መፈለግ የለባችሁም። መጠራጠር በማትችሉበት ሁኔታ እግዚአብሔር በግልጽ ወደ ልባችሁ ያመጣቸዋል። እንደዚያ በሚያደርግበት ጊዜ ሕመም ሊኖር እንደሚችል መዘንጋት የለባችሁም። ያም ቢሆን፣ አትፍሩ። እናንተን ለማጽናናት እርሱ ሁሌም ከጐናችሁ ነው ያለው።

እነዚያ በደል ያደረሱባችሁን ሰዎች ከወቀሳና ከበደል እየፈታችኃቸው እያለ፣ እያንዳንዱን በአእምሮአችሁ ውስጥ ሳለዋቸው፤ እያንዳንዱን ሰው በግል ይቅር በሉ። ለእናንተ ያለባቸውን ዕዳ ሰርዙ። ከዚያ ይህን ጸልዩ፤ ሆኖም፣ በእነዚህ ቃሎች መወሰን የለባችሁም። ይህን ጸሎት እንደ መመሪያ ተጠቀሙበት፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት አለባችሁ።

አባት ሆይ፣ በደል ያደረሱብኝን ሰዎች ይቅር ባለ ማለት፣ አንተ ላይ ኃጢአት ማድረጌን በኢየሱስ ስም እቀበላለሁ። ለዚህ ንስሐ እገባለሁ፤ የአንተን ይቅርታም እጠይቃለሁ።

ከአንተ ውጪ ይቅር ልላቸው እንደማልችልም አውቃለሁ። ስለዚህ..... (እዚህ ላይ የሰዎቹን ስም ጨምሩ፣ እያንዳንዱን ከእስራት ፍቱ) ከልቤ ይቅር ማለት እፈልጋለሁ። እኔ ላይ ያደረሱትን በደል ሁሉ ከኢየሱስ ደም በታች አኖራለሁ። ከእንግዲህ የእኔ ባለ ዕዳዎች አይደሉም። እኔ ላይ የፈጸሙትን ኃጢአት ይቅር ብያለሁ።

ሰማያዊ አባቴ፣ እርሱን የበደሉትን አንተ ይቅር እንድትል፣ ጌታዬ ኢየሱስ አንተን እንደ ጠየቀ ሁሉ፣ እኔም፣ እኔ ላይ ኃጢአት በፈጸሙ ሰዎች ላይ የአንተ ይቅርታ እንዲመጣ እጸልያለሁ። እንድትባርካቸውና ከአንተ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ማድረግ ወደሚችሉበት እንድትመራቸው እጸልያለሁ። አሜን። አሁን ከበደል እስራት የፈታችኃቸውን ሰዎች ስም በማስታወሻችሁ ጻፉ፤ በዚህ ቀን እነርሱን ይቅር ለማለት ውሳኔ ማድረጋችሁን አስፍሩ።

ነጻ እንደ ሆናችሁ ለመዝለቅ፣ ምናልባት ጥረት ወይም ልምምድ ማድረግ ይኖርባችሁ ይሆናል። (ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ ካልሆነላችሁ እንደ ገና ምዕራፍ ዐሥራ ሦስትን አንብቡ።) ልክ ለራሳችሁ በምትጸልዩበት ሁኔታ፣ ለእነርሱም ለመጸለይ ቁርጥ ውሳኔ አድርጉ። ማስታወሻው ያንን ለማስታወስ ይረዳችኃል። ክፉ ሐሳቦች ወደ አእምሮአችሁ መምጣት ከቀጠሉ፣ በእግዚአብሔር ቃል አፍርሷቸው፤ ይቅር ለማለት ውሳኔ ማድረጋችሁን ተናገሩ። ይቅር ማለት የምትችሉበትን ጸጋ እንዲሰጣችሁ ጸልያችሁ ነበር፤ ይቅር አለማለት ከእርሱ ጸጋ የበለጠ ብርቱ አይደለም፤ ደፋር ሁኑ፤ መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደሉ።

ልባችሁ እንደ ተስተካከለና እንደ ተረጋጋ እርግጠኛ ከሆናችሁ፣ ወደ በደሉዋችሁ ሰዎች ሂዱ፤ የምትሄዱት ለእናንተ ሳይሆን፣ ለእነርሱ ጥቅም ሲባል ዕርቅ ለማድረግ መሆኑን አስታውሱ። ይህን ስታደርጉ ድል ይረጋገጣል። አሸናፊዎች ትሆናላችሁ (ማቴዎስ 18÷15 ይመ.)። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው።

እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው፣ እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ ዘላለም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኃይልና ሥልጣን ይሁን።

- ይሁዳ 24-25

ማስታወሻዎች

ምዕራፍ አንድ
ማን ነው የሚሰናከል - እኔ?

1. W.E. Vine, Merrill Unger, and William White Jr., *An Expository Dictionary of Biblical Words* (Nashville, TN: Thomas Neison, 1984), s.v. "offence, Offend" **(ከዚህ በኃላ** *Vine's Expository Dictionary* **በመባል ይጠቀሳል)።**

ምዕራፍ ስድስት
ከእውነታ መደበቅ

1. Vine's Expository Dictionary, s.v. **‹‹ልጅ››** "Child"
2. Vine's Expository Dictionary, s.v. **‹‹ልጅ››** "Son"
3. *Vine's Expository Dictionary of New Testament Words* (unabridged edition) **‹‹ልጅ››** "Son" **በሚለው መግቢያ ላይ በመወለድ ልጅ በመሆንና (ቴክኖን)፣ መስሎ በመገኘት ልጅ በመሆን (ሁዮስ) መካከል ስላለው ልዩነት ጸሐፊው የሚከተለውን አሳማኝ ማብራሪያ ይሰጣል። ‹‹ሮሜ 8÷14-21 አማኞችን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች›› - ቴክኖን እና ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች›› – ሁዮስ እያለ ሲጠራቸው በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ያሳያል። ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች›› – (ቴክኖን) መሆናቸውንና ከዚህም የተነሣ ከክርስቶስ ጋር አብረው ወራሽ መሆናቸውን መንፈስ ለመንፈሳቸው ይመሰክራል። ይህ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ልደታቸውን ነው (ቁ. 16-17)። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ እግዚአብሔር ልጆች ናቸውና›› ይላል። ‹‹ሌላ ሳይሆን – እነዚህ›› ፀባይና ድርጊታቸው ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና እርሱን የሚመስሉ መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል።**
‹‹ቁጥር 44,45 ላይ ጌታ ኢየሱስ ሁዮስ (huios) **የሚለውን ቃል የተለየ ፋይዳ ባለው መልኩ ሲጠቀምበት፣ ‹‹ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኃለሁ። እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ›› ብሏል። ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ማድረግ የነበረባቸው የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ሳይሆን፣ ቀድሞውኑ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆኑ ነው (እዚህ ላይ፣ ‹‹አባታችሁ›› በማለት መናገሩን ልብ አድርጉ)።**

የእግዚአብሔር ልጆች የመሆናቸው እውነት በፀባያቸው እንዲገለጥ ነው። በተጨማሪ 2 ቆሮንቶስ 6÷17-18 ይመ።››

4. The Rockford Institute, Center on the Family in America (Rockford, IL).

ምዕራፍ ሰባት

ጽኑ መሠረት

1. *Zondervan Topical Bible* (Grand Rapids, MI: Zondervan, 1969), s.v. **‹‹ስምየን››**
2. *Vine's Expository Dictionary,* s.v. **‹‹ዐለት››**
3. **ከዚያው የተወሰደ።**

ምዕራፍ ስምንት

የሚናወጥ ነገር ሁሉ ይናወጣል።

1. Logos Bible Study Software for Microsoft, Version 1.6 (Oak Harbor, WA: Logos Research Systems Inc, 1993) s.v. **‹‹ማበጠር››**
2. J.D. Douglas, *New Bible Dictionary* (Wheaton, IL: Tyndale House, 1982), s.v. **ሁለተኛ እትም ‹‹ጴጥሮስ››**

ምዕራፍ ዐሥራ ዐንድ

ይቅር ካላላችሁ – ይቅር አትባሉም

1. Margin note: New King James Version (Nashville, TN: Thomas Nelson, 1988).
2. Logos Bible Study Software, version 1.6 (Oak Harter, WA: Logos Research Systems Inc., 1993).
3. Merriam-Webster's Collegiate Dictionary, **ዐሥረኛ እትም** (Springfield, MA: Merriam-Webster Inc., 1993)

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

በቀል – አደገኛው ወጥመድ

1. Francis Frangipane, *The Three Battlegrounds* (Cedar Rapides, IA: Advancing Church Publications, 1989), 50.

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

ከወጥመዱ ማምለጥ

1. *Vine's Expository Dictionary,* s.v. **‹‹ልምምድ››**

ምዕራፍ ዐሥራ አራት

የመጨረሻው ግብ – ዕርቅ

1. *Vine's Expository Dictionary,* s.v. **‹‹ራካ››**
2. **ከዚያው የተወሰደ**

የሰይጣን

ሽንገላ

በጽሞና ማሰላሰያ የታከለበት

John Bevere

ማውጫ

	መግቢያ	218
ቀን 1	ማን ነው የሚሰናከል – እኔ?	219
ቀን 2	የልብ እውነተኛ ሁኔታ	222
ቀን 3	የብዙዎች መሰናከል	225
ቀን 4	ራስን መጠበቂያ አጥር	228
ቀን 5	ይህ እንዴት እኔ ላይ ይሆናል?	232
ቀን 6	እግዚአብሔር ሁሉንም እየተቆጣጠረ ነውን?	235
ቀን 7	አባት ሲበድል	238
ቀን 8	ማን ይበቀልልኛል?	241
ቀን 9	መንፈሳዊ ከርታቶች	243
ቀን 10	የተተከለ ማደጉ አይቀርም	246
ቀን 11	ከእውነታው መደበቅ	249
ቀን 12	ራስን መከላከል	252
ቀን 13	ጽኑ መሠረት	255
ቀን 14	ከ... ሌላ ምርጫ የለም	258
ቀን 15	የሚናወጥ ነገር ሁሉ መናወጡ አይቀርም	261
ቀን 16	ለትሑታን ጸጋ ይሰጣል	265
ቀን 17	የመሰናከያ ዐለት	268
ቀን 18	እንዳናሰናክላቸው	271
ቀን 19	መብታችንን መተው	274
ቀን 20	ይቅር ካላላችሁ ይቅር አትባሉም	277

ቀን 21 ይቅር ያላለው አገልጋይ 280
ቀን 22 በቀል አደገኛው ወጥመድ 282
ቀን 23 ለንጉሥነት የታጨው ረክሶ ተገኘ 284
ቀን 24 ከወጥመዱ ማምለጥ 287
ቀን 25 ፊት ለፊት በመገናኘት መፈወስ 290
ቀን 26 የመጨረሻው ግብ – ዕርቅ 293
ቀን 27 ከተበደለው ወገን ይቅርታ መጠየቅ 296
ቀን 28 የበደላችሁትን ሰው መቅረብ 299
ቀን 29 የመጨረሻ ነገር 301
ቀን 30 ርምጃ መውሰድ 304

መግቢያ

የሰይጣን ሽንገላ የተሰኘው የዚህ ዐሥረኛ እትም ክፍል ወደ ሆነው የጽሞና ማሰላሰያ እንኳን መጣችሁ። ይህ የጽሞና ማሰላሰያ የተዘጋጀው በጽሞና ጊዜያችሁ እንድትጠቀሙበት ነው። ከመጽሐፉ ጋር የተያያዙትን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች በጥልቀት መመርመር እንድትችሉ ይረዳችኃል፤ የመሰናከል ወጥመድን እንድታርቁ፣ ባለፈው ጊዜ በሕይወታችሁ ላይ ካሳደረው ጫና ንስሐ እንድትገቡና ነጻ እንድትሆኑ ያስችላችኃል። መሰናክልን በተመለከተ እግዚአብሔር ያለውን ዕቅድ መረዳት እንድትችሉ ልንረዳችሁም እንፈልጋለን።

እያንዳንዱ የየዕለቱ የጽሞና ማሰላሰያ በሚከተለው መልኩ ተዘጋጅቷል።

- የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን በቀጥታ መቀበል እንድትችሉ።
- ከሰይጣን ሽንገላ ለዚሁ ዓላማ የተወሰኑ ገጾችን እንድታነቡ።
- ጤናማ፣ አፍቃሪና ከመሰናከል ወይም ከበደል ነጻ የሆነ ግንኙነትን በማዳበር ረገድ ሕይወት ሰጪ መርሖዎችን እንድትመለከቱ።
- ካለፈው ጊዜ በደል ቀንበር ነጻ ሆናችሁ መዝለቅ እንድትችሉ ይረዳችኃል።

ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከራሳችሁ ጋር፣ ከቤተ ሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከጓደኞቻችሁ፣ ከሥራ ባልደረቦቻችሁ ሌላው ቀርቶ፣ ራሳቸውን የእናንተ ጠላት አድርገው ከሚቆጥሩ ጋር የሰይጣን ሽንገላን ማለትም መሰናክልን ለመቃወም፣ የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት፣ ይህ የጽሞና ማሰላሰያ ውጤታማ መሣሪያ እንዲሆንላችሁ እንጸልያለን።

ቀን 1

ማን ነው የሚሰናከል – እኔ?

የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግሥተኛም መሆን ይገባዋል፤ እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር ንስሐን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ፣ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል፤ ይኸውም ወደ አእምሮአቸው ይመለሳሉ፤ ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጐ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመድም ያመልጣሉ በማለት ነው።

- 2 ጢሞቴዎስ 2÷24-26

(ገጽ 5-7 አንብብ)

አንድ ወጥመድ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ ሁለት ነገሮች መሟላት እንዳለባቸው ማንኛውም እንስሶችን አጥምዶ የሚያውቅ ሰው ይረዳል - እንስሳው ተደናቅፎ እንዲወድቅበት ስውር ቦታ መሆን አለበት፣ እንስሳውን ለማመለልና ለመሸንገል አንድ አጓጊ ነገር ላዩ ላይ መደረግ አለበት።

በሕይወታቸው ካለው ቁስል፣ ስብራት፣ መሰናክል ወይም በደል የተነሣ ብዙዎች እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ባለው ዓላማና ጥሪ መሠረት በሚገባ እየተንቀሳቀሱ አይደለም።

የነፍሳችን ጠላት ሰይጣንም እኛን ለመሸንገልና አጥምዶ ለመያዝ በሁለቱም ዘዴዎች ይጠቀማል። ሁለቱም ድብቅና የሚያማልሉ ናቸው። ሰይጣንና ሰራዊቱ ብዙዎች እንደሚያስቡት አሠራራቸው ግልጽና የታወቀ አይደለም። በጣም ተንኰለኛ ነው፤

ማሳሳትና ማታለል ደስ ያሰኘዋል። አሠራሩ ሸፍጠኛ ነው፤ ረቂቅና ዘዴኛ ነው።

በጣም አሳሳችና ስውር ከሆኑ ማጥመጃዎቹ አንዱ ማንኛውንም ክርስቲያን ገጥሞት የሚያውቅ ሲሆን፣ ያም መሰናከያ ወይም በደል ነው። ያንን ከተቀበልንና በልባችን ካብላላነው እንሰናከላለን ወይም እንበድላለን።

የተሰናከለ ሰዎች ብዙ ፍሬ ያፈራሉ።

ጉዳት	ቂጣ	ንዴት
ቅንዓት	ምቀኝነት	ቅርታ
ፀብ	መራራነት	ጥላቻ

በሕይወታቸው ካለው ቁስል፣ ስብራት፣ መሰናክል ወይም በደል የተነሣ ብዙዎች እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ባለው ዓላማና ጥሪ መሠረት በሚገባ እየተንቀሳቀሱ አይደለም። ውስጣቸው ያለውን ዕምቅ ኃይል ተግባር ላይ በማዋል ረገድ ሽባዎችና ስንኩሎች ሆነዋል። በተለይ ደግሞ እንደ እነርሱ አማኝ ከሆነ ወገን የሚደርስባቸው ጉዳት እንደ ዳዊት ሁሉ እነርሱም፣ ‹‹የሚዘልፈኝ ጠላት አይደለምና፤ ቢሆንማ ኖሮ በታገሥሁት ነበር፤ የሚጠላኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ ባላንጣ አይደለም፤ ቢሆንማ፣ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር። ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ፤ እኩያዬ፣ ባልንጀራዬና ወዳጄ፤ በእግዚአብሔር ቤት አብረን በሕዝብ መካከል ተመላለስን፤ ደስ የሚል ፍቅር በአንድነት ነበረን›› እንዲሉ አድርጐአቸዋል (መዝሙር 55÷12-14)።

አንተን ያሰናከሉ የአምስት ሰዎች (1 በጣም የቅርብህ የሆነ፣ 4 በጣም የራቀ ቀረቤታ ያላችሁ) ሰዎች ስም ዘርዝር።

1. _____
2. _____
3. _____
4. _____

5. _____

የተሰናከለ ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ማስተዋላቸውም ጨልሞአል። መስሎ በታያቸው፣ በግምት፣ ወይም ከሌሎች ከሰሙት ተነሥተው ሰዎች ላይ መፍረድ ይጀምራሉ። በዚህ የጽሞና ማሰላሰያ ከመሰናከያ ወጥመድ ለመራቅና አሁንም እስረኛ ያደረጉንን ባለፈ ጊዜ የደረሱብንን መሰናከያዎች ለማሸነፍ የሚረዳንን የእግዚአብሔር መንገድ እንማራለን።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

የሰይጣንን ሽንገላ ለማስወገድ የሚረዳህን ርዳታና ጥበብ እንዲሰጥህ እግዚአብሔር መለመን።

_____

_____

_____

ቀን 2

የልብ እውነተኛ ሁኔታ

አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኃል። እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው።

- 1 ጴጥሮስ 1÷6-7

(ገጽ 7-11 አንብብ)

ጣላት አንድን ሰው በተሰናከለበት ሁኔታ እንዲዘልቅ ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ መበደሉን ወይም መሞዳቱን በትዕቢት መሸፈኛ ሰውሮ እንዲይዝ በማድረግ ነው። ትዕቢት ያላችሁበትን እውነተኛ ሁኔታ እንዳትቀበሉ ያግዳችኃል። ትዕቢት ራሳችሁን እንደ ተጠቂ እንድታዩ ያደርጋችኃል። ተገቢ ያልሆነ ነገር እንደ ተደረገባችሁ ስለምታምኑ ይቅር ያለ ማለት ውስጣችሁ ይስተናገዳል። ምንም እንኳ የልባችሁ እውነተኛ ሁኔታ ከእናንተ ከራሳችሁ እንኳ ሊደበቅ ቢችልም፣ ከእግዚአብሔር ግን መደበቅ አይችልም። በሌሎች መበደላችሁ ይቅር ላለ ማለት መብት አይሰጣችሁም። ስሕተት ቢደራረብ ትክክለኛ ነገር አይሆንም።

የወርቅ እውነተኛነት በእሳት ተፈትኖ ይታያል (ራእይ 3÷18)። ወርቅ ከሌሎች ነገሮች ጋር ከተቀየጠ ይጠነክራል፤ በቀላሉ አይተጣጠፍም፤ በቀላሉ ይዝጋል። ወርቅ በእሳት ውስጥ

በሚያልፍበት ጊዜ ሌሎቹ ነገሮች ተቃጥለው ሲጠፉ፣ እርሱ ግን ይጠራል፤ ይነጻል፤ ተጣጣፊም ይሆናል።

በሌሎች መበደላችሁ ይቅር ላለ ማለት
መብት አይሰጣችሁም።
ስሕተት ቢደራረብ ትክክለኛ ነገር አይሆንም።

የእኛን ልብ በተመለከተም ይኸው ነው። የደረሰብንን በደል ስናወጣ ስናወርድ ይበልጥ ልባችን በትዕቢትና በኃጢአት እየጠነከረ በሄደ መጠን፣ በዚያው ልክ እግዚአብሔርን የምንቃወም እንሆናለን። እግዚአብሔር ልባችንን ማጥራትና ማንጻት ይፈልጋል።

1 ጴጥሮስ 1÷6-7 አንብብና በእንዴት ያለ ሁኔታ እግዚአብሔር እኛን እንደሚያጠራና እንደሚያነጻ በአጭሩ ግለጥ።

_____

_____

_____

በመከራ፣ በችግርና አዳጋች በሆኑ ሁኔታዎች አማካይነት እግዚአብሔር ያነጻናል፤ የእነዚህ ሁኔታዎች እሳት ይቅር ያለ ማለትን፣ ቂጣን፣ ምቀኝነትንና ቅንዓትን የመሳሰሉ ንጹሕ ያልሆኑ ነገሮች ይለያል፤ የእግዚአብሔር ባሕርይ (ንጽሕናና ቅድስና) ሕይወታችን ውስጥ እንዲያድግ ያደርጋል።

እስቲ፣ ስለ ራስህ ሕይወት አስብ። የእግዚአብሔር ባሕርይ በሕይወትህ እንዳያድግ መሰናክል የሆኑ ልብህ ውስጥ ያሉ ንጹሕ ያልሆኑ ነገሮች ምንድናቸው?

_____

_____

_____

አጥርተን ወይም በትክክል ማየት መቻል፣ ከመሳት ነጻ በመሆን ረገድ ቁልፍ መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮአል። በደል ሲደርስብን ወይም ስንሰናከል ብዙውን ጊዜ ራሳችንን እንደ ተጠቂዎች እንቆጥራለን፤ የበደሉንንም ሰዎች እናማርራለን። ውስጣችን እየተብላላ ያለ አለታዊ ነገሮች ይፋ በሚወጡበት ጊዜ ትክክልና ተገቢ መሆናቸውን ለማሳመን ምክንያት እንደረድራለን። አንዳንዴም የበደሉንን ሰዎች በሚያስታውሱን ወገኖች እንኳ ቅር እንሰኛለን። ኢየሱስ፣ ‹‹አጥርተህ ለማየት እንድትችል ዐይንህን በኩል እንድትኳል እመክርሃለሁ›› ይላል (ራእይ 3÷18)

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ሌሎችን በመውቀስህና በማማረርህ ንስሐ በማደረግ የልብህን እውነተኛ ሁኔታ ማየት የምትችልበትን ዐይን እንዲሰጥህ ጌታን ጠይቅ።

_____

_____

_____

ቀን 3

የብዙዎች መሰናከል

ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ ጥፋትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። በጐ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ካልቆረጥን፣ ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን።

- ገላትያ 6÷8-9

(ከገጽ 13-16 አንብብ)

ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚመለስ ብዙዎች ይስማማሉ። እርሱ የሚመለስብትን ትክክለኛ ቀን ለማመልከት መሞከር ጥቅም የለውም። ያንን የሚያውቅ አብ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ወቅቱን ማወቅ እንደምንችል ተናግሮአል፤ ያም በዚህ ዘመን ነው! በቤተ ክርስቲያን፣ በእስራኤልና በተፈጥሮ ላይ የአሁኑን ያህል ትንቢቶች ሲፈጸሙ የታየበት ዘመን አልነበረም። ከእርሱ መመለስ ምልክቶች አንዱ ‹‹የብዙዎች መሰናከል›› መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮአል፤ የሚሰናከሉት ብዙዎች እንጂ፣ አንዳንዶች አለመሆናቸውን ልብ አድርጉ። አንተ ራስህ ወይም አንተ የምታውቃቸው ሰዎች በቀላሉ የምትሰናከሉ ናችሁን?

ፍቅርን በምሰጥበት ጊዜ ሁሉ
በመንፈስ እየዘራሁ መሆኔንና ውሎ አድሮም
ፍቅርን እንደማጭድ መረዳት ችያለሁ።

በሚከተሉት ምን ያህል እንደምትሰናከል ለማሳየት በእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር መስመር ላይ X ምልክት አድርግ።

የቤተ ክርስቲያን ሰዎች በቀላሉ የሚሰናከሉ ይመስላል።

ብዙ ጊዜ እውነት ነው። አልፎ አልፎ እውነት ነው።

እኔም ራሴ በቀላሉ እሰናከላለሁ።

ብዙ ጊዜ እውነት ነው። አልፎ አልፎ እውነት ነው።

ጓደኞቼ በቀላሉ ይሰናከላሉ።

ብዙ ጊዜ እውነት ነው። አልፎ አልፎ እውነት ነው።

በመሥሪያ ቤቴ ያሉ ሰዎች በቀላሉ ይሰናከላሉ

ብዙ ጊዜ እውነት ነው። አልፎ አልፎ እውነት ነው።

የሥጋ ዘመዶቼ በቀላሉ ይሰናከላሉ።

ብዙ ጊዜ እውነት ነው። አልፎ አልፎ እውነት ነው።

ከመካከለ በስተ ግራ በኩል ባለው ላይ ብዙ X ካደረግህ፣ በዚህ ዘመን ሰዎች ምን ያህል የሚሰናከለ እንደሚመስለ አንተ ራስህ ልብ አድርገሃል ማለት ነው። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ አማኝ፣ የእርሱን ፍቅር ያጭዳል፤ የሰይጣን ሽንገላ የሆነውን መሰናክል ለመውሰድ ፈቃደኛ አይሆንም።

ፍቅርን በምሰጥበት ጊዜ ሁለ በመንፈስ እየዘራሁ መሆኔንና ውለ አድሮም ፍቅርን እንደማጭድ መረዳት ችያለሁ። ያ ፍቅር የሚታጨደው ከየት እንደ ሆነ በእርግጠኝነት ባላውቅም፣ የመከር ጊዜ እንደሚኖር ግን አውቃለሁ። ከምወዳቸው ሰዎች አንድ ዐይነት ፀባይ ወይም ዝንባሌ የምጠብቅ ከሆነ ራሴን ለመሰናከል አመቻችቼአለሁ ማለት ነው። ብዙ በጠበቅሁ መጠን፣ በዚያው ልክ ብዙ እሰናከላለሁ።

ከቁጥር 1 (በጣም በጥቂቱ) እስከ 5 (በጣም ብዙ) ባሉት የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ሕይወትህን እንዴት ትመዘነዋለህ፤ (መልስህን ክብ አድርግበት)

ከሌሎች ብዙ እጠብቃለሁ። 1 2 3 4 5

በቀላሉ ተስፋ እቆርጣለሁ። 1 2 3 4 5

የምወደው ሁኔታን በማገናዘብ ነው። 1 2 3 4 5

የምባርከው እኔም እንድባረክ ነው። 1 2 3 4 5

ክብ ያደረግህባቸውን ቁጥሮች በሙሉ ደምራቸው። ውጤቱ ከዐሥር በላይ ከሆነ፣ ራስህን ለመሰናከል እያመቻቸህ ነው ማለት ይቻላል።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ከሌሎች የመጠበቅ ዝንባሌህን ማስወገድ እንድትችል ሁኔታን ግምት ውስጥ ሳታስገባ ሰዎችን መውደድ እንድትችል እንዲረዳህ እግዚአብሔርን ጠይቅ።

_____

_____

_____

ቀን 4

ራስን መጠበቂያ አጥር

ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው። በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን።

- 2 ቆሮንቶስ 10÷4-5

(ከገጽ 16-21 አንብብ)

የተሰናከለ ወይም በደል የደረሰበትን ሰው ወደ ቀድሞው ቦታው መመለስ ዙሪያውን በጠንካራ ግንብ ከተከበበ ከተማ ይልቅ፣ በጣም ከባድ ነው። ግንቡ የከተማዋ ደኅንነትና ጥበቃ እንዲሆን ነበር የተሠራው። እንዲመጡ የማይፈለጉና ለመውረር የሚመጡ ሁሉ እንዳይገቡ ይከላከላል።

ራሳችንን ከመሰናከል ወይም ከበደል
በመከለል ረገድ በሥጋችን መተማመን ሳይሆን፣
በእግዚአብሔር ወደምንተማመንበት ደረጃ መምጣት አለብን።

አንዴ ጉዳት ከደረሰብን፣ ድጋሚ የዚያ ዐይነት ቁስል እንዳይደርስብን ራሳችንን ለመጠበቅ ስንል ብዙ ጊዜ ዙሪያችንን በግንብ እናጥራለን።

አንተ ውስጥ የምታየውን ዝንባሌ ✓ አድርግበት፤ ራሳችን የሠራነው ግንብ ውስጥ ሆነን...

☐ **ከእነማን ጋር መገናኘት እንዳለብኝ የምመርጥ ነኝ።**

- ☐ ለሌሎች ክፍት የምሆነውና ለጥቃት ለመጋለጥ እንኳ ፈቃደኛ የምሆነው።
- ☐ ይጐዱናል ብለን ለምንፈራቸው ዝግ እንሆናለን።
- ☐ የእኛ ዕዳ በደል ያለባቸውን ሰዎች በተመለከተ ከመናገር ቁጥብ ነን።
- ☐ ክፍት የምንሆነው የእኛ ለሆኑት ብቻ ይሆናል።

ራሳችንን ከመሰናከል ወይም በሌሎች ከመጐዳት ለመከላከል በምናደርገው ሙከራ ከሌሎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ የማንችል፣ ራሳችን በፈጠርነው ግንብ ውስጥ እስረኞች ሆነን ራሳችንን እናገኘዋለን። ትኩረታችን ወደ ውስጥ እና የእኛን ብቻ ማሰላሰል ላይ ይሆናል። መብታችንን ወደ ማስጠበቅና የሚኖረንን ግንኙነት በጥንቃቄ ወደ መምረጥ እናዘነብላለን። ወደ ፊት ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስብን ለማረጋገጥ በምናደርገው ጥረት ጉልበታችንን እናባክናለን። ይሁን እንጂ፣ ጉዳት ሊደርስብን የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ካልተገነዘብን፣ ሁኔታን ግምት ውስጥ ሳናስገባ መውደድ አንችልም። ሁኔታን ግምት ውስጥ የሚያስገባ ፍቅር ለሰዎች እኛን የመበደል መብት ይሰጣል።

እኛን ለመጉዳት መብት የሰጠናቸውና ከግንቡ አጥር ውጪ ያደረግናቸውን ሰዎች በመዘርዘር የሚከተለውን ዝርዝር አሟላ።

ሊጐዱኝ መብት የሰጠኋቸው ሰዎች

_____

_____

_____

ለግንቡ አጥር ውጪ ያደረግኋቸው ሰዎች

_____

_____

_____

ራሳቸውን የሚከልለበት ግንብ የሚሠሩ ሰዎች፣ ሁሌም ቢሆን ዐቋማቸውንና ሌሎችን የሚያርቁበትን ምክንያት የሚደግፍላቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ፈልገው ማግኘት አይሳናቸውም፤ ሆኖም፣ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ተረድተዋል ማለት አይደለም። ፍቅር የሌለው የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት፣ አደገኛ ነው፤ ትዕቢትና አጉል ሕግ አጥባቂነትን ያስከትል። (1 ቆሮንቶስ 8÷1-3)። ይቅር ባለ ማለት ኃጢአታችን ንስሐ ከማድረግ ይልቅ ባደረግነው ሁሉ ትክክል እንደ ሆንን ለማሳየት ምክንያት ይሰጠናል።

የእግዚአብሔር ፍቅር የሌለው ዕውቀት ወደ መሳት፣ በተለይ ደግሞ በሐሰተኛ ነቢያት ወደ መሳት ይመራል። ኢየሱስ፣ ‹‹ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ›› በማለት አስጠንቅቆናል (ማቴዎስ 24÷11)። እንዲህ ያሉ ነቢያት በዋናነት የሚያስቱት ፍቅር በቀዘቀዘበት ረጃጅም ግንቦች ተከብበው የሚኖሩትን ነው (ቁ. 12)።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ አማኞች መካከል ራሳችንን የመከላከል ወይም ሌሎችን አሳልፎ በመስጠት እንኳ ቢሆን ራስን የመጥቀም ፍላጐት ያይላል። ሌሎችን አሳልፎ መስጠት ወይም ሌሎች ላይ ክህደት መፈጸም ከኪዳኑ መራቃችን የሚገለጥበት የመጨረሻ ደረጃ ነው። የዚህ ዐይነቱ ክህደት ከተፈጸመ፣ ያንን ተክትሎ እውነተኛ ንስሐ ካልመጣ በቀር፣ ግንኙነቱን እንደ ገና ማደስ በጣም ይከብዳል።

ራሳችንን ከመሰናከል ወይም ከበደል በመከለል ረገድ በሥጋችን መተማመን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ወደምንተማመንበት ደረጃ መምጣት አለብን።

የመሰናከል ኃጢአት በጣም ከባድ ነው። ቶሎ መፍትሔ ካልተፈለገለት የኃላ ኃላ ወደ ሞት ሊመራ ይችላል። የመሰናከልን ግንብ የመሥራት ፈተናን ስንቃወም እግዚአብሔር ታላቅ ድል ይሰጠናል።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

የገነባኸውን ግንብ እንድታፈርስ፣ ለጥቃት ለመጋለጥና ከማንኛውም መሰናክል ንስሐ የምትገባበትን ጸጋ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን መጠየቅ።

_____

_____

_____

ቀን 5

ይህ እንዴት እኔ ላይ ይሆናል?

ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው... እናንተ እኔን ለመጉዳት አሰባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው።

- ዘፍጥረት 50÷19-20

(ገጽ 23-26 አንብብ)

የተሰናከለ ወይም በደል የደረሰባቸው ሰዎች ሁሉ በሁለት ይመደባሉ - በእርግጥ የተበደሉና ምንም በደል ሳይደርስባቸው እንደ ተበደሉ የሚያስቡ።

በእርግጥ በደል የደረሰባችሁ ከሆናችሁ፣ እንደዚያ መሆኑ ለመሰናከል በቂ ምክንያት ሊሆናችሁ እንደሚችል ታስቡ ይሆን? አንድ ሰው ሆን ብሎ እናንተን የጐዳበትን ጊዜ ለጥቂት ደቂቃ አስቡ። ምላሻችሁ ምን ነበር? ከደረሰባችሁ በደል የተነሣ በሰውየው ተሰናክላችኋልን? ይህ ለመሰናከል ወይም ለደረሰባችሁ በደል ሁሌም የምትሰጡት ምላሽ ነውን?

ከሚከተሉት ዝርዝሮች ስ1 (የሁልጊዜ ምላሽ) እስከ 5፣ (አልፎ አልፎ የምሰጠው ምላሽ) በደልን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ የምትሰጡትን ምላሽ አስፍሩ።

_____ በጣም እናደዳለሁ።

_____ ወዲያው ይቅር እላለሁ።

_____ ቶሎ አልናደድም።

_____ አንድን ሰው ይቅር ለማለት ብዙ እቸገራለሁ።

_____ ከበደለኝ ሰው እርቃለሁ።

_____ ዕርቅ እፈልጋለሁ።

ከላይ ላለ፡ት ዐረፍተ ነገሮች የሰጣችሁ፡ት አለ፡ታዊ ምላሾች ከበለጠ አንድ ሰው በደል ካደረሰባችሁ የመሰናከል መብት እንዳላችሁ ይሰማች፡ኃል ማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በዚያ መንገድ ምላሽ መስጠት የለባችሁም።

የዮሴፍን ታሪክ አስቡ። (ዘፍጥረት 37-48 አብብቡ)። የዮሴፍን ቃልና ተግባር እንዴት ነው የምትገመግሙ፡ት?

ዮሴፍ ምን ዐይነት ምላሽ እንደ ሰጠ ለማመልከት በእያንዳንዱ መስመር X አድርጉ።

ተሰናክሎአል። ይቅር ብሎአል።

ስላለበት ሁኔታ ሌሎችን ወቅሶአል። በእግዚአብሔር ተማምኖአል።

በቀል ፈልጓል። መታረቅ ፈልጐአል።

እናንተ በዮሴፍ ቦታ ብትሆኑ ኖሮ፣ ምን ዐይነት ምላሽ ነበር የምትሰጡት? ለመሰናከል ምክንያት እንዳላችሁ ታምኑ ነበርን?

ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች ጋር
ያለንን ግንኙነት ለማበላሸት
ወደ ሕይወታችን መግቢያ ቀዳዳ ማግኘት
እንዲችል በእርሱን የመሰናከል
ወጥመድ እንድንጠመድለት ሰይጣን ተስፋ ይፈልጋል።

ሰይጣን በፈለገ ጊዜ እኛን ማጥፋት ቢችል ኖሮ ከረጅም ጊዜ በፊት ጨርሶ ያጠፋን ነበር። ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች ጋር

ያለንን ግንኙነት ለማበላሸት ወደ ሕይወታችን መግቢያ ቀዳዳ ማግኘት እንዲችል በእርሱን የመሰናከል ወጥመድ እንደምንጠመድለት ሰይጣን ተስፋ ይፈልጋል። የእርሱን ማጥመጃ ወይም ሽንገላ አትቀበለ፣ ያኔ ሰይጣን እናንተን መንካት አይችልም!

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

መሰናክልን የምታሰወግድበትና በሕይወትህ ላለው አሰቸጋሪ ሁኔታ በሌሎች ከማማረር ይልቅ፣ በእርሱ እንድትታመን እግዚአብሔር የዮሴፍን ማስተዋል እንዲሰጥህ ጸልይ።

ቀን 6

እግዚአብሔር ሁሉንም እየተቆጣጠረ ነውን?

እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል፣ ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል። ... ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ።

- *ዘፍጥረት 45÷5,7-8*

(ገጽ 26-31 አንብብ)

ጌስር ቤት ውስጥ እየማቀቀ እያለ የሴፍ የግብፅ ገዢ ስለ መሆን አንድ ጊዜ እንኳ አስቦ ላያውቅ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ በሕይወቱ በደረሱ ሁኔታዎች ሁሉ፣ እግዚአብሔር የሴፍን ለዚሁ ዕቅዱ ሲያዘጋጀው ነበር። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ዕቅድ አለው። እርሱ ሁሉንም እየተቆጣጠረ ነው። በዮሴፍ ሕይወት ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር ለወንድሞቹ፣ ለጲጥፋራና ለገጠመው ሁኔታ የሰጠው ምላሽ ነበር። ለደረሰበት ስቃይ በወንድሞቹ ወይም በእግዚአብሔር ማማረር ይችል ነበር። በሕይወት ውስጥ ለሚደርስ ችግር ሰውን ሁሉ ተጠያቂ ማድረግና እነዚያ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ፣ ሕይወት ምን ያህል የተለየ ይሆን እንደ ነበር ማሰብ በጣም ቀላል ነው።

ፍጻሜያችን በእግዚአብሔር እንጂ፣ በሌላ በማንም እጅ አይደለም። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የትኛውም ወንድ፣ ሴት፣ ልጅ ወይም ጋኔን ወደ እናንተ መድረስ አይችልም!

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የትኛውም ወንድ፣ ሴት፣ ልጅ ወይም ጋኔን ወደ እናንተ መድረስ አይችልም!

የዮሴፍ ወንድሞች እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ሕልም ገድለናል ብለው አስበው ነበር፤ ግን ያን ማድረግ አይችሉም። ዮሴፍ እንደ ገና ከወንድሞቹ ጋር በተገናኘ ጊዜ ስለ ደረሰበት በደል ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ነበር ያሳሰባቸው።

ዘፍጥረት 45÷5-8 እና መዝሙር 105÷16-17 አንብብ። ምንም እንኳ የተለያየ መከራ ቢደርስበትም እግዚአብሔር ዮሴፍን የላከው ለምን እንደ ነበር በአጭሩ ጻፍ።

እግዚአብሔር ዮሴፍን የላከው _____

(ዘፍጥረት 45÷5)

እግዚአብሔር ዮሴፍን የላከው _____

(ዘፍጥረት 45÷7)

እግዚአብሔር ዮሴፍን የላከው _____

(ዘፍጥረት 45÷8)

እግዚአብሔር ዮሴፍን የላከው _____

(መዝሙር 105÷16-17)

ባለፈው ዓመት ውስጥ ስለ ደረሰብህ በጣም ትልቅ ችግር አስብ። በአንድ ዐረፍተ ነገር ግለጠው።

_____

_____

አሁን ቀጥሎ ያለውን ዐረፍተ ነገር ሙላ።

ለችግሩ የሰጠሁት ምላሽ _____

_____ ነበር።

የእግዚአብሔር ዕቅድ _____

_____ነበር።

ስለ ራሴ የተማርሁት _____

_____ነበር።

ከመሰናከል ወይም ከበደል ነጻ ሆናችሁ ከዘለቃችሁ፣ በእግዚአብሔር ፊቃድ ውስጥ እንደ ሆናችሁ ትዘልቃላችሁ። ከተሰናከላችሁና በበደል ከተጠመዳችሁ የእርሱን ዓላማና ፊቃድ ለመፈጸም በምርኮኝነት በጠላት ትወሰዳላችሁ። ስለዚህ የሚሻላችሁን ምረጡ፤ የትኛው ይሻላል?

ለእግዚአብሔር ተገዙ። ለማንኛውም መሰናክል እንቢ በማለት ዲያብሎስን ተቃወሙ። የሕይወታችሁ ሕልም ወይም ራእይ እናንተ ከጠበቃችሁት በተለየ መንገድ ይፈጸም ይሆናል፤ የእርሱ ቃልና ተስፋ ግን ጨርሶ አይወድቅም። የእግዚአብሔርን ፅቅድ የሚያስጨነግፍ አለመታዘዝ ብቻ ነው።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ለሕይወትህ መልካም ፅቅድ ስላለውና በሕይወትህ በሚደርሱ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ በጐ ነገር ለማምጣት ስለሚሠራ እግዚአብሔርን አመስግን።

_____

_____

_____

ቀን 7

አባት ሲበድል

መጥቼ ምድርን በርግማን እንዳላጠፋ፣ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።

- ሚልክያስ 4÷6

(ገጽ 33-38 አንብብ)

በአንድ ወንድም መናቅና በእርሱ መበደል አንድ ነገር ነው፤ በአንድ አባት መናቅና በእርሱ መበደል ግን ፍጹም የተለየ ነገር ነው። ስለ አባት ስናገር ስለ ወላጅ አባት ብቻ መናገሬ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ኃላፊነት ስለ ሰጣቸው ማንኛውም መሪዎች ጭምር መናገሬ ነው። እነዚህ ሰዎች ይወዱናል፤ ያስተምሩናል፤ ይመግቡናል፤ ይጠነቀቁልናል ብለን የምንተማመንባቸው ናቸው።

እስቲ ከዚህ በፊት ንቀት ወይም ጉዳት ስላደረሱባችሁ፣ ‹‹አባቶች›› አስቡ።

ንቀውናል ወይም ጉዳት አድርሰውብናል ብላችሁ በምታስቧቸው ላይ ክብ ሥሩ።

ወላጅ አባት	እንጀራ አባቴ	ፓስተሬ
የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ	የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ	ዲያቆን
አለቃ	አስተማሪዬ	መሪ

አባት ይሁኑልኛል ያልኳቸው ወዳጆቼ እና ሌሎች _____

ከአንድ አባት ስለሚደርስ ጥላቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ የሚሆነን የሳኦል ዳዊትን መጥላት ነው። *ከሰይጣን ሽንገላ* ገጽ 34-36 በጥንቃቄ አንብብ።

እያነበባችሁ እያለ ዳዊት ሳኦልን መጥላት ይችልባቸው የነበሩ መንገዶች በአጭሩ ጻፉ።

አሁን እነዚህ ዐረፍተ ነገሮችን ሙሉ።

ዳዊት ለሳኦል ያሳየው _____

ከበቀል ይልቅ ዳዊት ለሳኦል _____

ንጉሡ በነበረው፣ በአሳዳጊውና አባት ይሆነኛል ባለው ሰው ቢጠላም ዳዊት በደልን አልቆጠረም። ሳኦል ግን በአገልጋዩ በዳዊት ላይ ቅንዓትና ጥርጣሬ አደረበት። በዚህ ዘመን ብዙ መሪዎች በእነርሱ ሥልጣን ሥር ያሉ ግለ ሰቦችን ይጠራጠራሉ። እንደ ሳኦል ሁሉ እነርሱም በጥሪያቸው ዋስትና አይሰማቸውም። ያ ደግሞ ቅንዓትና ትዕቢትን ይወልዳል። ሌሎች ሰዎች ላይ መንፈሳዊ ባሕርያት መኖራቸውን ቢገነዘቡም፣ በእንዲህ ያሉ ሰዎች አገልግሎት የሚጠቀሙት እነርሱን የሚጠቅም መስሎ እስከ ታያቸው ድረስ ብቻ ነው። የዳዊት ስኬት ለእኔ ስጋት ነው ብሎ እስካሰበበት ጊዜ ድረስ ሳኦል በዳዊት ስኬት ደስተኛ ነበር። ከዚያ በኃላ ግን ዳዊትን አገለለው፤ እርሱን የሚያጠፋበትንም ምክንያት ይፈልግ ጀመር።

እንደ አባት የምትቆጥሩት ሰው ወይም መሪ እናንተ ላይ ኃጢአት ወይም ትክክል ያልሆነ ነገር ካደረገ፣ በእርሱ ከመሰናከል ይልቅ ጸልዩለት።

በጥርጣሬ የሚያያችሁ እንደ አባት የምትቆጥሩት ሰው አለ? ካለ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ የሚጠብቀው ምላሽ ምንድነው?

1 ሳሙኤል 24÷11 አንብበህ እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ።

አንድ ሰው ከበደለኝ፣ እግዚአብሔር እኔ እንዳደርግ የሚፈልገው

_____

_____

አንድ ሰው ከጠላኝ ወይም ከናቀኝ፣ እግዚአብሔር እኔ እንዳደርግ የሚፈልገው_____

_____

እንደ አባት የምትቆጥሩት ሰው ወይም መሪ እናንተ ላይ ኃጢአት ወይም ትክክል ያልሆነ ነገር ካደረገ፣ በእርሱ ከመሰናከል ይልቅ ጸልዩለት። እርሱን ማስተካከል የእግዚአብሔር እንጂ፣ የእናንተ ሥራ አይደለም። መሰናክልን ለመቀበል ፈቃደኛ አትሁኑ።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

እንደ አባት በምትቆጥሩዋቸው ሰዎች ሕይወት እንዲሠራና እናንተም ለእነርሱ መጸለይና ጥፋታቸውን ይቅር ማለት እንድትችሉ እግዚአብሔር ለምኑ።

_____

_____

_____

ቀን 8

ማን ይበቀልልኛል?

በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ፤ ይላል ጌታ።

- ሮሜ 12÷19

(ገጽ 38-43 አንብብ)

ሳኦል ግድለው ሲችል እንዳልገደለው በተረዳ ጊዜ ዳዊት መልካም ሰው መሆኑን ሳኦል ተቀብሎ ነበር። ሆኖም፣ ከዳዊት ሰዎች አንዱ የነበረው አቢሳ ዳዊት የነበረው ዐይነት ጸጋ አልነበረውም።

ሳኦል ተኝቶ እያለ ዳዊትና አቢሳ ወደ ሳኦል ሰፈር ሾልከው በገቡ ጊዜ አቢሳ፣ ‹‹ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል። አንድ ጊዜ በጦር ወግቼ ከመሬት ጋር እንዳጣብቀው እባክህ ፍቀድልኝ፤ ድጋሚ እርሱን መውጋት አያስፈልገኝም!›› በማለት ዳዊትን ለመነ።

ሳኦልን መግደል እንዲፈቅድለት ዳዊትን ለመጠየቅ አቢሳ ጥሩ ምክንያት ነበረው።

የሚከተሉትን ዝርዝሮች ተመልከት፤ ለፈጸመው በደል ሞት ይገባው ወይም አይገባው እንደሆነ ለማመልከት ✓ ምልክት አድርግ።

1. ሳኦል ሰማንያ አምስት ሺህ ምንም በደል ያልፈጸሙ ካህናትና ቤተ ሰቦቻቸውን ገድሎአል።
   ☐ ሞት ይገባዋል። ☐ ሞት አይገባውም።
2. ሦስት ሺህ ወታደሮች አስከትሎ ዳዊትንና ሰዎቹን ለመግደል ሳኦል የሚቻለውን ሁሉ አድርጎ ነበር።
   ☐ ሞት ይገባዋል። ☐ ሞት አይገባውም።

3. ምንም እንኳ የንግሥናው ቅባት ከእርሱ ተወስዶ ለዳዊት ቢሰጥም፣ ሳኦል እንደ ንጉሥ መግዛቱን ቀጥሎ ነበር።
   ☐ ቅጣት ይገባዋል። ☐ ቅጣት አይገባውም።
4. ዳዊትን በተመለከተ ሳኦል ዋሽቶአል፤ ሰዎችን ዳዊት ላይ ለማስነሣት ፈልጓል፤ ለዳዊት የገባውን ቃል አጥፏል።
   ☐ ሞት ይገባዋል። ☐ ሞት አይገባውም።

እነዚህ በደሎች ሳኦል እንዲገደል በቂ ምክንያት ባይሆኑም፣ እርሱን ለመቅጣትና በፈጸመው በደል ልክ እርሱን ለመበቀል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ ነበር። አሁን ከ1 ሳሙኤል 26÷9-11 ዳዊት ለአቢሳ የሰጠውን መልስ አንብቡ። ምንም እንኳ በተለመደው መልኩ እንደዚያ የማድረግ መብት ቢኖረውም፣ ዳዊት ሳኦልን አልገደለውም፤ ሌላው ቀርቶ እርሱን መቅጣት እንኳ አልፈለገም። በዚህ ዘመን የዳዊት ዐይነት ልብ ያላቸው ስንቶች ይሆኑ ይሆን?

በወንድማማች መካከል ማንኛውንም ፀብና መለያየትን መዝራት በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው

ከመጐዳትና ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ በሚነገሩ መጥፎ ቃሎች ቤተ ክርስቲያን ይከፋፈላል፤ ቤተ ሰብ ይበተናል፤ ትዳር ይፈርሳል፤ ፍቅር ይቀዘቅዛል። በጣም የሚጐዳ ምት ለማሳረፍ ታስቦ ከጓደኞች፣ ከቤተ ሰብ እና ከመሪዎቻችን በቁጣና በምሪት የተሳለ ቃሎች ይሰነዘሩብናል። ምንም እንኳ ያለን መረጃ ትክክልና አሳማኝ ቢሆንም፣ መነሻ ምክንያታችን ንጹሕ ላይሆን ይችላል። በወንድማማች መካከል ማንኛውንም ፀብና መለያየትን መዝራት በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው (ምሳሌ 6÷16-19)።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

በበደለህ ሰው ፊት ራስህን ዝቅ ለማድረግና ይቅርታ መጠየቅ እንዲያስተምርህ እግዚአብሔርን ለምን?

ቀን 9

መንፈሳዊ ከርታቶች

‹‹እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር ከማድረግና እግዚአብሔር የቀባው ስለሆነም እጄን በእርሱ ላይ ከማንሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ›› አላቸው፡፡ ዳዊት ሰዎቹን በዚህ ቃል ገሠጻቸው፤ በሳኦል ላይ አደጋ እንዲያደርሱበትም አልፈቀደላቸውም፡፡

- 1 ሳሙኤል 24÷6-7

(ገጽ 45-51 አንብብ)

በሳኦልና በዳዊት መካከል በነበረው ግንኙነት እግዚአብሔር የዳዊትን ልብ እየፈተነ ነበር (1 ሳሙኤል 24÷6-7)፡፡ ከሳኦል በኃላ የሚቀበለውን መንግሥት ለማጽናት ይገድለው እንደ ሆነ ወይም እርሱ ራሱ መንግሥቱን ለዘላለም እንዲያጸናለት ይጠብቅ እንደ ሆነ ግልጽ እንዲሆን እግዚአብሔር ፈልጓል፡፡

የመፍረድና የመበቀል መብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሮሜ 12÷19 ላይ፣ ‹‹ወዳጆቼ ሆይ፣ ለእግዚአብሔር ቁጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ›› የሚል እናነባለን፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ድርሻ እኛ መውሰድ የለብንም፡፡ ትክክል የሆነ ነገርን በተሳሳተ መንገድ ማድረግ ተገቢ አይደለም፡፡

አዎን፣ ሳኦል ሊፈረድበትና ሊቀጣ ይገባው ነበር፤ ያን ማድረግ የነበረበት ግን ዳዊት አይደለም፡፡

እግዚአብሔርን ከመጠበቅ ይልቅ፣ በገዛ ራስህ እጅ የተበቀልህበትን ጊዜ አስብ፡፡ ሁኔታውንና ውጤቱን ግለጥ፡፡

‹‹እግዚአብሔር ሰዎችን ከባድ ስሕተት በሚፈጽሙ፣ ከዚያም አልፎ ዐመፀኛ በሆኑ መሪዎች ሥር የሚያኖረው ለምንድነው?›› በማለት ብዙዎች ይጠይቃሉ፡፡ (እንደ ምሳሌ 1 ሳሙኤል 1-5 ይመ.) ግና ሕፃን እያለ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ብልሹ በነበረው ዔሊ ሥር አኑሮት ነበር፡፡ እዚያ በነበረ ጊዜ ሳሙኤል በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር መደገፍንና መታመንን፣ በእርሱም መመራትን ተማረ፡፡ በኃላም ብልሹ መሪዎቹን እግዚአብሔር ራሱ ቀጣቸው፡፡

በእርሱ ፍቅርና በሚያጠራ እሳቱ፣ ቅርጽና መልክ እንድንይዝ አንዳንዴ እግዚአብሔር አዳጋችና ከባድ ሁኔታዎች ውስጥ ያኖረናል፡፡ በደረሰብን በደል ተማርረን ጥለን ብንሄድ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ሳንቀበል እንቀራለን፤ ይልቁን በበደል ላይ በደል እንጨምራለን፡፡ በደል የደረሰባቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ የአጸፋ ምላሽ ይሰጣሉ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆንም፣ ለሰው ትክክል መስለው የሚታይ ነገር ያደርጋሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በታዛዥነት ለእግዚአብሔር ምላሽ እንድንሰጥ እንጂ፣ ለአዳጋች ሰዎች ወይም ሁኔታዎች የአጸፋ ምላሽ እንድንሰጥ አይደለም የተጠራነው፡፡

በእርሱ ፍቅርና በሚያጠራ እሳቱ፣ ቅርጽና መልክ እንድንይዝ አንዳንዴ እግዚአብሔር አዳጋችና ከባድ ሁኔታዎች ውስጥ ያኖረናል፡፡

በደል ሲደርስብን ወይም ደስ የማይል ሁኔታ ሲገጥመን፣ ከእግዚአብሔር እፎይታ የሚሰጥ ቃል እንፈልጋለን፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለ ነገሮች እንዲደርሱብን እግዚአብሔር የፈቀደው በሳሎች ሊያደርገን፣ ሊያጠራንና ሊያበረታን እንጂ፣ ሊያጠፋን አይደለም!

ራስህን የሚከተሉትን ጠይቅ፡፡

1. እኔን እንዲያጠራ እግዚአብሔር ከፈቀደለት አዳጋች ሁኔታ ሸሽቼ አመልጣለሁን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም
2. ከበድ ያለ ሁኔታዎች ሲገጥሙኝ አማርራለሁን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም
3. የራሴን ኃጢአት እንደ ትክክል እየቆጠርኩ፣ የሌሎችን ኃጢአት ግን አወግዛለሁን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም
4. እኔ ራሴ ፍጹም እንዳይደለሁ ባውቅም፣ መንፈሳዊ መሪዎች ፍጹም እንዲሆኑ እጠብቃለሁን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም
5. ከእግዚአብሔር ለመስማትና የእርሱን ምሪት ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነኝን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም
6. ኢሳይያስ 55÷12 አንብብ፡፡ በሰላም ለመኖር ፈቃደኛ ነኝን?
   ☐ አዎን ☐ አይደለም

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ኢየሱስ ፍጹም የሆነ እረኛ እንዲሆንልህና፣ በአንተ ላይ ኃላፊነት ለሰጣቸው ምድራዊ እረኞች በእርሱ ፍቅር እንዲሞላህ ጸልይ፡፡

_____

_____

_____

ቀን 10

የተተከለ ማደጉ አይቀርም

በእግዚአብሔር ቤት ተተክለዋል፤ በአምላካችንም አደባባይ ይንሰራፋሉ።። ባረጁ ጊዜ ያፈራሉ፤ እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩም ይኖራሉ።። እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤ እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን የለም ይላሉ።።

- መዝሙር 92÷13-15

(ገጽ 51-55 አንብብ)

የራሳቸውን አገልግሎት ያሳደጉ እየመሰላቸው ብዙ ሰዎች ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው፣ ቤተ ክርስቲያን ከአንዱ አገልግሎት ወደ ሌላው አገልግሎት ይንከራተታሉ።። እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ቦታ ታዋቂነትንና መበረታታትን ካላገኙ በቀላሉ ይከፋሉ።። ነገሮች እየተደረጉ ባሉበት መንገድ ካልተስማሙ ይሰናከላሉ፤ ያንን ቦታ ትተው ወደ ሌላ ይሄዳሉ።። የተሰናከለ ሰዎች ሥር እስኪሰዱ ድረስ አንድ ቦታ አይረጉም፤ ከተተከለበት ቦታ ይነቀላሉ፤ ይነጫነጫሉ፤ አመራሩን ይወቅሳሉ፤ የራሳቸውን ችግር ግን አይገነዘቡም።።

ማደግ በሚገባን አቅጣጫ ሊያሳድገን ጫናዎች እንዲኖሩ በመፍቀድ እግዚአብሔር በእሳት ያጠራናል፤ በሳሎች እንድንሆን ማንኛውንም ነገር ያደርጋል።። ከተተከልንበት ቦታ በቀላሉ የምንነቀል ከሆነ፣ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ በመንፈሳዊ ሕይወታችን አናድግም።።

ከተተከልንበት ቦታ በቀላሉ የምንነቀል ከሆነ፣
እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ
በመንፈሳዊ ሕይወታችን አናድግም።።

ባለፉት ዐሥር ዓመታት ውስጥ አባል የነበርህባቸውን ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ዘርዝር፡፡

_____

_____

_____

በአባልነት ወይም አዘውትረህ ወደ ተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች እየሄድህ ይሆን? ለምን? ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌሎች የሄድህበትን ምክንያት የሚጠቁም ዐረፍተ ነገር ላይ ✓ ምልክት አድርግ፡፡

☐ የመኖሪያ ሰፈር ስለ ለወጥሁ

☐ ቤተ እምነት (ዴኖሚኔሽን) ስለ ለወጥሁ

☐ በፓስተሩ ቅር ስለ ተሰኘሁ

☐ የቢሮ ሠራተኛ የሆነ ሰው ስላስቀየመኝ

☐ ከመሪዎቹ አንዱ ስላሰናከለኝ

☐ በአስተምህሮ ስላልተስማማሁ

☐ በአምልኮ ሥርዐቱ ደስተኛ ስላልሆንሁ

☐ _____ ቅር ስላለኝ

☐ ሌሎች ምክንያቶች

ቤተ ክርስቲያኖችን የምታለዋውጥበት ምክንያት የደረሰብህ በደል ከሆነ፣ እንግዲያውስ ከአንዱ ወደ ሌላው የሰይጣንን ሽንገላ እየተመላለስህ ነው፤ በምትሄድበት ቦታ ሁሉ መንፈሳዊ መካንነትንና አፍራሽ ዘር እየዘራህ ነው፡፡

የሚከተሉን ጥቅሶች አንብብና ከእግዚአብሔር ሕግ፣ ከመሰናከል፣ ከመንፈሳዊ ዕድገትና ፍሬ ከማፍራት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አስፍር፡፡

መዝሙር 1÷1-3

_____

_____

_____

መዝሙር 119÷165

_____

_____

_____

ማርቆስ 4÷16-17

_____

_____

_____

በደልን ባለ መቁጠር፣ የቤተ ክርስቲያን ጎብረት ውስጥ ለዘለቄታው በመተከል የምታገኛቸውን አምስት ጥቅሞች ዘርዝር።።

1. _____
2. _____
3. _____
4. _____
5. _____

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ተተክለህ ስላለበት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አመስግን፤ በሳልና ፍሬያማ እንድትሆን እንዲረዳህ ለምነው።።

_____

_____

_____

ቀን 11

ከእውነታው መደበቅ

ሁልጊዜ ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ ሊደርሱ አይችሉም።
- 2 ጢሞቴዎስ 3÷7

(ገጽ 57-60 አንብብ)

ብዙ ጊዜ ሰዎች አንድን ቤተ ክርስቲያን ወይም የአገልግሎት ድርጅት ለቅቀን መሄድ እንዳለብን የምውቀው እንዴት ነው በማለት ይጠይቁኛል። እኔም፣ ‹‹አሁን ወዳላችሁበት ቤተ ክርስቲያን የመጣችሁት በማን ፈቃድ ነበር?›› በማለት መልሼ እጠይቃቸዋለሁ።

ብዙዎች የሚመልሱልኝ፣ ‹‹በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው›› በማለት ነበር። ከዚያም፣ ወደዚያ የመጣችሁት በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ እርሱ ራሱ እስኪፈቅድ ድረስ ያንን ቦታ መልቀቅ የለባችሁም። ለቅቃችሁ እንድትሄዱ እግዚአብሔር ከመራችሁ ግን፣ የአገልግሎቱ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ በሰላም መሄድ ትችላላችሁ እላቸዋለሁ (ኢሳይያስ 55÷12)።

አንድን ቤተ ክርስቲያን ለቅቃችሁ እንድትሄዱ፣ ከሄዳችሁ በኃላም ቢሆን ግንኙነታችሁ ሰላም ያለበት እንዲሆን ከእግዚአብሔር ምሪት ያገኛችሁበት ጊዜ ካለ ያንን ግለጹ።

በዚህ መጽሐፍ በቴክኖን (teknon) ማለትም፣ ‹‹ሕፃናት፣ ገና ያልበሰለ ልጆች›› እና ሁዮስ (huois) ‹‹የበሰለ ልጆች›› መካከል ያለውን ልዩነት አመልክቻለሁ። ሮሜ 8÷14 ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች (ሁዮስ) ናቸውና›› ሲል በሳል ስለሆኑ ልጆች እየተናገረ ነው። እንደ ልጆቹ እግዚአብሔር እኛን በሳል የሚያደርገን እንዴት ነው? የመንፈሳዊ ብስለት ሂደትን ለመረዳት የበሳል የእግዚአብሔር ልጅ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነንን ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት እንችላለን።

በደል ወይም መሰናከል መንፈሳዊ ዕድገትን እንደሚገታ፣ መከራና መታዘዝ ግን ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ ወደምንችልበት ደረጃ እንደሚያደርሰን መማር አለብን።

ኢየሱስ በሳል የሆነው በመታዘዝና በመከራ ነበር።

አሁን ባለህበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከራንና መታዘዝን በተመለከተ እየተማርህ ያለው ምንድነው? መከራ ሲደርስብህ ወይም እንድትታዘዝ ስትጠየቅ፣ በእግዚአብሔም ሆነ በሰዎች እንዳትሰናከል በዝንባሌህ፣ በአስተሳሰብህና በሰሚታዊ ሕይወትህ የምታድገው እንዴት ነው?

_____

_____

_____

በደል ወይም መሰናከል መንፈሳዊ ዕድገትን እንደሚገታ፣ መከራና መታዘዝ ግን ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ ወደምንችልበት ደረጃ እንደሚያደርሰን መማር አለብን።

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ

መከራ ሲገጥመኝ የምሰጠው ምላሽ _____

_____

መታዘዝ ካለብኝ ሊኖረኝ የሚገባ ዝንባሌ _____

_____

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ሁለንተናህን ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ መሰጠትና ለክርስቶስ መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ በመሆን ራስህን ማቅረብ እንድትችል ጸልይ

_____

_____

_____

ቀን 12

ራስን መከላከል

ሰልፉ የእግዚአብሔር ስለ ሆነም ሁላችሁንም በእጆችን አሳልፎ ይሰጣል።

- 1 ሳሙኤል 17÷47

(ገጽ 60-65 አንብብ)

ራሳችንን ለመከላከል እንደ ሰበብ የምናቀርበው ባለፈው ጊዜ የደረሰብንን በደል ወይም መሰናከል ነው። በደልን መቁጠር ራስን ለመከለል ሐሰተኛ ምክንያት ይሆናል። በዳዩን ወገን ተወቃሽ ስለምታደርጉ የራሳችሁን ድካም እንዳትመለከቱ ያደርጋል። ሁልጊዜ የበደል አድራሹን ጥፋት ብቻ ስለምታዩ የራሳችሁን አለመብሰል ወይም ኃጢአት መጋፈጥ አትፈልጉም። ስለሆነም በዚያ አዳጋች ሁኔታ ውስጥ የእናንተን ባሕርይ ለማዳበር እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ ይጨናገፋል። ተበድያለሁ ባዩ ወገን የበደለ ምንጭ ከሆነው ቦታ ወይም ሰው ይርቃል፤ በኃላም ይሸሽና መንፈሳዊ ተንከራታች ይሆናል።

ሌሎችን መውቀስና በእነርሱ መፍረድን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የሚናገረው አለው።

የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና ሌሎችን ስለ መውቀስና ሌሎች ላይ ስለ መፍረድ የሚናገሩትን አስፍር።

ማቴዎስ 7÷1-5

_____

_____

_____

ማቴዎስ 5÷21-26

ሉቃስ 6÷36-37

ሮሜ 2÷1-2

ሮሜ 12÷17-21

ሮሜ 14÷10-13

ያዕቆብ 4÷11-12

ዮሐንስ 20÷23 **ላይ ኢየሱስ፤ ‹‹የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉ፣ ኃጢአታቸው ቅር ይባልላቸዋል፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም›› ብሏል።**

የወደ ፊቱን በተመለከተ ተስፋ ይኖር ዘንድ ፍቅር በደልን አይቆጥርም።

የሰዎችን በደል የምንለቅምና በውስጣችን ቅርታን የምናስተናግድ ከሆነ ኃጢአታቸውን ይቅር ማለት ይከብደናል።

ለዚህ ቁልፍ መፍትሔ ከችግሮች አለ መሸሽ፣ ከበደል አድራሾች መራቅ ሳይሆን መቅረብና ዕርቅ ማድረግ ነው። ለምን? ምክንያቱም ችግሩን ፊት ለፊት አለመጋፈጥ ወይም መፍትሔ ለመፈለግ አለመሞከር ከችግሩ ነጻ አያደርገንም። የችግሩ ሥረ መሠረት ሳይነካ ይቀራል። የእግዚአብሔር ዕቅድ ጉዳትንና እኛ መጋፈጥ የማንፈልገውን ዝንባሌ ፊት ለፊት እንድንጋፈጥና መፍትሔ እንድንሰጠው ነው። ሽሽትን ለማምለጥ የምንፈልገው አዳጋች ሁኔታ ለሕይወታችን ብርታትና ጥንካሬ መስጠት የሚችል ነው።

ይህን አትርሱ፣ የወደ ፊቱን በተመለከተ ተስፋ ይኖር ዘንድ ፍቅር በደልን አይቆጥርም። አንድን በደል ወይም መሰናከል በእውነት አሸንፈን ከሆነ፣ ሰላም መፍጠርን አጥብቀን እንፈልጋለን። ምናልባት አሁን ጊዜው አልደረሰም ይሆናል፤ ያም ሆኖ ግን፣ ዕርቅና ሰላም የሚወርድበትን አጋጣሚ በልባችን እንጠብቃለን።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

በደልን ወይም መሰናከልን ከመሸሽ ይልቅ ፊት ለፊት እንድትጋፈጥና መፍትሔ እንድትፈልግ እግዚአብሔር እንዲረዳህ መጸለይ።

ቀን 13

ጽኑ መሠረት

ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እነሆ የተፈተነ ድንጋይ፣ ለጽኑ መሠረት የሚሆን የከበረ የማእዘን ድንጋይ፣ በጽዮን አስቀምጣለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም።

- ኢሳይያስ 28÷16

(ገጽ 67-72 አንብብ)

የሚያምን ሰው ነገርን በችኮላ አያደርግም። ነገሮችን በችኮላ የሚያደርግ ያልተረጋጋ ሰው ነው፤ የሚሠራው ሁሉ ጽኑ መሠረት የለውም። የስደትና የፈተና ማዕበል በቀላሉ ያናውጠዋል።

በስደትና በፈተና መሐል አስተማማኝ መሠረት የሚሆነን የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። በምሰብክበት ጊዜ ሁሉ፣ እኔ ከምሰብከው ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዲያደምጡ ብዙ ጊዜ ሰዎችን እመክራለሁ። አንድ ጥሩ አገልጋይ ሲናገር ወይም መጽሐፍ ስናነብ፣ ከዚያ ውስጥ ለልባችን ብርሃን የሚሰጥ ቃል ወይም ሐሳብ መጠበቅ አለብን። ያ እግዚአብሔር ለእኛ የገለጠው እውነት ስለሆነ ብርሃንና መንፈሳዊ መረዳት ይሰጠናል።

ዘማሪው፣ ‹‹የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤ አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል›› ይላል (መዝሙር 119÷130)። መገለጥና መረዳት የሚሰጠን ጌታ ራሱ ቃሉን ለልባችን ሲተረጉምልን ነው።

እግዚአብሔር ብርሃን ወይም መረዳት የሰጠህ እንዴት ነበር። ከሚከተሉት በሕይወትህ የእግዚአብሔርን ድምጽ የሰማህባቸው መንገዶችን ✓ ምልክት አድርግ።

☐ መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት ☐ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ

☐ ቃሉን በመዘመር ☐ በስብከት አማካይነት

☐ በትምህርት አማካይነት ☐ ክርስቲያን መጻሕፍት በማንበብ

☐ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማቾች ሲዘመሩ በመስማት

☐ ሌሎች _____

እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚገልጥልን ከእኛ ሊወሰድ አይችልም። ውሳኔዎቻችንን በእርሱ ቃል ላይ እንተክላቸዋለን። በእርሱ ቃል መሠረት ላይ ካልሆንን፣ ያልተጠበቁ ችግሮችና ፈተናዎች ሲመጡ በቀላሉ እንሰናከላለን። የእግዚአብሔር ቃል ልባችን ውስጥ ሥር ካልሰደደ፣ መጀመሪያ ላይ በደስታ ብንቀበለውም ውሎ አድሮ ግን እንሰናከላለን (ማርቆስ 4÷16-17)።

በእርሱ ቃል መሠረት ላይ ካልሆንን፣
ያልተጠበቁ ችግሮችና ፈተናዎች ሲመጡ
በቀላሉ እንሰናከላለን።

ስሜትህን፣ ሐሳብህን ወይም ዝንባሌህን የሚቃረን ቃል ከእግዚአብሔር ስትሰማ የአንተ ምላሽ ምን መሆን አለበት?

_____ እቆጣለሁ

_____ግራ እጋባለሁ

_____እጐዳለሁ

_____ንስሐ አደርጋለሁ

_____እግዚአብሔር ከሚናገረው በመማር ደስ ይለኛል

_____እሰናከላለሁ

_____ሌሎችን ወይም እግዚአብሔርን እወቅሳለሁ

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከተመሠረትንና ከመንፈሱ አብርሆት ካገኘን፣ ያለ ምንም መሰናከል ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች እውነትን እንሰማለን።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ስለ ቃሉና በቃሉ አማካይነት ለሕይወትህ አብርሆት ስለሚሰጥባቸው አያሌ መንገዶች እግዚአብሔርን ማመስገን።

ቀን 14

ከ... በቀር ሌላ ምርጫ የለህም

በሰው ዘንድ ወደ ተናቀው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠውና ክቡር ወደ ሆነው ወደዚህ ሕያው ድንጋይ እየቀረባችሁ፣ እናንተ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕት ታቀርቡ ዘንድ፣ ቅዱሳን ካህናት ለመሆን እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ።

- 1 ጴጥሮስ 2÷4-5

(ገጽ 72-77 አንብብ)

የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትና አገልግሎችንን ልንመሠርትበት የሚገባ ጽኑ መሠረት ነው። ትእዛዞቹና ሕጐቹ ስንፈልግ የምንቀበላቸው፣ ሳንፈልግ የምንተዋቸው ሳይሆኑ፣ በፍጹም ተግባር ላይ መዋል ያለባቸው ናቸው። ቃሉ ውስጥ ያለ አንድ ትእዛዝ ወይም ሕግ ለእኛ ሳይመች ቢቀር እንኳ አለመታዘዝ ወይም አንቀበልም የማለት መብት የለንም። ያለን ምርጫ መታዘዝ ብቻ ነው።

በቃሉ የተሰናከልክበትና ሳትታዘዝ የቀረህበት ጊዜ ካለ ግለጥ። ውጤቱ ምን ነበር?

_____

_____

_____

በችግሮችና ተፅዕኖዎች መሐል እንደ ጴጥሮስ ሁሉ፣መንፈሳዊ ቤቶች የሚሠሩባቸው ትንንሽ ድንጋዮች ሆነን ራሳችንን እናገኘዋለን

ጴጥሮስ (ፔትራ) ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የመሰከረ ዐለት ነበር። ፈተናዎችና ችግሮች አንድ ሰው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ያሳያሉ። በሌላ አነጋገር እውነተኛ መንፈሳዊ ይዘታችሁን ያመለክታሉ ማለት ነው። ልባችሁ ያለበትን እውነተኛ ይዞታም ያመለክታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ በአሸዋ ላይ ስለ ተገነባ ቤት ይናገራል (ማቴዎስ 7÷26-27)። እንዲህ ዐይነቱ ቤት አምስት ፎቆች ያሉትና በጣም ያማረ ሊሆን ይችላል። ሁሉም ነገር መልካም እስከ ሆነ ድረስ ቤቱ ጠንካራና የተዋበ መስሎ ሊታይ ይችላል። ከዚያ ቤት አጠገብ አንድ ተራ የሆነ የማያምርና የማይማርክ ባለ አንድ ፎቅ ቤት ሊኖር ይችላል። ሆኖም፣ ይኸኛው ቤት እኛ ማየት ያልቻልነው ነገር ላይ፣ ማለትም ዐለት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል።

ፈተናዎችና ችግሮች አንድ ሰው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ያሳያሉ። በሌላ አነጋገር እውነተኛ መንፈሳዊ ይዘታችሁን ያመለክታሉ ማለት ነው።

ዝናብ እስካልዘነበና ማዕበል እስከሌለ ድረስ፣ ያ ባለ አምስት ፎቅ ቤት የበለጠ ውብ ሆኖ ይታያል። ከባድ ዝናብ ሲመጣና ዐውሎ ነፋስ ሲነሣ ግን፣ ባለ አምስት ፎቅ ቤቱ ይፈርስና እንዳልነበረ ይሆናል። ክርስቲያኖች ዐለት በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚሠሩ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው። ማዕበል ሲመጣ ሸሽተው አያመልጡም፣ አይሰናከሉም ወይም ሌሎችን አይወቅሱም። ይልቁን በሕይወት ማዕበሎች መሐል ጸንተው ይቆማሉ።

የአሸዋ መሠረት በሆነው የዚህ ዓለም ሥርዐት ላይ ቤት ለመሥራት የሞከርህበት ጊዜ ነበርን? ቤት ለመሥራት የሞከርህባቸው የዚህ ዓለም መሠረቶች ዝርዝር ላይ ✓ ምልክት አድርግ። ውጤቱ ምን እንደ ነበር በአጭሩ ግለጥ።

☐ ገንዘብ _____

☐ ስኬት _____

☐ ሥልጣን (ኃይል)_____

☐ ንብረት _____

☐ ዓለማዊ አለኝታ _____

☐ ሰዎች _____

☐ ሌሎች _____

ሌሎች በሚናገሩት ወይም በሚያደርጉት ላይ ሳይሆን፣ ሕይወትህን በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረትህን አረጋግጥ። ጌታን መፈለግህንና ለልብህ ሲናገር ቃሉን ማድመጥህን ቀጥል። ሰውን ደስ ለማሰኘት በማሰብ ምንም አታድርግ፣ ምንም አትናገር። እርሱን ፈልገው፤ በልብህ ባበራው ብርሃን መሠረት ጸንተህ ቁም!

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ቃሉን እንዲገልጥልህና ዐለት በሆነው ክርስቶስ ላይ ሕይወትህን እንድትመሠርት እንዲረዳህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ።

_____

_____

_____

ቀን 15

የሚናወጥ ነገር ሁሉ መናወጡ አይቀርም

በዚያን ጊዜ ድምፁ ያናወጠው ምድርን ነበር፤ አሁን ግን፣ ‹‹ምድርን ብቻ ሳይሆን፣ ሰማያትንም አንድ ጊዜ ደግሜ አናውጣለሁ›› ብሎ ቃል ገብቶአል። አንድ ጊዜ ደግሜ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማይናወጡት ጸንተው ይኖሩ ዘንድ፣ የሚናወጡት ይኸውም የተፈጠሩት የሚወገዱ መሆናቸውን ነው።

- ዕብራውያን 12÷26-27

(ገጽ 79-88 አንብብ)

ዓለም እንኳ ጴጥሮስ፣ ‹‹ዐለት›› ተብሎ ቢጠራም፣ ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ቢመሰክርም፣ የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማብቂያ ላይ በክርስቶስ ትሕትና መሠረት እየተመላለሰ እንዳልነበር መረዳት ችሎ ነበር። ሕይወትና አገልግሎቱን የመሠረተው ያለፈው ጊዜ ድልና ትምክህት ላይ ነበር። በክርስቶስ ላይ እንዴት መመሥረት እንዳለብን ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመክረናል።

> ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን፣ እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለበት። ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ መሠረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
>
> - 1 ቆሮንቶስ 3÷10-11

ከሕይወት ገጽታዎችህ ማንኛውም ክፍል በዓለማዊ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ ያንን ክርስቶስ ያናውጠዋል።

1 ዮሐንስ 2÷15-17 አንብብ። ከታች ያሉት እግዚአብሔር ከሕይወታችን የሚያናውጣቸው ዓለማዊ ነገሮች ናቸው። አንተ ያለህበትን ሁኔታ የሚያመለክተው መስመር ላይ X አድርግ።

የሥጋ ምኞት

አሁን እንኳ ተናውጠአል **መናወጥ ይገባዋል**

የዐይን አምሮት

አሁን እንኳ ተናውጠአል **መናወጥ ይገባዋል**

የኑሮ ትምክህት

አሁን እንኳ ተናውጠአል **መናወጥ ይገባዋል**

የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማብቂያ ላይ ጴጥሮስ ካሳየው ትምክህት የተነሣ ኢየሱስ፣ ‹‹ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፣ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ›› በማለት ነግሮት ነበር (ሉቃስ 22÷31)።

ኢየሱስ የጸለየው ጴጥሮስ ከዚያ ነውጥ
እንዲያመልጥ አልነበረም፤ ይልቁንም እርሱ
የጸለየው በዚያ ሂደት ውስጥ የጴጥሮስ
እምነት እንዳይጠፋ ነበር።

ጠላት ወደ ውስጥ እንዲመጣና ስምዖንን እንዲያበጥር በር የከፈተ ትዕቢት ነበር። ኢየሱስ በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ያለን ብዙዎች ያለን ዐይነት አመለካከት ቢኖረው ኖሮ፣ ‹‹ወገኖቼ፣ በጸሎት ይህን የሰይጣን ጥቃት እናስቁም። በምንወደው ወንድማችን ስምዖን ላይ ይህ እንዲደርስ መፍቀድ የለብንም›› ይል ነበር። ግን እርሱ የተናገረውን ተመልከቱ፤ ‹‹እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ

ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ›› (ሉቃስ 22÷32)።

ኢየሱስ የጸለየው ጴጥሮስ ከዚያ ነውጥ እንዲያመልጥ አልነበረም፤ ይልቁንም እርሱ የጸለየው በዚያ ሂደት ውስጥ የጴጥሮስ እምነት እንዳይጠፋ ነበር። ከዚያ ፈተና ውስጥ የታቀደለትን መፈጸም እንዲችልና ወንድሞቹንም እንዲያጸና ለስምዖን ጴጥሮስ የሚያስፈልግ አዲስ ማንነት እንደሚወጣ ኢየሱስ ያውቅ ነበር።

እምነቱን እስኪጥል ድረስ የስምዖን ጴጥሮስን እምነት ክፉኛ ለማናወጥ ሰይጣን ፈቃድ ጠይቆ ነበር። የሰይጣን ፍላጐት ይህን ታላቅ ዐቅም የነበረውንና መለኮታዊ መገለጥ ያገኘውን ሰው ጨርሶ ማጥፋት ነበር። እግዚአብሔር ግን ያንን ነውጥ በተመለከተ የተለየ ዓላማ ነበረው፤ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ እግዚአብሔር ከሰይጣን ቀድሞ ተገኝቷል።

ከሚከተሉት ዓላማዎች በአንዱ እግዚአብሔር ሕይወታችንን ያናውጥ ይሆናል። እርሱ ሕይወትህን እያናወጠ ከሆነ ከእነዚህ ምክንያቶች ለአንተ ያለው ዓላማ ምን እንደሆነ ነው የምታስበው? (አንተን የሚመለከተው ላይ ✓ አድርግ)

☐ ሕይወትህ ከመሠረቱ ጋር እንዲያያዝ

☐ እንደ ትዕቢት ያለውን የሞተ ነገር ከሕይወትህ ለማስወገድ

☐ አንተ ውስጥ በስሎ የነበረውን ፍሬ ለመሰብሰብ

☐ በመንፈሳዊ ሕይወትህ አንቀላፍቶ ወይም ሞቶ የነበረውን ነገር ለማንቃት

☐ መንፈሳዊ አንተነትህ ውስጥ ያለ እውነት፣ ከነፍስና ከሥጋህ ተለይቶ እንዳይኖር ያንን ማጽናት።

ራስ ወዳድነት ወይም ትዕቢት ላይ የተመሠረተ ማንኛውም የአስተሳሰብ ሂደት ወይም ዝንባሌ ይናወጣል፤ ተቆርጦም ይጣላል።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ከሕይወትህ ትዕቢትን፣ ራስ ወዳድነትና ዓለማዊ ምኞትን እንዲያበጥር ጌታን መለመን።

_____

_____

_____

ቀን 16

ለትሑታን ጸጋ ይሰጣል

ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣ ‹‹እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡››
- 1 ጴጥሮስ 5÷5

(ገጽ 88-92 አንብብ)

በዚህ ሕይወት የሚገጥምህ ፈተና የተሰናከልከው በእግዚአብሔር ላይ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ቢሆን ልብህ ውስጥ ያለውን ይገልጣል፡፡ ችግሮች በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ መራራ እንድትሆን ወይም እንድትጠነክር ያደርጉሃል፡፡ ትሑት የመሆንን ፈተና ካለፍክ ሥሮችህ ወደ ታች ይጠልቃሉ፤ አንተንም ሆነ የወደፊት ሕይወትህን የተረጋጋ ያደርጉታል፡፡ ፈተናውን ካላለፍክ ግን ትሰናከላለህ፤ ይህም ወደ ርኩሰትና ወደ መራራነት ይመራሃል፡፡

ስምዖን ጴጥሮስ እኔ የተሻልኩ ነኝ የሚል ትምክህቱ እስኪጠፋ ድረስ ተፈትኖአል፡፡ በተፈጥሮው የነበረው በራስ የመተማመን ትምክህቱ ጠፍቶአል፡፡ የራሱን ጠንካራ ፈቃድ ከንቱነት አጥርቶ ማየት ችሎአል፡፡ እንደ በፊቱ ትምክህተኛ ሳይሆን፣ አሁን ትሑት ሆኖአል፤ ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ጸጋ ወደሚቀበልበት ቦታ መጥቶአል፡፡ እግዚአብሔር ለትሑታን ጸጋ ይሰጣል፡፡ ትሕትና ቅደመ ሁኔታ ነው፡፡ ምናልባት እናንተ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንተን አገልግያለሁ፤ አንተን ለመከተል ብዙ ነገር ትቻለሁ፤ ታዲያ፣ እንዲህ ያለ ከባድ ችግር የደረሰብኝ ለምንድነው?›› በማለት እግዚአብሔርን የጠየቃችሁበት ጊዜ ይኖር ይሆን?

ችግሮች በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ መራራ እንድትሆን ወይም እንድትጠነክር ያደርጉሃል።

ጉዳትና ስብራት የደረሰባቸው ክርስቲያኖች ለእርሱ ካደረጉት የተነሣ የተለየ ግምት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ስለሚያስቡ፣ ብዙ ጊዜ በጌታ ይሰናከላሉ።

እርሱን እያገለገሉ ያሉት በተሳሳተ ዓላማ ነው። እግዚአብሔርን ማገልገል ያለብን ስለ ማንነቱና ቀድሞውኑ ካደረገልን የተነሣ እንጂ፣ ገና ለገና ያደርግልናል ብለን በምናስበው ምክንያት መሆን የለበትም። የተሰናከሉ ወይም በደል የደረሰባቸው ወገኖች፣ እነርሱን ነጻ ለማውጣት ምን ያህል ከባድ ዋጋ እንደ ተከፈለላቸው ዘንግተዋል። ከእንዴት ዐይነት ሞት እንደ ታደጋቸው ዘንግተዋል። እነርሱ የሚያዩት በዘላለማዊው ሳይሆን በተፈጥሮአዊ ዐይኖቻቸው ነው።

ጌታን የምታገለግሉት በትዕቢት፣ በራስ በመመካት ወይም እርሱን በማገልገላችሁ ቁሳዊ ነገር እንዲሰጣችሁ ወይም ችግር የሌለበት ሕይወት እንድትኖሩ ተስፋ በማድረግ ይሆን?

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ።

ክርስቶስን የማገለግልበት መነሻ ሐሳብ _____

_____ ነው።

የእኔ ተስፋና ትምክህት ያረፈው _____

_____ ላይ ነው።

ከእርሱ የምጠብቀው ሽልማት _____

_____ነው።

በራሳችን ጥረት ዘላለማዊ እሴት ያለው አንድ ነገር እንኳ ማድረግ አንችልም።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ጌታ ልብህን እንዲያጠራና በሥጋ መታመንህን ሁሉ እንዲያስወግድ መጸለይ።

_____

_____

_____

ቀን 17

የመሰናከያ ዐለት

እነሆ፣ የተመረጠና ክቡር የማእዘን ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ፤ በእርሱ የሚያምን ከቶ አያፍርም። እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ ድንጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ። ደግሞም፣ ‹‹ሰዎችን የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ›› የሚሰናከሉት ቃሉን ባለመታዘዛቸው ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና።

- 1 ጴጥሮስ 2÷6-8

(ገጽ 95-108 አንብብ)

በዚህ ዘመን ማመን የሚለው ቃል ትርጉም እየላላ መጥቶአል። በብዙዎች ዘንድ ከአንድ ሐቅ ጋር ከመስማማት፣ ወይም አንድን እውነት ከመቀበል ያለፈ ትርጉም የለውም። አብዛኞቹ ሰዎች ከመታዘዝ ጋር የተያያዘ መሆኑን አልተረዱም። ከላይ ባለው ምንባብ ግን ማመንና አለ መታዘዝ ተቃራኒ መሆናቸውን ነው የምንመለከተው።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) የሚያምን የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ፣ አይጠፋም›› ይላል (ዮሐንስ 3÷16)።

ማመን ለሚለው ቃል ካለን ምልከታ የተነሣ፣ ብዙዎች ማድረግ ያለባቸው በአንድ ወቅት ኢየሱስ የሚባል ሰው በዚህ ምድር እንደ ነበረና፣ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረን ለማድረግ መስቀል ላይ መሞቱን ማመን ያለብን መሆኑን ብቻ ነው የሚያስቡት። የሚያስፈልገው ይኸው ብቻ ከሆነ አጋንንት ከእርሱ ጋር ጥሩ ግንኙነት አላቸው ማለት ነው፤

ምክንያቱም መጽሐፍ፣ ‹‹አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣለ›› ይላል (ያዕቆብ 2÷19)። ያም ሆኖ ግን እነርሱ ድነት አይኖራቸውም።

እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ።

ለእኔ እምነት ማለት _____

_____

ለእኔ መታዘዝ ማለት _____

_____

አምናለሁ እያልኩ የማልታዘዝ ከሆነ _____

_____

በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ማመን ማለት አንድን ሐቅ ከመቀበል ያለፈ ትርጉም አለው። እንግዲህ ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት የማመን ዐቢይ ቁም ነገር መታዘዝ ነው ማለት እንችላለን። ምክንያቱም ቃሉ፣ ‹‹እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ ድንጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፤ ደግሞም ሰዎችን የሚሰናክል የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ›› ስለሚል ነው።

ከጌታ ጋር ላለን ግንኙነት መሠረቱ ፍቅር ማለትም የመርሐ ወይም የአስተምህሮ ፍቅር ሳይሆን፣ ለራሱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ፍቅር ነው።

የምትገዙለትን ሰው ባሕርይና ፍቅር ካወቃችሁ መታዘዝ ከባድ ነገር አይሆንም። ከጌታ ጋር ላለን ግንኙነት መሠረቱ ፍቅር ማለትም የመርሐ ወይም የአስተምህሮ ፍቅር ሳይሆን፣ ለራሱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ፍቅር ነው። ያ ፍቅር ጽናት ከሌለው ለመሰናከል ወይም ለውደቀት ይጋለጣል።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ የምትኖሩ ከሆነ፣ የሰዎችን ፍላጐት ለመፈጸም አትኖሩም። ከዚህም የተነሣ በሥጋችሁ ችግር ሊገጥማችሁ ይችላል። ኢየሱስ ከፍተኛ ተቃውሞ የደረሰበት ከሃይማኖት መሪዎች ነበር። የሃይማኖት ሰዎች እግዚአብሔር የሚሠራው በእነርሱ ክልል ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ። በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ከመኖሩ የተነሣ፣ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት እርሱ የሃይማኖት መሪዎቹን ካሰናከለ፣ ዛሬም የእርሱ ተከታዮች ያለ ጥርጥር ያሰናክሉዋቸዋል።

የምትሰጠው ምላሽ የወደ ፊት ሕይወትህን እንደሚወስን አስታውስ። ይህን ዐረፍተ ነገር ሙላ።

ከእኔ ጋር ያለት ለክርስቶስ ከመኖር ቢሰናከሉም እኔ _____

_____

ጳውሎስ፣ ‹‹እስከ አሁን ድረስ በሰዎች እስከ መጠላትና እስከ መሰደድ የደረሰኩት ደኅንነት የሚገኘው በመስቀል ላይ በሞተው በክርስቶስ በማመን ነው እያልኩ ስለ ሰበክሁ ብቻ ነው›› ብሎአል (ገላትያ 5÷11 ሕያው ቃል)።

አንድ ሰው የወንጌልን እውነት የሚጻረር ከሆነ፣ ያለ ምንም ይቅርታ ልንቋቋመው ይገባል። የቱንም ያህል ከባድ ዋጋ ቢያስከፍለንም ለእግዚአብሔር መንፈስ ለመታዘዝ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለብን።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

እንደምትወደው፣ እንደምትታመንበትና ለእርሱ እንደምትታዘዝ ለክርስቶስ በመናገር መጸለይ

_____

_____

_____

ቀን 18

እንዳናሰናክላቸው

ስለዚህ እርስ በርሳችን አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ እንቆጠብ፤ በዚያ ፈንታ በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቁርጥ ሐሳብ አድርግ።

- ሮሜ 14÷13

(ገጽ 111-116 አንብብ)

ማንም እንኳ ብዙዎች በኢየሱስ ቢሰናከሉም፣ የግል መብቱን ወይም ጥቅሙን ለማስጠበቅ በማሰብ ማንንም አላሰናከለም። ‹‹ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው›› በማለት ኢየሱስ ተናግሮአል (ማቴዎስ 18÷4)። እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ሐረግ፣ ‹‹ራሱን ዝቅ የሚያደርግ›› የሚለው ነው። ጥቂት ቆየት ብሎ ኢየሱስ ይህንኑ ሲያብራራ፣

> ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና። ብሎአል።
>
> - ማቴዎስ 20÷26-28

የሚገርም አባባል ነው! ኢየሱስ የመጣው ለማገልገል እንጂ፣ ለመገልገል አይደለም። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እርሱ ነጻ ነው። የማንም ዕዳ አልነበረበትም። የማንም ተገዢ አልነበረም። ይሁን እንጂ፣ ነጻነቱንና መብቱን ሌሎችን ለማገልገል ነበር የተጠቀመበት።

የሚከተሉን ምንባቦች አንብበህ፣ እያንዳንዱ ጥቅስ ስለ ማገልገልና አገልጋይ ስለ መሆን የሚናገረውን አስፍር።

ሉቃስ 16÷13

ሉቃስ 22÷26

ዮሐንስ 12÷26

ሮሜ 7÷6

ገላትያ 5÷13

ፊልጵስዩስ 2÷5-11

ገላትያ 5÷13 ላይ መብቱ ወይም ዕድሉ የተሰጠን፣ አንዳችን ሌላውን ለማገልገል መሆኑን ጳውሎስ አጽንያት ሰጥቶ መናገሩን ልብ አድርጉ። እንደ ሕያው እግዚአብሔር ልጆች መብታችንን ወይም ነጻነታችንን ራሳችንን ለማገልገል ልንጠቀምበት አይገባም። ነጻነት

ሌሎችን ለማገልገል ነው ጥቅም ላይ መዋል ያለበት። አገልጋይ በመሆን ነጻነት አለ፤ ባርያ በመሆን ግን ቀንበር አለ። ባርያ ወደደም ጠላም ያገለግላል፤ አገልጋይ ግን በነጻነት ለማገልገል ይኖራል።

በቅርታና በመራራነት መንፈስ የሚያገለግሉ ብዙ ክርስቲያኖች አይቻለሁ። እነዚህ ሰዎች በንፍገት ይሰጣሉ፤ ግብር ወይም ቀረጥ የሚከፍሉት እንኳ እየተነጫነጩ ነው። አሁንም የሕግ ባሪያዎች ሆነው እየኖሩ ነው፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከሕግ ባርነት ነጻ ወጥተው ነበር። ያም ሆኖ፣ አሁንም በልባቸው እንደ ባርያ ነው የሚኖሩት።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

የዓለም ባርነትን በመካድና የክርስቶስ አገልጋይ ለመሆን ራስን በመስጠት ጸልይ።

ቀን 19

መብታችንን መተው

ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ የምታደርጉት ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ።
- 1 ቆሮንቶስ 8÷9

(ገጽ 116-119 አንብብ)

ነጻነት የተሰጠን ለማገልገልና መብታችን ነው የምለውን ለመተው ነው። መግንባት እንጂ ማበላሸት የለብንም፤ ማነጽ እንጂ፣ ማፍረስ የለብንም። ይህ ነጻነት የተሰጠን ለራሳችን ጥቅም እንድናካብት አይደለም። ብዙ ጊዜ ግን እንዲህ ዐይነት አኗኗር ስለምንኖር፣ በዚህ ዘመን ብዙዎች በክርስቲያኖች ተሰናክለዋል። ብዙ ነገሮች ለማድረግ በክርስቶስ ነጻነት አለን፤ ይሁን እንጂ፣ የምናደርገው ሌላውን የሚያሰናክል ከሆነ፣ ለሌሎች ምስክር መሆን እንድንችል በፈቃደኝነት ራሳችንን መገደብ አለብን።

የማደርገው ነገር ሌላውን ሰው የሚያንጽ ነው ወይስ እኔ ራሴን ብቻ?

ሌሎችን ላለማሰናከል ወይም ዕንቅፋት ላለመሆን ሰትል በፈቃደኝነት የተወካችው ነገሮችን ዝርዝር አስፍር።

የተውኳቸው መብቶች	ሌሎችን ላለ ማሰናከል የተውኳቸው ነገሮች
_____	_____
_____	_____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

ሌሎችን ለክርስቶስ ለመማረክ መተው ያለብንን ነጻነትና መብት የምናውቀው እንዴት ነው? በበኩሌ ‹‹መተናነጽን ማስቀደም›› የምለውን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርብን ነው የማስበው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ፣ ‹‹ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ›› በማለት ይህን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ያቀርባል (ሮሜ 14÷19)፡፡

እያደረግን ያለው በቅዱሳት መጻሕፍት የተፈቀደ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም፣ የማደርገው ነገር ሌላውን ሰው የሚያንጽ ነው ወይስ እኔን ራሴን ብቻ? በማለት ራሳችንን መጠየቅ አለብን፡፡

የሚከተለውን ምንባብ ረጋ ብላችሁ አንብቡ፡፡ ለማድረግ የሚከብዳችሁን ክፍል ከሥሩ አሰምሩበት፡፡ አሁኑኑ ማድረግ ያለባችሁን ክበቡት፡፡

ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ ሁሉም ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር አያንጽም፡፡ እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ የራሱን ብቻ አይፈልግ፡፡ እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፡፡ ለአይሁድም ሆነ ለግሪኮች ወይም ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሰናክል አትሁኑ፤ እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር እናንተም እንዲሁ አድርጉ፤ ብዙዎች ይድኑ ዘንድ፣ ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን፣ ለእነርሱ የሚጠቅመውን እሻለሁና፡፡

- 1 ቆሮንቶስ 10÷23-24፣ 31-33

ማንኛውንም የሕይወታችሁን ገጽታ በዚህ ምንባብ መሠረት መንፈስ ቅዱስ እንዲቃኘው ፈቃደኛ ሁኑ። ለሌሎች ጥቅም ሳይሆን ለራሳችሁ ጥቅም የምታውለውትን ማንኛውንም ድብቅ መነሻ ሐሳብ ወይም አጀንዳ እንዲያሳያችሁ ጌታን ጠይቁት። በየትኛውም የሕይወት ደረጃ ብትሆኑም፣ የሁለም አገልጋይ መሆን እንዳለባችሁ የሚያቀርበውን ተግዳሮት ተቀበሉ።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

በሕይወትህ ያለውን ማንኛውንም ሌሎችን ሊያሰናክል የሚችል ነገር እንዲያሳይህ ጌታን ጠይቀ፤ ከዚያም አስወግደው።

ቀን 20

ይቅር ካላላችሁ ይቅር አትባሉም

ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኃል። እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፥ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ። ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

- *ማርቆስ 11÷24-26*

(ገጽ 121-126)

ኑን ትኩረታችንን የበደሉንን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ያለ መሆንን ውጤትና እንዴት ከበደል ነጻ መሆን እንደምንችል ማየት ላይ እናድርግ። ‹‹ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም›› በማለት ኢየሱስ የተናገረው፣ የተለየ አጽንየት ሰጥቶ ነው።

ብዙ ጊዜ የምንናገረውን ከልባችን አምነንበት አይደለም የምንናገረው፤ የምንኖረውም በእንደዚህ ያለ ማጎበረ ሰብ ውስጥ ነው። ስለዚህም ሌሎች የሚነግሩንንም ከልባቸው መሆኑ መቀበል ይከብደናል። በዚህ ዘመን አንድ ሰው የሚናገረው ከልቡ ነው ብለን አናስብም።

እንዲህ ያለው ነገር የሚጀምረው በልጅነት ዕድሜ ነው። አንድ ወላጅ ልጁን፣ ‹‹ያንን ነገር ድጋሚ ካደረግህ እገርፍሃለሁ›› አለው አንበል። ከዚያ በኃላ ግን ልጁ አንዴ ብቻ ሳይሆን በመደጋገም ያንኑ ያደርጋል። ያንን ነገር ባደረገ ጊዜ ሁሉ፣ ልጁ የበፊቱን ዐይነት ማስጠንቀቂያ ከወላጁ ይሰማል። ግን ሁሌም

የእርምት ርምጃ አይወሰድም። ምናልባት ርምጃ ቢወሰድ እንኳ ከተሰጠው ማስጠንቀቂያ በጣም የቀለለ፤ ወይም ደግሞ ወላጁ በጣም በመናደዱ ከልክ ያለፈ ሊሆን ይችላል።

እናንተ ራሳችሁ ይቅር እንድትባሉ ሌሎችን ይቅር ትላላችሁ?

ኢየሱስ ሲናገር ግን ከልባችን እንድንሰማው ይፈልጋል። እርሱ የሚናገረውን ሌሎች ባለ ሥልጣኖች ወይም በቅርብ የምናውቃቸው ሰዎች እንደሚናገሩት መውሰድ የለብንም። እርሱ አንድ ነገር ከተናገረ የተናገረው ከምር ወይም ከልቡ ነው የሚሆነው እኛ እምነት አጉዳዮች ብንሆንም፣ እርሱ ግን ታማኝ ነው። ከባሕላችን ወይም ከማኅበረ ሰባችን በላቀ እውነትና ታማኝነት ደረጃ ነው ያለው። ስለዚህም፣ ‹‹ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም›› በማለት ኢየሱስ ሲናገር የተናገረው እውነት መሆኑን ያለ አንዳች ማወላወል መቀበል እንችላለን ማለት ነው።

ከሚከተሉት ጥቅሶች ይቅር ማለትን አስመልክቶ ኢየሱስ ወንጌሎቹ ውስጥ የተናገረውን አስፍር።

ማቴዎስ 6÷14-15

_____

_____

_____

ሉቃስ 6÷37

_____

_____

_____

ማቴዎስ 6÷12

_____

_____

_____

ኢየሱስ የተናገረውን ከልባችሁ ታምናላችሁ? እናንተ ራሳችሁ ይቅር እንድትባሉ ሌሎችን ይቅር ትላላችሁ? ልባችሁ ይቅር ባለ ማለት ከተሞላ፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ የምትቀበሉበት ስፍራ አይኖራችሁም።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

አንተ ራስህ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መቀበል እንድትችል፣ የበደለህን ሰው በእውነት ይቅር ማለት እንዲያስችልህ እግዚአብሔርን ጠይቅ።

_____

_____

_____

ቀን 21

ይቅር ያላለው አገልጋይ

በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ሰንት ጊዜ ይቅር ልበለው? ሰባት ጊዜ ነውን?›› አለው።። ኢየሱስም፣ ‹‹እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፣ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም›› አለው።።

- ማቴዎስ 18÷21-22

(ገጽ 126-132 አንብብ)

ሌሎችን ይቅር ማለት መሠረት የሚያደርገው ገደብ የለሽ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደ ሆነ ኢየሱስ ለጴጥሮስና ለሌሎች ደቀ መዛሙርት አስተማረ። ለዚህ ትምህርቱ አጽንየት ለመስጠት ይቅር ማለት ያልፈለገውን አገልጋይ ምሳሌ አቀረበ።

ከማቴዎስ 18÷23-35 እንደ ገና ይህ ምሳሌ አንብብ። ከዚያም እነዚህ ዐረፍተ ነገሮችን ሙላ።

እኔ እንደምረዳው የምሳሌው ዋና ነጥብ _____

_____ነው።

በዚህ ምሳሌ አማካይነት ለእኔ እግዚአብሔር የተናገረኝ_____

_____ነው።

ሌሎች ላይ የምንቆጥረው በደል፣ እኛ ራሳችን እግዚአብሔር ላይ ከፈጸምነው በደል ጋር ሲነጻጸር 4,000 ብርንና 4.5 ቢሊዮን ብርን የማነጻጸር ያህል ይሆናል። ምናልባት አንድ ሰው በድሎን ይሆናል፤ ሆኖም እኛ እግዚአብሔር ላይ ከፈጸምነው በደል ጋር ጨርሶ

ሊነጻጸር አይችልም። ኢየሱስ ከዘላለም ሰቃይና ሞት እንዳዳነን ከተቀበልን፣ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሌሎችን ከበደል እስራት እንፈታለን።

ለሚከተለው በደሎች ነጥብ ስጥ፤ ይቅር ለማለት በጣም አስቸጋሪ ለሆነባችሁ (1) በመጠኑ አስቸጋሪ ለሆነባችሁ (7) ነጥብ ስጥ።

_____ እኔ ላይ ሐሜት ከተፈጸመ።

_____ አንድ ሰው አካላዊና ስሜታዊ ጉዳት ካደረሰብኝ።

_____ አንድ ሰው እኔ በጣም የምወደው ሰው ላይ አካላዊና ስሜታዊ ጉዳት ካደረሰ

_____ አንድ ሰው ከዋሸኝ።

_____ አንድ ሰው ከሰረቀኝ።

_____ አንድ ሰው ጫና ሊያደርግብኝ ከሞከረ።

_____ ሌሎች

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ይቅር አለማለት ልብህ ላይ ያኖረውን ማነቆ እንዲያስወግድልህ እግዚአብሔርን መጠየቅ። በተለይ ደግሞ በደላቸው ማነቆ ውስጥ እንድትሆን ምክንያት ለሆኑብህ ሰዎች መጸለይ።

_____

_____

ቀን 22

በቀል - አደገኛው ወጥመድ

ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤
በሰው ሁሉ ፊት በጐ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ።
- ሮሜ 12÷17

(ገጽ 135-139 አንብብ)

ሰዎችን ይቅር አለማለት እነርሱ ላይ ዕዳ የማኖር ያህል ነው። አንድ ሰው በሌላው ሰው ከተበደለ በዳዩ ላይ ዕዳ እንዳለው ያስባል። ገንዘብም ይሁን ወይም ሌላ ነገር አንድ ዐይነት ክፍያ ይጠብቃል። ይሁን እንጂ፣ እኛ ራሳችን መበቀል፣ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆንነው ለእኛ ትክክል አይደለም።

የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና በቀልን በተመለከተ ምን እንደሚያስተምሩ በአጭሩ ጻፍ።

ሮሜ 12÷19

_____

_____

ያዕቆብ 4÷12 ፤ 5÷9

_____

_____

_____

ሮሜ 5÷38-42

_____

_____

_____

ቂም መያዝን በተመለከተ ኢየሱስ በግልጽ ነው የተናገረው። እንዲያውም፣ ሰዎች በድጋሚ መጠቀሚያ ቢያደርጉን እንኳ የእኛ ዝንባሌ ከበቀል የራቀ መሆን እንዳለበት ተናግሮአል።

በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እንድንተከልና ሥር እንድንሰድ ተመክረናል።

ኢየሱስ ስለ ልባችን ሲናገር በአፈር መስሎታል። በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እንድንተከልና ሥር እንድንሰድ ተመክረናል። ያኔ የእግዚአብሔር ቃል ዘር ልባችን ውስጥ ሥር ይሰዳል፤ ከዚያም ያድግና ፍቅርን፣ ደስታን፣ ትዕግሥትን፣ ሰላምን፣ ቸርነትን፣ በጐነትን፣ ታማኝነትን፣ ገርነትንና ራስን መግዛትን የመሳሰሉ የጽድቅ ፍሬ ያፈራል (ገላትያ 5÷22-23 ይመ.)።

አንድ እርሻ የሚያፈራው የተዘራበትን ወይም የተተከለበትን ብቻ ነው። የጥርጥርን፣ ይቅር ያለ ማለትንና የበደልን ዘር ከዘራን በእግዚአብሔር ፍቅር ቦታ ሌላ ነገር ይበቅላል። ይህም የመራራነት ሥር ይባላል (ዕብራውያን 12÷14-15)። መራራነት ሥር ነው። ያንን ሥር ከተንከባከብነው፣ ውሃ ካጠጣነው፣ ከመገብነውና ትኩረት ከሰጠነው ጥልቀቱ እየጨመረና የበለጠ እየጠነከረ ይሄዳል። ቶሎ ካልተቀጨ አንድን ሥር መንቀል በጣም ከባድ ነው። የበደል ዘር ማደጉን ይቀጥላል። ያኔ የጽድቅን ፍሬ ሳይሆን የቁጣን፣ የቅርታን፣ የቅንዓትን፣ የጥላቻን፣ የመለያየትና የጸብን ፍሬ እናጭዳለን። እነዚህን ፍሬዎች መጥፎ ፍሬዎች እንደ ሆኑ ኢየሱስ ተናግሮአል (ማቴዎስ 7÷19-20)።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ልብህ ውስጥ ማነቆ ሆኖ የነበረውን በደል ከመፍታትህ የተነሣ የእርሱ ሰላም ወደ ሕይወትህ ስለ መጣ እግዚአብሔርን ማመስገን።

ቀን 23

ለንጉሥነት የታጨው ረክሶ ተገኘ

አቤሴሎም አምኖንን ክፉም ሆነ ደግ አንዳች ቃል አልተናገረውም፤ ምክንያቱም አምኖን እኅቱ ትዕማርን ስላስነወራት ጠልቶት ነበር።

- 2 ሳሙኤል 13÷22

(ገጽ 139-143 አንብብ)

አምኖንን በመግደል አቤሴሎም የትዕማርን መደፈር ተበቀለ። እኅቱ ትዕማርን በመድፈሩ አምኖንን ሳይቀጣው በመቅረቱ ዳዊትም ላይ ቂም ይዞ ነበር። የአቤሴሎም ሐሳብ በመራራነት ተመረዘ። የዳዊትን ደካማ ጐን በመንቀፍና በመተቸት የተዋጣለት ሆኖ ተገኘ። ያም ሆኖ፣ አንድ ቀን አባቱ እንደሚያስጠራው ተስፋ አድርጐ ነበር። ዳዊት እንደዚያ ባለ ማድረጉ የአቤሴሎምን ቅርታ የበለጠ አቀጣጠለው።

በደልን መሠረት ካደረገው ነቃፊ ዝንባሌ በመነሣት፣ አቤሴሎም ዳዊት ላይ ቅርታ ያደረባቸውን ሁሉ ወደ ራሱ መሰብሰብ ጀመረ። ወደ እርሱ የሚመጡ ሁሉ በቀላሉ የሚያገኙትና የእነርሱን ማጉረምረም ለመስማት ዝግጁ ሆኖ ተገኘ። እርሱ ንጉሥ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሮች የተለየ መልክ ይኖራቸው እንደ ነበር ይናገር ነበር። ንጉሡ ለእነርሱ ጊዜ የሌለው መስሎ በመታየቱ፣ ወደ እርሱ የሚመጣውን ጉዳይ አቤሴሎም ፍርድ መስጠት ጀመረ። አቤሴሎም ለእነርሱ ፍርድ የሰጠው እርሱ ራሱ ፍትሕ ጠብቆ ሳያገኝ ከመቅረቱ የተነሣ ሊሆን ይችላል።

ለሕዝቡ የሚያስብና የሚቆረቆር መስሎ ታይቶ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ከአባቱ ከዳዊት ላይ የእስራኤልን ሕዝብ ልብ ሰረቀ

ይላል፡፡ ነገር ግን በእርግጥ ለሕዝቡ የሚያስብና የሚቆረቆር ነበር ወይስ በድሎኛል የሚለው ዳዊትን ለመጣል ያደረገው ሤራ ነው?

በጎሊናችን በኩል መንፈስ ቅዱስ ሲናገር እንወቀሳለን፡፡

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ረዳት ሆነው የሚሠሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ እያገለገለ ባለ·ት ሰው ይሰናከላለ·፡፡ መሪው ላይ ወይም እርሱ በመረጣቸው ሰዎች ላይ ያለ· ደካማ ጐኖችን ሲያጋልጡና ሲያጣጥለ· ይሰማል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን የእንዲህ ያለ· ሰዎች አመለካከት ይጣመማል፡፡ እግዚአብሔር ከሚያይበት ፍጹም ልዩ በሆነ ሁኔታ ነገሮችን ያያለ·፡፡

የሚከተለ·ትን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ፡፡

የቤተ ክርስቲያንን አመራር የሚመለከት ነቀፋ ወይም ትችት ይዘው ሰዎች ወደ እኔ ሲመጡ _____

_____

_____ አደርጋለሁ፡፡

የቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ነቀፋ ካለኝ _____

_____

_____አደርጋለሁ፡፡

በክርስቶስ አካል ማለትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚችለውን በደል በተመለከተ ውጤታማ የአያያዝ መንገድ _____

_____

_____ነው፡፡

አመራሩን ጨምሮ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በድለውኛል ወይም አሰናክለውኛል የምትላቸውን ሰዎች ዘርዝር። ስማቸውን ከጻፍህ በኃላ ወደ እነርሱ በመሄድ ይቅርታ የምትጠይቅበትንም ቀን ጻፍ።

ስም **ይቅርታ መጠየቅ የማስብበት ቀን**

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የተመለከትከው ድካም እውነት ሊሆን ይችላል። ምናልባት ዳዊት አምኖን ላይ ርምጃ መውሰድ ነበረበት። ምናልባት መሪው የተሳሳተበት አቅጣጫ ይኖራል። ያም ሆኖ ግን፣ ፈራጅ ማን ነው – አንተ ወይስ እግዚአብሔር? ፀብን የምትዘራ ከሆነ ያንኑ እንደምታጭድ ልብ አድርግ።

በጎሊናችን በኩል መንፈስ ቅዱስ ሲናገር እንወቀሳለን። የእርሱን ወቀሳ ችላ እንዳንል ወይም ሰምተን እንዳልሰማ እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን። እንዲህ አድርገህ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ግባ፤ ለእርሱ እርምት ልብህን ክፈት።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ነቃፊና ተቺ መንፈሰን ከአንተ እንዲያርቅ እግዚአብሔር መጠየቅ።

ቀን 24

ከወጥመዱ ማምለጥ

ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ።

- ሐዋርያት ሥራ 24÷16

(ገጽ 145-149 አንብብ)

ከበደል ነጻ ሆኖ ለመኖር ጥረት ይጠይቃል። ጳውሎስ ከአካላዊ ከልምምድ ጋር ያመሳስለዋል። አካላችንን በልምምድ ካዳበርነው ለአደጋ የመጋለጥ ዕድላችን ጠባብ ይሆናል። ይቅር ማለትን የምንለማመድን፣ ከሆነና በደልን አለመቁጠር ከተለማመድን፣ ያኔ ኅሊናችን ለመልካም ነገር የተመቻቸና ንጹሕ ይሆናል።

ከበደል ነጻ ሆኖ ለመኖር ጥረት ይጠይቃል።

አንዳንዴ ሰዎች ሲበድሉን ይቅር ማለት ከባድ አይሆንብንም። ልባችንን በደል አለመቁጠር ስላለማመድነው በቀላሉ አንጐዳም ወይም ዘላቂ ጉዳት አይደርስብንም። አንዳንድ በደሎች ልምምድ ካደረግንባቸው የበለጠ ይቅር ለማለት ይከብዱናል። ይህም ተጨማሪ ውጥረት፣ ቁስል ወይም ስብራት ያስከትላል፤ ከዚያ ለመፈወስና መንፈሳዊ ልምምድ ማድረግ ይኖርብን ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ውጤቱ መልካም ነው የሚሆነው። ምናልባትም ጉዳት ወይም ከባድ ቁስል ደርሶባችሁ ይሆን? ከዚያ ለመፈወስ ለመውጣት የሚያስፈልጉ ልምምዶች ከታች ተዘርዝረዋል።

እያንዳንዱን ርምጃ ካነበብክ በኃላ ከዚያ ለመውጣት የምትሰጠውን ምላሽ ጻፍ።

1. መሞዳትህን ተቀበል።

   _____

   _____ ተጐድቻለሁ።

2. ጉዳትህን ለሌታ ግልጽ አድርግ።

   ጌታ ሆይ፣ _____

   በመሆኑ ተጐድቻለሁ _____

3. ለሚሰጥህ እርምትና ምሪት ዝግጁ ሁን።

   ጌታ ሆይ፣ አንተ_____እንደምትፈልግ ዐውቃለሁ።

   ስለዚህ _____ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።

4. በመጨረሻ የጐዳንን ሰው ይቅር ማለት ይኖርብናል።

   ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ _____ ለደረሰብኝ _____ ጉዳት ይቅር እላለሁ።

አንድን ሰው ይቅር ካልን በኃላ ሊገጥመን የሚችል ችግር፣ እንደገና ወደዚያ መመለስን ማስወገድ ነው። አልፎ አልፎ ያንን ሰው ይቅር ከማለታችን በፊት የነበረን ምሬት ብቅ እያለ ያስቸግረን ይሆናል። እንዲህ ሲሆን እኛ ማድረግ ያለብን ለዚያ ሰው መጸለይ እንደሚገባን ማስታወስ ነው። ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ ያሳዩዋችኃል።

ጥቅሶቹን አንብብና ለበደሉን ሰዎች ምን ዐይነት ዝንባሌ እንዲኖረን እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ጻፍ።

ማቴዎስ 5÷44

_____

_____

መዝሙር 35÷11-14

2 ቆሮንቶስ 10÷5

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ
ለበደሉን ሰዎች ጥልቅ ፍላጐት መጸለይ።

ቀን 25

ፊት ለፊት በመገናኘት መፈወስ

ፍቅር ብዙ ኃጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ።።

- *1 ጴጥሮስ 4÷8*

(ገጽ 149 — 152 አንብብ)

አንዳንዴ ፈውስ የምናገኝበት መንገድ ፊት ለፊት በመገናኘት ብቻ ሊሆን ይችላል። ምንም በደል ያላደረሱብንን ሰዎች መውደድ ቀላል ነው፤ እንዲህ ያለው ፍቅር የጫጉላ ፍቅር ይባላል። በደል ያደረሱብንን ሰዎች መውደድ ግን ፍጹም ሌላ ነገር ነው።።

አዳጋች ቦታዎችና ከባድ ተግዳሮቶች ምንጊዜም ቢሆን ከጌታ ጋር የምናደርገው ጉዞ አካል ናቸው። እንዲህ ያለ ሁኔታዎችን በፍጹም ማምለጥ አንችልም። በእርሱ ፍጹማን የመሆን ሂደት አካል በመሆናቸው ፊት ለፊት ልንገናኛቸው ይገባል፤ ከእንዲህ ዐይነት ሁኔታዎች ሸሽተህ ማምለጥን ከመረጥህ ግን ዕድገትህን በጣም ታሰናክላለህ።።

የተለያዩ መሰናክሎችን እያሸነፍህ ስትሄድ፣ የበለጠ ብርቱ፣ የበለጠ ርኅሩኅ ትሆናለህ። ኢየሱስን የበለጠ ትወዳለህ። ከአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ በአሸናፊነት ስትወጣ፣ እንዲህ የማይሰማህ ከሆነ፣ ምናልባት ከደረሰብህ ጉዳት በሚገባ አልተፈወስህም ይሆናል። ከዚያ ሙሉ በሙሉ መውጣትን መምረጥ አለብህ። ብዙዎች ያንን ማድረግ ባለ መምረጣቸው፣ ከደረሰባቸው ጉዳት መፈወስ አልሆነላቸውም።።

- ካለፈ በደል የተነሣ አሁንም ጉዳት የሚሰማህ ከሆነ፣ ምክንያቱ አሁንም ጉዳቱን ማብላላት በመምረጥህ ነው።
- ለመፈወስ መንገዱ ይቅር ማለት ብቻ ነው። በደሉንና በደል አድራሹን ሰው ለጌታ መተው አለብን።
- ለሌሎች ሩኅሩኅ አለመሆን የሚመጣው ድካማቸውን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ባለ መሆን ነው።
- መንፈሳዊ ዕድገትህ መሠረት የሚያደርገው ፊት ለፊት ለመጋፈጥ፣ ይቅር ለማለትና ያለፈ በደልን ላለ መቁጠር ፈቃደኛ መሆንን ነው።

ከደረሰበት መከራ የተነሣ ኢየሱስ መታዘዝን ተማረ። ከደረሰበት መከራ የተነሣ ጴጥሮስ መታዘዝን ተማረ። ከደረሰበት መከራ የተነሣ ጳውሎስ መታዘዝን ተማረ።

መንፈሳዊ ዕድገትህ መሠረት የሚያደርገው
ፊት ለፊት ለመጋፈጥ፣ ይቅር ለማለትና
ያለፈ በደልን ላለ መቁጠር ፈቃደኛ መሆንን ነው።

አንተን በተመለከተስ? የሚገባውን ትምህርት ተምረሃል? ባለፈው ጊዜ ከደረሰብህ በደል የተነሣ አሁን ምንድነው የሚሰማህ?

ከታች በሁለት መደዳ ባሉት ውስጥ አሁን የሚሰማህን በትክክል የሚያመላክት ቃል ሳጥን ውስጥ ✓ አድርግ።

የተፈወሱ ስሜቶች	የተጐዱ ስሜቶች
☐ ነጻነት	☐ ሸክም
☐ ይቅር ማለት	☐ ይቅር አለማለት
☐ ፍቅር	☐ በቀል
☐ ገርነት	☐ ግትርነት
☐ ርኅሩኅነት	☐ ፈራጅነት
☐ ተቀባይነት	☐ ንቀት

☐ ትሕትና
☐ መፈታት
☐ ሰላማዊነት
☐ ደስተኝነት
☐ ፈውስ
☐ መታደስ
☐ ትዕቢት
☐ እስራት
☐ ቁጣ
☐ ሐዘን
☐ ስብራት
☐ መራራነት

ከተፈወሱት ይልቅ አሁንም ጉዳት ላይ ያሉ ምልክቶች ላይ የበለጠ ምልክት አድርገህ ከሆነ፣ የፈውስ ሂደትህ አቁሞአል፤ ምናልባት ለእግዚአብሔር ምሪት እየታዘዝህ አይደለም፤ በመንፈሳዊ ሕይወትህ እየበሰልህ አይደለም ማለት ነው።

በሳልነት በቀላሉ አይመጣም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ሰው ሁሉ በሳል ይሆን ነበር። ከሚገጥማቸው ተቃውሞ የተነሣ እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርሱ ጥቂቶች ናቸው። ይህ ዓለም፣ ‹‹በአየር ላይ ሥልጣን ባለው አለቃ›› እየተገዛ ነው (ኤፌሶን 2÷2)። የማጎበረ ሰባችን መንገድ የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም፤ ይልቁን ራስ ወዳድ ነው። ከዚህም የተነሣ በክርስቶስ ወዳለው በሳልነት መግባት ራስ ወዳድ ከሆነው ሥርዐት የሚመጣ ተቃውሞ ይገጥመዋል።

ለክርስቶስ ስንል ሕይወታችንን ብናጣ፣ የእርሱን ሕይወት እንደምንቀበል አትርሱ። ትኩረታችሁን ትግሉ ላይ ሳይሆን፣ የመጨረሻው ውጤት ላይ አድርጉ። (1 ጴጥሮስ 4÷12-13 ይመ.)።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

እያለፍህበት ስላለው ፈተናና ተቃውሞ እግዚአብሔርን ማመስገን። ከእነዚህ ውጣ ውረዶች የተነሣ ስለሚመጣው ውጤት እግዚአብሔርን ማመስገን።

ቀን 26

የመጨረሻው ግብ – ዕርቅ

ለቀደሙት ሰዎች - አትግደል የገደለ ይፈረድበታል፤ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን ‹ጅል› የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ ‹ደደብ› የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል። በመጀመሪያ ሂደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ።

- ማቴዎስ 5÷21-22፣24

(ገጽ 155-157 አንብብ)

በተራራው ስብከቱ ኢየሱስ መጀመሪያ ውጫዊ ተግባራችንን የሚመለከት ሕግ ጠቀሰ። ከዚያም ያንን ከልብ ጋር በማያያዝ የሕጉን ፍጻሜ አሳየ (ማቴዎስ 5÷21-22፣24 ይመ.)። በእግዚአብሔር ዐይን ግድያ አካልን በመግደል ብቻ አይወሰንም፤ ወንድምን መጥላትም ግድያ ነው። ማንኛችንም ብንሆን፣ ልባችን ውስጥ ያለውን ነው በእውነት የምንሆነው!

በዚህ የስብከቱ ክፍል ኢየሱስ የበደል ውጤቶችን በግልጽ አሳይቶአል። ቂጣን ወይም የመራራነትን በደል መያዝ ምን ያህል ከባድ መሆኑን አመልክቷል። አንድ ሰው ያለ በቂ ምክንያት ወንድሙ ላይ ከተቆጣ ይፈረድበታል። ቂጣ ቶሎ መፍትሔ ካልተደረገለት ወደ ጥላቻ እንደሚመራ ኢየሱስ እያመለከተ ነው። ጥላቻም ቶሎ መፍትሔ ካልተደረገለት ለገሃነም ፍርድ ያደርሳል። ኢየሱስ ተከታዮቹን በተቀዳሚ ደረጃ ዕርቅን እንዲፈልጉ መክሯል።

በእንዲህ ያለ ሁኔታ ዕርቅ እንድንፈልግ የተነገረን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን፣ ለወንድማችንም ጥቅም ነው። ከተፈጸመው በደል

እንዲወጣ እርሱን የምንረዳ መሣሪያዎች እንሆናለን። እርሱን አግኝተን ወደ መታደስ ከማምጣት ይልቅ፣ ወንድማችንን ቁጣ ላይ ባለበት ሁኔታ እንድንተወው የእግዚአብሔር ፍቅር አይፈቅድልንም። ምናልባት እኛ ራሳችን ምንም በደል አልፈጸምን ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ የእኛን ትክክል መሆን ከማረጋገጥ የተሰናከለውን ወንድም መርዳት የበለጠ ጠቃሚ ነው።

ብዙ ጊዜ ራሳችን ላይ የምንፈርደው በነበረን ፍላጐት መሠረት ቢሆንም፣ ሌሎች ላይ የምንፈርደው ግን በድርጊታቸው ነው።

ከዚህ በፊት ተቀያይማችሁ የነበሩ ሰዎችን ዘርዝር። ከእያንዳንዱ ሰም ጐን ወደዚያ ሰው ሂደህ ዕርቅ የምታወርድበትን ቀን እና ሰዓት ጻፍ።

የሰዎቹ ስም	ቀን	ሰዓት

ብዙ ጊዜ ራሳችን ላይ የምንፈርደው በነበረን ፍላጐት መሠረት ቢሆንም፣ ሌሎች ላይ የምንፈርደው ግን በድርጊታቸው ነው። አንድን ነገር አስቦ ፍጹም የተለየ ነገር ማስተላለፍ ይቻላል። አንዳንዴ ደግሞ እውነተኛው መነሻ ሐሳባችን ከእኛ ከራሳችን እንኳ የተደበቀ ሊሆን ይችላል። ያም ሆኖ ግን፣ እውነት ወይም ትክክል

እንደ ሆነ ነው የምናምነው። በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ስንመለከተው ግን በተለየ ዐይን እናየዋለን። ዕርቅ ማድረግ የምትፈልግ ከሆነ፣ ጥሩ መነሻ ሐሳብ ብቻ አይበቃም። ወዲያውኑ መሄድና ዕርቁን ማድረግ ይኖርብሃል።

እናንተስ ዕርቅ ማድረግ ትፈልጋላችሁ?

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

በደል ወዳደረሰብህ ማንኛውም ሰው ሂደህ ዕርቅ እንድታደርግ እግዚአብሔር የፍቅርንና የድፍረትን ኃይል እንዲሰጥህ መጸለይ።

ቀን 27

ከተበደለው ወገን ይቅርታ መጠየቅ

ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ።

- ሮሜ 14÷19

(ገጽ 157-158 አንብብ)

ሮሜ 14÷19 የበደልነውን ሰው እንዴት መቅረብ እንዳለብን ያሳየናል። በንዴትና በቁጣ መንፈስ ከሄድን ሰላም አናመጣም፤ ይልቁን ለተጐዳው ሰው የበለጠ ከባድ እናደርግበታለን። ትዕቢትን አስወግደን በትሕትና ዕርቅ መፈለግ አለብን። እውነተና ዕርቅ የሚኖረው ያኔ ብቻ ነው።

የጐዳሁዋቸውን ወይም እኔ ላይ የተቆጡ ሰዎችን የቀረበኩበት ጊዜ ነበር። እነዚህ ወገኖች ራስ ወዳድ፣ ለሌሎች የማያስብ፣ ትዕቢተኛ፣ ደፋር ቁጡና ሌላም የበለጠ ነገር እንደ ሆንኩ ነግረውኛል።

በተፈጥሮአዊ ደረጃ የእኔ መልስ፣ ‹‹የለም፣ እኔ እንደዚያ አይደለሁም፤ ችግሩ እኔን ካለመረዳታችሁ የተነሣ ነው!›› ማለት ይሆን ነበር። ይሁን እንጂ፣ ለራሴ መከራከሬ እነርሱን ከማስቆጣት ያለፈ ውጤት ሲያስገኝ አላየሁም። ሰላም የሚመጣው በዚህ መንገድ አይደለም። ለራሳችንና ‹‹ለመብታችን›› ብቻ መከራከር እውነተኛ ሰላም አያስገኝም።

ይልቁንም የሚናገሩትን ተናግረው እስኪጨርሱ ድረስ ማድመጥና ዝም ማለት እንዳለብኝ ነው የተማርኩት። ካልተስማማሁ፣ የተናገሩትን እንደማከብርና የእኔን ልብና ዓላማ

እንደምመረምር እንዲያውቁ አደርጋለሁ። ከዚያም እነርሱን በመጉዳቴ ማዘኔን እነግራቸዋለሁ።

ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብ፣ ይቅር ባይና ዕርቅ አድራጊ ነው።

አንዳንዴ ደግሞ፣ እኔን በተመለከተ የተናገሩት ሁሉ ትክክል ሊሆን ይችላል፤ እንዲህ ከሆነ፣ ‹‹የተናገራችሁ ትክክል ነው፤ ይቅርታችሁን እጠይቃለሁ›› በማለት ችግሩ የእኔ መሆኑን እቀበላለሁ።

በቅርቡ ይቅርታ እንዲያደርግልህ ጠይቀኸው የነበረ ሰው አስታውስ። በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እንደ ቀረብኸው በአጭሩ አመልክት። አንተ የተናገርከውን ወይም ያደረግኸውን ከትዕቢት የሆነ ነገር ክብ አድርግበት።

ራሳችንን ዝቅ ማድረግ ዕርቅ ያስገኛል። ትዕቢት ለራሱ ይከራከራል፤ ትሕትና ግን፣ ‹‹ትክክል ነህ፤ አጥፍቻለሁ፤ እባክህ ይቅር በለኝ›› በማለት ይስማማል።

ያዕቆብ 3÷17 አንብብና በራስህ ቃል ጻፍ።

ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብ፣ ይቅር ባይና ዕርቅ አድራጊ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብ ግጭት ወይም አለ መግባባት ሲኖር አንገተ ደንዳና ወይም ግትር አያደርግም። መንፈሳዊ

ማስተዋል ያለው ሰው እውነትን እስካልተጻረረ ድረስ፣ ሌላው ሰው የሚያቀርበውን ሐሳብ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል አይፈራም።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ልብህ ውስጥ ያለውን በደል እንዲያሳይህና የበደልካቸውን ሰዎች ለማናገር ጥበብ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን መለመን።

ቀን 28

የበደላችሁትን ሰው መቅረብ

ወንድምህ በበድልህ ሂደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው፡፡ ቢሰማህ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ፡፡

- ማቴዎስ 18÷15

(ገጽ 158-161 አንብብ)

ብዙዎች ማቴዎስ 18÷15 ተግባር ላይ የሚውሉት ኢየሱስ ከተናገረበት ፍጹም በተለየ መንፈስ ነው፡፡ ተበድለው ከሆነ በዳዩን የሚያናግሩት በበቀልና በቁጣ ነው፤ ያድረጉት ትክክል መሆኑን ለማሳየት፣ ይህን ጥቅስ ያቀርባሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በደል ወዳደረሰብን ሰው መሄድ እንዳለብን ኢየሱስ የተናገረበትን ምክንያት በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል፡፡ ያንን ማድረግ ያለብን ሌላው ወገን ላይ ለመፍረድ ሳይሆን ለዕርቅ ነው፡፡ ወደ ወንድማችን ሂደን ምን ያህል እንደ በደለንና ክፉ ሰው መሆኑን እንድንነግረው አይደለም፡፡ ኢየሱስ ይህን የተናገረው በእኛና በበደለን ሰው መካከል የነበረውን ግንኙነት እንድናስተካክል ነው፡፡

እኛን ወደ ራሱ ለመመለስ እግዚአብሔር የሚጠቀምበትም መንገድ ይኸው ነው፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ብንበድልም፣ ‹‹ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል›› (ሮሜ 5÷8)፡፡ ከበደለን ሰው ጋር የነበረንን ግንኙነት ለማደስ፣ ለራስ የመከላከል ዝንባሌያችንን ለመተውና ለትዕቢታችን ለመሞት ፈቃደኞች ነን? እግዚአብሔር ወደ እኛ የመጣው እኛ ይቅርታ ከመጠየቃችን በፊት ነበር፡፡ ኢየሱስ እኛን ይቅር ለማለት የወሰነው እኛ በደል መፈጸማችንን እንኳ ከመገንዘባችን በፊት ነበር፡፡

ሮሜ 5÷6-11 በጥንቃቄ አንብብና ለሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ምላሽ ስጥ፡፡

እግዚአብሔር ወደ እኔ ሲመጣ እኔ _____
_____ነበርኩ።

እግዚአብሔር ወደ እኔ መምጣቱ የእርሱን _____
_____ያሳያል።

እርሱ ወደ እኔ የመጣበት ምክንያት _____
_____ነበር።

ወደ እኔ በመምጣቱ እግዚአብሔር ያደረገው _____
_____ነበር።

ምንም እንኳ እርሱ ወደ እኛ ቢመጣም፣ የእርሱን የዕርቅ ቃል እስካልተቀበልን ድረስ ከአብ ጋር መታረቅ አንችልም።

ኢየሱስ ይህን የተናገረው በእኛና በበደለን ሰው መካከል የነበረውን ግንኙነት እንድናስተካክል ነው።

ሰዎች እግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንደ ፈጸሙ አዲስ ኪዳን ውስጥ ደቀ መዛሙርት ሰብከዋል። ግን ሰዎች ኃጢአት ማድረጋቸውን መንገር ለምን አስፈለገ? በእርሱ ለመፍረድ ነውን? እግዚአብሔር ግን በማንም ላይ አይፈርድም። ‹‹እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው›› (ዮሐንስ 3÷17)። ሰዎች ኃጢአት ማድረጋቸውን መንገር አስፈላጊ የሆነው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት፣ በኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡና ይቅርታ እንዲጠይቁ ነው።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ንስሐ ማድረግና ከበደልከው ወይም ከበደለህ ሰው ጋር ዕርቅ ለማድረግ እግዚአብሔር እንዲረዳህ መጸለይ

_____

_____

_____

ቀን 29

የመጨረሻ ነገር

ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡

- ሮሜ 12÷18

(ገጽ 162-163)

ወንሻ ሐሳባችን የእግዚአብሔር ፍቅር ከሆነ ጨርሶ አንጠፋም፤ ምክንያቱም ፍቅር ጨርሶ አይጠፋም፡፡ ኢየሱስ እኛን በወደደበት መንገድ እኛም ሌሎችን ከወደድን፣ ሌላው ሰው ከእኛ ጋር መታረቅ ባይፈልግ እንኳ እኛ ነጻ እንሆናለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ቢቻላችሁስ›› ነው ያለው፤ ምክንያቱም አንዳንዴ ሰዎች ከእኛ ጋር በሰላም ለመኖር የማይፈልጉበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ወይም ደግሞ ዕርቅ ለማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንድናመቻምች የሚያደርግ ቅድመ ሁኔታ ይጠይቁ ይሆናል፡፡ በሁለቱም መንገድ ከእነርሱ ጋር የነበረንን ግንኙነት ማደስ አይቻልም፡፡

ለእውነት ያለን ታማኝነት እስከ ተጠበቀ ድረስ፣ ከሌሎች ጋር ለመታረቅ የሚቻለንን ማንኛውንም ነገር ማድረግ አለብን፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ግንኙነታችንን ቶሎ እናቋርጣለን፡፡

ኢየሱስ ‹‹ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና›› ብሏል (ማቴዎስ 5÷9) ‹‹ሰላማቸውን የሚያስጠብቁ›› አይደለም ያለው፡፡ ሰላሙን የሚያስጠብቅ ሰው እውነትን ማመቻመች እንኳ ቢሆን፣ ምንም ግጭት እንዳይኖር ፊት ለፊት አይጋፈጥም፡፡ የእንዲህ ዓይነቱ ሰው

ሰላም እውነተኛ ሰላም አይደለም፤ ዘለቄታ የሌለው እንዲሁ ላይ ላዩን የሆነ የውሸት ሰላም ነው።

ፍቅር አይወድቅም፣ አያረጅም፣ ጨርሶ አይጠፋም።
የራሱን አይፈልግም በቀላሉ አይበሳጭም

ሰላም የሚያወርድ ሰው ማንኛውንም ነገር ወይም ሁኔታ ፊት ለፊት በፍቅር ይጋፈጣል፤ ዕርቁ ዘላቂነት እንዲኖረው እውነትን ያመጣል። አርቲፊሻልና አስመሳይ ግንኙነት አይቀበልም። ግልጽነትን፣ እውነትንና ፍቅርን ይፈልጋል። ከልብ ያልሆነ ፈገግታ ለማሳየት ጥፋትን አይደብቅም። ሰላምን የሚያወርደው እውነትን በድፍረት በሚናገርና ጨርሶ በማይጠፋ ፍቅር ነው።

ምን ያህል ውጤታማ ሰላም የምታወርድ ሰው ነህ? ከታች ሰላም የሚያወርድ ሰው ጥቂት ባሕርያት ቀርበዋል። አንተን የሚያመለክት መሰመር ላይ X አድርግ።

ሰላም የሚያወርዱ...

ሰው ወዳድ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ታጋሽ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ይቅር ባይ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ግልጽ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ለጥቃት የተጋለጠ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ለመስማት የፈጠነ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ለቁጣ የዘገየ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ለመናገር የዘገየ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ታዛዥ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ከእግዚአብሔር የሚሰማ

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

እውነተኛ ትሑት

☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ ☐ ነኝ ☐ መሆን አለብኝ

ኢየሱስ እነዚህ ባሕርያት ሁሉ ነበሩት። የሰላም ንጉሥ መንፈስ እኛ ውስጥ መኖር ሲጀምር እኛም እነዚህን ሁሉ እንሆናለን። እርሱ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም። ይሁን እንጂ፣ ዝምድና እንዳይቋረጥ ብሎ በእውነት ላይ አይደራደርም። እንዲሁ ላይ ላዩን በሆነ ድርድር ሳይሆን፣ በእውነተኛ መሰጠት ዕርቅ እንዲኖር ይፈልጋል። ይህም ማንኛውንም ክፉ ኃይል የማይበጥሰው ጠንካራ የፍቅር ማሰሪያ ይሆናል። እርሱ ለእኛ ሕይወቱን ሰጥቷል። እኛም እንደዚያ ማድረግ ይኖርብናል።

ፍቅር አይወድቅም፣ አያረጅም፣ ጨርሶ አይጠፋም። የራሱን አይፈልግም በቀላሉ አይበሳጭም (1 ቆሮንቶስ 13 ይመ.)።

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

ሌሎችን ይልቁንም ጠላቶችህንና ሊበድሉህ የሚችሉ ሰዎችን ለመውደድ ልብህን በእርሱ ፍቅር እንዲሞላው መጸለይ።

ቀን 30

ርምጃ መውሰድ

እንግዲህ መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው ኃጢአት ያደርጋል።

- ያዕቆብ 4÷17

(ገጽ 165-167 አንብብ)

አሁን ወደ ተግባር የምንገባበት ጊዜ ነው! የደበቅሃቸውን፣ የረሳሃቸውን ወይም እንደሌለ የቆጠርካቸውን በደሎች እንዲያሳስብህ ጌታን ጠይቅ። ባለፈው ጊዜ የተቀያየማችኃቸው ሰዎችን ወደ አእምሮህ እንዲያመጣ መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ።

ልብህ ካለፈ በደል ወይም መሰናክል
መንጻቱን ካወቅህና የተረጋጋ ከሆነ፣
ጸንተህ በመቆም ወደ ፊት ሊኖር
የሚችለውን የሰይጣን ሽንገላ መቋቋም አለብህ።

ለመጸለይና ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ሁን። ወደ እነርሱ ሄደህ ይቅርታ ለመጠየቅና ዕርቅ ለማድረግ ተዘጋጅ። ለጸሎትህ እንደ መመሪያ እንዲሆን ገጽ 166 ላይ ባለው ጸሎት መጠቀም ትችላለህ።

ለጸሎት እየተዘጋጀህ እያለ ለሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የምትሰጠውን ምላሽ አስፍር።

በዚህ የሰላሣ ቀን የጽሞና ማሰላሰያ ፕሮግራም የተማርኩት በጣም አስፈላጊ ነገር _____

_____

_____ነው።

በሰይጣን ሽንገላ በምፈተንበት ጊዜ _____

_____

_____ አደርጋለሁ።

ከሰዎች ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት መቀያየም እንዳይኖር በግል መውሰድ ያለብኝ ቀጣዩ ርምጃ _____

_____

_____ ነው።

በአስቸኳይ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ አንድ ሰው _____

_____

_____ ነው።

መንፈሳዊ ውሎ ማስታወሻ መያዝ ያለብኝ አንድ ምክንያት_____

_____

_____ ነው።

በተለያየ ምክንያት የሚገጥመኝን በደል ወይም መሰናክል በተመለከተ በየቀኑ _____

_____

_____ በማለት መጸለይ አለብኝ።

ልብህ ካለፈ በደል ወይም መሰናክ መንጻቱን ካወቅህና የተረጋጋ ከሆነ፣ ጸንተህ በመቆም ወደ ፊት ሊኖር የሚችለውን የሰይጣን ሽንገላ መቋቋም አለብህ። ከኤፌሶን 6÷10-18 የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃዎች በተመለከተ አንብብ። አሸናፊ ትሆናለህ ጠላትን ታሸንፋለህ!

ጸሎትህን እዚህ ጻፍ

እርሱ ለአንተ ካዘጋጀው ከእያንዳንዱ መንፈሳዊ መሣሪያ ጋር አብሮ ሰላለው መከላከያ እግዚአብሔርን ማመስገን።

_____

_____

_____

በጣም ልቤን የነካኝን ምስክርነት የሰማሁት በኔፕልስ ፍሎሪዳ እያገለገልኩ በነበረ ጊዜ ነበር። ገና ንግግር ማድረግ ከመጀመሬ በፊት በመካከለኛው ዕድሜ ክልል ያለ አንድ ሰው ጉባኤው መካከል ቆሞ፣ ‹‹በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በእኔና በእግዚአብሔር መካከል አንድ ዓይነት ግድግዳ ያለ ያህል ይሰማኝ ነበር። እንዲህ ያሉ ስብሰባዎች ላይ ብዙ ጊዜ እገኛለሁ፣ ግን ሌሎች በእግዚአብሔር መገኘት ሲባረኩ እኔ ግን ገለልተኛና ድንዙዝ ሆኜ እታዘባለሁ። ሌላው ቀርቶ በምጸልይበት ጊዜ እንኳ መፈታትና የእግዚአብሔር ሐልዎት አይሰማኝም። ከጥቂት ሳምንቶች በፊት *የሰይጣን ሸንገላ* የተሰኘው መጽሐፍ እጄ ገባ፤ ወዲያውኑ ዳር እስከ ዳር አነበብኩት። ከዓመታት በፊት በሰይጣን ሽንገላ ተታልዬ እንደ ነበር ገባኝ። ገና የስድስት ወር ልጅ እያለሁ ትታኝ በመሄድዋ እናቴን በጣም እጠላት ነበር። ወደ እርሷ ሄጄ ይቅር ልላት እንደሚገባ ተረዳሁ። በሰላሣ ስድስት ዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ደውዬ አነጋገርኳት። ‹‹እማማ፣ ትተሽኝ በመሄድሽ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አንቺ ላይ ቂም ይዤ ኖሬአለሁ›› አልኳት። እርሷም ማልቀስ ጀመረች፣ ‹‹አንተን ትቼ በመሄዴ ላለፈው ሰላሣ ስድስት ዓመት ራሴን በመጥላት ነው የኖርኩት›› አለችኝ።

በመቀጠል፣ ‹‹ይቅር አልኳት፤ እርሷም ራሷን ይቅር አለች፤ አሁን በሁለታችን መካከል ዕርቅ ሆኖአል።›› እጅግ በጣም የሚገርም ነገር የተናገረው ይህን ካለ በኃላ ነበር፤ ‹‹አሁን ከእግዚአብሔር የለየኝ ግድግዳ ተወግዷል!››

እዚህ ነጥብ ላይ ፍጹም ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። እንደ ምንም ብሎ ታግለና፣ ‹‹አሁን በእግዚአብሔር ፊት እንደ አንድ ሕፃን አለቅሳለሁ›› አለ።

የእንዲህ ዓይነቱን እስራት እውነታና ብርታት እኔም ዐውቀዋለሁ። ለዓመታት የዚህ ስቃይ ምርኮኛ ሆኜ ነበር። ይህ መጽሐፍ የግምት ወይም የይመስለኛል አነጋገር አይደለም፤ በጉልህ የሚታይ፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እኔ ራሴ ያለፍኩበትን እውነት ይዞአል። እያነበባችሁ እያለ፣ እምነታችሁን እንዲጨምር ጌታን ጠይቁት! እምነታችሁ ሲያድግ እርሱ ይከበራል፣ እናንተም በደስታ ትሞላላችሁ! እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።

- ጆን ቢቭሬ

መንፈስ ቅዱስ - እንደ መግቢያ

ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደ አንዳች፣ ‹‹ግራ አጋቢ›› ነገር ተደርጐ ይታሰባል። ሆኖም፣ መንፈስ እንዳች ነገር እንዳይደለ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጓል። እርሱ የራሱ ሰብዕና ያለውና፣ ሁሌም ከጐናችን ሆኖ እንደሚረዳን ቃል የተገባለት ነው።

በዚህ አሳታፊ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን እጅግ ችላ የተባለውንና ሰዎች በተሳሳተ ሁኔታ የተረዱትን እካል ማለትም መንፈስ ቅዱስን በግል ሕይወታችሁ ወደ ማወቅ እንድትመጡ ጆን ቢቨሬ ጥሪ ያቀርባል።

አሳታፊው መጽሐፍ የሚከተሉትንም ያካትታል

- የየዕለቱ ማሰላሰያ
- በቡድን መወያያ ጥያቄዎች
- መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ ለሚነሡ አንዳንድ ከባድ ጥያቄዎች መልስ የያዘ ተጨማሪ ምዕራፍ

ይህ ድንቅ መጽሐፍ አያምልጣችሁ።

ለተጨማሪ ምንጮች

www.CloudLibrary.org

ሌላም ትፈልጋልህ?
እዘህ አስካን አድርግ

ከአደገኛ የጠላት ወጥመድ ማምለጥ

የሰይጣን ሽንገላ፣ የተሰኘው ይህ መጽሐፍ አማኞችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ለማስወጣት ጠላት ከሚጠቀምበት አሳሳች ወጥመዶች አንዱን ያጋልጣል - ይኸውም መሰናከያ ነው። አብዛኞቹ ሰዎች በዚህ መሰናከያ ተጠምደዋል፣ ያም ሆኖ ግን፣ መጠመዳቸውን እንኳ አላወቁም።

አትሞኑ! መሰናከያ ሳይመጣ አይቀርም፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ግንኙነት በሚያላድግ መልኩ በእርሱ መጠቀም አለመጠቀማችሁ የእናንተ ጉዳይ ነው። መሰናከያን በሚገባ ካስተናገዳችሁ፣ መራራ ሳይሆን ብርቱና ጠንካራ ትሆናላችሁ።

በዚህ ተወዳጅ መጽሐፍ ዐሥረኛ ዕትም መታሰቢያ ጆን ቢቭሬ ከመሰናከያ ነጻ ሆናችሁ የምትኖሩበትንና ከተጠቂነት ገንዘቤ የምታመልጡበትን መንገድ ያሳያችኋል። ከ1,000,000 ኮፒዎች በላይ በዓለም ዙሪያ እየታተመ ያለው የመጀመሪያውን መጽሐፍና የውይይት ጥያቄዎች፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችና ጸሎቶች የታከሉበት የዕለት ተዕለት ማሰላሰያ አንብበው ሕይወታቸው የተለወጠ ሰዎችን ምስክርነት አካትቶአል።

ቀጥሎ ያሉትን ለመሳሰሉ ከባድ ጥያቄዎች መልስ ታገኛላችሁ

- የታሪኩን ‹‹የእኔን ዕይታ›› ለመናገር የምነሣሣው ለምንድው?
- የተጠራጣሪነትን ወይም ሌሎችን ያለማመን ሐሳብ መዋጋት የምችለው እንዴት ነው?
- ያለፉ ጊዜ ጉዳቶችን ማውጠንጠን ማቆም የምችለው እንዴት ነው?
- አንድ ሰው በጣም ከጐዳኝ በኃላ ያንኑ ሰው መልሼ ማመን የምችለው እንዴት ነው?

ይህ መጽሐፍ ከጠላት፣ ‹‹መሰናከያ ወጥመድ›› እንድታመልጡ ይረዳችኃል፣ ከመሰናከያ ነጻ ሆናችሁ እንድትኖሩና ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ኃይል ይሰጣችኃል።

ጆን ቢቭሬ፣ ከፍተኛ ተነባቢነት ያላቸው መጻሕፍት ደራሲና ተወዳጅ የኮንፈረንስ ተናጋሪ ነው። እንደ እርሱ የተዋጣለት ደራሲ የሆነችው ባለቤቱ ሊዛና እርሱ በ1990 ጆን ቢቭሬ ሚኒስትሪስ የተሰኘ አገልግሎት መሥርተዋል። በ214 አገሮች የሚሰራጨው ሚስንጀር የተባለው ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራማቸውን ጨምሮ ባለ ብዙ ገጽታዎች የሆነው አገልግሎት ዓለም አቀፍ ሽፋን ያለው ወደ መሆን ደረጃ አድጓል። ቢቭሬ Breaking Intimidation The fear of the Lord እና Under cover የተሰኙትን ጨምሮ በርካታ መጻሕፍት ጽፈዋል።

ይህን ጽሑፍና ሌሎች ትምህርቶችን ከ www.CloudLibrary.org መውሰድ ይቻላል።

Messenger International

MessengerInternational.org

ይህ መጽሐፍ የደራሲው ስጦታ ነው አይሸጥም